# ሕያው ፡ ቃል

## አዲስ ፡ ኪዳን

ሊቪንግ ባይብልስ ኢንተርናሽናል
LIVING BIBLES INTERNATIONAL
Box 60595, Nairobi, Kenya

*Amharic New Testament*
First printing, 1985

Copyright © 1985 by
Living Bibles International
All rights reserved

ISBN 0 86660 010 8 Red
ISBN 0 86660 011 6 Black
ISBN 0 86660 012 4 Blue

# መግቢያ

ቋንቋ በየዘመኑና በየትውልዱ እየተሻሻለና እየተለዋወጠ የመሄድ ባሕርይ አለው። የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ የሆነው አዲሱ ትውልድ፣ በጥንታዊ የአነጋገር ዘይቤ ተተርጉመው የሚቀርቡለትን ቅዱሳት መጻሕፍት መልእክት ለመረዳትና ለማስተዋል ሲቸገር ቆይቷል።

'ሕያው ቃል'–አብዛኛው የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሊገባው በሚችል ቀላል አማርኛ፣ የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት ይዞ ቀርቧል። ይህም የሆነው፣ 'ሊቪንግ ባይብልስ ኢንተርናሽናል'፣ በከባድ ቃላት ተውጦ ለአንባብያን አእምሮ ምሥጢር ሆኖ የቆየውን የመጽሐፍ ቅዱስ ሕያው መልእክት፣ ማንም ሰው ሊረዳው በሚችል ቀላል አማርኛ ለማቅረብ ታላቅ ጥረት በማድረጉ ነው።

የ'ሊቪንግ ባይብልስ ኢንተርናሽናል' ዋና ዓላማ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ጊዜ ሲጻፍ የነበረውን አሳብ ሳይለውጥ፣ እውነትን በእውነት፣ አሳብን በአሳብ፣ ስሜትን በስሜት እየተካ፣ በተለያዩ ቋንቋዎች መጽሐፍ ቅዱስን ተርጉሞ ማቅረብ ነው። በዚህ የአተረጓጎም ስልቱም፣ ቃልን በቃል በመተካት ብቻ ሳይወሰን፣ የሚተረጎምለትን ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ወቅታዊ የአነጋገር ፈሊጥና ለዛ፣ ከባህሉ ጋር አዋሕዶ በመጠቀም፣ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ተነባቢነት ባለው የአቀራረብ ዘዴ ለማስተላለፍ የተቻለውን አድርጓል።

በቀድሞይቱ ግሪክ፣ በቋንቋቸው የሰዋሰው ድንጋጌ የተራቀቀ ምሁራን የሚነጋገሩበትና መጻሕፍት የሚደርሱበት ግሪክኛ የተለየ ሲሆን፣ ሠፊው የግሪክ ሕዝብ ግን አሳቡን የሚያስተላልፍበት 'ኮይኔ' ግሪክ የተባለ የዘወትር ቋንቋ ነበር። የኢየሱስ ደቀመዛሙርትም አዲስ ኪዳንን የጻፉት ተራው ሕዝብ በሚጠቀምበት በዚሁ 'ኮይኔ' በተባለው የዕለት ተዕለት መግባቢያ በሆነው ግሪክኛ ነበር። ደቀመዛሙርቱ፣ ይህን ብዙዎቹ ግሪኮች ይነጋገሩበት የነበረውን ቋንቋ የተጠቀሙበት ዋና ምክንያት፣ ሠፊው ግሪክ ተናጋሪ ሕዝብ የምሥራቹን ቃል መስማት የሚችልበት ምርጥ መሣሪያ መሆኑን በመገንዘባቸው ነበር። ደቀመዛሙርት የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት በ'ኮይኔ' ግሪክ የጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ብቻ ሳይሆን፣ የሰው ልጆች ሁሉ በቀላሉ ሊገባቸው በሚችል ቋንቋ እንዲቀርብላቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን በመረዳታቸውም ጭምር ነው። 'ሕያው ቃል'–የተሰኘው ይህ አዲስ ኪዳን የተተረጎመውም፣ አንባቢ መልእክቱን ሊረዳውና ሊያስተውለው በሚችለው ቀላልና ግቡ በሆነ አማርኛ ነው።

'ሕያው ቃል'–የተሰኘውን ይህን አዲስ ትርጉም 'ሊቪንግ ባይብልስ' ሲያዘጋጅ ብዙ ዓመታት ፈጅቶበታል። በብዙ ጥረት ታትሞ ሊወጣ የበቃው ይህ ትርጉም፣ የቋንቋ አቀራረቡም ሆነ የትርጉም ጥራቱ፤ በትምህርተ መለኮት፣ በግሪክ ቋንቋ ምሁራንና በሥነ ጽሑፍ አዋቂዎች፣ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ተመርምሯል። ይሁን እንጂ፣ ይህን የመጀመሪያውን እትም የሚመለከቱ አንባብያን የሚሰጡት ገንቢ አስተያየት፣ እርማትና፣ ምክር ለሁለተኛው አዲስ ኪዳን እትምም ሆነ፣ ባሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ ለሚገኘው የብሉይ ኪዳን የትርጉም ሥራ ጠቃሚ እንደሚሆን እንተማመናለን።

'ሕያው ቃል'–እግዚአብሔር በዘመናችን ለሰው ልጆች ሊያስተላልፈው የሚፈልገውን ሕያው መልእክት በቀላል አማርኛ ይዞ በመቅረቡ፣ የሚያነቡት ሁሉ መንፈሳዊ በረከት እንዲያገኙበት ጸሎታችንና ምኞታችን ነው።

# የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት


| | |
|---|---|
| ማቴዎስ | 1 |
| ማርቆስ | 39 |
| ሉቃስ | 63 |
| ዮሐንስ | 103 |
| የሐዋርያት ሥራ | 136 |
| ለሮም ሰዎች | 178 |
| 1 ቆሮንቶስ | 196 |
| 2 ቆሮንቶስ | 215 |
| ገላትያ | 227 |
| ኤፌሶን | 234 |
| ፊልጵስዩስ | 239 |
| ቈላስይስ | 244 |
| 1 ተሰሎንቄ | 248 |
| 2 ተሰሎንቄ | 252 |
| 1 ጢሞቴዎስ | 254 |
| 2 ጢሞቴዎስ | 259 |
| ቲቶ | 263 |
| ፊልሞና | 265 |
| ዕብራውያን | 267 |
| ያዕቆብ | 280 |
| 1 ጴጥሮስ | 285 |
| 2 ጴጥሮስ | 290 |
| 1 ዮሐንስ | 294 |
| 2 ዮሐንስ | 298 |
| 3 ዮሐንስ | 299 |
| ይሁዳ | 300 |
| የዮሐንስ ራእይ | 303 |



# የጌታ ኢየሱስ ምድራዊ ሕይወት

ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ገጾች ላይ የሠፈሩት ቃላት አራቱ ወንጌላውያን የክርስቶስን ምድራዊ ሕይወት እንዴት አድርገው ከአራት አቅጣጫ እንደ ተመለከቱት ያሳዩናል።

ያለ የሌለ ንብረቱን ትቶ ጌታን የተከተለው ማቴዎስ፥ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት ስለመምጣቱ ነቢያት አስቀድመው ትንቢት የተናገሩለት የዓለም መድኀኒት፥ኢየሱስ መሆኑን ያበሥራል።

ለግላጋው ወጣት ማርቆስ፥ ከጴጥሮስ ባገኘው መረጃ መሠረት ፥ ሰው ወዳድ የሆነው ክርስቶስ እህል ውኃ የሚቀምስበት ጊዜ እስኪያጣ ድረስ፥ ችግረኞችን የቱን ያህል ይረዳቸውና ያበረታታቸው እንደ ነበር እንደ ሥዕል ቁልጭ አድርጎ አቅርቦልናል።

የሕክምና ጥበብ ባለሙያ የሆነው ሉቃስ ደግሞ፥ ጌታ ሕመምተኞችንና ተስፋ የቆረጡትን ምን ያህል ይወዳቸው እንደ ነበር አሳምሮ አስፍሮልናል።

ቀድሞ ዓሣ አጥማጅ የነበረውና ኋላም ጌታ የሚወደው ደቀመዝሙር ዮሐንስ በበኩሉ፥ ስለኢየሱስ ወሰን የሌለው ፍቅርና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ስለሚያረጋግጡለት ተአምራቱ ያወሳናል።

አራቱም ወንጌላውያን ክርስቶስ በምድራዊ ሕይወቱ ከፈጸማቸው ታላላቅ ድርጊቶች ሁሉ፥የላቀ ግምት ልንሰጠውና እጅግ ከፍ ባለ አንክሮ ልንመለከተው የሚገባንን ጉዳይ፥ ተርከውታል። ይህም፥ በሚጠሉት ወገኖች ላይ ያለውን ፍቅሩን ሳይቀንስ አስቀድሞ በተነገረው ትንቢት መሠረት፥ ስለ ሰው ልጆች ቤዛነት ልዩ ልዩ መከራ ተቀብሎ በመስቀል ላይ መሞቱን፥መቀበሩንና በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ መነሣቱን ነው።

# ማቴዎስ የጻፈው

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ቃል

### መግቢያ

ማቴዎስ ከመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነው። የጻፈውም በዓይኑ ያየውንና በጆሮው የሰማውን ስለሆነ፥ለክርስቶስ ሥራ የዓይን ምስክሮች ከሆኑት አንዱ ነበር። ማቴዎስ ወንጌሉን የጻፈው ክርስቶስ ወደ ሰማይ ካረገ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ነው። የማቴዎስ ወንጌል ዋና ዓላማ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ማስተማር ሲሆን፥በጣም የታወቀው የተራራው ስብከትም በዚሁ ወንጌል ውስጥ ይገኛል።

---

## ምዕራፍ 1

1 ዘሩ ከአብርሃምና ከዳዊት ሲወርድ
ሲዋረድ የመጣው የኢየሱስ ክርስቶስ
ትውልድ ሲቆጠር ከዚህ እንደሚከተለው
ነው፤
2 አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ይስሐቅ ያዕ
ቆብን ወለደ፤ያዕቆብ ይሁዳንና ወን
ድሞቹን ወለደ፤
3 ይሁዳ ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤
ፋሬስ አስሮምን ወለደ፤አስሮም አራ
ምን ወለደ፤
4 አራም አሚናዳብን ወለደ ፤ አሚናዳብ
ነአሶንን ወለደ ፤ ነአሶን ሰልሞንን
ወለደ፤
5 ሰልሞን ቦኤዝን ከራኬብ ወለደ፤ቦኤዝ
ከሚስቱ ከሩት ኢዮቤድን ወለደ ፤
ኢዮቤድ እሴይን ወለደ፤
6 እሴይ ንጉሥ ዳዊትን ወለደ ፤ ንጉሥ
ዳዊት የኦሪዮን ሚስት ከነበረችው
ከቤርሳቤህ ሰሎሞንን ወለደ፤
7 ሰሎሞን ሮብአምን ወለደ፤ሮብአም አቢ
ያን ወለደ፤አቢያ አሣፍን ወለደ፤
8 አሣፍ ኢዮሳፍጥን ወለደ ፤ ኢዮሳፍጥ
ኢዮራምን ወለደ፤ኢዮራም ዖዝያንን
ወለደ፤
9 ዖዝያን ኢዮአታምን ወለደ፤ኢዮአታም
አካዝን ወለደ ፤ አካዝ ሕዝቅያስን
ወለደ፤
10 ሕዝቅያስ ምናሴን ወለደ፤ምናሴ አሞንን
ወለደ፤አሞንም ኢዮስያስን ወለደ፤
11 ኢዮስያስ በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኢኮንያን
ንና ወንድሞቹን ወለደ፤
12 ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ኢኮንያን ሰላትያ
ልን ወለደ፤
13 ሰላትያል ዘሩባቢልን ወለደ ፤ ዘሩባቢል
አብዩድን ወለደ ፤ አብዩድ ኤልያቄ
ምን ወለደ፤ኤልያቄም አዛርን ወለደ፤
14 አዛር ሳዶቅን ወለደ ፤ ሳዶቅ አኪምን
ወለደ፤አኪም ኤልዩድን ወለደ፤
15 ኤልዩድ አልዓዛርን ወለደ ፤ አልዓዛር
ማታንን ወለደ ፤ ማታን ያዕቆብን
ወለደ፤
16 ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤ዮሴፍ የኢየሱስ
ክርስቶስ እናት የማርያም እጮኛ
ነበር።
17 ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት
ትውልድ ፤ ከዳዊት እስከ ባቢሎን
ምርኮ አሥራ አራት ትውልድ፥ከባቢ
ሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ ልደት
አሥራ አራት ትውልድ ይሆናል።
18 የኢየሱስ ክርስቶስ የልደቱ ታሪክ እን
ዲህ ነበር። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ ታጭታ
ሳለ፥በድንግልናዋ በመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገ
ኘች። 19 እጮኛዋ ዮሴፍም ደግ ሰው ስለ
ነበር ፥ ማርያምን በሰው ፊት ሊያጋልጣት
ስላልፈለገ ውላቸውን ሰው ሳይሰማ ለማፍ
ረስ ወሰነ።
20 አሊጋው ላይ ጋደም ብሎ ይህንኑ
ሲያወጣና ሲያወርድ ፥ እንቅልፍ ወስዶት
ሕልም አየ። በሕልሙም የእግዚአብሔር
መልአክ በአጠገቡ ቆሞ እንዲህ አለው።
«የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥እጮኛህ ማርያ
ምን ለመውሰድ አታመንታ። 21 ፅንሱም
የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንጂ የሌላ መስሎህ
እንዳትጠራጠር። እርስዋም ወንድ ልጅ
ትወልዳለች ፤ ስሙን ኢየሱስ ብለህ አውጣ
ለት ፤ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋ
ልና። 22 ይህ ሁሉ የሚሆነው ፥ እግዚአብ
ሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አድሮ 23 ‹እነሆ!

ድንግል ትፀንሳለች፤ወንድ ልጅም ትወልዳ
ለች፤ስሙም አማኑኤል ይባላል’ ብሎ የተና
ገረው ቃል መፈጸም ስላለበት ነው።» አማ
ኑኤል ማለትም በዕብራይስጥ ቋንቋ ‘እግዚ
አብሔር ከእኛ ጋር ነው’ ማለት ነው።
24 ዮሴፍም ከእንቅልፉ እንደነቃ የእግዚአ
ብሔር መልአክ እንዳዘዘው ማርያምን ወደ
ቤቱ ወሰዳት። 25 የፀነሰችው ልጅዋ እስከተ
ወለደበት ጊዜ ድረስ ድንግል ነበረች። ዮሴ
ፍም የተወለደውን ሕፃን፣ «ኢየሱስ» ብሎ
ስም አወጣለት።

## ምዕራፍ 2

1 ንጉሥ ሄሮድስ የይሁዳን ክፍለ አገር
ይገዛ በነበረበት ዘመን፣ ኢየሱስ በቤተል
ሔም ከተማ ተወለደ። በዚያኑ ጊዜ የከዋክ
ብት ተመራማሪ የሆኑ የምሥራቅ አገር
ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው፣ 2 «በቅ
ርቡ የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ የሚገ
ኘው የት ነው? በምሥራቅ አገር ሆነን ኮከ
ቡን ስላየን ልንሰግድለት መጥተናል» ሲሉ
ጠየቁ።

3 የከዋክብት ተመራማሪዎቹን ጥያቄ
ሄሮድስ ሲሰማ በጣም ተደናገጠ። ወሬውም
የኢየሩሳሌምን ከተማ አተራመሳት። 4 ሄሮ
ድስ የካህናት አለቆችንና የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራንን በቤተ መንግሥቱ ሰብ
ስቦ፣ «ለመሆኑ ነቢያት ክርስቶስ የሚወለድ
በት ሥፍራ የት እንደሆነ ተናግረዋል?»
ሲል ጠየቃቸው። 5 እነርሱም፣ «አዎን፣በቤ
ተልሔም እንደሚወለድ ተናግረዋል። ነቢዩ
ሚክያስ ስለዚሁ ጉዳይ፣ 6 ‘ትንሺቱ ከተማ
ቤተልሔም ሆይ፣ከሌሎቹ የይሁዳ ከተሞች
በምንም አታንሺም፤ምክንያቱም፣ሕዝቤን
እሥራኤልን የሚጠብቅ ንጉሥ ከአንቺ ይወ
ጣልና’ በማለት ተናግሯል» አሉት።

7 ከዚህ በኋላ፣ሄሮድስ የከዋክብት ተመ
ራማሪዎቹን አስጠርቶ በቆይታ በማነጋገር
ኮከቡን ያዩበትን ትክክለኛ ጊዜ ተረዳ።
8 ለጥያቄው መልስ ካገኘ በኋላም፣የከዋክ
ብት ተመራማሪዎቹን፣ «የሚወለድበት ቦታ
ስለታወቀ ወደ ቤተልሔም ሂዱና ሕፃኑን
ፈልጉ። ስትመለሱ ግን በዚሁ መጥታችሁ
ማግኘታችሁን ንገሩኝ። እኔም ሄጄ ልሰግድ
ለት እፈልጋለሁ» አላቸው።

9 የከዋክብት ተመራማሪዎቹም ከሄሮድስ
ጋር ቆይታ ካደረጉ በኋላ፣ ጉዞአቸውን
ቀጠሉ። በመንገድ ላይም ያው ኮከብ እንደ
ገና ታያቸው። እየመራም ወስዶ ሕፃኑ
ከሚገኝበት ቦታ አደረሳቸው። 10 የከዋክ
ብት ተመራማሪዎቹ ኮከቡን ሲያዩ የተሰማ
ቸው ደስታ ከመጠን በላይ ነበር።

11 ከዚያም ሕፃኑና እናቱ ማርያም ወደ
ነበሩበት ቤት ገቡ። ተንበርክከውም ለሕፃኑ
ሰገዱለት። ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው
ወርቅ፣ዕጣንና ከርቤ አበረከቱለት። 12 ወደ
አገራቸው በሚመለሱበትም ጊዜ እግዚአብ
ሔር በሕልም ተገልጦ ወደ ሄሮድስ እንዳይ
መለሱ አስጠነቀቃቸው። እነርሱም በኢየሩ
ሳሌም በኩል በማለፍ ፈንታ፣መንገድ አሳብ
ረው ወዳገራቸው ሄዱ።

13 የከዋክብት ተመራማሪዎቹ ከሄዱ
በኋላ፣የእግዚአብሔር መልአክ ለዮሴፍ በሕ
ልም ተገለጠለት። «ተነሥ! መቼ እንደም
ትመለስ እስካስታውቅህ ድረስ ሕፃኑንና እና
ቱን ይዘህ፣ ወደ ግብፅ ሂድና በዚያ ቆይ።
ሄሮድስ ሕፃኑን ለመግደል ጥረት በማድረግ
ላይ ይገኛል» አለው። 14 ዮሴፍም በዚያው
ምሽት ሕፃኑንና ማርያምን ይዞ ወደ ግብፅ
ሸሸ። 15 ከዚያም፣ ንጉሥ ሄሮድስ እስከ
ሞተበት ዘመን ድረስ በግብፅ አገር ኖረ።
ይህም የሆነው፣ «ልጄን ከግብፅ አገር ጠራ
ሁት» በማለት እግዚአብሔር በነቢዩ አፍ
የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነበር።

16 ሄሮድስ፣ የከዋክብት ተመራማሪዎቹ
እንዳታለሉት በተረዳ ጊዜ፣በጣም ተናደደ።
ወታደሮቹ ወደ ቤተልሔም ከተማና በአካባ
ቢዋ ወደሚገኙት መንደሮች ሄደው፣ዕድሜ
ያቸው ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች የሆ
ናቸውን ሕፃናት ሁሉ እንዲፈጁዋቸው
አዘዘ። ምክንያቱም የከዋክብት ተመራማሪ
ዎቹ ኮከቡን ያዩት ከሁለት ዓመት በፊት
መሆኑን ነግረውት ነበርና። ወታደሮቹም
በታዘዙት መሠረት ወደ ከተሞቹ ሄደው
ሕፃናቱን ፈጁዋቸው። 17 ሄሮድስ በሕፃናቱ
ላይ የፈጸመው ግድያ ነቢዩ ኤርምያስ፣
18 «በራማ ብዙ ልቅሶና ዋይታ የሞላበት
የኀዘን ጩኸት ተሰማ። ራሔል ስለ ልጆ
ችዋ አለቀሰች። ነገር ግን ልጆችዋ ሁሉ
በማለቃቸው ለመጽናናት አልቻለችም»
ብሎ የተናገረውን ቃል መፈጸም ያመለክ
ታል።

19 ሄሮድስ ከሞተ በኋላ የእግዚአብሔር
መልአክ ለዮሴፍ በሕልም ተገልጦ፣
20 «ሕፃኑን ለመግደል ይጥሩ የነበሩት ስለ
ሞቱ፣ ተነሣ፣ ሕፃኑንና እናቱን ይዘህ ወደ
እሥራኤል አገር ተመለስ» አለው።

21 ዮሴፍም ውሎ ሳያድር ሕፃኑንና እና
ቱን ይዞ ወደ እሥራኤል አገር ተመለሰ።
22 ነገር ግን የሄሮድስ ልጅ አርኬላዎስ የይ



ሁዳ ንጉሥ መሆኑን በጉዞ ላይ እንዳለ በመ
ስማቱ ሥጋት አደረበት። እግዚአብሔርም
በሕልም እንደገና ተገልጦ ወደ ይሁዳ
ክፍለ አገር እንዳይሄድ አስጠነቀቀው።
23 ስለዚህ ወደ ገሊላ ሄዶ ናዝሬት በምት
ባል ከተማ መኖር ጀመረ። ይህም በመሆኑ፣
በነቢያት አንደበት ስለ መሲሑ፣ «ናዝራዊ
ይባላል» ተብሎ የተነገረው ቃል ተፈጸመ።

## ምዕራፍ 3

1 በዚያን ወራት መጥምቁ ዮሐንስ በይ
ሁዳ በረሃ ያስተምር ነበር። 2 ትምህር
ቱም፣ «መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና
ንስሐ ግቡ፤ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ»
የሚል ነበር። 3 ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት
ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ መጥምቁ ዮሐንስ መም
ጣት እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር። «በበረሃ
ውስጥ እንዲህ የሚል ድምፅ ሰማሁ። ‘የጌ
ታን መንገድ አዘጋጁ፤መሄጃውንም አስተካ
ክሉ።’»

4 ዮሐንስ ከግመል ጠጉር የተሠራ ባና
ይለብስና ወገቡንም በቆዳ ቀበቶ ይታጠቅ
ነበር። የሚበላውም አንበጣና የጣዝማ ማር
ነበር። 5 ብዙ ሰዎች የዮሐንስን ትምህርት
ለማዳመጥ ከኢየሩሳሌምና ከዮርዳኖስ ወንዝ
አካባቢ፣ እንዲሁም ከይሁዳ ክፍለ ሀገር
ይመጡ ነበር። 6 ኃጢአታቸውን እየተናዘ
ዙም በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ያጠምቃ
ቸው ነበር።

7 ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን በመባል የታ
ወቁ ሁለት የተለያዩ የአይሁድ ሃይማኖት
ክፍሎች፣ ወደ እርሱ በብዛት ለመጠመቅ
ሲመጡ ባየ ጊዜ እንዲህ አላቸው፣ «እና
ንተ የእባብ ልጆች፣ለመሆኑ ከሚመጣው
የእግዚአብሔር ቁጣ ለማምለጥ እንደምት
ችሉ ማን ጠቆማችሁ? 8 መጠመቅ ከፈለጋ
ችሁ ኃጢአታችሁን የተዋችሁ መሆናችሁን
የሚያረጋግጥ መልካም ሥራ አሳዩ።
9 ‘ወዲህ አይሁዶች፣ ወዲህ የአብርሃም
ዘሮች በመሆናችን ምንም አይነካንም’ እያላ
ችሁ ራሳችሁን አታታልሉ። እንዲህ ያለው
አቋም ምንም አያዋጣችሁም። እግዚአብ
ሔር እነዚህን ድንጋዮች እንሥቶ የአብር
ሃም ዝርዮች ሊያደርጋቸው ይችላል።

10 «የእግዚአብሔር የፍርድ መጥረቢያ
ፍሬ የማያፈራውን ዛፍ ለመቁረጥ ተሰንዝሮ
አል። ፍሬ የማያፈሩ ዛፎች ተቆርጠው
ይቃጠላሉ።

11 «ኃጢአታችሁን ተናዛችሁ የተመለሳ
ችሁትን እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ነገር
ግን ከእኔ የበለጠ ይመጣል። ከእኔ በጣም
የበለጠ ከመሆኑ የተነሣም፣ ጫማውን እን
ኳን ለመሸከም፣ ብቃት የለኝም። እርሱ
በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል።
12 መንሹም በእጁ ነውና ፍሬውን ከገለባው
ይለያል፤ገለባውንም በማይጠፋ እሳት ያቃጥ
ለዋል፤ ፍሬውን ግን ለይቶ ጎተራ ይከተ
ዋል።»

13 በዚያኑ ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ እጅ
ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ
ወረደ። 14 ዮሐንስ ግን፣ «ፈጽሞ አላደርገ
ውም። አንተ አጥምቀኝ እንጂ እንዴት እኔ
አጠምቅሃለሁ? የተገላቢጦሽ እኔ አንተን
ላጠምቅህ? አይደረግም!» አለው።

15 ኢየሱስም፣ «ግድ የለህም አይጭን
ቅህ፣ ዝም ብለህ አጥምቀኝ። ይህንን ማድ
ረጉ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ሆኖ አግኝቼዋ
ለሁና» አለው። ከዚያም ዮሐንስ ኢየሱስን
አጠመቀው። 16 ተጠምቆም ከውኃው
ሲወጣ፣ሰማይ ተከፍቶ መንፈስ ቅዱስ በር
ግብ አምሳል በላዩ አንዣቦበት አየ፤ 17 ከሰ
ማይም፣ «የምወደው ልጄ ይህ ነው፣በእ
ርሱ እጅግ ደስ ይለኛል» የሚል ድምፅ
ተሰማ።

## ምዕራፍ 4

1 ከዚህ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስ
በሰይጣን እንዲፈተን ወደ ምድረ በዳ
ወሰደው። 2 በምድረ በዳም አርባ ቀንና
አርባ ሌሊት ስለ ጾመ በጣም ተራበ።
3 ከዚያም፣ሰይጣን ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ድን
ጋዮችን ወደ እንጀራ ለውጦ እንዲመገብ
በማሳሰብ፣ «እንዲህ ብታደርግ እኮ! የእግዚ
አብሔር ልጅ መሆንህ ይረጋገጥ ነበር»
ሲል ፈተነው።

4 ኢየሱስም፣ «አንተ እንደምትለው ሳይ
ሆን፣ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው፣
‘ሰው በእንጀራ ብቻ መኖር አይችልም።
ዋናው ቁም ነገር፣ የእግዚአብሔርን ቃል
መቀበልና በእርሱም እየተመሩ መኖር
ነው’» ሲል መለሰለት።

5 ቀጥሎም ሰይጣን ኢየሱስን ወደ ኢየሩ
ሳሌም ከተማ ወስዶ፣ ከቤተመቅደሱ ጣራ
አናት ላይ አወጣው። 6 «የእግዚአብሔር
ልጅ መሆንህ እንዲታወቅ፣ እስቲ ከዚህ
ጣሪያ ላይ ወደ ምድር ዝለል! በመጽሐፍት
ውስጥ እንደተጻፈው፣ ‘እግዚአብሔር መላ
እክቱን ልኮ ከጉዳት ስለሚጠብቅህ፣ አትፈ
ጠፋጥም’» አለው።

7 ኢየሱስም መለሰና፣ «እንደዚሁም በመ

ጸሕፍት፣ ‘እግዚአብሔር አምላክህን አትፈ
ታተነው’ ተብሎ ተጽፎአልና፣እንዲህ ያለ
ውን ነገር ፈጽሞ አላደርገውም» አለው።
8ከዚያም ሰይጣን ኢየሱስን ከትልቅ
ተራራ ላይ አወጣው። የዓለምንም መንግሥ
ታት ከነክብራቸው አሳየውና፣ 9«ወድቀህ
ስገድልኝና ይህንን የምታየውን ሁሉ ልሰ
ጥህ» አለው።
10ኢየሱስም፣ «አንተ ሰይጣን! ከፊቴ
ራቅ! የእግዚአብሔር ቃል፣ ‘ጌታ አምላክ
ህን ብቻ አምልክ፤ለእርሱም ብቻ ስገድ፤’
ነው የሚለው» አለው።
11ሰይጣንም ወዲያው ከፊቱ ጠፋ። የእ
ግዚአብሔር መላእክትም መጥተው ኢየሱ
ስን አገለገሉት።
12-13ኢየሱስ፣የመጥምቁ ዮሐንስን መታ
ሠር እንደሰማ፣የይሁዳን ክፍለ ሀገር ትቶ
በገሊላ አውራጃ ወደምትገኘው ወደ ናዝ
ሬት ከተማ ለመኖር ሄደ። በዚያም ብዙ
ሳይቆይ በዛብሎንና በንፍታሌም አውራጃ
አቅራቢያ፣ከገሊላ ሐይቅ አጠገብ በምትገ
ኘው በቅፍርናሆም ከተማ መኖር ጀመረ።
14እንዲህ ሊሆን የቻለውም፣ ነቢዩ ኢሳይ
ያስ፣ 15-16«በሐይቅ አካባቢ የሚገኙ የዛብ
ሎንና የንፍታሌም ምድር ነዋሪዎች፤እንዲ
ሁም ብዙ አሕዛብ የሚኖሩባቸው ከዮርዳ
ኖስ ወንዝ ማዶ የሚገኙ የላይኛው ገሊላ
አካባቢዎች ሁሉ፣ጨለማው ተወግዶላቸው
ታላቅ ብርሃን አዩ። በሞት ጥላ ሥር ለሚኖ
ሩትም ብርሃኑ ደረሳቸው» በማለት የተናገ
ረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ነው። 17ከዚ
ያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስ፣ «ንስሐ ግቡ፤ወደ
እግዚአብሔርም ተመለሱ፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት ቀርባለችና» እያለ ማስተማር
ጀመረ።
18አንድ ቀን ኢየሱስ በገሊላ ሐይቅ
አጠገብ ሲያልፍ፣ ዓሣ በማጥመድ ሥራ
የሚተዳደሩ ሁለት ወንድማማች በአንዲት
ጀልባ ሆነው ዓሣ ሲያጠምዱ አየ። አንዱ
በኋላ ጴጥሮስ ተብሎ የተሠየመው ስምዖን
ሲሆን፣ሌላው ደግሞ እንድርያስ ይባላል።
19ኢየሱስም ወንድማማቹን፣ «ተከተ
ሉኝ፤እኔም የሰው ነፍስ እንድታጠምዱ አደ
ርጋችኋለሁ» አላቸው። 20እነርሱም መረባ
ቸውን ትተው ወዲያውኑ ተከተሉት።
21ጥቂት እልፍ እንዳለም፣ ያዕቆብና
ዮሐንስ የተባሉ ሌሎች ወንድማማች፣ከአባ
ታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በጀልባ ሆነው
መረባቸውን ሲጠግኑ አያቸው። እነርሱ
ንም እንዲከተሉት ጠራቸው። 22እነርሱም
ሥራቸውን ወዲያውኑ አቁመው፣አባታቸ
ውን ጀልባው ላይ እንዳለ ትተው፣ኢየሱስን
ተከተሉት።
23ኢየሱስም ምኩራቦች (የአይሁድ
ጸሎት ቤቶች) ውስጥ እያስተማረ፣የእግዚአ
ብሔርንም መንግሥት የምሥራች ቃል በደ
ረሰበት ሁሉ እያወጀ፣በገሊላ አገር ይዘዋ
ወር ነበር። በደረሰበትም ቦታ ሁሉ፣ ልዩ
ልዩ በሽታና ደዌ ያለባቸውን ሰዎች ይፈ
ውስ ነበር። 24ይፈጽመው የነበረው ተአ
ምር ከገሊላ ወሰን አልፎ በመሰማቱም፣ከሶ
ርያ ድረስ ፈውስ የሚሹ በሽተኞች ወደ
እርሱ ይመጡ ነበር። የሚያሰቃያቸው
በሽታ ምንም ዓይነት ቢሆን መፈወስ አያቅ
ተውም ነበር። ርኩስ መንፈስ ያደረባቸ
ውን፣ያበዱትንና ሽባ የሆኑትን ሁሉ ይፈው
ሳቸው ነበር። 25ከዚህም የተነሣ ከገሊላና
ከ‘አሥሩ ከተሞች’፣ ከኢየሩሳሌምና ከመ
ላው ይሁዳ፣ እንዲሁም ከዮርዳኖስ ማዶ
የመጡ ብዙ ሰዎች ኢየሱስን ይከተሉት
ጀመር።

## ምዕራፍ 5

1አንድ ቀን ብዙ ሕዝብ እንደተሰበ
ሰበ፣ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ይዞ ወደ
ተራራ ወጣና ተቀመጠ። 2እንደሚከተለ
ውም አስተማራቸው።
3«በመንፈሳቸው ትሑት የሆኑ የተባረኩ
ናቸው፤መንግሥተ ሰማይ ለእነርሱ ናትና።
4«የሚያዝኑ የተባረኩ ናቸው፤መጽናና
ትን ያገኛሉና።
5«የዋሆች የተባረኩ ናቸው፤ የምድር
በረከት የእነርሱ ነውና።
6«ትክክለኛውን ነገር ማድረግ የሚመኙ
የተባረኩ ናቸው፤ እግዚአብሔር ምኞታቸ
ውን ይፈጽምላቸዋልና።
7«ሰዎችን የሚያፈቅሩና ይቅርታ የሚያ
ደርጉ የተባረኩ ናቸው፤እነርሱም ይቅርታ
ይደረግላቸዋልና።
8«ንጹሕ ልብ ያላቸው የተባረኩ
ናቸው፤እግዚአብሔርን ያዩታልና።
9«ሰላምን ለመመሥረት የሚጥሩ የተባ
ረኩ ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብ
ለው ይጠራሉና።
10«በጎ ነገርን በመፈጸማቸው ምክንያት
መከራን የሚቀበሉ የተባረኩ ናቸው፤የእግዚ
አብሔር መንግሥት ወራሾች ይሆናሉና።
11«በእኔ በማመናችሁ ምክንያት ሰዎች
ቢዘልፉአችሁ መከራ ቢያሳይዋችሁና
በሐሰት ስማችሁን ቢያጠፉት ፈጽሞ



አይከፋችሁ!
12«ይልቁንም በሰማይ ዋጋችሁ እጥፍ
መሆኑን አውቃችሁ ደስ ይበላችሁ። ከእና
ንተ በፊት የነበሩ ነቢያት ስደትና መከራ
የተቀበሉ መሆናቸውን አትርሱ።
13«እናንተ፣ የሰው ኑሮ ጣዕምና ጤና
እንዲኖረው የምታደርጉ የዓለም ጨው
ናችሁ። ነገር ግን የጨውነት ጣዕማችሁ
ከተለያችሁ ዓለምን ምን ሊበጀው ነው?
ጣዕም እንደሌለው ጨው ከሆናችሁ እንደ
ማይረባ ነገር ተጥላችሁ በእግር ትረገጣላ
ችሁ። 14እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ።
በኮረብታ ላይ የተሠራች ከተማ ልትሰወር
አትችልም። 15-16እንዲሁም ብርሃናችሁ
ለሰው ሁሉ እንዲታይ አድርጉ እንጂ አትሰ
ውሩት። መልካም ሥራችሁን አይተው የሰ
ማይ አባታችሁን እንዲያመሰግኑት ሥራ
ችሁ ለሰዎች ደምቆ ይታይ።
17«ወደዚች ምድር የመጣሁበት ምክን
ያት ግልጽ እንዲሆንላችሁ ያስፈልጋል።
አመጣጤ፣የሙሴን ሕግና የነቢያትን ቃል
ለመፈጸም፣በተግባርም ላይ ለማዋል እንጂ
ለመሻር አይደለም። 18በመጽሐፍ የተጻ
ፈው የሕግ ቃል ሁሉ ወደ ታለመለት ግብ
ሳይደርስ እንደማይቀር ላረጋግጥላችሁ እወ
ዳለሁ። 19ስለዚህ፣ ማንም ሰው ከተጻፈው
የሕግ ቃል መካከል አነስተኛዋን ክፍል
እንኳን ቢተላለፍና፣ሌሎችም የእርሱን አር
አያ እንዲከተሉ ቢያስተምር፣ በመንግሥተ
ሰማይ ዝቅተኛ ሥፍራ ይሰጠዋል። ነገር
ግን የሕጉን ቃል ራሱ እየፈጸመ፣ሌሎችም
እንዲፈጽሙት የሚያስተምር በመንግሥተ
ሰማይ ከፍተኛ ሥፍራ ይሰጠዋል።
20«ጽድቃችሁ ከፈሪሳውያንና ከአይ
ሁድ ሃይማኖት መምህራን ሥራ ልቆ ካል
ተገኘ፣ በምንም ዓይነት መንግሥተ ሰማይ
መግባት እንደማትችሉ አስገነዝባችኋለሁ።
21«በሙሴ ሕግ፣ ‘የገደለ ይሙት’
ተብሎ መታዘዙን ታውቁ የለም? 22እኔ
ግን ይህን ሕግ በማጠናከር፣በውጪም ሆነ
በቤታችሁ ውስጥ በከንቱ ብትቆጡ የሚፈረ
ድባችሁ መሆኑን እንድታውቁ እፈልጋ
ለሁ። ማንም ጓደኛውን ‘ደጋ’ ብሎ ቢሳ
ደብ ለፍርድ ይቀርባል። ጓደኛውን ‘ደን
ቆሮ’ ብሎ የተራገመ ደግሞ ለገሃነም እሳት
ይዳረጋል።
23«ስለዚህ፣ መሥዋዕትህን ለእግዚአብ
ሔር ለማቅረብ ከመሠዊያው ፊት ቆመህ
ሳለህ፣ ጓደኛህን ማስቀየምህ ትዝ ካለህ
24መሥዋዕትህን ከማቅረብህ በፊት፣በቀጥታ
ወደ ጓደኛህ ዘንድ ሄደህ ይቅርታ ጠይቀህ
ታረቀው። መሥዋዕትህን ለእግዚአብሔር
ማቅረብ የሚገባህ ከዚያ በኋላ ነው። 25እን
ዲሁም ባላጋራህ ከስሶህ ፍርድ ቤት አቅርቦ
እንዳያስፈርድብህ አስቀድመህ ተስማማ።
26ካስፈረደብህ ግን ያለህን ሁሉ እስክትጨ
ርስ ድረስ ከእሥር ቤት እንደማትወጣ
እወቅ።
27«የሙሴ ሕግ፣ ‘አታመንዝር’ ይላል።
28እኔ ግን እላችኋለሁ፣ሴትን አይቶ የሚመ
ኛት በልቡ ውስጥ ከእርሷ ጋር አመንዝ
ሯል። 29ስለዚህ ኃጢአት ላይ ለመውደቅ
የበቃኸው በዓይንህ ምክንያት ከሆነ፣ዓይን
ህን ያሳተውን የልብህን ክፉ አሳብ አውጣና
ጣለው። በመጨረሻ ለዘላለም ወደ ገሃነም
ከምትወርድ ጊዜያዊ የሆነውን ሥጋዊ ፈቃ
ድህን ብታጣ ይሻልሃልና። 30የቀኝ እጅህ
ኃጢአት እንድትሠራ ካደረገህ፣እጅህን ያሳ
ተውን የልብህን ክፉ አሳብ ከአንተ አስወግ
ደው። በመጨረሻ ወደ ገሃነም ከመጣል
ይልቅ ክፉ ሥራህን ቆርጠህ ጥለህ መንግ
ሥተ ሰማይ መግባት ይሻልሃልና።
31«የሙሴ ሕግ፣ ‘ሚስቱን ለመፍታት
የሚፈልግ የፍቺ ወረቀት በመስጠት ሊያሰ
ናብታት ይችላል’ ይላል። 32እኔ ግን እንደ
ዚህ አልላችሁም። ስታመነዝር ካላገኛት
በስተቀር፣ሚስቱን የሚፈታ ባል እንድታመ
ነዝር ያደርጋታል። የተፋታችውንም ሴት
ያገባ ያው አመንዝራ ነው።
33«አሁንም የሙሴ ሕግ፣ ‘ለእግዚአብ
ሔር የገባኸውን ቃለ መሐላ በሙሉ ፈጽ
መው እንጂ አታፍርሰው’ ይላል። 34እኔ
ግን፣ መማል ፈጽሞ አይገባም እላችኋለሁ።
ሰማያት የእግዚአብሔር ዙፋን የተዘረጋባ
ቸው ስለሆኑ ሰማያትን ጠርቶ መማል አይገ
ባም። 35ምድርም የእግሩ ማረፊያ በመሆኗ
የምድርን ስም ጠርታችሁ አትማሉ። ኢየሩ
ሳሌምም የታላቁ ንጉሥ ዋና ከተማ በመ
ሆኗ ስሟን ጠርታችሁ አትማሉ። 36በራሳች
ሁም ቢሆን አትማሉ፣ምክንያቱም ከጠጉራ
ችሁ መካከል አንዲቷን እንኳን ነጭ
ወይም ጥቁር የማድረግ ችሎታ የላችሁ
ምና። 37ስለዚህ ስትናገሩ፣ የሚሆነውን፣
‘ይሆናል’፤ የማይሆነውንም፣ ‘አይሆንም’
ማለት ብቻ ይበቃል። ከአንደበታችሁ የሚ
ወጣውን የተስፋ ቃል በመሐላ ለማጠናከር
መሞከሩ ግን፣ከክፉው ከሰይጣን የሚመጣ
አሳብ ነው።
38«የሙሴ ሕግ፣ ‘የሰውን ዓይን ያጠፋ
የራሱም ዓይን እንዲጠፋ፣የሰውን ጥርስ የሰ

በረ የራሱም ጥርስ እንዲሰበር’ ይላል።
39 እኔ ግን እንዲህ እልሃለሁ፣ ‘እከሌ አጥቅ
ቶኛልና እኔም ሳጥቃው’ አትበል። አንዱን
ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታ ሌላውን ጉንጭ
ህን አዙርለት። 40 ከሳሽህ ፍርድ ቤት አቅር
ቦህ ሸሚዝህ ቢፈረድለት፣ ኮትህን ጨምረህ
ስጠው። 41 ሰዎች ዕቃቸውን አሸክመው
አንድ ኪሎ ሜትር እንድትሄድ ቢያስገድ
ዱህ፣ ሁለተኛውን ኪሎ ሜትር በፈቃድህ
ተሸክመህላቸው ሂድ። 42 ለሚለምንህ ስጥ፤
ከአንተ ሊበደር ለሚፈልግም አትከልክ
ለው።

43 «በሙሴ ሕግ ‘ወዳጅህን ውደድ፤ ጠላ
ትህን ጥላ’ የሚል ቃል አለ። 44 እኔ ግን፣
ጠላቶቻችሁን ውደዱ ለሚያሳድዷችሁም
ጸልዩ እላችኋለሁ። 45 እንደዚህም በማድረ
ጋችሁ በሰማይ ላለው አባታችሁ እውነተኛ
ልጆች መሆናችሁን ታረጋግጣላችሁ። በእግ
ዚአብሔር ዘንድ ማድላት የለም። ለክፉዎ
ችም ለደጎችም ፀሐይን እኩል ያወጣል።
ዝናብንም የሚያዘንበው ለኃጢአተኞችም
ሆነ ለጻድቃን እኩል ነው። 46 የሚወዷች
ሁን ብቻ የምትወዱ ከሆነ ምን ፋይዳ
አለው? ክፉዎችስ ይህንኑ ያደርጉ የለምን?
47 የቅርብ ጓደኞቻችሁን ብቻ የምትወዱ
ከሆነ፣ በእናንተና በሌሎች መካከል ልዩነቱ
ከምኑ ላይ ነው? ይህንንማ አሕዛብስ ያደር
ጉት የለምን? 48 ስለዚህ የሰማዩ አባታችሁ
እንከን የማይገኝበት እንደሆነ ሁሉ፣ እናን
ተም እንደ እርሱ እንከን የማይገኝባችሁ
ሁኑ።»

## ምዕራፍ 6

1 «በሰዎች ዘንድ ይታይልን፣ ይታወቅ
ልን፣ ብላችሁ በጎ አድራጎታችሁን በይፋ
አታውጡት። የዚህ ዓይነቱ ከንቱ አድራጎት
ከሰማዩ አባታችሁ ዘንድ የሚጠብቃችሁን
ዋጋ ያሳጣችኋልና።
2 «ችሮታቸው እንዲታይላቸው በየአ
ውራ ጐዳናው፣ በያደባባዩና በየምኩራቡ
አካባቢ፣ ጥሩምባ እንደሚያስነፉ ግብዞች፣
አንተም ለድሆች ምጽዋት በምትሰጥበት
ጊዜ፣ ይሰማልኝ ይታወቅልኝ ብለህ አታድር
ገው። እውነቱን ልንገራችሁ? እነርሱ የሚ
ያገኙት ዋጋ ቢኖር፣ በሰዎች ዘንድ መታየ
ትን ብቻ ነው። 3 አንተ ግን፣ ለድሆች ስት
ሰጥ በምሥጢር አድርገው። ቀኝ እጅህ
የሚያደርገውን እንኳን ግራ እጅህ አይ
ወቅ። 4 የልብህን መርምሮ የሚያውቀው
የሰማዩ አባትህም፣ በምሥጢር ላደረግኸው
በጎ ሥራ ዋጋህን በግልጽ ይከፍልሃልና።
5 «ስትጸልይም በመንገድ ዳርና በምኩ
ራብ ውስጥ ለሰዎች በሚታይ ቦታ ቆመው፣
ጸሎተኛ ለመምሰል እንደሚፈልጉት እንደ
ግብዞች አትሁን። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እነ
ርሱ የሚያገኙት ዋጋ ቢኖር፣ በሰዎች ዘንድ
መታየትን ብቻ ነው። 6 አንተ ግን፣ ስትጸ
ልይ ለብቻህ ሁነህ፣ በርህንም ዘግተህ፣ በስ
ውር ወደ ሰማዩ አባትህ ጸልይ። የልብህን
መርምሮ የሚያውቀው አባትህም ዋጋህን
በግልጽ ይከፍልሃል።
7-8 «አንዱን ጸሎት ደግመው ደጋግ
መው በማነብነብ ብቻ፣ ጸሎታቸው የሚሰማ
ላቸው እንደሚመስላቸው እንደ አሕዛብ
ስትጸልዩ አታነብንቡ። የሰማዩ አባታችሁ
ከመጸለያችሁ በፊት ምን ምን እንደሚያስፈ
ልጋችሁ ያውቃልና። እናንተ ግን ስትጸልዩ
እንደዚህ በሉ፣
9 ‘በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፣
ስምህ ይቀደስ፤
10 መንግሥትህ ትምጣ። ፈቃድህ በሰማይ
እንደሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን።
11 የዕለት እንጀራችንን ዛሬም ስጠን።
12 የበደሉንን ይቅር እንደምንል፣ በደላችንን
ሁሉ ይቅር በለን።
13 ወደ ፈተናም አታግባን። ከክፉ ሁሉ
ጠብቀን እንጂ። መንግሥትና ኃይል፣
ክብርም ለዘላለም የአንተ ነውና፤
አሜን።’
14-15 «ለበደሏችሁ ሰዎች ይቅርታ ካደረ
ጋችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁ የእናንተንም
በደል ይቅር ይላችኋል። ነገር ግን ለበደሏ
ችሁ ይቅርታ የምታደርጉላቸው ካልሆና
ችሁ፣ እግዚአብሔር የእናንተንም በደል
ይቅር አይልላችሁም።
16 «በምትጾሙበትም ጊዜ መጾማቸው
እንዲታወቅላቸውና ከንፈር እንዲመጠጥላ
ቸው፣ ደክመውና ጠውልገው እንደሚታዩ
እንደ ግብዞች አትሁኑ። እንደ እውነቱ
ከሆነ፣ እነርሱ የሚያገኙት ዋጋ ቢኖር፣ በሰ
ዎች ዘንድ መታየትን ብቻ ነው። 17 አንተ
ግን፣ በምትጾምበት ጊዜ ራስህን ዘይት ተቀባ
ፊትህም የፈካ ይሁን። 18 መጾምህን፣ የልብን
መርምሮ ከሚያውቀው ከሰማዩ አባትህ በስ
ተቀር ሌላ አይወቀው። እርሱም ዋጋህን
በግልጽ ይከፍልሃል።
19 «ሊዝግና ሊሻግት፣ እንዲሁም ሊሰረቅ
በሚችልበት በዚህ ምድር ላይ ሀብትህን
አታከማች። 20 ነገር ግን ሀብትህን ሌባ ሊሰ
ርቀው በማይችልበትና የዋጋም ውጣ



ውረድ በሌለበት በሰማይ አከማች። 21 ሀብ
ትህ በሰማይ ከሆነ ልብህም እዚያው ይሆና
ልና።
22 «ዓይንህ የጠራ ከሆነ ሁለንተናህ በብ
ርሃን የተጥለቀለቀ ይሆናል። 23 ነገር ግን
ዓይንህ በክፉ አሳብና ምኞት ከታወረ፣ ጥቅ
ጥቅ ካለ ጨለማ ውስጥ ትገኛለህ ማለት
ነው። እንዲህ ያለው ጨለማ ደግሞ የዋዛ
እንዳይመስልህ!
24 «ሁለት ጌቶች ማገልገል አትች
ሉም–እግዚአብሔርንና ገንዘብን–የግድ አን
ዱን ጠልታችሁ ሌላውን መውደዳችሁ፣
ወይንም ለአንዱ ተገዝታችሁ ሌላውን መና
ቃችሁ አይቀርምና። ስለዚህ ነገር ልንገራ
ችሁ፤
25 «‘ምን እንበላለን? ምን እንጠጣለን?
ምንስ እንለብሳለን?’ በማለት አትጨነቁ።
ሕይወታችሁና መላ ሰውነታችሁ ከሚበላና
ከሚለበስ ነገር ይበልጣሉ። 26 ለምን ወፎ
ችን አትመለከቱአቸውም? ‘ምን እንበላ
ለን?’ በማለት ይጨነቃሉ? ፈጽሞ! እነርሱ
እንደሆኑ አያርሱም፤ አይዘሩም፤ አያጭዱም፤
በጎተራም አይከቱም። የሰማዩ አባታችሁ
ግን ይመግባቸዋል። እግዚአብሔር ለወፎች
ይህን ያህል የሚያስብላቸው ከሆነ፣ ለእናን
ተስ? በእውነቱ ከዚህ የበለጠ ነው የሚያስ
ብላችሁ። 27 ለመሆኑ ከእናንተ መካከል
ተጨንቆና ተጠቦ በዕድሜው ላይ የአንዲት
ቀን ጊዜ መጨመር የሚችል አለ?
28 «‘ምን እንለብሳለን?’ ብላችሁም አት
ጨነቁ። የሜዳ አበቦችን ተመልከቱአቸው።
አይፈትሉም፣ ልብስ ለማግኘትም አይለ
ፉም። 29 ያን ያህል ክብር የነበረው ንጉሥ
ሰሎሞን እንኳ፣ የአበቦችን ያህል ባማረ
ልብስ አላሸበረቀም። 30 እግዚአብሔር ዛሬ
ታይተው ነገ የሚጠፉትን አበቦች ይህን
ያህል እንዲያሸበርቁ ካደረገ፣ ለእናንተስ እን
ዴት የበለጠ አያስብላችሁም? እናንተ እም
ነት የጎደላችሁ!
31-32 «ስለዚህ፣ ‘ምን እንበላለን? ምንስ
እንለብሳለን?’ ብላችሁ ፈጽሞ አትጨነቁ።
ለምንስ እንደ አሕዛብ ትሆናላችሁ? አሕ
ዛብ ስለ እነዚህ ነገሮች አጥብቀው መጨነ
ቅና መጠበብ ያበዛሉ። እናንተ ይህ ሁሉ
እንደሚያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ
ስለሚያውቅ አትጨነቁ። 33 ከሁሉ አስቀድ
ማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና
ጽድቁን ፈልጉ። የሚያስፈልጋችሁንም ሌላ
ውን ነገር ሁሉ ለእርሱ ተዉለት። እርሱ
ይሰጣችኋል።
34 «ስለነገም አትጨነቁ። ነገ በእግዚአብ
ሔር እጅ መሆኑን እወቁ። ቁም ነገሩ ለነ
ገና ለተነገወዲያ ማሰቡን ትቶ የዕለት ዕለ
ቱን ኑሮ መኖር፣ ችግሩንና ውጣ ውረዱንም
በጽለቱ መቋቋም ነው።»

## ምዕራፍ 7

1 «ሰዎች እንዳይዘልፏችሁ በሰዎች
ላይ የዘለፋ ቃል አትሠንዝሩ። 2 በሰዎች
ላይ የምታደርጉትን ነገር እነርሱም በእና
ንተ ላይ ማድረጋቸው የማይቀር ነገር
ነውና። 3 ስለዚህ ይህን ከመሰለው አድራ
ጎት ተጠበቁ። አስቀድመህ በራስህ ዓይን
ውስጥ ያለውን ፍልጥ አውጣና ከዚያ
በኋላ በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን
ጉድፍ እይ። 4 በዓይንህ ውስጥ በተጋረ
ጠው ፍልጥ ምክንያት ማየት ተስኖህ
እያለ፣ ‘ወንድሜ ሆይ! ዓይንህ ውስጥ የገባ
ውን ጉድፍ ላውጣልህ’ እንዴት ማለት
ትችላለህ? 5 አንተ ግብዝ! አስቀድመህ በዓ
ይንህ ውስጥ የተጋረጠውን ፍልጥ አውጣ!
ከዚያ በኋላ በወንድምህ ዓይን ውስጥ የገባ
ውን ጉድፍ ለማውጣት አጥርተህ ማየት
ትችላለህ።
6 «ቅዱስ የሆነውን ነገር ለውሾች አት
ስጡ። ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት
አትጣሉ። ዕንቁውን በእግራቸው ረግግጠው
እናንተን ለማጥቃት ፊታቸውን ያዞሩባችኋ
ልና።
7 «ለምኑ፣ ይሰጣችኋል። ፈልጉ፣ ታገኛላ
ችሁ። በር አንኳኩ፣ ይከፈትላችኋል። 8 የሚ
ለምን ሁሉ ይሰጠዋል፤ የሚፈልግም ሁሉ
ያገኛል። በር ለሚያንኳኳም በሩ ይከፈትለ
ታል። 9 ከእናንተ መካከል አንድ አባት
ልጁ ዳቦ እንዲሰጠው ቢለምነው በዳቦ
ፈንታ ድንጋይ ይሰጠዋል? 10 ወይም ደግሞ
ልጁ አባቱን ዓሣ ስጠኝ ብሎ ቢለምነው፣
ዓሣ ነው ብሎ መርዛም እባብ ይሰጠዋል?
እንዴት ተደርጎ! 11 ታዲያ፣ እናንተ ልበ
ደንዳኖችና ኃጢአተኞች ሆናችሁ ሳለ ለል
ጆቻችሁ መልካም ስጦታ ማድረግ ካወቃ
ችሁ፣ የሰማዩ አባታችሁማ ለሚጠይቁት
ሁሉ መልካም ስጦታን እንዴት አይሰጣቸ
ውም?
12 «ሌሎች ሊያደርጉላችሁ የምትፈልጉ
ትን ነገር እናንተም አድርጉላቸው።
ሙሴም ነቢያትም አበክረው ያስተማሩት
ይህንኑ ነውና።
13 «መንግሥተ ሰማይ መግባት የሚቻ
ለው በጠባቡ በር በማለፍ ብቻ ነው። ወደ

ጥፋት የሚወስደው መንገድ ግን ጥርጊያ
ጐዳና ነው። ብዙዎችም ወደዚያ ጐዳና
ይጓዛሉ። [14] ነገር ግን ወደ ዘላለም ሕይወት
የሚያደርሰው መንገዱም በሩም ጠባብ
ነው። የሚገቡበትም በጣም ጥቂቶች
ናቸው።

[15] «ተኩላ መሆናቸውን በበግ ለምድ
ሰውረው ከመካከላችሁ በመግባት ከሚያሽ
ምቁ ሐሰተኞች መምህራን ተጠንቀቁ።
[16] ዛፍ በፍሬው እንደሚታወቅ፣ የእነርሱ
ንም ማንነት በሥራቸው ልታውቁ ትችላላ
ችሁ። [17] ማንኛውም ዓይነት ዛፍ በፍሬው
ተለይቶ ይታወቃል። [18] መልካም ፍሬ የሚ
ያፈራ ዛፍ፣ የማይበላ ፍሬ ሊያፈራ አይች
ልም። የማይበላ ፍሬ የሚያፈራም ዛፍ፣
ጣፋጭ ፍሬ ሊያፈራ አይችልም። [19] መል
ካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ተቆርጦ ወደ
እሳት ይጣላል። [20] ስለዚህ እነዚህንም ሐሰ
ተኞች መምህራን በሥራቸው ፍሬ ልታው
ቋቸው ትችላላችሁ።

[21] «ሃይማኖተኛ መስለው በመታየት
የሚመጻደቁ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባ
ቸው ናቸው ማለት አይደለም። እርግጥ
ብዙዎቹ፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ’ ብለው
ሊጠሩኝ ይችላሉ። ይሁን እንጂ መንግሥተ
ሰማይ ሊገቡ አይችሉም። መንግሥተ ሰማይ
መግባት የሚቻለው፣የአባቴን ፈቃድ በመፈ
ጸም ብቻ ነው። [22] በፍርድ ዕለት ብዙ
ዎች፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ ስለ አንተ
ለብዙ ሰዎች መሰክረን፣ በስምህም አጋንን
ትን አውጥተን፣ ተአምራቶችንም ሠርተን
የለም ወይ? እንዴት እንደዚህ ታደርገና
ለህ?’ ይሉኛል። [23] እኔም መልሼ፣ ‘አላው
ቃችሁም፤እናንተ ክፉ አድራጊዎች፣ከዚህ
ሂዱ!’ እላቸዋለሁ።

[24] «የማስተምረውን ትምህርት ሰምተው
የሚቀበሉና በተግባር የሚያውሉት ልባ
ሞች ናቸው። እንዲህ ያሉት ሰዎች፣ቤቱን
በጠንካራ መሠረት ላይ የሠራን ብልህ ሰው
ይመስላሉ። [25] ዝናብ ዘንቦ፣ ጐርፍ ቢጐ
ርፍ፣ ኀይለኛ ነፋስ ተነሥቶ ቤቱን ቢመታ
ውም፣ መሠረቱ ጽኑ በመሆኑ ቤቱ አይፈር
ስም።

[26] «እኔ የማስተምረውን ትምህርት ሰም
ተው የማይቀበሉና በተግባር የማያውሉት
ግን ሞኞች ናቸው። እንዲህ ያሉት ሰዎች፣
ቤቱን ባሸዋ መሠረት ላይ የሠራን ሰነፍ
ሰው ይመስላሉ። [27] ዝናብ ዘንቦ፣ ጐርፍ
ጐርፎ ኀይለኛ ነፋስም ተነሥቶ ቤቱን
ቢመታው፣ ጽኑ መሠረት ላይ ስላልቆመ
ቤቱ ይደረመሳል።» [28] ይህን ብሎ ኢየሱስ
ማስተማሩን ፈጸመ። ሕዝቡም በትምህርቱ
በጣም ተደነቀ። [29] ምክንያቱም እንደ አይ
ሁድ ሃይማኖት መምህራን ሳይሆን፣ ታላቅ
ሥልጣን እንዳለው መምህር ያስተምር ስለነ
በር ነው።

## ምዕራፍ 8

[1] ኢየሱስ ከተራራው እንደ ወረደ ብዙ
ሕዝብ ተከተለው።

[2] እነሆ፣ አንድ የለምጽ በሽታ የያዘው
ሰው ወደ ኢየሱስ ቀረበ። በጉልበቱ ተንበር
ክኮ እየሰገደለትም፣ «ጌታ ሆይ፣ ብትፈቅ
ድስ የሚያቅትህ ነገር ስለሌለ እባክህን ፈው
ሰኝ» አለው። [3] ኢየሱስም የለምጽ በሽታ
የያዘውን ሰው እየዳሰሰ፣ «ፈቅጃለሁ፣ ተፈ
ወስ» አለው። ሰውየውም ወዲያውኑ ከለ
ምጽ በሽታው ተፈወሰ። [4] ኢየሱስም ከለ
ምጽ በሽታ የተፈወሰውን ሰው፣ «መፈወስ
ህን ለማንም አታውራ፤በቀጥታ ወደ ካህን
ሄደህ እንዲያይህ አድርግ። በሙሴ ሕግ
ውስጥ፣የለምጽ በሽታ የያዘው ሰው ሲድን
ያቅርብ የተባለውንም መሥዋዕት ይዘህ
ሂድና ከለምጽ መንጻትህ በይፋ እንዲረጋ
ገጥ አድርግ» አለው።

[5-6] ኢየሱስ ቅፍርናሆም እንደ ደረሰ
አንድ ሮማዊ መኰንን ወደ እርሱ ቀርቦ
የታመመ አገልጋዩን እንዲፈውስለት ለመ
ነው። የጦር መኰንኑ አገልጋይ ሽባ ሆኖ
ነበር። [7] ኢየሱስም፣ «መልካም፣መጥቼ እፈ
ውሰዋለሁ» አለው። [8-9] ነገር ግን የጦር
መኰንኑ መልሶ፣ «ጌታ ሆይ፣ ቤቴ አንተ
የምትገባበት ቤት አይደለም፤ ከዚሁ ሆነህ
ብቻ በሽተኛውን ‘ተፈወስ!’ ብትለው ይፈ
ወሳል። እኔ ራሴ የምታዘዛቸው አለቆች
አሉ። የሚታዘዙኝ የበታቾችም አሉ። ከእነ
ርሱ አንዱን፣ ‘ሂድ!’ ስለው ይሄዳል፣ ‘ና!’
ስለውም ይመጣል። አገልጋዬም ‘አድርግ’
ብዬ ያዘዝሁትን ይፈጽማል። አንተም፣አገል
ጋዬን የያዘው በሽታ እንዲለቀው ለማድረግ
ሥልጣን እንዳለህ አውቃለሁ» አለው።

[10] ኢየሱስም መኰንኑ በተናገረው ነገር
ተገርሞ ወደ ሕዝቡ መለስ ብሎ፣ «ከእሥ
ራኤል መካከል እንዲህ ያለ እምነት ያለው
አንድ ሰው እንኳ አላገኘሁም። [11] እውነቱን
ልንገራችሁ፤ ከመላው ዓለም የመጡ ብዙ
አሕዛብ በመንግሥተ ሰማይ ግብዣ ከአብር
ሃም፣ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር አንድ ላይ
ይቀመጣሉ። [12] ነገር ግን መንግሥተ ሰማይ
ተዘጋጅቶላቸው የነበሩ ብዙ እሥራኤላው



ያን ደግሞ ልቅሶና ሥቃይ ወዳለበት
ጨለማ ይጣላሉ» አለ።

[13] የጦር መኰንኑንም፣ «ይሆንልኛል
ብለህ ያመንከው ተፈጽሞልሃልና ወደ
ቤትህ ልትሄድ ትችላለህ» አለው። የጦር
መኰንኑም አገልጋይ በዚያኑ ቅጽበት ተፈ
ወሰ።

[14] ኢየሱስም ጴጥሮስ ቤት ሲደርስ፣የጴ
ጥሮስ አማት በከባድ ትኩሳት ተይዛ ስትሠ
ቃይ አገኛት። [15] በእጁም ሲዳስሳት ወዲያ
ውኑ ትኩሳቱ ለቀቃት። ተነሥታም የሚበ
ሉትን አዘጋጀችላቸው።

[16] በዚያን ምሽት በአጋንንት የተያዙ
ብዙ ሰዎችን ወደ ኢየሱስ አመጡ። እር
ሱም ገና አንዲት ቃል ሲተነፍስ አጋንንቱ
ሁሉ ወጡ፤በሽተኞቹም ተፈወሱ። [17] በዚ
ህም፣ኢሳይያስ በትንቢቱ፣ «እርሱ ድካማች
ንን ወሰደልን፤ሕመማችንንም ተሸከመልን»
ብሎ የተናገረው ተፈጸመ።

[18] ኢየሱስ ብዙ ሰዎች በዙርያው ተሰብ
ስበው ባየ ጊዜ ደቀመዛሙርቱን ከባሕሩ
ማዶ ለመሻገር እንዲዘጋጁ አዘዛቸው።

[19] በዚህ ጊዜ፣አንድ የአይሁድ ሃይማኖት
መምህር ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፣ወደምትሄድ
በት ሁሉ ልከተልህ ተዘጋጅቻለሁ» አለው።

[20] ኢየሱስም፣ «ቀበሮዎች ጉድጓድ፣ወፎ
ችም ጎጆ አላቸው፤እኔ ግን ለራሴ እንኳ
መጠለያ የለኝም» ሲል መለሰለት።

[21] ከተከታዮቹ አንዱ ደግሞ፣ «ጌታ
ሆይ፣መጀመሪያ ሄጄ አባቴን እንድቀብረው
ፍቀድልኝ» አለ።

[22] ኢየሱስም፣ «በመንፈስ ሙታን የሆኑ
ሙታናቸውን ይቅበሩ። አንተ ግን ተከተ
ለኝ» አለው።

[23] ከዚያም በጀልባ ሆኖ ከደቀመዛሙ
ርቱ ጋር ሐይቁን ያቋርጥ ነበር። [24] በጉዞም
ላይ እንዳሉ፣ ኃይለኛ ማዕበል ተነሥቶ ያስ
ቸግራቸው ጀመር። ኢየሱስ ተኝቶ ስለ
ነበር፣ [25] ደቀመዛሙርቱ ቀሰቀሱትና፣
«ጌታ ሆይ! ማለቃችን ነው፣ አድነን!»
አሉት።

[26] እርሱም፣ «እናንተ እምነት የጐደላ
ችሁ! እኔ እያለሁ እንዴት ትፈራላችሁ?»
አለና ተነሥቶ ነፋሱንና ማዕበሉን ገሠጸ።
ወዲያውም ማዕበሉ ቆመ፤አካባቢውም ጸጥ
አለ። [27] ደቀመዛሙርቱም በመደነቅ፣ «ነፋ
ሱም ማዕበሉም እንዲህ የሚታዘዙለት እሱ
ማን ነው?» እያሉ እርስ በእርሳቸው ተጠያ
የቁ።

[28] ባሕሩን ተሻግረው ጌርጌሴኖን ወደሚ
ባለው ቦታ እንደደረሱ፣በአጋንንት የተለከፉ
ሁለት ሰዎች ወደ ኢየሱስ ቀረቡ። እነዚ
ህም ሰዎች በመቃብር ቤት ውስጥ ይኖሩ
ነበር። ያገኙትንም ሁሉ ክፉኛ ይተናኰሉ
ስለ ነበር እነርሱ ወደሚኖሩበት አካባቢ
ለመድረስ የሚደፍር አልነበረም።

[29] በሰዎቹም ውስጥ ያደሩት አጋንንት፣
«የእግዚአብሔር ልጅ ሆይ፣ከእኛ ጋር ምን
ጉዳይ አለህ? ፍዳ የምንቀበልበት ጊዜ ሳይ
ደርስ ልታሠቃየን ነውን?» እያሉ ጮኹ።

[30] በአካባቢውም አንድ የአሳማ መንጋ
ተሰማርቶ ነበር። [31] አጋንንቱም ኢየሱስን፣
«ከሰዎቹ የምታስወጣን ከሆነ፣ አሳማዎቹ
ውስጥ እንድንገባ አድርገን» ሲሉ ለመኑት።
ኢየሱስም ፈቀደላቸው።

[32] አጋንንቱም ከሰዎቹ ወጥተው በአሳማ
ዎቹ ውስጥ ገቡባቸው። አሳማዎቹም ከነበ
ሩበት አፋፍ እየደነበሩ በጥድፊያ ወርደው
ባሕር ውስጥ ሰጥመው አለቁ። [33] የአሳማ
ዎቹ እረኞችም በአቅራቢያው ወደ ነበረች
ከተማ እየሮጡ ሄደው በአሳማዎቹና በአጋን
ንት በተለከፉት ሰዎች ላይ የሆነውን ሁሉ
ለከተማው ሕዝብ አወሩ። [34] ሕዝቡም ኢየ
ሱስን ለማየት እንዳለ ተገልብጦ ወጣ። በመ
ጨረሻም፣ አገራቸውን ለቅቆ እንዲሄድላ
ቸው ለመኑት።

## ምዕራፍ 9

[1] ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጀልባ ሐይቁን
ተሻግሮ ማረፊያው ወደ ሆነው ወደ ቅፍ
ርናሆም ሄደ።

[2] ወዲያውም ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በቃ
ሬዛ ተሸክመው ወደ እርሱ አመጡ። ኢየሱ
ስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን ሰው፣
«ልጄ ሆይ፣ አይዞህ! ኃጢአትህን ይቅር
ብዬልሃለሁ» አለው።

[3] በዚያ የነበሩ የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራንም ይህን ሲሰሙ፣ «ይኸማ እግዚ
አብሔርን መድፈር ይባላል። እንዴትስ
ራሱን ከእግዚአብሔር እኩል አድርጎ ይቆጥ
ራል?» በማለት ማጉረምረም ጀመሩ።

[4] ኢየሱስ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራ
ንን አሳብ በማወቅ፣ «ለምን እንዲህ ያለ
ክፉ አሳብ ታስባላችሁ? [5] የቱ እንደሚቀል
እስቲ ልጠይቃችሁ? ‘ኃጢአትህን ይቅር
ብዬልሃለሁ’ ማለት ይቀላል? ወይንስ ‘ተነ
ሥና ሂድ’ ማለት? [6] በዚህች ምድር ላይ
ኃጢአትን ይቅር ለማለት እንደምችል አታ
ውቁምን? ኃጢአትን ይቅር ለማለት ሥል
ጣን እንዳለኝ ላረጋግጥላችሁ» አለና ወደ

ሽባው ልጅ ሆር ብሎ፣ «ተፈውሰሃል፤
ተነሥ! ቃሬዛህንም ይዘህ ወደ ቤትህ ሂድ»
አለው።
7 ሽባውም ሰው ተነሥቶ መንገዱን
ቀጠለ።
8 ሕዝቡም በፊታቸው የተፈጸመውን
ይህን ተአምር ካዩ በኋላ ፈሩ። እንዲህ ያለ
ውን ሥልጣን ለሰው በመስጠቱም እግዚአ
ብሔርን ከልብ አመሰገኑት።
9 ኢየሱስም ከዚያ ተነሥቶ እንደ ሄደ፣
ቀረጥ ሰብሳቢውን ማቴዎስን በቀረጥ መቀበ
ያው ሥፍራ ተቀምጦ አገኘውና፣ «ደቀመ
ዝሙሬ አደርግሃለሁ፤ ተከተለኝ» አለው።
ማቴዎስም ከቀረጥ መቀበያ ሥፍራው ተነ
ሥቶ ኢየሱስን ተከተለው።
10 ከዚያም ማቴዎስ ለኢየሱስ የምሳ
ግብዣ እቤቱ አደረገለት። በግብዣው ላይ
ቀራጮችና ኃጢአተኞች ከኢየሱስና ከደቀ
መዛሙርቱ ጋር ተቀምጠው ነበር። 11 ፈሪሳ
ውያንም በቁጣ ቃል ደቀመዛሙርቱን፣
«መምህራችሁ ከኃጢአተኞችና ከቀራጮች
ጋር እንዴት አብሮ ይበላል?» ሲሉ ጠየቋ
ቸው። 12 ኢየሱስም የሰጣቸው መልስ፣
«በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈ
ልጋቸውም» የሚል ነበር። 13 ንግግሩንም
በመቀጠል፣ «'ከእናንተ የምፈልገው መሥ
ዋዕታችሁንና ስጦታችሁን ሳይሆን፣ ምሕረ
ትን እንድታደርጉ ነው' ተብሎ የተነገረ
ውን የመጽሐፍ ቃል ሄዳችሁ በሚገባ
አጢኑ። እኔ ወደዚች ዓለም የመጣሁት
'እለኛ ማን ሰው አለ!' ብለው የሚመጻደቁ
ትን ለመንከባከብ ሳይሆን፣ ኃጢአተኞች
ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ጥሪ ለማድ
ረግ ነው» አላቸው።
14 አንድ ቀን የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመ
ዛሙርት ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ «ደቀመዛ
ሙርትህ እንደ እኛና እንደ ፈሪሳውያን የማ
ይጾሙት ለምንድነው?» ሲሉ ጠየቁት።
15 ኢየሱስም፣ «ሙሽራ አብሮአቸው እያለ
ሚዜዎች ማዘን፣ መጾም ይገባቸዋል?» ሲል
ጠየቃቸው። ከዚያም፣ «እኔ ከእነርሱ የምለ
ይበት ጊዜ ይመጣል፤ ያኔ ይጾማሉ» አላ
ቸው።
16 «ለመሆኑ በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ
እራፊ የሚጥፍ ሰው አለ? ይህ ከሆነማ፣
አዲሱ እራፊ አሮጌውን ልብስ በጭቆ በማን
ጣት ቀዳዳውን የባሰ ያሰፋዋል። 17 በአሮጌ
የወይን ማስቀመጫ ስልቻ አዲስ የወይን
ጠጅ ማን ያኖራል? ይህ ከሆነማ ወይኑ
ሲፈላ ስልቻው ይፈነዳል፤ የወይን ጠጁም
ይፈስሳል፤ ስልቻውም ከጥቅም ውጭ ይሆ
ናል። ለአዲስ የወይን ጠጅ ማስቀመጫ
የሚሆነው አዲስ ስልቻ ነው። እንዲህ
ከሆነ፤ ወይኑንም ስልቻውንም ማቆየት ይቻ
ላል» አላቸው።
18 ኢየሱስ ይህንን ሲናገር፣ የአካባቢው
ምኩራብ አለቃ ከፊቱ ቀርቦ እጅ ከነሣው
በኋላ፣ «ልጄ አሁን ሞተችብኝ፤አንተ መጥ
ተህ ብትዳስሳት ግን በሕይወት ትኖራለች»
ሲል ተማጸነው።
19 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ
ወደ መምህሩ ቤት ሲሄድ፣ 20 አሥራ
ሁለት ዓመት ሙሉ ደም እየፈሰሳት ትታ
መም የነበረች አንዲት ሴት ቀስ ብላ ከኋ
ላው በኩል የልብሱን ጫፍ ነካች። 21 ይህን
ንም ልታደርግ የበቃችው ቀደም ሲል፣
«የልብሱን ጫፍ እንኳ ብዳስስ እፈወሳ
ለሁ» የሚል እምነት ስላደረባት ነበር።
22 ኢየሱስም ወደኋላው ዘወር ብሎ ሴቲ
ቱን፣ «ልጄ ሆይ፣አይዞሽ፣እምነትሽ አድኖ
ሻል» አላት። ሴቲቱም ወዲያውኑ ፍጹም
ጤነኛ ሆነች።
23 ኢየሱስ ወደ አይሁዱ መምህር ቤት
ሲደርስ፣ ሰዎች ተሰብስበው ሲላቀሱ አገኛ
ቸው። 24 ኢየሱስም፣ «አልቃሾቹን ወደ
ውጭ አውጧቸው። ልጅቱ ተኝታለች
እንጂ አልሞተችም» አላቸው። ሰዎቹም
ኢየሱስ የተናገረውን ቃል ሲሰሙ፣ «የሞተ
ችውን ልጅ ተኝታለች ይለናል እንዴ?»
ብለው አፌዙበት።
25 አልቃሾቹ ወደ ደጅ ከወጡ በኋላ
ኢየሱስ ልጅቷ ወደ ተኛችበት ክፍል ገባ።
እጅዋንም ያዘ። ልጅቱም ብድግ ብላ
ቆመች። 26 ኢየሱስ ያደረገው ተአምር በአ
ካባቢው ሁሉ ተሰራጨ።
27 ኢየሱስ ከልጅቱ ቤት እንደ ወጣ
ሁለት ዕውር ሰዎች «የዳዊት ልጅ ሆይ፣
ማረን» እያሉ በመጮኽ ተከተሉት።
28 ሁለቱ ዕውሮችም ኢየሱስ ወደሚኖር
በት ቤት ተከትለውት ገቡ። ኢየሱስም ሁለ
ቱን ዕውሮች፣ «ዓይናችሁን ላበራላችሁ እን
ደምችል ታምናላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው።
እነርሱም፣ «ጌታ ሆይ፣አዎን እናምናለን»
ሲሉ መለሱለት።
29 ከዚያም ኢየሱስ ዓይናቸውን በመዳ
ሰስ፣ «በማመናችሁ ምክንያት ተፈውሳች
ኋል» አለ። 30 ወዲያውም ሁለቱ ዕውሮች
ዓይኖቻቸው በርተውላቸው ለማየት ቻሉ።
በዚህ ጊዜ ኢየሱስ፣ የፈወሳቸው መሆኑን
ለማንም እንዳይናገሩ በጥብቅ አስጠነቀቃ



ቸው። 31 እነርሱ ግን የኢየሱስን ዝና በከተ
ማው ሁሉ ነዙት።
32 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ሌላ ቦታ
ሲሄድ፣ ጋኔን አድሮበት እንደበቱ የተዘጋ
ሰው አጋጠመው። 33 ኢየሱስም ሰውየውን
ድዳ ያደረገውን ጋኔን አስወጣለት። ድዳ
ውም እንደበቱ ወዲያውኑ ተፈትቶ መናገር
ቻለ። ሕዝቡም፣ «ይህስ እፁብ ድንቅ
ነው። እንዲህ ያለውን ተአምር በእሥራኤል
ምድር አይተን አናውቅም!» አሉ።
34 በዚህ ጊዜ ፈሪሳውያን፣ «አጋንንትን
የሚያወጣው፣የአጋንንት አለቃ የሆነው ሰይ
ጣን ስላደረበት ነው» አሉ።
35 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በከተሞችና በአካ
ባቢው መንደሮች፣ እንዲሁም በአይሁድ
ምኩራቦች እየተዘዋወረ የእግዚአብሔርን
መንግሥት የምሥራች ቃል ሰበከ። በደረሰ
በት ሁሉ ሕመምተኞችን ከተለያዩ በሽታ
ዎች ፈወሰ። 36 ወደ እርሱም ይጐርፉ የነበ
ሩት ሰዎች፣ችግራቸው የበዛና እርዳታ ለማ
ግኘት ወዴት መሄድ እንደሚገባቸው የማ
ያውቁ መሆናቸውን በመረዳቱ ራራላቸው።
ሁኔታቸው ሁሉ ልክ እረኛ እንደ ሌላቸው
በጎች ነበር።
37 ደቀመዛሙርቱንም፣ «መከሩ ብዙ
ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው።
38 የመከሩ ባለቤት ተጨማሪ ሠራተኞች
በእርሻው ቦታ እንዲያሠማራ ጸልዩ» አላ
ቸው።

## ምዕራፍ 10

1 ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙ
ርት ወደ ፊቱ እንዲቀርቡ አድርጎ፣ርኩ
ሳን መናፍስትን እንዲያወጡ፣ እንዲሁም
ማንኛቸውንም ዓይነት በሽታና ሕመም የያ
ዛቸውን ሰዎች እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣ
ቸው።
2-4 የአሥራ ሁለቱም ደቀመዛሙርት
ስም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፣
ስምዖን (ጴጥሮስ የተባለው)
እንድርያስ (የጴጥሮስ ወንድም)
ያዕቆብ (የዘብዴዎስ ልጅ)
ዮሐንስ (የያዕቆብ ወንድም)
ፊልጶስ
በርተሎሜዎስ
ቶማስ
ማቴዎስ (ቀረጥ ሰብሳቢው)
ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)
ታዲዎስ
ስምዖን («ቀናተኞች» በሚል ስም የታ
ወቀው ስውር የፖለቲካ ቡድን አባል
የነበረው)
የአስቆሮቱ ይሁዳ (በኋላ ኢየሱስን አሳ
ልፎ የሰጠው)።
5 ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሚከተለውን
መመሪያና ትዕዛዝ ሰጣቸውና በሥራ ላይ
እንዲሠማሩ አደረጋቸው፤ «ወደ አሕዛብና
ወደ ሳምራውያን አትሂዱ። 6 ነገር ግን ወደ
ጠፉት በጎች ወደ እሥራኤል ሕዝብ ብቻ
ሂዱ። 7 የእግዚአብሔር መንግሥት መቅረብ
ዋንም ንገሩአቸው። 8 ሕመምተኞችን
ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን
አንጹ፤አጋንንትን አውጡ። በነፃ የተቀበላች
ሁትንም በነፃ ስጡ።
9 «ለስንቅ ብላችሁ ገንዘብ አትያዙ።
10 ትርፍ ልብስና ትርፍ ጫማ፣ ከረጢት
ወይም ለምርኩዝ የሚሆን በትር እንኳ አት
ያዙ። አገልግሎታችሁን የምታበረክቱላቸው
ሰዎች ምግባችሁን ይሰጡአችኋል። 11 ከአ
ንድ ከተማ ወይም መንደር በምትደርሱበት
ጊዜ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ሰው
ፈልጋችሁ፣ ያንን ከተማ ለቅቃችሁ እስከም
ትሄዱበት ጊዜ በቤቱ እረፉ። 12 ማንኛውም
ሰው ቤት፣ ሰላምታ ሰጥታችሁ ግቡ።
13 ቤቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረበት ከሆነ
ቡራኬአችሁ ይድረሰው፣ ፈሪሃ እግዚአብ
ሔር ያላደረበት ቤት ከሆነ ግን ቡራኬአ
ችሁ አይድረሰው። 14 አንድ ከተማ ወይም
አንድ ቤት ደርሳችሁ የሚያስተናግዳችሁ
ካጣችሁ፣ ያንን ሥፍራ ለቅቃችሁ ከመሄዳ
ችሁ በፊት የጫማችሁን አቧራ አራግፉ።
15 አትጠራጠሩ፣ በመጨረሻው የፍርድ ቀን
ከእነዚህ ከተሞች ፍርድ ይልቅ፣ በክፋታ
ቸው የታወቁት የሰዶምና የገሞራ ፍርድ
ይቀላል።
16 «እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል
እልካችኋለሁ። ስለዚህ እንደ እባብ ብል
ሆች፣ እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።
17 ሰዎች ይይዟችኋል፤ ያስሯችኋል፤ ፍርድ
ቤትም ያቀርቧችኋል። በምኩራቦቻቸውም
ውስጥ ይገርፏችኋል። 18 በእኔ ምክንያት
ተከሳችሁ በገዥዎችና በባለሥልጣኖች ፊት
ትቀርባላችሁ። የዚያን ጊዜ ስለ እኔ ለመና
ገር፣ አልፎ ተርፎም ለዓለም ለመመስከር
ዕድል ታገኛላችሁ።
19-20 «ተይዛችሁ ስትታሰሩና ስትመረ
መሩ፣ 'ለዚህ የምንሰጠው መልስ ምን
ይሆን?' ብላችሁ አትጨነቁ። ምክንያቱም
ለሚቀርብላችሁ ጥያቄ ተገቢውን መልስ
በተገቢው ጊዜ ታገኛላችሁና። እንደ እው

ነቱ ከሆነ ለሚቀርብላችሁ ጥያቄ መልስ
የምትሰጡት እናንተ ሳትሆኑ፣የሰማዩ አባታ
ችሁ፣መንፈስ ቅዱስ በእናንተ አንደበት እን
ዲናገር ያደርገዋል።
21 «ወንድም የገዛ ወንድሙን ለሞት
አጋልጦ ይሰጣል፤አባቶች የገዛ ልጆቻቸውን
አሳልፈው ይሰጣሉ። ልጆችም በወላጆቻ
ቸው ላይ ተቃውሞ ያነሣሉ፤ ያስገድሏቸ
ዋል። 22 በእኔ በማመናችሁ ምክንያት
ሰዎች ይጠሉአችኋል። ይህንን ሁሉ እስከ
መጨረሻው የታገሠ ግን ይድናል።
23 «ከአንድ ከተማ ሲያሳድዱአችሁ ወደ
ሌላ ከተማ ሽሹ። በመላው እሥራኤል ያሉ
ትን ከተሞች ሁሉ ከማዳረሳችሁ በፊት
ተመልሼ እመጣለሁ። 24 ተማሪ ከመምህሩ፣
ሎሌ ከጌታው አይበልጥም። 25 ተማሪ የመ
ምህሩ ፣ ሎሌም የጌታው ዕድል ተካፋይ
መሆን ይበቃዋል። ስለዚህ እኔን የቤ
ቱን ጌታ ‘ብዔል ዜቡል’–የአጋንንት
አለቃ–ብለው ከሰደቡ እናንተንማ ከዚህ የበ
ለጠ መሳደባቸው የት ይቀራል! 26 ሆኖም
የሚያስፈራሩዋችሁን አትፍሩአቸው። እው
ነት የምትገለጥበት፣ስውር ሴራቸው በአደባ
ባይ የሚወጣበት ጊዜ ይመጣልና።
27 «ስለዚህ አሁን በጨለማ የምነግራች
ሁን ፀሐይ ስትወጣ በገሀድ ተናገሩት። በጆ
ሮአችሁ የምነግራችሁን በአደባባይ አው
ጁት!
28 «ሥጋችሁን እንጂ ነፍሳችሁን ሊገ
ድሉ የማይችሉትን አትፍሩ። መፍራት ያለ
ባችሁ ፣ ሥጋችሁንና ነፍሳችሁን በገሃነም
እሳት ሊያጠፋ የሚችለውን እግዚአብሔርን
ብቻ ነው። 29 ሁለቱ ባንድ ሳንቲም ከሚሸ
ጡት ድንቢጦች አንዲቷ እንኳን የሰማዩ
አባታችሁ ሳያውቅ በምድር ላይ ወድቃ
አትቀርም። 30 ሌላው ቀርቶ የጸጉራችሁ
ብዛት እንኳን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቆ
ጥሮ የተቀመጠ ነው። 31 ስለዚህ ፣ለእግዚአ
ብሔር ከብዙ ድንቢጦች ስለምትበልጡ
በት፣በምንም አትጨነቁ።
32 «በሰው ፊት በግልጽ የሚመሰክር
ልኝ፣እኔም በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመ
ሰክርለታለሁ። 33 ነገር ግን በሰው ፊት በግ
ልጽ የሚክደኝን ፣ እኔም በሰማይ ባለው
አባቴ ፊት በይፋ እክደዋለሁ።
34 «እኔ የመጣሁት ለዓለም ሰላምን ለማ
ምጣት አይምሰላችሁ ፤ ሰይፍን ለማምጣት
እንጂ። 35 እኔ የመጣሁት፣ወንድ ልጅን በአ
ባቱ፣ሴት ልጅን በእናትዋ፣ምራትን በአማ
ትዋ ላይ ፣ በቃሌ ምክንያት ለማስነሣት
ነው። 36 የሰው ጠላቶቹ የገዛ ቤተሰቦቹ ይሆ
ናሉ። 37 እናትና አባታችሁን ከእኔ አብልጣ
ችሁ የምትወዱ ከሆነ የእኔ አይደላችሁም።
ወንድ ልጃችሁን ወይም ሴት ልጃችሁን
ከእኔ አብልጣችሁ ከወደዳችሁም የእኔ አይ
ደላችሁም። 38 የሚመጣባችሁን መከራ
ታግሣችሁ ልትከተሉኝ ካልፈቀዳችሁ፣የእኔ
አይደላችሁም።
39 «ነፍሱን የሙጥኝ የሚል ያጣታል፤
ነፍሱን ለእኔ ሲል አሳልፎ የሚሰጥ ግን
ይታደጋታል።
40 «እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል።
እኔንም የሚቀበል የላከኝን አባቴን ይቀበ
ላል። 41 የእግዚአብሔር መልእክተኛ በመ
ሆኑ ምክንያት አንድን ነቢይ የሚቀበል ፣
ነቢዩ የሚያገኘውን ዋጋ ያገኛል። የእግዚአ
ብሔር ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት፣ፈሪሃ
እግዚአብሔር ያደረባቸውን ሰዎች የሚቀ
በል ፣ ለእነርሱ የሚሰጠውን ዋጋ ያሀል ያገ
ኛል። 42 የእኔ ደቀመዝሙር በመሆኑ ከእነ
ዚህ ከታናናሾች ለአንዱ ፣ አንድ ብርጭቆ
ውኃ የሰጠ ዋጋውን አያጣም።»

## ምዕራፍ 11

1 ኢየሱስ ለአሥራ ሁለቱ ደቀመዛሙ
ርት መመሪያውን ሰጥቶ ከጨረሰ በኋላ፣
እነርሱ እንዲጉበኙአቸው በተመደቡበት
ከተሞች እየተዘዋወረ ስብከቱን ቀጠለ።
2 ታስሮ የነበረው መጥምቁ ዮሐንስም ኢየ
ሱስ ያደርጋቸው ስለነበሩት ተአምራት
በመስማቱ ደቀመዛሙርቱን ወደ ኢየሱስ
ሄደው ፣ 3 «ይመጣል ብለን የምንጠብቀው
በእርግጥ አንተ ነህ? ወይስ ሌላ ተስፋ እና
ድርግ?» ብለው እንዲጠይቁት አደረገ።
4 ኢየሱስም ለመልእክተኞቹ የሚከተለ
ውን መልስ ሰጣቸው። «ሂዱና ያያችሁትን
ተአምራትና የሰማችሁትን ሁሉ ለዮሐንስ
ንገሩት። 5 ዕውሮች ያያሉ ፤ አንካሶች ያለ
ምርኩዝ ይራመዳሉ፤ለምጻሞች ይነጻሉ፤ደን
ቆሮዎች ይሰማሉ ፤ ሙታን ይነሣሉ። ለድሆ
ችም ወንጌል መሰበኩን ንገሩት። 6 በተጨ
ማሪም ፣ ‘በእኔ የማይጠራጠር ምስጉን ነው’
በሉት።»
7 የዮሐንስ ደቀመዛሙርት ከሄዱ በኋላ
ኢየሱስ ለሕዝቡ ፣ ስለ ዮሐንስ የሚከተለውን
ተናገረ። «ዮሐንስን ለማየት ወደ በረሃ በሄ
ዳችሁ ጊዜ ፣ ለመሆኑ ምን ይመስላል ብላ
ችሁ ገምታችሁ ነበር? ነፋስ የሚያወዛውዘ
ውን ሸንበቆ ይመስላል ብላችሁ ነበርን?
8 ወይስ በቤተ መንግሥት ውስጥ እንደሚ



ኖር መስፍን አሸብርቆ የምታገኙት መስሏ
ችሁ ነበር? 9-10 ወይስ አንድ የእግዚአብ
ሔር ነቢይ እናያለን ብላችሁ ገምታችሁ
ነበር? አዎን ፣ ዮሐንስ ከነቢይም የበለጠ
ነው። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ፣ ከእኔ
ቀደም ብሎ እንደሚመጣና ስለመምጣቴም
ለሰዎች እያወጀ እንዲቀበሉኝ እንደሚያዘጋ
ጃቸው የተጻፈለት ዮሐንስ ነው። 11 እስከ
ዛሬ ድረስ በምድር ላይ ከተወለዱት ሰዎች
መካከል ፣ ዮሐንስን የሚስተካከለው የለም።
ይሁን እንጂ በመንግሥተ ሰማይ ከሁሉ
ያነሰ ነው የሚባለው ሰው ይበልጠዋል።
12 እርሱ መስበክና ማጥመቅ ከጀመረበት
ጊዜ አንሥቶ እስከ ዛሬ ድረስ ፣ መንግሥተ
ሰማይ ብዙ የኃይል ግፊት ደርሶባታል፣ጉል
በተኞችም ገፍተው ሊይዟት ይታገላሉ።
13 የሙሴ ሕጎችና ነቢያት እስከ ዮሐንስ
ድረስ ትንቢት ተናገሩ። 14 ወቅቱ ሲደርስ
ዮሐንስ መጣ፤እኔ የምናገረውን ቃል ለማስ
ተዋል ፈቃደኞች ከሆናችሁ ፣ ነቢያት የጊ
ዜው ፍጻሜ ሲደርስ ይመጣል ብለው ትን
ቢት የተናገሩለት ኤልያስ ፣ ዮሐንስ ራሱ
ነው። 15 ለመስማት ፈቃደኞች ከሆናችሁ
ልብ ብላችሁ አድምጡ።
16 «ስለዚህ ዘመን ሰዎች ምን ማለት
እችላለሁ? የዚህ ዘመን ሰዎች በጨዋታ
ላይ ያሉ ልጆችን ይመስላሉ። 17 ልጆቹ
እርስ በርሳቸው እንዲህ ይባባላሉ ፣ ‘ከበሮ
መታንላችሁ፤እናንተ ግን አልዘፈናችሁም፤
ሙሾ አወረድንላችሁ፤እናንተ ግን አላለቀሳ
ችሁም።’ 18 መጥምቁ ዮሐንስ ፣ የወይን
መጠጥ በአፉ የማይዞር አብዛኛውን ጊዜ
እህል እንኳን የማይቀምስ ሰው ነው። እናን
ተም ፣ ‘ይህስ ያበደው ነው!’ አላችሁት።
19 እኔ የሰው ልጅ ደግሞ ፣ ስበላና ስጠጣ
ብታዩኝ፣ ‘ይህማ ሆዳምና ጠጪ ነው፤ውሎ
ውም ከኃጢአተኞች ጋር ነው’ አላችሁኝ።
ከእግዚአብሔር የሚገኝ ጥበብ በሥራው
ውጤት ይታወቃል።»
20 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ብዙ ተአምራት
የሠራባቸውን ከተሞች በንስሐ ወደ እግዚአ
ብሔር ባለመመለሳቸው ምክንያት፣እንዲህ
ሲል ይወቅሳቸው ጀመር።
21 «ወዮልሽ ኮራዚን! ወዮልሽ ቤተ
ሳይዳ! በእናንተ ዘንድ የሠራሁትን ተአም
ራት፣ክፉ በተባሉት በጢሮስና በሲዶና ከተ
ሞች ብሠራ ኖሮ ፣ ገና ድሮ ማቅ ለብሰው
አመድ ነስንሰው ንስሐ በመግባት ወደ እግ
ዚአብሔር በተመለሱ ነበር። 22 እንደ እው
ነቱ ከሆነ ፣ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ
የጢሮስና የሲዶና ከተሞች የተሻለ ዕድል
ይገጥማቸዋል። 23 አንቺም ቅፍርናሆም
ሆይ! ምንም እንኳን ለጊዜው ከፍ ያልሽ
መስለሽ ብትታይ ፣ ወደ አዘቅት (ገሃነም)
መውረድሽ የማይቀር ነው። ምክንያቱም
በአንቺ ዘንድ የተሠሩት ተአምራት በሰዶም
ተሠርተው ቢሆን ኖሮ ሰዎችዋ ንስሐ በገቡ
ነበር። 24 ስለዚህ በፍርድ ቀን ከአንቺ
ቅጣት ይልቅ የሰዶም ከተማ ነዋሪዎች
ቅጣት ይቀላል።»
25 ቀጥሎም ኢየሱስ የሚከተለውን
ጸሎት ጸለየ። «የሰማይና የምድር ፈጣሪ
የሆንከው አባቴ ሆይ፣ይህንን እውነት ከጥበ
በኞችና ከአዋቂዎች ሰውረህ ለሕፃናት ስለገ
ለጥክላቸው አመሰግንሃለሁ። 26 አዎን፣አባት
ሆይ! ቀድሞውኑ እንዲህ እንዲሆን ፈቃ
ድህ ነውና።»
27 «አብ ሁሉን ነገር ሰጥቶኛል። ወል
ድን የሚያውቀው አብ ብቻ ነው፤አብንም
የሚያውቀው ወልድና ወልድም የሚገልጽ
ላቸው ብቻ ናቸው። 28 የሸከማችሁ ብዛት
ያደከማችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ፣እኔም አሳር
ፋችኋለሁ። 29 የእኔን ቀንበር ብትሸከሙ
ከእኔም ብትማሩ ፣ እኔ ታጋሽ በልቤም
ትሁት ነኝና የነፍስ እረፍት ታገኛላችሁ።
30 ቀንበሬ ቀላል ነው ፣ ሸክሜም አይከብ
ድም።»

## ምዕራፍ 12

1 በዚሁ ጊዜ አካባቢ ፣ ኢየሱስ ደቀመዛ
ሙርቱን አስከትሎ በእርሻ መካከል አቋ
ርጦ ያልፍ ነበር። ዕለቱ የሰንበት ቀን
ነበር። ደቀመዛሙርቱ ተርበው ስለነበር የስ
ንዴ እሸት እየቀጠፉ አሽተው ይበሉ
ጀመር።
2 ይህንንም የተመለከቱ ፈሪሳውያን በተ
ቃውሞ ቃል ፣ «ደቀመዛሙርትህ በሰንበት
ቀን ስንዴ ቀጥፈው አሽተው መብላታ
ቸው ፣ ሕግን መተላለፍ አይደለም ወይ?»
አሉት።
3 ኢየሱስም እንዲህ አላቸው ፤ «እርሱና
አብረውት የነበሩት ሰዎች በተራቡ ጊዜ
ንጉሥ ዳዊት ምን እንዳደረገ የተጻፈውን
አላነበባችሁም? 4 ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ
ለካህናት ብቻ የተፈቀደውን ሕብስት ከወ
ሰደ በኋላ ከተከታዮቹ ጋር በልተዋል።
ታዲያ በዚህ አድራጎታቸው ሕግን ተላለፉ
ተብለው ተወቀሱ? 5 በሙሴ መጻሕፍት ፣
ቤተ መቅደስ ውስጥ በአገልግሎት ላይ የተ
መደቡት ካህናት በሰንበት ቀን መሥራት

ያለባቸው መሆኑንስ አላነበባችሁም?
6 እንደ እውነቱ ከሆነ፣ከቤተ መቅደስ የሚ
በልጥ እነሆ ከፊታችሁ አለ! 7 ‘መሥዋዕት
ከምታቀርቡልኝ ይልቅ ምሕረትን እንድታ
ደርጉ እመርጣለሁ’ የሚለውን የመጽሐፍት
ቃል አስተውሉ። ይህን ካስተዋላችሁ በንጹ
ሐን ላይ ለመፍረድ አይቃጣችሁም። 8 የሰን
በት ጌታዋ እኔ ነኝና።»
9 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በአቅራቢያው ወዳ
ለው ምኵራብ ሲገባ፣ 10 አንድ እጁ ሽባ
የሆነ ሰው አየ። ኢየሱስን በተንኰል ለማጥ
መድ የሚፈልጉ ሰዎችም ቀርበው፣ «በሰን
በት ቀን በሽተኛን መፈወስ ይገባል? ወይስ
አይገባም?» ብለው ጠየቁት። 11 ኢየሱስም
እንዲህ ሲል መለሰላቸው። «ከእናንተ መካ
ከል አንድ በግ ያለው ሰው ቢኖርና ይህ
ችው በግ፣ በሰንበት ቀን ጉድጓድ ውስጥ
ብትገባበት፣ ያችን በግ በሰንበት ቀን ከጉድ
ጓድ ያወጣታል? ወይስ አያወጣትም? እን
ደሚያወጣት ግን ጥርጥር የለውም።
12 ታዲያ አንድ ሰው ከአንዲት በግ በጣም
የከበረ አይደለምን? አዎን፣ በሰንበት ቀን
በጎ ነገር መሥራት ተገቢ ነው።» 13 ይህን
ንም ተናግሮ እንደ ጨረሰ ሽባውን ሰው፣
«እጅህን ዘርጋ!» አለው። ሰውየውም እጁን
ዘረጋ። እጁም ፍጹም ጤነኛ ሆነ። 14 ፈሪሳ
ውያንም ኢየሱስን ለማስያዝና ለማስገደል
ውስጥ ውስጡን አድማ ይመቱ ጀመር።
15 ኢየሱስ ግን ተንኰላቸውን ስለተረዳ
ከተከታዮቹ ጋር ከምኵራባቸው ወጣ። ከተ
ከተሉትም መካከል በሽታ የነበረባቸውን
ፈወሰ። 16 ነገር ግን እርሱ ስለሚሠራቸው
ተአምራት ወሬው እንዳይዛመት አስጠንቀ
ቃቸው። 17 ይህም ሁሉ የሆነው፣ነቢዩ ኢሳ
ይያስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ የተናገረው
ቃል ይፈጸም ዘንድ ነበር።
18 «የመረጥኩትን አገልጋዬን ተመል
ከቱ። ነፍሴ በእርሱ ደስ ይላታል፣መንፈሴ
ንም በላዩ አደርጋለሁ ለሰዎች ሁሉ ያለ
አድልዎ ይፈርዳል። 19 ማንንም አይፋለ
ምም ፤ ከፉ ቃል ከአንደበቱ አይወጣም ፤
ድምፁንም አያሰማም። 20 ደካሞችን አይጫ
ንም ፤ የመጨረሻዋን ተስፋም አያፍንም።
ጠብን ሁሉ በመጨረሻ ድሉ ይሽራል።
21 የዓለምም ሕዝቦች በስሙ ተስፋ ያደር
ጋሉ።»
22 ከዚያም ጋኔን አድሮበት ማየትና መና
ገርም የተሳነው አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ
አመጡ፤እርሱም ፈወሰው። በሽተኛው መስ
ማትም መናገርም ቻለ። 23 ይህንንም የተመ
ለከቱት ሰዎች እጅግ ተደንቀው፣ «ኢየሱስ
መሲሕ ሳይሆን አይቀርም» አሉ።
24 ፈሪሳውያንም ጌታ ስላደረጋቸው ተአ
ምራት ሲሰሙ፣ «እርሱ እኮ አጋንንትን
የሚያወጣቸው በአጋንንት አለቃ በብዔል
ዜቡል ኃይል ነው» አሉ።
25 ኢየሱስም የሚያስቡትን ያውቅ ስለ
ነበር እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ «ውስጣዊ
ኅብረት የጐደለው መንግሥት ይወድቃል።
ጠብና መለያየት ያለበት ከተማ ወይም
ትዳር ጸንቶ አይኖርም። 26 እናንተ እንደም
ታስቡት ሰይጣን ሰይጣንን የሚያስወጣ
ከሆነ፣ሰይጣን ራሱን በራሱ ይጻረራል፤መን
ግሥቱንም በገዛ እጁ ያፈርሳል ማለት
ነው። 27 እኔ አጋንንትን የማወጣው በሰይ
ጣን ኃይል ከሆነ፣ ታዲያ የገዛ ወገኖቻችሁ
አጋንንትን የሚያወጡት በማን ኃይል
ሊሆን ነው? ስለዚህ እነርሱ ራሳቸው እንዳ
ይፈርዱባችሁ! 28 እኔ አጋንንትን የማወጣ
ቸው በእግዚአብሔር መንፈስ ከሆነ፣የእግዚ
አብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀርባለች
ማለት ነው። 29 ለምሳሌ የአንዱን ኃይለኛ
ሰው ንብረት ለመዝረፍ ያሰበ ሰው በቅድ
ሚያ ኃይለኛውን ሰው አሸንፎ መያዝ አለ
በት። አጋንንትንም ማውጣት የሚቻለው
በዚሁ መንገድ ነው። 30 የእኔ ደጋፊ ያል
ሆነ ሁሉ ተቃዋሚዬ ነው። ከእኔ ጋር የማ
ይሰበስብም እርሱ የተሰበሰበውን ይበትናል።
31-32 «ማናቸውም ዓይነት ኃጢአት፣በእ
ኔም ላይ የተሰነዘረ ስድብም ቢሆን፣ይቅርታ
ይኖረዋል። በመንፈስ ቅዱስ ላይ የተሰነዘረ
ስድብ ግን፣በዚህም ሆነ በሚመጣው ዓለም
ፍጹም ይቅርታ የለውም።
33 «ዛፍ በፍሬው ይታወቃል። መልካም
ዛፍ መልካም ፍሬ ያፈራል፤ከመጥፎ ዛፍ
ግን መልካም ፍሬ አይጠበቅም። 34 እናንተ
የእባብ ልጆች! እናንተን የመሰሉ ክፉ
ሰዎች መልካሙንና ትክክለኛውን ነገር እን
ዴት አድርገው መናገር ይችላሉ? 35 የመል
ካም ሰው ንግግር የተናጋሪውን ውስጣዊ
መልካምነት አጉልቶ ያሳያል። ክፉ ልብ
ያለው ሰው ግን፣ነገሩ መርዝ ነው። በንግግ
ሩም መርዘኛነቱን ይገልጻል። 36 እውነቱን
ልንገራችሁ፣በመጨረሻው የፍርድ ቀን ለም
ትናገሩት ያልታረመ ቃል ሁሉ መልስ ለመ
ስጠት የምትገደዱ መሆናችሁን አትርሱ።
37 ዛሬ ከአንደበታችሁ የሚወጣው ቃል
የነገ ዕድላችሁን ይወስናል። ምክንያቱም
ማንም ሰው የሚፈረድለትም ሆነ የሚፈረድ
በት እንደአነጋገሩ ነውና።»



38 አንድ ቀን የአይሁድ ሃይማኖት መም
ህራንና ፈሪሳውያን ወደ ኢየሱስ ዘንድ ቀር
በው «በእርግጥ መሲሕ ከሆንክ ይህንኑ
የሚያረጋግጥ ተአምር ሠርተህ ለምን አታሳ
የንም?» ብለው ጠየቁት።
39-40 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላ
ቸው «በጉልህ የሚታይ ማረጋገጫ የሚፈ
ልግ፣በእግዚአብሔር ላይ እምነት የሌለውና
ልበ ደንዳና ሕዝብ ብቻ ነው። እናንተም
ብትሆኑ በነቢዩ ዮናስ ሕይወት ላይ ከተፈጸ
መው ምልክት የተለየ እናገኛለን ብላችሁ
የምታስቡ ከሆነ እንደዚያው ናችሁ። ዮናስ
ዓሣ ነባሪ ሆድ ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት
ሌሊት እንደ ኖረ፣ እኔም በምድር ሆድ
ውስጥ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እኖራ
ለሁ። 41 በፍርድ ዕለት የነነዌ ሰዎች በዚህ
ሕዝብ ላይ ተነሥተው ይፈርዳሉ። ምክንያ
ቱም፣ የዮናስን ስብከት ሰምተው ከክፉ
ሥራቸውም ተጸጽተው፣በንስሐ ወደ እግዚ
አብሔር ለመመለስ በቅተዋልና። እናምንበ
ትም ብላችሁ አሻፈረኝ አላችሁ እንጂ፣ከዮ
ናስ የሚበልጥ እዚሁ አጠገባችሁ አለ።
42 ንግሥተ ሳባ በፍርድ ቀን ተነሥታ በዚህ
ሕዝብ ላይ ትፈርዳለች። ምክንያቱም የሰሎ
ሞንን ጥበብ ለማየት ከሩቅ አገር ተጉዛ
መጥታለችና። አሻፈረኝ ብላችሁ እናምንበ
ትም አላችሁ እንጂ፣ ከሰሎሞን የሚበልጥ
እዚሁ አጠገባችሁ አለ፤እርሱም እኔ ነኝ»
አላቸው።
43-45 «ይህ ክፉ ሕዝብ ጋኔን ባደረበት
ሰው ይመስላል። በሰውየው ያደረው ጋኔን
ዕረፍት ለመሻት ከሰውየው ወጥቶ ወደ
በረሃ ይሄዳል። ዳሩ ግን የተመኘውን ዕረ
ፍት ሳያገኝ ሲቀር፣እንዲህ ማለት ይጀም
ራል ፤ ‘ተመልሼ ሄጄ ድሮ በነበርኩበት
ሰው ውስጥ ለምን አላድርም?’ ተመልሶ
ሲመጣም፣ የሰውየው ልብ ከበፊቱ ይልቅ
አምሮና ተሰናድቶ ያገኘዋል። ጋኔኑም በክ
ፋት ከእርሱ የባሱ ሌሎች ሰባት አጋንንት
ይዞ መጥቶ በሰውየው ውስጥ ያድራሉ።
ከዚህም የተነሣ የሰውየው ሁኔታ መጀመ
ሪያ ከነበረበት ይልቅ የከፋ ይሆናል። በዚህ
ክፉ ሕዝብም የሚደርስበት እንዲሁ
ነው።»
46-47 ኢየሱስም ለተሰበሰቡት ሰዎች ንግ
ግር በማድረግ ላይ ሳለ፣እናቱና ወንድሞቹ
ሊያነጋግሩት ፈልገው፣ እርሱ ወዳለበት
መጡ። የእናቱንና የወንድሞቹን መምጣት
ሲነግሩትም 48 እንዲህ አለ፣ «እናቴ ማን
ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው?»
49 ወደ ደቀመዛሙርቱም እያመለከተ፣
50 «እናቴም ወንድሞቼም እነዚህ
ናቸው።» ከዚያም በመቀጠል፣ «በሰማይ
ያለውን ያባቴን ፈቃድ የሚፈጽም፣እርሱ፣
ወንድሜ፣እኅቴና እናቴ ነው!» አለ።

## ምዕራፍ 13

1 በዚያኑ ቀን ኢየሱስ ከነበረበት ቤት
ወጥቶ ወደ ሐይቁ ዳርቻ ሄደ። 2-3 ብዙ
ሰዎችም ተሰበሰቡ። እርሱም በጀልባ ላይ
ሆኖ በሐይቁ ዳር ለነበሩት ሰዎች ብዙ
ምሳሌዎችን እየመሰለ አስተማራቸው።
ከምሳሌዎቹም መካከል አንዱ የሚከተ
ለው ነው። «ገበሬ እህል ሊዘራ ወደ
እርሻው ቦታ ሄደ። 4 ከተዘራው ዘር መካ
ከል አንዳንዱ መንገድ ዳር ወደቀ። ወፎ
ችም መጥተው ለቅመው በሉት። 5 አንዳ
ንዱም ዘር ጥልቀት በሌለው ጭንጫ
መሬት ላይ ወደቀ። ለጊዜው ቡቃያው
ስሩን አፈር ዘልቆ በፍጥነት ብቅ አለ።
ግን በጭንጫነቱ ምክንያት ዘሩ ሥር
ሊሰድ ባለመቻሉ፣ 6 ፀሐይ አጠውልጎት
ደረቀ። 7 አንዳንዱ ዘር በእሾህ መካከል
ወደቀ። በቅሎ እንደ ማደግ ሲል በቡቃያ
ነቱ እሾሁ አንቆ አስቀረው። 8 ሌላው ዘር
ግን በጥሩ መሬት ላይ ወደቀ። ይህም ዘር
መቶ፣ ስድሳና ሠላሳ እጥፍ ፍሬ አፈራ።
9 ይህንን ምሳሌ ልብ ያለው፣ ልብ ያድር
ገው።»
10 ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱ፣ «ለእነ
ዚህ ሰዎች ምሳሌዎችን እየመሰልክ የምታ
ስተምራቸው ለምንድነው?» ሲሉ ጠየ
ቁት።
11 ኢየሱስም፣የመንግሥተ ሰማይን ምሥ
ጢር የማወቅ ጸጋ ለደቀመዛሙርቱ ብቻ
የተሰጠና ሌሎች ግን ሊያስተውሉት የማይ
ችሉ መሆኑን ገለጠላቸው።
12-13 ቀጥሎም ፤ «ላለው ይጨመርለ
ታል ፤ የተትረፈረፈም ይኖረዋል። ከሌለው
ግን፣ ያቺ ያለችው እንኳ ትወሰድበታለች።
በምሳሌ የማስተምረውም እያዩ የማያስተ
ውሉ፣እየሰሙ ልብ የማይሉ ስለሆኑ ነው።
14 ይህም በነቢዩ ኢሳይያስ፣ ‘ይሰማሉ፣ነገር
ግን ልብ አይሉም፤ያያሉ፣ነገር ግን አያስተ
ውሉም። 15 ልባቸውን አደንድነውታል ፤
ጆሮአቸውን ጠቅጥቀውታል ፤ ዓይኖቻ
ቸውንም ጨፍነዋል። ስለዚህም፣ በዓይ
ናቸው አይተው በጆሮአቸው ሰምተው፣
በልባቸውም አስተውለው ወደእኔ በመመ
ለስ ፈውስ እንዳያገኙ ሆነዋል’ ተብሎ

ተነግሮባቸዋል።
16 «እናንተ ግን ዓይኖቻችሁ የታደሉ
ናቸው፣ ያያሉና። ጆሮቻችሁም የታደሉ
ናቸው፣ይሰማሉና። 17 ብዙ ነቢያትና የእግ
ዚአብሔር ወዳጆች እናንተ የምታዩትን
ለማየት፣ እናንተ የምትሰሙትን ለመስማት
ተመኝተው ነበር። እነርሱ ግን ለዚህ አልበ
ቁም።
18 «ቅድም የተናገርኩት የገበሬውና
የዘሩ ምሳሌ ትርጉም እንደሚከተለው
ነው። 19 ያ ዘሩ የወደቀበት የተደለደለ መን
ገድ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት የምሥ
ራች ቃል ሰምቶ የማያስተውለውን ልበ ደን
ዳና ሰው ያመለክታል። ሰይጣንም የሰማ
ውን ከልቡ ውስጥ ለቅሞ ይወስደዋል።
20 ጭንጫው መሬት ላይ የወደቀው ዘር
ደግሞ፣የምሥራቹን ቃል ሰምቶ ለጊዜው
በደስታ የሚቀበለውንና፣ ሕይወቱ ጥልቀት
ስለሌለው ዘሩ ሥር ለመስደድ በቂ አፈር
የሚያንሰውን ሰው ልብ ያመለክታል።
21 ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ችግር ሲገጥመው
ወይም ደግሞ በእምነቱ ምክንያት ስደት
ሲደርስበት፣ስሜቱ ይቀዘቅዝና ወደ ክህደት
ይደርሳል። 22 እሾህማው መሬት፣የምሥራ
ቹን ቃል ሰምቶ ወዲያውኑ የሚቀበለውን
ሰው ልብ ያመለክታል። ነገር ግን፣ ስለ
ኑሮው የሚሰማው ጭንቀትና ለገንዘብም
ያለው ጉጉት፣ የሰማውን የእግዚአብሔርን
ቃል አንቆ ይይዘዋል። ከዚህም የተነሣ፣ለእ
ግዚአብሔር የሚያበረክተው አገልግሎት
እያነሰና እየተቀነሰ ይሄዳል። 23 መልካሙ
መሬት ግን የምሥራቹን ቃል የሚሰሙት
ንና የሚያስተውሉትን ሰዎች ልብ ያመለክ
ታል። እነዚህም ሰዎች በሕይወት ሳሉ
አንዱ መቶ፣ሌላው ስድሳ፣እንዲሁም ሌላው
ሠላሳ እጥፍ መንፈሳዊ ፍሬ ያፈራሉ።»
24 ኢየሱስም ሌላም ምሳሌ እንዲህ ሲል
ነገራቸው። «መንግሥተ ሰማይ በእርሻው
ላይ ጥሩ ዘር በዘራ ገበሬ ትመሰላለች።
25 አንድ ቀን ሰው ሁሉ ተኝቶ ሳለ፣ጠላት
መጥቶ በስንዴው ውስጥ እንክርዳድ ዘርቶ
ሄደ። 26 ስንዴው መብቀል ሲጀምር እንክር
ዳዱም አብሮ ብቅ አለ።
27 «የገበሬውም ሠራተኞች፣ ‘ጌታው!
ጥሩ ዘር የዘራህበትን መሬት እንክርዳድ
ወርሶታል’ ብለው ነገሩት።
28 «ገበሬውም፣ ‘ይህን ያደረገው ሌላ
እንዳይመስላችሁ፣ ጠላት ነው’ አላቸው።
አገልጋዮቹም መልሰው፣ ‘ታዲያ እንክርዳ
ዱን ብንነቅለውስ?’ አሉት። 29 ባለቤቱ
ግን፣ ‘አይሆንም! ግድ የለም፣እንክርዳዱን
እንነቅላለን ስትሉ ስንዴውንም አብራችሁ
ትነቅሉብኛላችሁ። 30 እስከ ሰብል መሰብሰ
ቢያ ወራት ድረስ ስንዴውም እንክርዳዱም
አብሮ ይደግ። ያን ጊዜ አጫጆች እንክርዳ
ዱን ከስንዴው እየለዩ እንዲያጭዱ አደርጋ
ለሁ። ከዚያም ስንዴው በጎተራ ሲገባ እንክ
ርዳዱ በእሳት ይቃጠላል!’» አላቸው።
31-32 ሌላም ምሳሌ ነገራቸው። «መንግ
ሥተ ሰማይ በእርሻ ውስጥ በተዘራች በአን
ዲት የሰናፍጭ ዘር ትመሰላለች። ከዘር ዓይ
ነቶች ሁሉ የሰናፍጭ ቅንጣት ታንሳለች።
ነገር ግን ባደገች ጊዜ ከእህል ዘር ሁሉ
በመብለጥ፣ ወፎች መጠለያ የሚያገኙበት
ትልቅ ዛፍ ትሆናለች።»
33 ሌላም ምሳሌ ነገራቸው፣ «መንግ
ሥተ ሰማይ ዳቦ በምትጋግር በአንዲት ሴት
ትመሰላለች። ሴትዮዋ ለክታ ያወጣችውን
ዱቄት ከእርሾ ጋር ደባልቃ በማቡካት፣
ቡኮው ኩፍ እስኪል ትጠብቃለች።»
34-35 ኢየሱስ ሕዝቡን ሲያስተምር እነዚ
ህንና እነዚህን የመሳሰሉትን ምሳሌዎች እየ
መሰለ ያስተምራቸው ነበር። ልዩ ልዩ ምሳ
ሌዎችን በመመሰል እንጂ ፍሬ ነገሩን ብቻ
በቀጥታ እንደማያስተምር፣ነቢዩ አስቀድሞ
ተናግሮለት ነበር። እንዲህ ሲል፣ «በምሳሌ
እናገራለሁ፣ከጥንት ጀምሮ የተሰወረውንም
ምሥጢር እገልጻለሁ።»
36 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሕዝቡን ደጅ እን
ዳሉ ትቶአቸው ወደ ቤት ገባ። ደቀመዛሙ
ርቱም የስንዴውንና የእንክርዳዱን ምሳሌ
እንዲያብራራላቸው ጠየቁት።
37 ኢየሱስም፣ እንደሚከተለው አስረዳ
ቸው። «መልካሙን ዘር የዘራው ገበሬ እኔ
ነኝ። 38 የእርሻውም ቦታ ይህ ዓለም ነው።
ስንዴው የጻድቃን፣ እንክርዳዱ የኃጥአን
ምሳሌ ነው። 39 እንክርዳዱን በስንዴው
መካከል የዘራው ሰይጣን ነው። ሰብሉ የዓ
ለም መጨረሻ ሲሆን፣የሰብሉ ሰብሳቢዎች
ደግሞ መላእክት ናቸው። 40 በዚህ ምሳሌ
ውስጥ እንክርዳዱ ከስንዴ ተለይቶ እንደሚ
ቃጠል ሁሉ፣በዓለም መጨረሻ ጊዜም እን
ደዚሁ ይሆናል። 41 ወደ ጥፋት የሚያደርሱ
ፈተናዎችንና ክፉ ሠሪዎችን ሁሉ ከእግዚአ
ብሔር መንግሥት ለይተው እንዲያወጡና
42 በእሳት እንዲያቃጥሉ መላእክትን እልካ
ለሁ። በዚያም ክፉ አድራጊዎች ጥርሳቸ
ውን እያፋጩ ያለቅሳሉ። 43 ጻድቃን ግን
በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበ
ራሉ። የልቦና ጆሮ ያለው ይህን ምሳሌ



ልብ ያድርገው።
44 «መንግሥተ ሰማይ በእርሻ መካከል
ተቀብሮ አንድ ሰው ያገኘውን የከበረ ሀብት
ትመስላለች። ያም ሰው ከደስታው ብዛት
የተነሣ ያንን ሀብት ለማግኘት ሲል ያለ
የሌለውን ሁሉ ሸጦ መሬቱን ይገዛል። የተ
ቀበረውንም ሀብት የራሱ ያደርጋል።
45 «እንዲሁም መንግሥተ ሰማይ ዕንቁ
ለመግዛት ገበያ በወጣ ነጋዴ ትመሰላለች።
46 ነጋዴው ገበያው ውስጥ ሲዘዋወር በጣም
የተዋበና ዋጋው ውድ የሆነ ዕንቁ ያጋጥመ
ዋል። ዕንቁውን ለመግዛት ያለ የሌለውን
ሁሉ ይሸጣል።
47-48 «በተጨማሪም፣ መንግሥተ ሰማይ
ከሁሉም ዓይነት ዓሣ ለመያዝ ባሕር ውስጥ
የተጣለን መረብ ትመስላለች። ዓሣ አጥማ
ጆች መረቡ ሲሞላላቸው ጎትተው ወደ
ባሕሩ ዳርቻ ያወጡታል። ከዚያም ደህና
ደህናውን ዓሣ እየመረጡ ይሰበስባሉ፤ መጥ
ፎውን ዓሣ ግን እየለዩ ይወረውሩታል።
49 በዓለም መጨረሻ ላይም ልክ እንደዚሁ
ይሆናል። መላእክት ይመጡና ኃጢአተኞ
ችን ከጻድቃን ይለዩአቸዋል። 50 ኃጢአተኞ
ችን ወደ እሳት ይጥሉአቸዋል። በዚያም
ጥርሳቸውን በማፋጨት ያለቅሳሉ።»
51 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፣
«የተናገርኩት ገብቷችኋል?» ሲል ጠየቃ
ቸው። እነርሱም፣ «አዎን» ሲሉ መለሱ
ለት። 52 ኢየሱስም በተናገረው ላይ በማ
ከል፣ «የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥ
ጢር የተቀበሉ የአይሁድ ሃይማኖት መምህ
ራን የአሁኑንም የጥንቱንም ጠንቅቀው የተ
ረዱ በመሆናቸው፣ መንፈሳዊ ዕውቀታቸው
እጥፍ ድርብ ነው» አላቸው።
53-54 ኢየሱስ እነዚህን ምሳሌዎች ተና
ግሮ እንደ ጨረሰ፣ በገሊላ ክፍለ ሀገር
ውስጥ በምትገኘው መኖሪያው ወደ ሆነ
ችው፣ ወደ ናዝሬት ከተማ ሄደ። በዚያም
በአይሁድ ምኩራቦች ውስጥ በማስተማር፣
በትምህርቱ ጥልቀትና በሚሠራቸው ተአም
ራት ሕዝቡን አስደነቀ። 55 አንዳንዶቹም፣
«እንዴት ያለ ነገር ነው? ይህ የአናጢው
የዮሴፍ ልጅ አይደለምን? እናቱን ማርያም
ንስ እናውቃት የለምን? ወንድሞቹስ ያዕ
ቆብ፣ዮሴፍ፣ስምዖንና ይሁዳ አይደሉምን?
56 እኅቶቹስ እዚሁ ከእኛው ጋር ይኖሩ የለ
ምን? እንዴት ነው እንደዚህ ዝናው ሊገን
የቻለው?» አሉ። 57 በዚህም ምክንያት አላ
መኑበትም። ኢየሱስ ግን፣ «ነቢይ ባገ
ሩና በወገኖቹ ይናቅ እንጂ፣ በሌላ ሥፍራ
ይከበራል» አላቸው።
58 ካለማመናቸውም የተነሣ፣ በናዝሬት
ብዙ ተአምራትን አላደረገም።

## ምዕራፍ 14

1 ንጉሥ ሄሮድስ የኢየሱስን ዝና
ሲሰማ፣ 2 ለአገልጋዮቹ፣ «መጥምቁ ዮሐንስ
ከሞት ተነሥቶ ነው መሰለኝ ይህ ሁሉ ተአ
ምራት ሊደረግ መቻሉ!» አላቸው።
3 ሄሮድስ፣ከዚህ ቀደም መጥምቁ ዮሐን
ስን አስይዞ ወህኒ ቤት አግብቶት ነበር።
ምክንያቱም፣ የወንድሙ የፊልጶስ ሚስት
የነበረችው፣ በኋላም ራሱ ሄሮድስ ያገባት
ሄሮድያዳ የተባለችው ሴት፣ዮሐንስን እንዲ
ያሥርላት ለምናው ነበር። 4 ይህም ሊሆን
የቻለው፣ «የገዛ ወንድምህን ሚስት ማግባት
አይገባህም» ብሎ ዮሐንስ ሄሮድስን ወቅ
ሶት ስለነበር ነው። 5 ከዚህ የተነሣ ሄሮድስ
ዮሐንስን ሊገድለው ቢፈልግም፣ በሕዝቡ
ዓይን ዮሐንስ እንደ ነቢይ የሚታይ ስለ
ነበር፣ ‘ይህን ባደርግ ሁከት ይፈጠራል’
ብሎ በመፍራት ሊገድለው አልደፈረም።
6 ሄሮድስ የልደት በዓሉን በሚያከብር
በት ዕለት፣የሄሮድያዳ ልጅ በግብዣው ላይ
ዘፈን ዘፍና እስክስታ ወርዳ፣ሄሮድስን ደስ
አሰኘችው። 7 ሄሮድስም ልጅቱን ጠርቶ፣
«የምትፈልጊውን ነገር ጠይቂኝና እሰጥሻ
ለሁ» ሲል ቃል ገባላት። 8 ልጅቱም ሄሮድ
ስን ምን ስጠኝ ብላ መጠየቅ እንዳለባት
ከእናቷ ተመካክራ ባገኘችው አሳብ፣የዮሐ
ንስ አንገት ተቆርጦ ራሱ በሳህን ወዲያውኑ
እንዲሰጣት ጠየቀች።
9 ይህም ሄሮድስን በጣም አሳዘነው።
ይሁን እንጂ በእንግዶቹ ፊት የገባላትን
ቃል ማጠፍ አልፈለገም። ስለዚህ የዮሐንስ
ራስ ተቆርጦ እንዲሰጣት አዘዘ። 10 ወዲያው
ኑም የእሥረኛው የዮሐንስ አንገት ተቆ
ርጦ፣ 11 ራሱ በሳህን ላይ ተደርጎ ለሄሮድ
ያዳ ልጅ ተሰጣት። ልጅቱም የዮሐንስን
ራስ በሳህን እንዳለ ይዛ ወደ እናቷ ሄደች።
12 የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርትም
የዮሐንስን ሬሣ ከቀበሩ በኋላ፣ወደ ኢየሱስ
ሄደው የሆነውን ሁሉ ነገሩት።
13 ኢየሱስም የዮሐንስን መገደል ሲሰማ
ብቻውን በጀልባ ሆኖ ወደ አንድ ገለልተኛ
ቦታ ሄደ። ሰዎችም ይህን እንደሰሙ ከየመ
ንደሩ እየወጡ፣ ኢየሱስ በሄደበት አቅጣጫ
የሐይቁን ጠርዝ ይዘው በእግር ተከተሉት።
14 ኢየሱስም ከነበረበት ሥፍራ ሲመ
ለስ፣ ብዙ ሰዎች ሲጠብቁት አይቶ አዘነላ

ቸው። ከመካከላቸው ሕመምተኞች የነበሩ
ትን ፈወሳቸው።
15 ደቀመዛሙርቱም ወደ ኢየሱስ ቀር
በው፣ «ቀኑ መሽቷል፤የራት ጊዜም ደር
ሷል። በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ምንም
ምግብ ማግኘት ስለማይቻል፣ በአቅራቢያ
ወዳሉት መንደሮች ሄደው ምግባቸውን እን
ዲገዙ ሰዎቹን በጊዜ አሰናብታቸው»
አሉት።
16 ኢየሱስም፣ «መሄድ አያስፈልጋቸ
ውም። እናንተ የሚበሉትን እዚሁ ስጡዋ
ቸው» አላቸው።
17 ደቀመዛሙርቱም፣ «እንዴት ተደ
ርጎ! እኛ ያለን አምስት ጥቢኛ ዳቦና
ሁለት ዓሣ ብቻ ነው» አሉት።
18 ኢየሱስም፣ «ግድ የለም ያንኑ ያለ
ውን ወደ እኔ አምጡልኝ» አላቸው።
19 ከዚያም፣ ሕዝቡ በሳር ላይ እንዲቀመጥ
አዘዘ። አምስቱን ጥቢኛ ዳቦና ሁለቱን ዓሣ
በእጁ ይዞ ወደ ሰማይ በመመልከት እግዚአ
ብሔርን አመሰገነ። ዳቦዎቹንም ቆራርሶና
ለሰዎቹ እንዲያድሉ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣ
ቸው። 20 በዚያ የነበሩት ሰዎች ሁሉ በል
ተው ከጠገቡ በኋላ አሥራ ሁለት መሶብ
ፍርፋሪ ተነሣ። 21 የበላውም ሕዝብ ብዛት፣
ሕፃናትና ሴቶች ሳይቆጠሩ፣ ወደ አምስት
ሺህ ይጠጋ ነበር። 22 ወዲያውኑም ኢየሱስ፣
በጀልባ ተሳፍረው ከሐይቁ ማዶ እንዲሻገሩ
ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸውና እርሱ ሕዝቡን
ለማሰናበት ወደ ኋላ ቀረት አለ።
23-24 ሕዝቡን ካሰናበተ በኋላም ለመጸ
ለይ በአቅራቢያው ወዳለ ተራራ ወጣ። በመ
ሸም ጊዜ፣እርሱ በዚያ ብቻውን ነበር። በጀ
ልባ ርቀው የሄዱትን ደቀመዛሙርት ግን
ችግር አጋጠማቸው። ኃይለኛ ነፋስ ተነ
ሥቶ የነበሩባትን ጀልባ ማዕበል ያንገላታት
ጀመር። እነርሱም እንዳይሰጥሙ የተቻላቸ
ውን ሁሉ ቢያደርጉም ማዕበሉን ለመቋ
ቋም አልቻሉም።
25 ኢየሱስም፣ ከሌሊቱ አሥር ሰዓት
ሲሆን በውኃው ላይ እየተራመደ ወደ እነ
ርሱ መጣ።
26 እነርሱ ግን ምትሀት ያዩ መሰላቸውና
በጣም ደነገጡ።
27 ኢየሱስም፣ «አትፍሩ እኔ ነኝ!»
ብሎ አረጋጋቸው።
28 ጴጥሮስም፣ «ጌታ ሆይ፣ በእርግጥ
አንተ ከሆንክ፣በውኃው ላይ ተራምጄ ወደ
አንተ እንድመጣ ፍቀድልኝ» አለው።
29 ኢየሱስም፣ «በል ና!» አለው። ወዲ
ያውም ጴጥሮስ ከጀልባው ወርዶ፣ውኃውን
እየረገጠ ወደ ኢየሱስ ሲሄድ፣ 30 በዙሪያው
ያለውን ማዕበል አይቶ በመፍራቱ ሊሰጥም
ጀመረ። በዚህ ጊዜ፣ «ጌታ ሆይ፣አድነኝ!»
ሲል ጮኸ።
31 ኢየሱስ ወዲያው እጁን ዘርግቶ ከመስ
ጠም አዳነው። ከዚያም፣ «አንተ እምነተ
ደካማ! ለምን ተጠራጠርህ?» አለው።
32 ኢየሱስ ከጴጥሮስ ጋር ሆኖ ጀልባው
ውስጥ እንደ ገባ ማዕበሉ ጸጥ አለ። 33 በጀ
ልባው ውስጥ የነበሩትም በመደነቅ፣ «በእ
ርግጥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ»
አሉት።
34 ከዚህ በኋላ ሐይቁን ተሻግረው ጌንሴ
ሬጥ ከተባለ ቦታ ደረሱ። 35 በዚያ ቦታ የመ
ገኘታቸውም ወሬ በከተማው ሁሉ ተሰ
ራጨ። ሰዎች ሁሉ ተጠራርተው ሕመምተ
ኞቻቸውን እየያዙ መጡ። 36 በሽተኞችም
የኢየሱስን የልብሱን ጫፍ እንዲዳስሱ
ለመኑ። የዳሰሱትም ሁሉ ተፈወሱ።

## ምዕራፍ 15

1 ፈሪሳውያንና የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራን ኢየሱስን ለማነጋገር ከኢየሩሳ
ሌም ተነሥተው መጡ።
2 ኢየሱስንም፣ «ደቀመዛሙርትህ ለምን
ድነው ከቀድሞ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣውን
ሥርዓታችንን የማይጠብቁት? ከምግብ
በፊት እጃቸውን የማይታጠቡት ለምንድ
ነው?» አሉት። 3 ኢየሱስም እንዲህ ሲል
መልስ ሰጣቸው። «እናንተስ ባህላችሁን
ብቻ በመከተል በመጻሕፍት የተደነገገውን
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለምን ትጥሳላ
ችሁ? 4 ለምሳሌ፣በሙሴ ሕግ፣ ‘አባትህንና
እናትህን አክብር፤ አባትና እናቱን የሚሳ
ድብ ይሙት’ ይላል። 5-6 እናንተ ግን ይህ
ንን አፍርሳችሁ፣ ‘አንድ ሰው አባትና
እናቱ ቢቸገሩም እንኳ፣ለእነርሱ ያሰበውን
እርዳታ ለቤተ መቅደስ ቢሰጥ ምንም አይደ
ለም’ ትላላችሁ። ይህን በመሳሰለው ሰው
ሠራሽ ወግና ሥርዓት፣ወላጆች እንዲከበሩና
እንዲጦሩ እግዚአብሔር በቃሉ ያዘዘውን፣
ዋጋ ለማሳጣት ትጥራላችሁ። 7 እናንተ ግብ
ዞች! ኢሳይያስ ስለ እናንተ የተናገረው ትክ
ክለኛ ነገር ነው። 8 ‘ይህ ሕዝብ በአፉ እወ
ድሃለሁ ይለኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ
ነው፤ 9 አምልኮውም ዋጋ ቢስ ነው። ምክን
ያቱም የእግዚአብሔርን ሕግ በሰው ሠራሽ
ሕጉ ለውጦታልና።’»
10 ኢየሱስም ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ፣



«እኔ የምነግራችሁን አስተውሉ። 11 በአፍ
ተበልቶ ወደ ሆድ የሚገባ ነገር ሰውን አያ
ረክሰውም። ሰውን የሚያረክሰው፣ በልብ
ታስቦ ከአንደበት የሚወጣው ቃል ነው።»
12 ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን፣
«ጌታ ሆይ፣ አሁን በተናገርከው ነገር ፈሪሳ
ውያን ተቀይመዋል» አሉት።
13-14 ኢየሱስም፣ «በአባቴ እጅ ያልተተ
ከለ ተክል ሁሉ ይነቀላል። ስለዚህ ስለ እነ
ርሱ አትጨነቁ፤እነርሱ ዕውራንን የሚመሩ
ዕውሮች ናቸው። እነርሱም ሆኑ በእነርሱ
የሚመሩ ሁሉ ገደል ከመግባት አይድኑም»
ሲል መለሰላቸው።
15 ጴጥሮስም ቀበል አድርጎ፣ «በአፍ
ተበልቶ ወደ ሆድ የሚገባ ነገር ሰውን አያ
ረክሰውም ያልከው እንዴት ነው?» ሲል
ጠየቀው።
16 ኢየሱስም፣ «የተናገርኩት አልገባ
ህም? 17 ማንኛውም የሚበላ ምግብ ሆድ
ከገባ በኋላ ዓይነምድር ሆኖ ይወጣል።
18 ክፉ ቃል ግን ከክፉ ልብ ይመነጫል።
ሰውን የሚያረክሰውም ይኸው ከልብ የሚ
ወጣው ክፉ ቃል ነው። 19 ክፉ አስተሳሰብ
ነፍስ መግደል፣ማመንዘር፣ዝሙት፣ስርቆት፣
ውሸትና ስድብን የመሳሰሉት ክፉ ነገሮች
ሁሉ፣ከክፉ ልብ መንጭተው ይወጣሉ።
20 «ሰውን የሚያረክሱም እነዚህ ነገሮች
እንጂ፣ እጅን ሳይታጠቡ መብላቱ አይደ
ለም» አለው።
21 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ጢሮስና
ሲዶና ሄደ።
22 እዚያ እንደ ደረሰም የአገሩ ነዋሪ የሆ
ነች አንዲት ከነናዊት ሴት፣ «የዳዊት ልጅ
ጌታ ሆይ፣ እባክህን ምሕረትህን አሳየኝ፤
ልጄን ጋኔን ይዞ ያሠቃያታልና እባክህን
ማርልኝ» ስትል ተማጸነችው።
23 ኢየሱስ ግን ምንም ቃል አልመለሰላ
ትም። ደቀመዛሙርቱም ኢየሱስን፣ «ይህች
ሴት እየወተወተች እንዳታስቸግረን እባክህን
አሰናብታት» አሉት።
24 ኢየሱስም፣ «እኔ የመጣሁት አሕዛ
ብን ሳይሆን የጠፉትን የእሥራኤልን ሕዝብ
ለመታደግ ነው» ሲል መለሰ። 25 ሴቲቱ
ግን ከፊቱ ተንበርክካ፣ «ጌታ ሆይ፣ እር
ዳኝ!» አለችው። 26 ኢየሱስም፣ «የልጆችን
ምግብ አንሥቶ ለውሾች መጣል አይገባም»
አላት።
27 ሴቲቱም፣ «ቢሆንም፣ውሾች እኮ ከጌ
ቶቻቸው ማዕድ ሥር የሚወድቀውን ፍር
ፋሪ መብላት አይከለከሉም» አለችው።
28 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ሴቲቱን፣ «አንቺ
ሴት፣እምነትሽ በጣም ትልቅ ነው። ስለዚህ
ልጅሽ ተፈውሳልሻለች!» አላት። ቢጋኔን
ተይዛ ትሠቃይ የነበረች ልጅዋም ወዲያ
ውኑ ተፈወሰች።
29 ከዚያም ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሐይቅ
አካባቢ ተመልሶ ከአንድ ጉብታ ቦታ ላይ
ተቀመጠ። 30 ብዙ ሰዎችም አንካሶችን፣
ዕውሮችን፣ሽባዎችን፣ድዳዎችንና ልዩ ልዩ
በሽታ ያለባቸውን ሰዎች አምጥተው ከኢየ
ሱስ ፊት አቀረቧቸው። እርሱም ሁሉንም
ፈወሳቸው። 31 አንዲት ቃል እንኳ ተናግ
ረው የማያውቁ ድዳዎች በሚያስደንቅ መን
ገድ ይናገሩ ጀመር፤አካለ ስንኩሎች የነበሩ
ጤነኞች ሆኑ፤ አንካሶችና ሽባዎች እንደ
ልባቸው መራመድ ቻሉ። ዕውሮችም ዓይና
ቸው በራላቸው። ይህን ያዩ ሰዎችም በአድ
ናቆት ተሞልተው የእሥራኤልን አምላክ
አመሰገኑ።
32 ከዚህ ሁሉ በኋላ ኢየሱስ ደቀመዛሙ
ርቱን ጠርቶ፣ «እነዚህ ሰዎች ሦስት ቀን
ሙሉ ከእኔ አልተለዩም። ምግባቸው አልቆ
ባቸዋል። በጣምም አዝንላቸዋለሁ። እንዲህ
እንደ ተራቡ ወደ ቤታቸው እንዲሄዱ ባሰና
ብታቸው መንገድ ላይ ጠኔ ይጥላቸዋል»
አላቸው።
33 ደቀመዛሙርቱም፣ «አሁን በዚህ
በረሃ ለዚህ ሁሉ ሕዝብ የሚሆን ምግብ
ከየት ይመጣል ብለህ ነው?» አሉት።
34 ኢየሱስም፣ «ለመሆኑ ስንት ዳቦ አላ
ችሁ?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም፣
«ሰባት ጥቢኛ ዳቦና ጥቂት ዓሣ ብቻ አለን»
አሉት።
35 ኢየሱስም ሰዎቹን መሬት ላይ እንዲ
ቀመጡ አደረገና፣ 36 ሰባቱን ጥቢኛ ዳቦና
ዓሣዎቹን በእጁ ይዞ እግዚአብሔርን አመሰ
ገነ። ቆራርሶም ለሕዝቡ እንዲያድሉ ለደቀ
መዛሙርቱ ሰጠ። 37-38 በዚያ የነበረው
ሁሉ እስኪጠግብ ድረስ በላ። የሕዝቡም
ብዛት–ሴቶችና ሕፃናት ሳይቆጠሩ–አራት
ሺህ ነበር። በልተው ከጠገቡ በኋላም ሰባት
መሶብ ሙሉ ፍርፋሪ ተሰበሰበ።
39 ከዚያም ኢየሱስ አብረውት የነበሩትን
ሰዎች ወደየቤታቸው እንዲሄዱ ካሰናበታ
ቸው በኋላ በጀልባ ተሳፍሮ ወደ ማጌዶል
ተሻገረ።

## ምዕራፍ 16

1 አንድ ቀን ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን
ኢየሱስን ለመፈተን፣ በሰማይ ላይ አንድ

ዓይነት ተአምር ሠርቶ እንዲያሳያቸው ጠየ
ቁት።
2-4 ኢየሱስም፣ «እናንተ የአየሩን ሁኔታ
በመመርመር በኩል የሚስተካከላችሁ
የለም። ማምሻውን ሰማዩ ሲቀላ፣ 'ዝናብ
አይዘንብም' ትላላችሁ። በማግስቱ ጠዋት
ደግሞ፣ 'ሰማዩ ደምኖ ከብዷል፣ ጠቁሯ
ልም፣ስለዚህ ዛሬ ይዘንባል' ትላላችሁ። እና
ንተ ግብዞች! የሰማዩን መልክ በማየት የአየ
ሩን ሁኔታስ መመርመር ታውቃላችሁ፤የጊ
ዜውን ግልጽ ምልክት ግን፤ልታጤኑት አል
ቻላችሁም። ክፉና የማያምን ትውልድ፣ትን
ግርት የተሞላበት ምልክት በሰማይ ላይ
ማየት ይፈልጋል። ይሁን እንጂ፣ከነቢዩ ከዮ
ናስ ምልክት በቀር ሌላ አይሰጠውም» ሲል
መለሰላቸው። ይህን ከተናገረ በኋላም ኢየ
ሱስ ትቷቸው ሄደ።
5 ሐይቁን አቋርጠው ከዳርቻው ሲደርሱ
ምግብ ይዘው አለመምጣታቸውን ደቀመዛ
ሙርቱ ተረዱ። 6 ወዲያውም ኢየሱስ፣
«ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠን
ቀቁ!» በማለት አስጠነቀቃቸው።
7 ደቀመዛሙርቱ ግን፣ኢየሱስ ይህን ማስ
ጠንቀቂያ የተናገረው ምግብ መያዝ በመርሳ
ታቸው የተነሣ መሰላቸው።
8 እሱ ግን ደቀመዛሙርቱ ያሰቡትን በማ
ወቁ፣ «እናንተ እምነት የጐደላችሁ!
ምግብ ባለመያዛችሁ ይህን ያህል ምን ያስ
ጨንቃችኋል?
9 «ለምንስ ማስተዋል ያቅታችኋል? ለአ
ምስት ሺህ ሰዎች አምስት ጥቢኛ ዳቦ ስመ
ግብ፣ስንት መሶብ ሙሉ ትርፍራፊ ማንሣ
ታችሁን ዘነጋችሁት? 10 አራት ሺህ ሰዎች
በሰባት ጥቢኛ ዳቦ እስኪጠግቡ መመገቤንና
ብዙ መሶብ ትርፍራፊ መነሣቱንስ አታስታ
ውሱም? 11 'ይህን ቃል የተናገረው ምግብ
መያዝ በመርሳታችን ነው' ብላችሁ እን
ዴት ታስባላችሁ? አሁንም ደግሜ ደጋግሜ
ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠን
ቀቁ እላችኋለሁ!»
12 ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱ፣ ኢየሱስ
ስለ እርሾ የተናገረው፣ከፈሪሳውያንና ከሰዱ
ቃውያን የተሳሳተ ትምህርት እንዲጠበቁ
ሲያስጠነቅቃቸው መሆኑ ገባቸው።
13 የፊልጶስ ቂሣርያ ከተባለው ከተማ
እንደ ደረሱ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፣
«ለመሆኑ ሰዎች እኔን ማን ይሉኛል?»
ሲል ጠየቃቸው።
14 ደቀመዛሙርቱም፣ «አንዳንድ ሰዎች፣
'መጥምቁ ዮሐንስ ነው' ሲሉህ፣ አንዳን
ዶቹ፣ 'ኤልያስ ነው' ይሉሃል። ሌሎች
ደግሞ፣ 'ኤርምያስ ነው' ሲሉህ፣የቀሩት
ደግሞ፣ 'ከነቢያት አንዱ ነው' ይላሉ»
ሲሉ መለሱለት።
15 ኢየሱስም፣ «እነርሱስ እንዲህ አሉ፤
እናንተስ ማን ነው ትላላችሁ?» ሲል ጠየ
ቃቸው።
16 ስምዖን ጴጥሮስም ቀበል አድርጎ፣
«አንተ መሲሕ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብ
ሔር ልጅ ነህ» አለ።
17 ኢየሱስም፣ «የዮና ልጅ ስምዖን
ሆይ! እግዚአብሔር ባርኮሃል፤ይህ በሰማይ
የሚኖረው አባቴ የገለጠልህ እውነት
እንጂ፣ ከሰው ትምህርት የተገኘ ዕውቀት
አይደለም። 18 አንተ ጴጥሮስ ነህ። በዚህ
አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እመሠርታ
ለሁ። ይህችንም የምመሠርታትን ቤተ ክር
ስቲያን የገሃነም ኃይሎች ሁሉ ሊቋቋሟት
አይችሉም። 19 እነሆ የመንግሥተ ሰማይ
መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ። በምድር ያሠር
ከው በሰማይም የታሠረ ይሆናል። በምድር
የፈታኸው በሰማይም የተፈታ ይሆናል»
አለው።
20 ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱን ስለ
እርሱ መሲሕነት ለማንም እንዳያወሩ አስጠ
ነቀቃቸው።
21 ከዚህ ጊዜ ጀምሮ፣ኢየሱስ ወደ ኢየሩ
ሳሌም እንደሚሄድ፣ በኢየሩሳሌምም የካህ
ናት አለቆች፣የአይሁድ ሃይማኖት መምህራ
ንና፣የአገር ሽማግሌዎች ይዘው፣መከራ ካደ
ረሱበት በኋላ እንደሚገድሉት፣ከሦስት ቀን
በኋላ ከሞት እንደሚነሣ ለደቀመዛሙርቱ
ገልጦ ነገራቸው።
22 ጴጥሮስም ኢየሱስ የተናገረውን ከሰማ
በኋላ፣ «ይህንንስ እግዚአብሔርም አይበ
ለው! ይህ በአንተ ላይ ፈጽሞ አይድረስ
ብህ!» በማለት አሳቡን ሊያስለውጠው
ሞከረ።
23 ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዞር ብሎ፣
«አንተ ሰይጣን፣ከአጠገቤ ሂድ! አስተሳሰ
ብህ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን ከሰው
ፈቃድ ጋር የሠመረ በመሆኑ እንቅፋት አት
ሁንብኝ» አለው።
24 ከዚያም ደቀመዛሙርቱን እንዲህ አላ
ቸው፣ «ደቀመዝሙሬ ለመሆን የወሰነ
ራሱን ክዶ፣ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተ
ለኝ። 25 ነፍሱን ለራሱ ጥቅም የሚጠብቃት
ሁሉ ያጣታል። ነገር ግን ነፍሱን ለእኔ
ሲል አሳልፎ የሚሰጥ መልሶ ያገኛታል።
26 አንድ ሰው ዓለምን ሁሉ አትርፎ የዘላለ



ምን ሕይወት ቢያጣ ምን ፋይዳ አለው?
ለመሆኑ ከዘላለም ሕይወት ጋር የሚስተካከ
ልስ ምን ነገር አለ? 27 እኔ የሰው ልጅ በአ
ባቴ ክብርና በመላእክት ታጅቤ እመጣ
ለሁ። ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን
የሚገባውን ፍርድ እሰጠዋለሁ። 28 አሁን
እዚህ ከቆሙት መካከል አንዳንዶቹ በሕይ
ወት ቆይተው በመንግሥቴ ሰመጣ ያዩ
ኛል።»

## ምዕራፍ 17

1 ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮ
ስን፣ያዕቆብን፣የያዕቆብን ወንድም ዮሐንስን
አስከትሎ፣ ወደ አንድ ከፍተኛ ተራራ
ወጣ። 2 በተራራው ላይ ሳሉ የኢየሱስ ፊቱ
ተለውጦ እንደ ፀሐይ አበራ። የልብሱም
ንጣት በጣም አንጸባረቀ።
3 ሦስቱ ደቀመዛሙርትም ሙሴና ኤል
ያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ አዩዋቸው።
4 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፣እዚሁ
ብንኖር በጣም ግሩም ነው! እንዲያውም
ፈቃድህ ከሆነ፣ አንድ ለአንተ፣ አንድ
ለሙሴ፣ አንድ ለኤልያስ የሚሆን ሦስት
ዳሶች ልሠራ እችላለሁ» አለ።
5 ጴጥሮስ ንግግሩን ሳይጨርስ ብሩህ
ደመና ከበባቸውና፣ «በጣም የምደሰትበት
ልጄ ይኸውላችሁ፣ እርሱን ታዘዙት»
የሚል ድምፅ ከደመናው ውስጥ ተሰማ።
6 ደቀመዛሙርቱ ፍርሃት ይዟቸው
መሬት ላይ በግምባራቸው ተደፉ። 7 ኢየ
ሱስ ግን በእጁ ነካ ነካ እያደረጋቸው፣
«ተነሡ፣አትፍሩ!» አላቸው።
8 ደቀመዛሙርቱም ቀና ብለው ቢመለ
ከቱ፣ ኢየሱስን ብቻ አጠገባቸው ቆሞ አገ
ኙት።
9 ከተራራው በመውረድ ላይ ሳሉ፣ ኢየ
ሱስ ደቀመዛሙርቱን፣ ከሞት ከመነሣቱ
በፊት ያዩትን ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛ
ቸው።
10 ደቀመዛሙርቱም፣ «የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራን ከመሲሑ መምጣት በፊት
ኤልያስ ተመልሶ ይመጣል የሚሉት ለምን
ድን ነው?» ሲሉ ጠየቁት።
11 ኢየሱስም፣ «አዎን፣እውነት ነው።
ኤልያስ አስቀድሞ መጥቶ ሁሉን ነገር ማስ
ተካከል አለበት። 12 እንደ እውነቱ ከሆነ፣
ኤልያስ መምጣቱን መጥቶአል። ሰዎች ግን
የመጣው ኤልያስ ማን እንደሆነ አላወቁም።
እንዲያውም መከራ አሳይተውታል። እኔም
ብሆን በእነዚህ ሰዎች እጅ መከራ መቀበሌ
የማይቀር ነው» ሲል መለሰላቸው።
13 በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስ
የተናገረው ስለ ዮሐንስ መጥምቁ መሆኑ
ገባቸው።
14 ከተራራው እንደ ወረዱ ብዙ ሕዝብ
ተሰብስቦ ሲጠብቃቸው አገኙ። አንድ ሰው
ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ከእግሩ ሥር ተንበረከ
ከና፣ 15 «ጌታ ሆይ፣ልጄ ጋኔን ይዞ ያሠቃየ
ዋልና እባክህን ማርልኝ፤ጊዜ እየለየም ከእ
ሳት ላይ ይጥለዋል፤ከውኃ ውስጥ ይጨምረ
ዋል። 16 ወደ ደቀመዛሙርትህ አምጥቼው
ነበር። ነገር ግን ሊፈውሱት አልቻሉም»
አለው።
17 ኢየሱስም፣ «እናንተ እምነት የጐደላ
ችሁ! ለመሆኑ እስከ መቼ እታገሣችኋለሁ?
እስቲ ልጁን ወደ እኔ አቅርቡት» አለ።
18 ከዚያም በልጁ ያደረበትን ጋኔን ገሠ
ጸው። ጋኔኑም ልጁን ለቅቆ ወጣ። ልጁም
ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ፍጹም ጤናማ ሆነ።
19 ከዚህ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን
በግል፣ «እኛ ጋኔኑን ልናወጣ ያልቻልነው
በምን ምክንያት ነው?» ሲሉ ጠየቁት።
20 ኢየሱስም፣ «በእምነታችሁ ማነስ
ምክንያት ነው። የሰናፍጭ ዘር የምታህል
እምነት ቢኖራችሁ፣ ይህን ተራራ 'ከዚህ
ተነሥ' ብትሉት ይነሣል። የሚያቅታችሁ
ምንም ነገር አይኖርም። 21 ነገር ግን የዚህ
ዓይነቱ ጋኔን ካልጾማችሁና ካልጸለያችሁ
በቀር፣ ሊወጣ አይችልም» ሲል መለሰላ
ቸው።
22-23 አንድ ቀን በገሊላ ምድር ሳሉ፣
ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የሚከተለውን ነገ
ራቸው። «ሰዎች አሳልፈው ይሰጡኛል፤ይገ
ድሉኛልም። ሆኖም በሦስተኛው ቀን
ከሞት እነሣለሁ።» ኢየሱስ በተናገረው
ነገር ምክንያት የደቀመዛሙርቱን ልብ
ጨነቀው፤ጠበበው።
24 ቅፍርናሆም ሲደርሱ፣ለቤተ መቅደስ
አገልግሎት የሚሆን የቀረጥ ገንዘብ የሚሰበ
ስቡ ሰዎች ጴጥሮስን፣ «መምህራችሁ ቀረጥ
አይከፍልምን?» ሲሉ ቀስ ብለው ጠየቁት።
25 ጴጥሮስም፣ «ለምን አይከፍልም? ይከ
ፍላል እንጂ» ሲል መለሰ። ከዚያም ጴጥ
ሮስ ስለዚሁ ጉዳይ ከኢየሱስ ጋር ለመነጋ
ገር ወደ ቤት እንደገባ፣ጴጥሮስ ያሰበውን
ከመናገሩ በፊት ኢየሱስ ቀድሞት፣ «ጴጥ
ሮስ እስቲ አንድ ነገር ልጠይቅህ። ነገሥ
ታት ግብር የሚቀበሉት ከዜጎቻቸው ነው
ወይስ ጦርነት ገጥመው ካስገበሩት ሕዝብ
ነው?» ሲል ጠየቀው።

26-27 ጴጥሮስም፣ «ከሰነበሯቸው የሌላ
አገር ዜጎች ነው» ብሎ መለሰ። ወዲያውም
ኢየሱስ፣ «ጥሩ ብለሃል፤እንዲህ ከሆነ የአገ
ራቱ ዜጎች ነፃ ናቸው ማለት ነዋ! ሆኖም
የቀረጥ ሰብሳቢዎቹን ሥራ ማደናቀፍ እንዳ
ይሆንብን፣ ወደ ሐይቁ ሂድና መረብህን
ጣል። ከዚያም መጀመሪያ የምትይዘውን
ዓሣ አፉን ስትከፍት ገንዘብ ታገኛለህ። የም
ታገኘውም ገንዘብ፣ ለእኔና ለአንተ ቀረጥ
ስለሚበቃ ሂደህ ክፈል» አለው።

## ምዕራፍ 18

1 በዚያኑ ወቅት ደቀመዛሙርቱ ኢየሱ
ስን፣ከመካከላቸው በመንግሥተ ሰማይ ማን
እንደሚበልጥ እንዲነግራቸው ጠየቁት።
2 ኢየሱስም አንድ ሕፃን ጠርቶ በፊታ
ቸው አቆመና እንዲህ አላቸው። 3 «ከኃጢ
አታችሁ ካልተመለሳችሁና እንደ ሕፃንም
ካልሆናችሁ ወደ መንግሥተ ሰማይ ልት
ገቡ አትችሉም። 4 እንደዚህ ሕፃን ራሱን
ዝቅ የሚያደርግ ነው በመንግሥተ ሰማይ
ታላቅ የሚሆን። 5 ይህን ለመሰለው ሕፃን
በስሜ ርኅራኄ የሚያሳይና መልካም አቀባ
በል የሚያደርግ፣እኔን እንደ ተቀበለ ይቆጠ
ራል። 6 ነገር ግን በእኔ ከሚያምኑት ከእነ
ዚህ ታናናሾች አንዱን ከእምነቱ እንዲሰና
ከል ከምታደርጉ፣ድንጋይ በአንገታችሁ ላይ
ታሥሮ ባሕር ውስጥ ቢጥሏችሁ ይሻላች
ኋል።
7 «ዓለም ሥራዋ ክፉ በመሆኑ ወዮላት!
ወደ ክፋት የሚመራ ፈተና ሚገጠሙ የማ
ይቀር ነገር ነው። ለፈተናው ሰበብ ለሚሆን
ለዚያ ሰው ግን ወዮለት! 8 ስለዚህ እጅህ
ወይም እግርህ ኃጢአት እንዲሠራ ልብህ
የሚገፋፋህ ከሆነ ይህን የልብህን ክፉ አሳብ
ቆርጠህ ጣለው። በልብህ ክፉ አሳብ ምክን
ያት ገሃነም ከምትገባ ይልቅ፣ክፋትህን አስ
ወግደህ መንግሥተ ሰማይ መግባት ይሻልሃ
ልና። 9 ዓይንህ ኃጢአት እንዲሠራ ልብህ
የሚገፋፋህ ከሆነ፣ ይህን የልብህን ክፉ
አሳብ አውጣና ጣለው። ክፋውን የልብህን
አሳብ ይዘህ ገሃነመ እሳት ከምትገባ ይልቅ፣
ከክፉ አሳብ ነፃ ሆነህ መንግሥተ ሰማይ
ብትገባ ይሻልሃልና።
10 «ከእነዚህ ትንንሽ ልጆች መካከል
አንዱን እንኳን በንቀት ዓይን እንዳትመለ
ከቱ ተጠንቀቁ። ምክንያቱም የእነርሱ መላ
እክት አባቴ ፊት ሳያቋርጡ ይቀርባሉና።
11 እኔ የሰው ልጅ የመጣሁት የጠፉትን
ለማዳን ነው።

12 «አንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩትና
ከመቶ በጎቹ መካከል አንዱ ቢጠፋበት ምን
ያደርግ መሰላችሁ? ዘጠና ዘጠኙን በጎች
ትቶ የጠፋውን አንዱን ፍለጋ ይሄዳል።
13 የጠፋውን በጉን ሲያገኝም፣ ባልጠፉት
ዘጠና ዘጠኙ በጎቹ ከሚሰማው ደስታ
ይልቅ፣ጠፍቶ በተገኘው በአንዱ በግ የሚሰ
ማው ደስታ የበለጠ ይሆናል! 14 እንደዚ
ሁም ደግሞ፣ ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱ
እንኳ እንዲጠፋ በሰማይ ያለው አባቴ
ፈቃድ አይደለም።
15 «ወንድምህ ቢያስቀይምህ ጥፋቱን
ለብቻው አስታውቀው። ጥፋቱን ተረድቶ
ከተጸጸተና ንስሐ ከገባ ወንድምህን ጠቀም
ከው። 16 ነገር ግን ጥፋቱን አምኖ ካልተጸ
ጸተ፣እንደገና በአንድ ወይም በሁለት ምስክ
ሮች ፊት ውቀሰው። ነገር ሁሉ በሁለት
ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ይጸናልና።
17 በምስክሮች ፊት ስታናግረው ቃልህን
መስማት ካልፈቀደ፣ ጉዳዩን ለቤተ ክርስቲ
ያን አቅርብ። ቤተክርስቲያን ጉዳዩን አመዛ
ዝና ጉዳትህን በመረዳት የምትሰጠውን
ውሳኔ ለመቀበል አሻፈረኝ የሚል ከሆነ
ግን፣ቤተ ክርስቲያን ከምዕመናን ለይታ እን
ደአረመኔ ትቁጠረው። 18 ይህንን እንድት
ረዱ እፈልጋለሁ። በምድር ላይ ያሠራች
ሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል፤እንዲሁም
በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆ
ናል።
19 «በምድር ላይ ሁለት ሆናችሁ በአ
ንድ ልብ የለመናችሁትን ሁሉ በሰማይ
ያለው አባቴ ይሰጣችኋል። 20 ሁለት ወይም
ሦስት ሆነው በስሜ በሚሰበሰቡት መካ
ከል፣ከዚያ ምን ጊዜም እኔ እገኛለሁና።»
21 ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ ኢየሱስን፣ «ጌታ
ሆይ፣ ወንድሜ ቢበድለኝስንት ጊዜ ይቅር
ልበለው? ሰባት ጊዜ ይቅር ልበለውን?»
ሲል ጠየቀው። 22 ኢየሱስም እንዲህ ብሎ
መለሰለት። «ሰባት ጊዜ ብቻ አልልህም።
ሰባ ጊዜ ሰባት ይቅር በለው።»
23 «የእግዚአብሔር መንግሥት የሒሳብ
መዝገቡን ለማስዘጋት በተነሣ ንጉሥ ትመሰ
ላለች። 24 ንጉሡ ሒሳቡን ሲቆጣጠር
ቍጥር ስፍር የሌለው ዕዳ ያለበት ሰው ፊቱ
ቀረበ። 25 ይህ ሰው ያለበትን ዕዳ ለመክፈል
ባለመቻሉ፣ ራሱ፣ ሚስቱ ልጆቹና ያለው
ንብረት በሙሉ ተሸጦ ዕዳው እንዲከፈል
ንጉሡ ትእዛዝ ሰጠ። 26 በዚህ ጊዜ ሰውየው
ከንጉሡ እግር ላይ ወድቆ፣ ‘ንጉሥ ሆይ፣
ያለብኝን ዕዳ መክፈሉን እከፍላለሁ፤ ብቻ



ቀን ይስጡኝ’ ሲል ለመነ። 27 ንጉሡም አዘ
ነለትና የነበረበትን ዕዳ በሙሉ ማረው።
28 «ይህ ሰው ከንጉሡ ተሰናብቶ ከወጣ
በኋላ፣ ጥቂት ገንዘብ ተበድሮት ያልከፈለ
ውን ባለዕዳ መንገድ ላይ አገኘ። ወዲያ
ውም ባለዕዳውን ማንቁርቱን ይዞ ያለበትን
ገንዘብ በቅጽበት እንዲከፍለው አስጨነ
ቀው። 29 ባለዕዳውም እግሩ ላይ ወድቆ፣
‘እባክህን ትንሽ ጊዜ ስጠኝ፤ያለብኝን ዕዳ
አልከፍልም አላልኩም። የምለምንህ ግን
ጊዜ እንድትሰጠኝ ብቻ ነው’ ሲል ለመ
ነው። 30 እርሱ ግን፣ ‘ገንዘቤን አሁኑኑ ካል
ከፈልከኝ’ በማለት፣ ሰውየው ተይዞ ዕዳው
በሙሉ እስኪከፈል ድረስ ወህኒ ቤት እንዲ
ገባ አደረገው።
31 «ከዚህ በኋላ የታሠረው ሰው ወዳጆች
ንጉሡ ፊት ቀርበው ታሪኩን ዘርዝረው ነገ
ሩት። 32 ንጉሡም የሆነውን ነገር ሲሰማ
አሣሣሪውን ሰው አስጠርቶ፣ ‘አንተ ክፉ
ጨካኝ! እኔ እግሬ ላይ ወድቀህ ብትለም
ነኝ ያንን ቍጥር ስፍር የሌለውን ገንዘብ
ምሬህ የለም? 33 ታዲያ እኔ እንደ ማርኩህ
አንተስ እንደዚሁ ባለዕዳዎችህን መማር
አይገባህም?’ ሲል ጠየቀው። 34 ከዚህ በኋላ
ንጉሡ፣ ‘ያለበትን ዕዳ በሙሉ ሳይከፍል
እንዳይለቀቅ!’ በማለት ሰውየውን ወህኒ
ቤት አስገባው። 35 ስለዚህ፣እናንተም ወንድ
ሞቻችሁ ሲበድሏችሁ ከልብ ይቅር ካላላች
ሁአቸው፣ በሰማይ ያለው አባቴም በደላች
ሁን ይቅር አይላችሁም።»

## ምዕራፍ 19

1 ኢየሱስ ይህንን ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ፣ገሊላን ትቶ ከዮርዳኖስ ወንዝ ባሻገር
ወደሚገኘው ወደ ይሁዳ አገር ተመለሰ።
2 ብዙ ሰዎችም ተከተሉት። እርሱም በሽተ
ኞችን ሁሉ ፈወሳቸው።
3 ከፈሪሳውያን መካከል አንዳንዶቹ ተና
ግረው በማናገር አጥምደው ሊያጠፉት ስለ
ፈለጉ፣ «ለመሆኑ በማንኛውም ምክንያት
መፋታትን ትፈቅዳለህን?» ሲሉ ጠየቁት።
4 እርሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤
«ስለዚህ ጉዳይ ማወቅ ከፈለጋችሁ መጻሕፍ
ትን ለምን አታነቡም? እግዚአብሔር በመ
ጀመሪያ ወንድና ሴትን እንደፈጠረ በመጻሕ
ፍት ተጽፏል። 5-6 ሰው እናትና አባቱን
ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተሳሰራል። ሁለት
መሆናቸውም ይቀርና አንድ አካል ይሆ
ናሉ። ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር አንድ
ስላደረጋቸው ማንም ሰው ሊለያያቸው
አይገባም።»
7 ፈሪሳውያንም መልሰው፣ «ታዲያ
ሙሴ ‘ሰው ሚስቱን መፍታት ካለበት፣
የፍቺ ወረቀት ሰጥቶ ሊያሰናብታት ይች
ላል’ ያለው ለምንድን ነው?» ሲሉ ጠየ
ቁት።
8 ኢየሱስም፣ «ሙሴ እንደዚያ ያለው፣
የልባችሁን ጠንካራነት አውቆ ነው እንጂ፣
ከጥንት ከመሠረቱማ የእግዚአብሔር ፈቃድ
ይህ አልነበረም። 9 ስለዚህ ከሌላ ወንድ ጋር
ዝሙት ካልፈጸመች በቀር፣ሚስቱን የሚፈ
ታና ሌላ ሴት የሚያገባ አመንዝሯል፤የተፋ
ታችውንም የሚያገባ እርሱ አመንዝራ
ነው» አላቸው። 10 ደቀመዛሙርቱም፣ «እን
ዲህ ከሆነማ አለማግባት ይሻላል!» አሉት።
11 እርሱም፣ «ሳያገቡ መኖር ለማንኛ
ውም ሰው የሚቻል ነገር ስላይደለ፣ ይህን
ትምህርት ሁሉም አይቀበለው ይሆናል።
በድንግልና መኖር የሚችሉ እግዚአብሔር
የፈቀደላቸው ብቻ ናቸው። 12 አንዳንዶች
ስልቦች ሆነው ይወለዱና ማግባት አይሆንላ
ቸውም። ሌሎች ደግሞ፣ሰዎች የሰለቧቸው
አሉ። ለእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉ ግን
በገዛ ፈቃዳቸው ከማግባት የሚቆጠቡም
አሉ። እንግዲህ ይህን ትምህርት መቀበል
የሚችል ይቀበለው» ብሎ መለሰላቸው።
13 ከዚህ በኋላ እጁን ጭኖ እንዲባርካ
ቸው ሕፃናትን ወደ ኢየሱስ አቀረቡለት።
ደቀመዛሙርቱ ግን ሕፃናትን ይዘው የመጡ
ትን ሰዎች፣ «ለምን ታስቸግሩታላችሁ?»
በማለት ተቆጥተው ሊመልሷቸው ቃጡ።
14 ኢየሱስ ግን፣ «ሕፃናት ወደ እኔ
ይምጡ፤አትከልክሏቸው፤መንግሥተ ሰማይ
የተዘጋጀችው እንደ እነርሱ ላሉት ነውና»
አለ። 15 እጁንም ጭኖ ባረካቸው።
16 እንዲሁም ደግሞ አንድ ሰው መጥቶ
ኢየሱስን፣ «መምህር ሆይ፣የዘላለምን ሕይ
ወት ለመውረስ ምን መልካም ነገር ላድ
ርግ?» ሲል ጠየቀው።
17 ኢየሱስም፣ «ምን መልካም ነገር ላድ
ርግ አልከኝ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር
መልካም የለም። ወደ መንግሥተ ሰማይ
መግባት ከፈለግህ ግን ትእዛዛትን ፈጽም»
አለው።
18 ሰውየውም፣ «የትኞቹን ትእዛዛት
ማለትህ ነው?» ሲል ጠየቀው። ኢየሱስም፣
«አትግደል፣አታመንዝር፣አትስረቅ፣በሐሰት
አትመስክር፣ 19 እናትና አባትህን አክብር፣
ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ» አለው።
20 ሰውየውም፣ «ይህማ ስፈጽመው የኖር

ኩት ነው። ሌላ የሚቀረኝ እንዳለ ብዬ ነው
እንጂ» አለው።
21 ኢየሱስም፣ «እንግዲያው ፍጹም ለመ
ሆን ከፈለግህ ፣ ሄደህ ንብረትህን ሁሉ
ሸጠህ፣ ገንዘቡን ለድሆች ስጥ። ዋጋህን በሰ
ማይ ታገኛለህ። ከዚያ በኋላ ና ተከተ
ለኝ።» አለው። 22 ሰውየውም ይህንን ሲሰማ
ከሀብቱ ለመላቀቅ ባለመፈለጉ በጣም አዝኖ
ሄደ።
23 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን
እንዲህ አላቸው። «ለሀብትና ለንብረቱ ለሚ
ስገበገብ፣ መንግሥተ ሰማይ መግባት በጣም
አስቸጋሪ ነው። 24 እንዲያውም ፣ ሀብታም
ሰው መንግሥተ ሰማይ ከሚገባ፣ግመል በመ
ርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል።»
25 ደቀመዛሙርቱም ኢየሱስ በተናገረው
ቃል በመገረም፣ «እንዲህ ከሆነ ታዲያ ማን
ሊድን ይችላል?» አሉ።
26 ኢየሱስም ፣ «እንደ ሰው አስተሳሰብ
ከሆነ ማንም ሊድን አይችልም። ነገር ግን
ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር
የለም» አላቸው።
27 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፣እንደ
ምታየው ይኸው እኛ ያለ የሌለ ሀብታችንን
ትተን ተከትለንሃል። ታዲያ ይህንን በማድረ
ጋችን የምናገኘው ምንድነው?» ሲል ጠየ
ቀው።
28 ኢየሱስም፣ «እናንተማ በክብር ዙፋኔ
ላይ በምቀመጥበት በዳግም ምጽአት ጊዜ፣
በአሥራ ሁለት ዙፋን ላይ ተቀምጣችሁ
በአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች ላይ
ትፈርዳላችሁ። 29 ስለዚህ እኔን ለመከተል
ሲል ቤቱን፣ወንድሞቹን፣እኅቶቹን፣አባትና
እናቱን፣ልጆቹንና ንብረቱን የሚተው፣ለእኔ
ሲል የተዋቸውን የእነዚህን ነገሮች ዋጋ፣
በመቶ እጥፍ አግኝቶ የዘላለምን ሕይወት
ይወርሳል። 30 ሆኖም ፣ ብዙዎች የፊተኞች
የኋለኞች ይሆናሉ ፤ ብዙዎች የኋለኞች
ደግሞ የፊተኞች ይሆናሉ» አላቸው።

## ምዕራፍ 20

1 ኢየሱስ ስለ መንግሥተ ሰማይ የሚከ
ተለውን ምሳሌ ተናገረ። «አንድ የእርሻ
መሬት የነበረው ሰው ሰብሉን የሚሰበስ
ቡለት የቀን ሙያተኞችን ለመቅጠር
ማልዶ ከቤቱ ወጣ። 2 ከዚያም ለእያንዳ
ንዱ የቀን ሙያተኛ ፣በአገሩ ሒሳብ በቀን
አንድ ብር ሊከፍል ተስማምቶ፣በሥራ ላይ
አሰማራቸው።
3 «ረፋዱ ላይ በገበያው በኩል ሲያልፍ
ሌሎች ሥራ ፈላጊዎች ቆመው አገኘ።
4 እነርሱንም ከሥራ ሰዓት በኋላ የድካማቸ
ውን ዋጋ ለመክፈል ተስማምቶ፣በሥራ ላይ
አሰማራቸው። 5 በስድስትና በዘጠኝ ሰዓት
ላይም፣እንደዚሁ ሌሎች የቀን ሙያተኞች
አግኝቶ ቀጠረ።
6 «ከሰዓት በኋላ በአሥራ አንድ ሰዓት
ላይ እንደ ገና ወደ ከተማ ሲወጣ፣በርከት
ያሉ ሌሎች ሥራ ፈላጊዎች ቆመው
አገኘ። እነርሱንም፣ ‘ምነው ሥራ ፈትታች
ኋል?’ አለና ጠየቃቸው።
7 «እነርሱም፣ ‘የሚቀጥረን ሰው አላገኘ
ንም’ ሲሉ መለሱለት። እርሱም፣ ‘በሉ እን
ግዲያው ሂዱና እርሻዬ ላይ ከተሰማሩት
የቀን ሙያተኞች ጋር አብራችሁ ሥሩ’ አላ
ቸው።
8 «ጀንበር ልትጠልቅ ስትል ም ፣ የእር
ሻው ባለቤት ደመወዝ ከፋዩን፣የቀን ሙያ
ተኞቹን በሙሉ ጠርቶ መጨረሻ ሥራ ላይ
ከተሰማሩት በመጀመር፣የድካማቸውን ዋጋ
እንዲከፍላቸው አዘዘው። 9 ስለዚህ በመጀመ
ሪያ በአሥራ አንድ ሰዓት ላይ የተቀጠሩት
ቀርበው አንድ አንድ ብር ተቀበሉ።
10 ቀደም ብለው የተቀጠሩት ይህንን
ሲያዩ ፣ ለእነርሱ የበለጠ ገንዘብ የሚከፈላ
ቸው መስሏቸው ነበር። ነገር ግን ለእነር
ሱም አንድ አንድ ብር ብቻ ተከፈላቸው።
11-12 «በዚህ ጊዜ፣ ‘እነዚህ ሰዎች የሠ
ሩት አንድ ሰዓት ብቻ ሲሆን፣ቀኑን ሙሉ
በፀሐይ ሐሩር ስንቃጠልና ስንለፋ ከዋል
ነው ከእኛ እኩል እንዴት ይከፈላቸዋል?’
ሲሉ ተቃውሞ አሰሙ።
13 «የእርሻው ባለቤትም ከቀን ሙያተ
ኞቹ አንዱን፣ ‘ወዳጄ ሆይ፣ ምን ጥፋት
አጥፍቼ ነው የምትወቅሰኝ? የተዋዋልነው
በቀን አንድ ብር እንድከፍልህ አይደለምን?
14 ታዲያ ያስቀረሁብህ ነገር አለ? በተዋዋል
ነው መሠረት የተስማማነውን ዋጋ ተቀብ
ለህ መሄድ ትችላለህ። ሥራውን ለሠሩልኝ
ሁሉ እኩል መክፈሌ አያስገርምህ። 15 የገዛ
ገንዘቤን እንኳ እኩል መክፈልና፣እንደፈለ
ገኝ እንሥቼ ብሰጥ የሚከለክለኝ ሕግ ያለ
መሰለህ? ይህ ሊያስቆጣህ አይገባም’
አለው።»
16 ኢየሱስ ምሳሌውን ተናግሮ ከጨረሰ
በኋላ፣ «አዎን፣የኋለኞች የፊተኞች፣የፊተ
ኞችም የኋለኞች ይሆናሉ» አለ።
17 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም
ሲሄድ፣ደቀመዛሙርቱን ለብቻቸው ጠርቶ፣
18 በኢየሩሳሌም ስለሚደርስበት ነገር ፣



«በኢየሩሳሌም ለካህናት አለቆችና ለአይ
ሁድ ሃይማኖት መምህራን አሳልፈው ይሰ
ጡኛል። እነርሱም የሞት ፍርድ ይፈርዱብ
ኛል። 19 በሮማውያን ገዢዎች ፊትም እቀ
ርባለሁ። ካፌዙብኝ በኋላ ይሰቅሉኛል።
ነገር ግን በሦስተኛው ቀን ከሞት እነሣ
ለሁ» በማለት በቆይታ አዋያቸው።
20 ከዚያም የዘብዴዎስ ሚስት ፣ የያዕቆ
ብና የዮሐንስ እናት ፣ ኢየሱስ ፊት በመቅ
ረብ፣ «አንድ ነገር አድርግልኝ» ብላ ለመነ
ችው። 21 ኢየሱስም፣ «ምን እንዳደርግልሽ
ትፈልጊአለሽ?» አላት። «በመንግሥትህ
ዙፋን ላይ ስትቀመጥ፣እነዚህ ሁለት ልጆቼ
ከአንተ ጋር በግራና በቀኝ እንዲቀመጡ
አድርግልኝ» አለችው።
22 ኢየሱስም፣ «የምትለምኚውን አታው
ቂም» አላት። ከዚያም ወደ ያዕቆብና ወደ
ዮሐንስ ፊቱን በመመለስ ፣ «ለመሆኑ እኔ
ከምጠጣበት የሥቃይ ጽዋ መጠጣት ትችላ
ላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም ፣
«አዎን እንችላለን!» ሲሉ መለሱለት።
23 ኢየሱስም፣ «በእርግጥ ከጽዋው ልት
ጠጡ ትችላላችሁ። ነገር ግን አጠገቤ ማን
መቀመጥ እንደሚችል የምወስነው እኔ አይ
ደለሁም። ምክንያቱም እነዚህ ቦታዎች
አባቴ ለመረጣቸው ሰዎች ተለይተው የተቀ
መጡ ናቸውና» አላቸው።
24 የቀሩት አሥሩ ደቀመዛሙርት የያዕቆ
ብና የዮሐንስ ፍላጎት ደስ አላሰኛቸውም።
25 ኢየሱስ ግን ሁሉንም በአንድ ላይ
ሰብስቦ እንዲህ አላቸው። «የአሕዛብ ነገሥ
ታት ፈላጭ ቆራጭ ናቸው። እያንዳንዱም
የበታች ባለሥልጣን ከሥሩ ያሉትን አሽቆጥ
ቁጦ ይገዛል። 26 በእናንተ መካከል ግን እን
ዲህ ያለው ሁኔታ መኖር አይገባውም።
ከመካከላችሁ ኃላፊ ለመሆን የሚመኝ
ቢኖር አገልጋያችሁ ይሁን። 27 ማንባር
ቀደም ሆኖ መገኘት የሚፈልግ ቢኖር ፣
እርሱ የበታቻችሁ ይሁን። 28 በዚህም አስተ
ሳሰባችሁ ከአስተሳሰቤ ጋር ሠምሮ መገኘት
አለበት። እኔ የመጣሁት ሰዎች እንዲያገለግ
ሉኝ ሳይሆን፣ሰዎችን ለማገልገልና ሕይወቴ
ንም ለብዙዎች ቤዛ አድርጌ ለመስጠት
ነው።»
29 ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ
የኢያሪኮን ከተማ ለቅቀው ወጡ። ብዙ
ሕዝብም ተከተላቸው። 30 ሁለት ዓይነ ስው
ሮችም በመንገድ ዳር ቊጭ ብለው ነበር።
ኢየሱስ በዚያ በኩል ማለፉን ሲሰሙ፣ «የዳ
ዊት ልጅ ጌታ ሆይ ፣ እባክህን ማረን!»
እያሉ ጮኹ።
31 ሕዝቡም ፣ ዝም ሊያሰኛቸው ሞክሮ
ነበር። ዓይነ ስውሮቹ ግን እሺ አላሉም።
እንዲያውም «የዳዊት ልጅ ጌታ ሆይ!
ማረን!» እያሉ ከበፊቱ አብልጠው ጮኹ።
32-33 ኢየሱስም ቆም አለና ወደ እርሱ
ጠርቶ ፣ «ምን እንዳደርግላችሁ ትፈልጋላ
ችሁ?» አላቸው። እነርሱም፣ «ጌታ ሆይ፣
ዓይኖቻችንን እንድታበራልን እንፈልጋለን»
አሉት።
34 ኢየሱስም አዘነላቸው። በእጁም ዓይ
ኖቻቸውን ዳሰሰ። ወዲያውም ማየት ቻሉ።
ከዚያም ተከተሉት።

## ምዕራፍ 21

1 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ
ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ተቃረበና ደብረ
ዘይት ተራራ አጠገብ ወደምትገኘው ወደ
ቤተ ፋጌ መንደር እንደ ደረሰ፣ከደቀመዛ
ሙርቱ መካከል ሁለቱን ወደ አቅራቢያው
መንደር ላካቸው። 2 «እዚያም እንደ ደረሳ
ችሁ አንዲት አህያና ውርንጫዋ ታሥረው
ታገኛላችሁ። ከታሠሩበት ፈትታችሁ አም
ጡልኝ። 3 ምናልባት ሰው፣ ‘ለምንድን ነው
የምትፈቷቸው’ ብሎ ቢጠይቃችሁ፣ ‘ጌታ
ይፈልጋቸዋል’ ብቻ በሉት አይከለክላች
ሁም» አላቸው።
4-5 ይህም ሁኔታ ሊፈጸም የቻለው ፣
ነቢዩ ፣ «ኢየሩሳሌምን፣ ‘ንጉሥሽ ትሑት
ሆኖ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ
አንቺ ይመጣል’ በሏት» በማለት የተናገ
ረው ቃል መፈጸም ስላለበት ነበር።
6 ሁለቱ ደቀመዛሙርት የታዘዙትን በመ
ፈጸም ፣ 7 አህያዋን ከነውርንጫዋ አመጡ
ለት። ልብሳቸውንም በአህዮቹ ጀርባ ላይ
አመቻችተው ኢየሱስ ተቀመጠባቸው።
8 ከሕዝቡ መካከል አንዳንዶቹ መደረቢያቸ
ውን ከላያቸው እያነሡ እርሱ በሚያልፍ
በት መንገድ ላይ ሲያነጥፉ፣የቀሩት ደግሞ
የዘንባባ ቅርንጫፍ እየቀጠፉ በመንገዱ ላይ
ይጎዝጉዙ ነበር። 9 ሕዝቡም ከፊትና ከኋ
ላው ሆኖ ፣ «ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፣በጌታ
ስም የሚመጣው የተባረከ ይሁን። እነሆ
መጥቷልና በሰማያት ከፍ ከፍ አድርጉት!»
እያሉ ጮኹ።
10 ኢየሱስ በዚህ ዓይነት ወደ ኢየሩሳ
ሌም ሲገባ ፣ የከተማዋ ነዋሪዎች ግልብጥ
ብለው በመውጣት ፣ «ለመሆኑ ይህ ሰው
ማን ነው?» እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያ
የቁ።

[11] ከሕዝቡም መካከል፣ «በገሊላ ከምት
ገኘው ከናዝሬት የመጣው፣ ነቢዩ ኢየሱስ
ነው» ይሉ ነበር።
[12] ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በቀጥታ ወደ
ቤተ መቅደስ ሄደ። በዚያም የገንዘብ መንዛ
ሪዎችን ጠረጴዛና የርግብ ሻጮችን መደ
ብር ገለባበጠ።
[13] «ቤቴ የጸሎት ቤት ነው ተብሎ በቅ
ዱሳት መጻሕፍት ተጽፏል። እናንተ ግን
የሌቦችና የቀማፊዎች ዋሻ አደረጋችሁት!»
አላቸው።
[14] ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ እንዳለ
ዓይነ ስውሮችንና ሽባዎችን ወደ እርሱ
አመጡ። እርሱም ፈወሳቸው። [15] የካህናት
አለቆችና የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን
እንዚህን አስደናቂ ተአምራት ሲያደርግ
በማየታቸውና በተለይም ሕፃናት፣ «ሆሣዕና
ለዳዊት ልጅ» እያሉ ሲዘምሩ በመስማታ
ቸው ተቆጡ። ኢየሱስንም፣ «እነዚህ
ልጆች የሚሉትን ትሰማ የለ?» ብለው ጠየ
ቁት።
[16] ኢየሱስም፣ «አዎን፣ እሰማለሁ፤ በቅዱ
ሳት መጻሕፍት ‘ሕፃናት እንኳ ምስጋና
ያቀርቡለታል’ ተብሎ የተጻፈውን እናንተስ
አላነበባችሁምን?» በማለት መልሶ ጠየቃ
ቸው።
[17] ከዚያም ወደ ቢታንያ ሄዶ አደረ።
[18] በማግስቱም ወደ ኢየሩሳሌም ሲመለስ
መንገድ ላይ እንዳለ ተራበ። [19] ከመንገዱ
ዳር የበለስ ዛፍ አይቶ የሚበላ ፍሬ እንዳለ
ባት በማለት ተጠጋ። ነገር ግን የበለሲቱ
ዛፍ ከቅጠል በቀር ፍሬ አልነበረባትም።
«ከዛሬ ጀምሮ ፍሬ አታፍሪ፣ መካን ሁኚ»
ብሎ የበለሲቱን ዛፍ ረገማት። ዛፊቱም ወዲ
ያውኑ ጠወለገች።
[20] ደቀመዛሙርትም በመደነቅ፣ «ዛፊቱ
እንዴት ነው እንዲህ ባንድ አፍታ ልትጠወ
ልግ የቻለችው?» በማለት ኢየሱስን ጠየ
ቁት።
[21] እርሱም፣ «እውነቱን ልንገራችሁ።
ካመናችሁና ካልተጠራጠራችሁ እኔ አሁን
ያደረግሁትን ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ ይህንን
ተራራ ተነሥተህ ወደ ባሕር ግባ ብትሉት
ተነሥቶ ይገባል። [22] ስለዚህ አምናችሁ በጸ
ሎት የምትጠይቁትን ማንኛውንም ነገር
ታገኛላችሁ» አላቸው።
[23] ኢየሱስ እንደ ገና ቤተ መቅደስ
ገብቶ በማስተማር ላይ ሳለ፣ የካህናት አለቆ
ችና የአገር ሽማግሌዎች ወደ ኢየሱስ በመ
ቅረብ፣ «ይህን ለማድረግ ምን ሥልጣን
አለህ? ይህንንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ?»
አሉት
[24] እርሱም፣ «በመጀመሪያ እኔ ለማቀር
ብላችሁ ጥያቄ መልስ ስጡኝና ከዚያ በኋላ
የጠየቃችሁኝን እመልስላችኋለሁ። [25] የዮሐ
ንስ ጥምቀት ከእግዚአብሔር ነበር ወይስ
ከሰው?» እነርሱም እርስ በእርሳቸው፣ ተያ
ዩና፣ «አሁን እኮ ‘ከእግዚአብሔር ነበር’
ብንለው፣ ‘ትምህርቱን ለምን አልተቀበላች
ሁም?’ ሊለን ነው፤ [26] ወይ ደግሞ፣ ከሰው
ብለን እንዳንመልስለት፣ ሕዝቡ የዮሐንስን
ነቢይነት አምኖ የተቀበለው በመሆኑ ትልቅ
ሁከት ይፈጥርብናል» በማለት ከተንሾካሾኩ
በኋላ፣ [27] «እንጃ እኛ አናውቅም» ሲሉ
መለሱለት። ኢየሱስም፣ «እንግዲያውስ
እኔም በምን ሥልጣን ይህን እንደማደርግ
አልነግራችሁም!» አላቸው።
[28] ቀጥሎም ኢየሱስ የሚከተለውን
ምሳሌ ተናገረ። «አንድ ሰው ሁለት ልጆች
ነበሩት። እርሱም ትልቁን ልጁን፣ ‘ዛሬ
ወደ እርሻ ቦታችን ሄደህ ስትሠራ ዋል’
ብሎ አዘዘው። [29] ልጁም፣ ‘እምቢ፣ አልሄ
ድም!’ በማለት ካንገራገረ በኋላ፣ አሳቡን
ለውጦ ወደ አባቱ እርሻ ሄዶ ሲሠራ ዋለ።
[30] አባቱም ትንሹን ልጁን ጠርቶ፣ ‘ወደ
እርሻችን ሄደህ ስትሠራ ዋል’ አለው። ትን
ሹም ልጅ፣ ‘እሺ እሄዳለሁ’ ብሎ ሳይሄድ
ቀረ። [31] ታዲያ በእናንተ አስተሳሰብ ከሁ
ለቱ ልጆች የአባቱን ፈቃድ የፈጸመው የት
ኛው ይመስላችኋል?» አላቸው። እነር
ሱም፣ «ታላቀየው ነው» ሲሉ መለሱለት።
ኢየሱስም የምሳሌውን ትርጉም እንደ
ዚህ ሲል አብራራላቸው። «እንደ እውነቱ
ከሆነ፣ ግፈኞችና አመንዝራዎች ከእናንተ
ቀድመው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ይገባሉ። [32] ምክንያቱም ዮሐንስ፣ ‘ንስሐ
ግቡ ፤ ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ’ ብሎ
አስተማረ ፤ እምቢተኞችና አመንዝራዎች
እንኳ ንስሐ ሲገቡ እያያችሁ፣ ወደ እግዚአ
ብሔር ሳትመለሱ ቀራችሁ። ማመንም አል
ፈለጋችሁም።»
[33] እንደ ገናም ኢየሱስ የሚከተለውን
ሌላ ምሳሌ ነገራቸው። «አንድ የወይን አት
ክልት ቦታ የነበረው ሰው የአትክልቱን ቦታ
ዙሪያውን አጠረ። ለዘበኛም የሚሆን ማማ
ሠራ። ከዚያም የወይኑን አትክልት ተንከባ
ክበው ፍሬውን ለሚያካፍሉት ሠራተኞች
አከራይቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ይኖር
ጀመር።
[34] «የወይኑ ፍሬ መሰብሰቢያ ጊዜ ሲደ



ርስ፣ ድርሻውን ተቀብለው እንዲያመጡለት
አገልጋዮቹን ወደ ወይኑ ጠባቂዎች ላካ
ቸው። [35] የወይኑ ጠባቂዎችም የተላኩትን
ሰዎች ይዘው፣ አንዱን በዱላ ቀጠቀጡት፤
ሌላውን ገደሉት ፤ ሦስተኛውን በድንጋይ
ወገሩት።
[36] «የወይኑ አትክልት ባለቤትም እንደ
ገና ከበፊቱ ይልቅ ቁጥራቸው በዛ ያሉ
ሰዎች ላከ። ሆኖም በአትክልት ቦታው ላይ
ያስቀመጣቸው ገበሬዎች አሁንም እንደበ
ፊቱ አደረጉ። [37] በመጨረሻ፣ ‘ልጄንስ ያከ
ብሩታል’ ብሎ በማሰብ፣ ወደ እነዚሁ
ሰዎች ልጁን ላከው።
[38] «እነርሱም የልጁን መምጣት ገና
በሩቅ እንዳዩ፣ ‘ወራሹ መጥቷል፣ ይዘን ከገ
ደልነው የዚህ የወይን አትክልት ቦታ ባለ
ቤት እንሆናለን’ በማለት እርስ በእርሳቸው
ተማከሩ። [39] ልጁንም ከአትክልቱ ቦታ ጎት
ተው አውጥተው ገደሉት።
[40] «የወይኑ ባለቤት ወደ ርስቱ ሲመለስ
የልጁን ገዳዮች ምን የሚያደርጋቸው ይመ
ስላችኋል?» ሲል ጠየቃቸው።
[41] የካህናት አለቆቹና የአገር ሽማግሌዎ
ቹም፣ «እነዚያን ክፉ ገበሬዎች የሞት
ቅጣት ይፈጽምባቸዋል። የአትክልቱንም
ቦታ፣ የሚገባውን ድርሻ በወቅቱ ለሚሰጡት
ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል» ሲሉ መለሱ
ለት።
[42] ኢየሱስም፣ «‘ግንበኞች የናቁት ድን
ጋይ የማዕዘኖች ማዕዘን ሆነ’ ተብሎ በእግዚ
አብሔር ቃል ውስጥ የተጻፈውን አላነበባች
ሁም? ይህም እግዚአብሔር ራሱ የሠራው
ድንቅ ሥራ ነው! [43] እንድትረዱት የምፈል
ገው ነገር ቢኖር፣ የእግዚአብሔር መንግ
ሥት ከእናንተ ተወስዳ፣ ለእግዚአብሔር
የሚገባውን የምርት ድርሻ ለሚሰጡ
ሌሎች ሕዝቦች ትሰጣለች። [44] ይህ የእው
ነት አለት የሚያደናቅፋቸው ሁሉ ይሰበ
ራሉ፣ አለቱ የሚወድቅባቸው ደግሞ ትቢያ
እስኪሆኑ ድረስ ይደቀቃሉ።»
[45] የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን፣ ኢየ
ሱስ ስለ ገበሬዎቹ የተናገረው ምሳሌ እነር
ሱን የሚነካ መሆኑን ስለተገነዘቡ፣
[46] ይዘው ሊያሥሩት ፈለጉ። ነገር ግን
ሕዝቡ የኢየሱስን ነቢይነት አምኖ ስለተቀበ
ለው፣ እጃቸውን ሊያነሡበት አልደፈሩም።

## ምዕራፍ 22

[1] ኢየሱስ የእግዚአብሔር መንግሥት
በምን እንደምትመሰል ለማስረዳት ብዙ
ምሳሌዎችን እየመሰለ አስተማረ። ከምሳሌ
ዎቹም አንዱ የሚከተለው ነው። [2] «መን
ግሥተ ሰማይ ለልጁ ሠርግ ትልቅ ድግስ
በደገሰ ንጉሥ ትመሰላለች። [3] ንጉሡ በግ
ብዣው ላይ እንዲገኙ ብዙ ሰዎችን
ጋበዘ። የግብዣውም ጊዜ ሲደርስ እንግዶ
ቹን እንዲጠሩ መልእክተኞቹን ላከ።
ነገር ግን የተጋበዙት እንግዶች ድግሱን
ለመብላት ፈቃደኞች አልሆኑም። [4] እንደ
ገናም መልእክተኞቹ በድጋሚ ወደ ተጋ
በዙት ሰዎች ሄደው፣ ‘ማናቸውም ነገር
ተዘጋጅቶ ይጠብቃችኋልና በቶሎ ኑ!’
ብለው እንዲነግሩአቸው ላካቸው።
[5] «ተጋባዦቹ አሁንም ወደ ግብዣው
ለመምጣት ፈቃደኞች አልሆኑም። እንዲያ
ውም የግብዣውን ጥሪ በመናቅ አንዱ ወደ
እርሻው፣ ሌላው ወደ ንግዱ ሄደ። [6] የቀሩት
ደግሞ ከንጉሡ የተላኩትን መልእክተኞች
ክፍ ዝቅ አድርገው አዋርደው ከሰደቡአ
ቸው በኋላ ደበደቡአቸው፤ ሌሎቹንም ይባስ
ብለው ገደሉአቸው።
[7] «ንጉሡም ይህንን ሲሰማ ተቆጣ።
የጦር ሠራዊቱንም አዝምቶ የመልእክተኞ
ቹን ገዳዮች አጠፋቸው። የሚኖሩበትንም
ከተማ አቃጠለ። [8] ከዚህ በኋላ ንጉሡ አገል
ጋዮቹን ሰብስቦ፣ ‘የሠርጉ ድግስ ተዘጋጅ
ቷል። ተጠርተው የነበሩት እንግዶች ግን
በሠርጉ ድግስ ላይ የመገኘት ክብር የሚገ
ባቸው ሆነው አልተገኙም። [9] ስለዚህ ወደ
ከተማ ሂዱና ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ
ግብዣው እንዲመጣ ጋብዙ’ ብሎ አዘዛ
ቸው።
[10] «አገልጋዮቹም በታዘዙት መሠረት
በጎም ክፉም ሳይሉ ያገኙትን ሁሉ ሰብስ
በው ወደ ግብዣው ይዘው መጡ። ተጋባ
ዦም እንደገባ አዳራሹ ግጥም ብሎ ሞላ።
[11] ንጉሡ በአዳራሹ እንደተገኘ፣ ከተጋባ
ዦቹ መካከል የተዘጋጀለትን የሠርግ ልብስ
ሳይለብስ የገባ አንድ ሰው አየ።
[12] «ወዲያውም ወደዚህ ሰው ቀረብ
ብሎ፣ ‘ምነዋ ወዳጄ፣ የሠርጉን ልብስ ሳትለ
ብስ በግብዣዬ ላይ የተገኘኸው እንዴት
ነው?’ ሲል ጠየቀው። ሰውየውም ምንም
መልስ መስጠት አልቻለም። [13] ንጉሡም
አገልጋዮቹን ጠራና፣ ‘ይህንን ሰው የፈጥኝ
ቅሥራችሁ ጥርስ ማፋጨትና ልቅሶ ወዳለ
በት ጨለማ ውስጥ ጣሉት’ ሲል ትእዛዝ
ሰጠ። [14] አያችሁ፣ የተጠሩት ብዙዎች የተ
መረጡት ግን ጥቂቶች ናቸው።»
[15] ከዚህ በኋላ ፈሪሳውያን ኢየሱስ የሚ

ናገረውን ቃል አንድ ባንድ እየተከታተሉ፣
በነገር ሊያጠምዱትና ሊወነጅሉት በማሰብ
ተሰብስበው መዶለት ጀመሩ። 16 ከዚያም
ከራሳቸው ተከታዮችና ከሄሮድስ ደጋፊዎች
ጥቂቶቹን በማስተባበር፣የሚከተለውን ጥያቄ
እንዲጠይቁት ላኩዋቸው። የተላኩትም
ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ «ጌታ ሆይ፣ አንተ
ማንንም እንደማትፈራ እናውቃለን። ‘ለእ
ከሌ’ ብለህ እንደማታዳላና ምን ጊዜም
እውነቱን ብቻ የምትናገር መምህር መሆን
ህን እናውቃለን። 17 ለመሆኑ፣ለቄሣር ግብር
መገበር ይገባል? ወይስ አይገባም?» ሲሉ
ጠየቁት።

18 ኢየሱስም ነገሩ የተንኰል መሆኑን
በማወቁ፣ «እናንተ ግብዞች! ማንን ልታሳ
ስቱ ነው የምትፈልጉት? 19 ለግብር የምት
ከፍሉትን ገንዘብ እስቲ አሳዩኝ?» አላ
ቸው። እነርሱም ገንዘቡን አውጥተው
ሰጡት። 20 እርሱም፣ «እዚህ ገንዘብ ላይ
ያለው ምስል የማን ነው? ከሥሩስ የተጻ
ፈው ስም ማን ይላል?» ሲል ጠየቃቸው።
21 እነርሱም፣ «የቄሣር ነው» ሲሉ መለሱ
ለት። እርሱም፣ «እንግዲያውስ፣ ለቄሣር
የሚገባውን ለቄሣር፣ለእግዚአብሔር የሚገባ
ውንም ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጡ» አላ
ቸው።

22 በነገር ሊያጠምዱት የተላኩትም
ሰዎች ኢየሱስ በሰጣቸው መልስ በመደነ
ቅና የሚሉትን በማጣት ወደ መጡበት
ተመለሱ።

23 በዚያኑ ቀን፣ «የሙታን ትንሣኤ የሚ
ባል ነገር የለም» የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው የሚከተለውን ጥያቄ ጠየ
ቁት። 24 «ጌታ ሆይ! ሙሴ፣ ‘አንድ ሰው
ልጅ ሳይወልድ የሞተ እንደሆነ ወንድሙ
የሚቹን ሚስት ያግባና የሚወለዱት ልጆች
የሚቹን ንብረት ይውረሱ’ ብሏል። 25 በእኛ
ዘንድ ሰባት ወንድማማች የነበሩበት ቤተ
ሰብ ነበር። የሁሉም ታላቅ የነበረው ሰው
ሚስት አገባና ልጅ ሳይወልድ ሞተ። ታና
ሽየውም የሚች ወንድሙን ሚስት አገባ።
26 እርሱም ልጅ ሳይወልድ በመሞቱ ሴቲ
ቱን ተከታይ ወንድሙ አገባት። በዚህ ዓይ
ነት መንገድ ሴቲቱን ሰባቱም ወንድማማች
በየተራ አገቧት። 27 በመጨረሻ ሴቲቱም
ሞተች። 28 ስለዚህ ይህችን ሴት ሰባቱም
ወንድማማች ስላገቧት በትንሣኤ ጊዜ የማን
ኛቸው ሚስት ትሆናለች?»

29 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው።
«ይህን ከመሰለው ስሕተት ውስጥ የምትወ
ድቁት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጻፈ
ውን እውነትም ሆነ የእግዚአብሔርን
ኃይል ባለማወቃችሁ ነው። 30 የሰማይ መላ
እክት እንደማያገቡና እንደማይጋቡ ሁሉ፣
ሰዎችም ከትንሣኤ በኋላ እንደ መላእክት
ይኖራሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም።
31 ትንሣኤን በሚመለከት ረገድ ደግሞ መጻ
ሕፍት ምን እንደሚሉ አላነበባችሁም?
32 እግዚአብሔር በቁጥቋጦ ውስጥ ሆኖ፣
‘እኔ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ አም
ላክ ነኝ’ ሲል የተናገረውስ ይህንኑ የሚያስ
ረዳ አይደለምን? በዚህም እግዚአብሔር
የሕያዋን አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ
አለመሆኑ ይታወቃል።»

33 በዚያ የነበረውም ሕዝብ ኢየሱስ በሰ
ጠው መልስ በጣም ተደነቀ።

34-35 ኢየሱስ በሰጣቸው መልስ ሰዱቃ
ውያን አፋቸው እንደተያዘ በተረዱ ጊዜ፣
ፈሪሳውያን ደግሞ ሌላ ጥያቄ ሊጠይቁት
ተዘጋጁ። ከመካከላቸውም አንድ የሕግ ባለ
ሞያ የነበረ ሰው፣ 36 «ጌታ ሆይ፣ ከሙሴ
ትእዛዛት መካከል ቀድሚያ ሊሰጠው የሚገ
ባው የትኛው ነው?» ሲል ጠየቀው።

37 ኢየሱስም፣ «እግዚአብሔር አምላክ
ህን በፍጹም ልብህ፣በፍጹም ነፍስህና በፍ
ጹምም አእምሮህ ውደድ። 38-39 ይህ የመ
ጀመሪያውና ታላቁም ትእዛዝ ነው። ሌላ
ውና በቀላሉም ሊታይ የማይገባው ደግሞ፣
‘ጐረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ’ የሚለው
ትእዛዝ ነው። 40 ሌሎች ትእዛዛትም ሆኑ፣
በነቢያት አንደበት የተነገሩት ቃላት፤ከእነ
ዚህ ሁለት ትእዛዛት ክልል አይወጡም።
እነዚህን ሁለት ትእዛዛት ከፈጸማችሁ ሌሎ
ቹን በሙሉ ፈጽማችኋል ማለት ነው» አላ
ቸው።

41 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ተሰብስበው የነበ
ሩትን ፈሪሳውያን እንዲህ ሲል ጠየቃቸው፣
42 «መሲሕ ክርስቶስ ማን ነው? የማንስ
ልጅ ነው?» እነርሱም፣ «የዳዊት ልጅ
ነው» ሲሉ መለሱለት። 43 እርሱም፣ «ይህ
ከሆነ ታዲያ፣ ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ
ተመርቶ ክርስቶስን፣ ‘ጌታዬ’ እያለ የጠ
ራው ለምንድን ነው? 44 ‘እግዚአብሔር
ጌታዬን፣ ጠላቶችህን ከእግርህ በታች እስካደ
ርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው’ በማ
ለት ለምን ይናገራል? 45 ዳዊት ‘ጌታዬ’
እያለ ከጠራው፣ ክርስቶስ እንዴት የዳዊት
ልጅ ሊሆን ይችላል?» አላቸው።

46 እነርሱም ምንም መልስ ሊሰጡት
አልቻሉም። ከዚያች ቀን ጀምሮ ይህን ስለ
መሰለው ነገር ጥያቄ ሊያቀርብለት የደፈረ
አልነበረም።

## ምዕራፍ 23

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በዚያ ለነበረው
ሕዝብና ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ ሲል
ተናገረ። 2 «የአይሁድ ሃይማኖት መምህራ
ንና ፈሪሳውያን በሙሴ እግር የተተኩ
መምህራን ናቸው። 3 እነርሱ አድርጉ
የሚሏችሁን አድርጉ፤ የሚያስተምሯችሁ
ንም ጠብቁ። ነገር ግን እነርሱ የሚያደርጉ
ትን አታድርጉ። 4 እነርሱ ራሳቸው ለመፈ
ጸም የማይሞክሩትን ሕግ እናንተን አድርጉ
ይሏችኋል።

5 «የሚያደርጉትም ነገር ቢኖር፣ ሰዎች
እንዲያዩላቸው የሚፈልጉትን ብቻ ነው።
ከእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች የተጻፈበትን
ክታብ በክንዳቸው ላይ በማሠርና ረዥም
ልብስ በመልበስ ቅዱስ መስለው ይታያሉ።
6 በግብዣ ቦታ ሲገኙና ጸሎት በሚደረግበት
ምኵራብ ሲሄዱም የክብሩን ሥፍራ ተሽቀ
ዳድመው ይይዛሉ። 7 በደረሱበት ቦታ ሁሉ
ሰዎች እንዲሽቆጠቆጡላቸውና፣ ‘መምህር
እገሌ፣ መምህር እገሌ’ እያሉ እንዲጠሩዋ
ቸው ይፈልጋሉ። 8 እናንተ ግን መምህራ
ችሁ እግዚአብሔር ስለሆነና በመካከላችሁ
ልዩነት ሳይኖር ወንድማማች ስለሆናችሁ፣
ማንም ተነሥቶ መምህር በሉኝ ቢላችሁ
በዚህ ስም አትጥሩት። 9 እንዲሁም አባታ
ችሁ በሰማይ ያለው እግዚአብሔር ስለሆ
ነና፣ ‘አባት’ ተብሎ መጠራት የሚገባው
እርሱ ብቻ በመሆኑ፣በዚህ ምድር ላይ ማን
ንም፣ ‘አባት’ ብላችሁ አትጥሩ። 10 መምህ
ራችሁ አንዱ ክርስቶስ ብቻ ስለሆነ፣ማንም
‘መምህር’ ብሎ እንዲጠራችሁ አታድርጉ።

11 «የእናንተ ትልቅነት የሚታወቀው
ሌሎችን በትሕትና ስታገለግሉ ብቻ ነው።
ከእናንተ መካከል ትልቅ ለመሆን የሚፈ
ልግ የሌሎች ቅን አገልጋይ ይሁን።
12 ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ይዋረዳል።
ራሱን ዝቅ ዝቅ የሚያደርግ ግን ከፍ ከፍ
ይላል።

13-14 «እናንተ ግብዞች የሃይማኖት መም
ህራንና ፈሪሳውያን፣ወዮላችሁ! ራሳችሁም
ወደ መንግሥተ ሰማይ አትገቡም፤ሌሎችም
እንዳይገቡ እንቅፋት ትሆኑባቸዋላችሁ።
መበለቶችን ከቤታቸው እያስወጣችሁ በሌላ
በኩል ደግሞ፣ ቅዱሳን መሽሎ ለመታየት
በመንገድ ዳር ቆማችሁ ረዥም ጸሎት ታደ
ርጋላችሁ። 15 እናንተ ግብዞች የሃይማኖት
መምህራንና ፈሪሳውያን፣ ወዮላችሁ! አን
ድን ሰው ለማሳመን የማይገባበት ቦታ ከመ
ግባት ወደ ኋላ አትሉም። የሚያምንላችሁ
ስታገኙ ደግሞ ከእናንተ ሁለት እጥፍ የባሰ
የገሃነም ልጅ ታደርጉታላችሁ። 16 ራሳችሁ
የታወራችሁ የዕውራን መሪዎች፣ ወዮላ
ችሁ! ‘በቤተ መቅደሱ መማል ምንም
ጉዳት የለበትም፤ነገር ግን መቅደሱ ውስጥ
በሚገኘው ወርቅ ከተማለ መሐላው ሊፈ
ርስ አይችልም’ ትላላችሁ። 17 ለመሆኑ
ከመቅደሱና ከወርቁ የትኛው የሚበልጥ
ይመስላችኋል? ወርቁን የሚቀድሰው መቅ
ደሱ አይደለምን? 18 ‘በመሠዊያው የተማለ
መሐላ ሊፈርስ ይችላል፤ መሠዊያው ላይ
በቀረበው መሥዋዕት የተማለ መሐላ ግን
ሊፈርስ አይችልም’ ትላላችሁ። 19 ከመሥዋ
ዕቱና ከመሠዊያው የትኛው የሚበልጥ
ይመስላችኋል? መሥዋዕቱን የሚቀድሰው
መሠዊያው አይደለምን? 20 በመሠዊያው
በምትምሉበት ጊዜ በመሠዊያውና በላዩ
ላይ ባለው ነገር ሁሉ መማላችሁ ነው፤
21 በመቅደሱ በምትምሉበት ጊዜ በመቅደ
ሱና በመቅደሱ ውስጥ በሚያድረው በእግዚ
አብሔር መማላችሁ ነው። 22 በሰማይ በም
ትምሉበት ጊዜ በእግዚአብሔር ዙፋንና
በዙፋኑ ላይ በሚቀመጠው በእግዚአብሔር
በራሱ መማላችሁ ነው።

23 «እናንተ ግብዞች፣የሃይማኖት መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፣ ወዮላችሁ! ከትንሽዋ
የጓሮ አትክልት ሳይቀር አሥራት ታወጣላ
ችሁ። ነገር ግን ፍርድ፣ምሕረትና ታማኝነ
ትን የመሳሰሉትን አስፈላጊ ነገሮች ቸል
ትላላችሁ። አሥራት ማውጣታችሁ ትክክል
ቢሆንም፣ የበለጠ ቁም ነገር ያለበትን ተግ
ባር ከመፈጸም ቸል ማለት ባልተገባችሁም
ነበር። 24 እናንተ ዕውራንን እንመራለን የም
ትሉ ዕውሮች! ትንኝን ታጠራላችሁ፤ግመ
ልን ግን እንዳለ ትውጡታላችሁ።

25 «እናንተ ግብዞች፣የሃይማኖት መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፣ ወዮላችሁ! የብርጭቆ
ውን ውጪ በጥንቃቄ ትወለውላላችሁ፤
ውስጡ ግን በክፋትና በስስት የቆሸሸ ነው።
26 እናንተ ማስተዋል የጐደላችሁ! መጀመ
ሪያ የብርጭቆውን ውስጥ አጽዱ! ውስጡ
ከጸዳ ውጪውም ጸዳ ማለት ነው።

27 «እናንተ ግብዞች፣የሃይማኖት መምህ
ራንና ፈሪሳውያን፣ወዮላችሁ! እናንተ በዕብ
ነበረድ አምሮና አሸብርቆ የተሠራ የመቃ
ብር ሐውልት ትመስላላችሁ—ውስጡ ግን
በበሰበሰና በፈረሰ አጽም የተሞላ ነው።

28 ቅዱስ መስሎ ለመታየት ብዙ ትለፋላ
ችሁ። ነገር ግን ከለበሳችሁት የማዕረግ
ልብስ ውስጥ ያለው ልባችሁ፥በኃጢአትና
በግብዝነት የተሞላ ነው።
29-30 «እናንተ ግብዞች ፥ የሃይማኖት
መምህራንና ፈሪሳውያን፥ወዮላችሁ! አባቶ
ቻችሁ ለገደሏቸው ነቢያት ሐውልት ታሠ
ራላችሁ፤እንዲሁም በአባቶቻችሁ እጅ የሞ
ቱትን ንጹሐን ሰዎች መቃብር ታስጌጣላ
ችሁ። አልፎ ተርፎም፥በነርሱ ዘመን ኑረን
በነበርን ‘አባቶቻችን የሠሩትን ግፍ ፈጽሞ
አንሠራም ነበር’ በማለት ትመጻደቃላችሁ።
31 በዚህ አባባላችሁ፥የክፉዎች ልጆች መሆ
ናችሁን ታረጋግጣላችሁ። 32 እናንተም፥የአ
ባቶቻችሁን ፈለግ በመከተል፥እነርሱ የጀመ
ሩትን የክፋት ተግባር ከፍጻሜ ለማድረስ
ወደ ኋላ የምትሉ አይደላችሁም። 33 እና
ንተ የእባብ ልጆች! ለመሆኑ ከገሃነም
ፍርድ እንዴት ታመልጡ ይሆን?
34 «እኔ ነቢያትን፥ጥበበኞችንና የሃይማ
ኖት መምህራንን ወደ እናንተ እልካለሁ።
እናንተም አንዳንዶቹን በመስቀል ላይ ሰቅላ
ችሁ ትገድሏቸዋላችሁ፤አንዳንዶቹንም በጸ
ሎት ቤቶቻችሁ ውስጥ ትገርፏቸዋላችሁ።
የቀሩትንም ከከተማ ወደ ከተማ ታሳድዷቸ
ዋላችሁ። 35 ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ
በመቅደሱና በመሠዊያው መካከል እስከ
ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካር
ያስ ደም ድረስ ላፈሰሳችሁት የቅዱሳን ደም
ተጠያቂዎች ናችሁ። 36 ከዘመናት ጀምሮ
ሲጠራቀም የቆየው በደል ይህን ትውልድ
ይፋረደዋል።
37 «ነቢያትን የምትገድይ ፥ ከእግዚአብ
ሔር ተልከው ወደ አንቺ የሚመጡትን
ሁሉ በድንጋይ የምትወግሪ ኢየሩሳሌም
ሆይ ፥ ወዮልሽ! ዶሮ ጫጩቶችዋን በክን
ፎቿ ሥር እንደምትሰበስብ ሁሉ ፥ እኔም
ልጆችሽን ለመሰብሰብ ስንት ጊዜ ሞከርኩ።
አንቺ ግን ፈቃደኛ አልሆንሽም፤ 38 ስለዚህ
ከእንግዲህ ወዲህ ቤታችሁ ወና፥ምድራችሁ
ባድማ ይሆናል። 39 በጌታ ስም ወደ እናንተ
የሚላከውን ለመቀበል ዝግጁ እስካልሆና
ችሁ ድረስ ደግሞ እንደ ገና አታዩኝም።»

## ምዕራፍ 24

1 ኢየሱስ ከቤተ መቅደስ ግቢ ወጥቶ
ሲሄድ ደቀመዛሙርቱ ቀርበው የቤተ
መቅደሱን ሕንጻዎች ሊያሳዩት ፈለጉ።
2 እርሱም፥ «ይህ የምታዩት ሕንጻ ሁሉ
ይፈርሳል። እንዲህ እንደምታዩት ድንጋይ
በድንጋይ ላይ ተከቦ አይቀርም፤ይወድቃል»
አላቸው።
3 ደብረ ዘይት ተራራ ላይ እንደ ተቀመ
ጡም ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን፥ «ይህ ሁሉ
ነገር መቼ ይሆናል? አንተስ የምትመጣበት
ጊዜና የዓለም መጨረሻ መቅረቡ የሚታወ
ቀውስ በምን ምልክት ነው?» ሲሉ ጠየ
ቁት።
4 ኢየሱስም፥ «ስለዚህ ነገር ማንም ሰው
እንዳያታልላችሁ ተጠንቀቁ። 5 ብዙ
ሰዎች፥ ‘እኔ መሲሕ ክርስቶስ ነኝ’ እያሉ
ይመጣሉ። ብዙ ሰዎችንም ያታልላሉ።
6 ጦርነት መነሣቱን በምትሰሙበት ጊዜ
አትደናገጡ። ይህ ሁሉ በቅድሚያ መሆን
ያለበት ነገር ነው እንጂ የመጨረሻው ጊዜ
ደርሶአል ማለት አይደለም። 7 አንድ ሕዝብ
ከሌላ ሕዝብ፥ አንዱ መንግሥት ከሌላው
መንግሥት ይጋጫሉ። በብዙ ሥፍራዎች
ረሃብና የምድር መናወጥ ይሆናል፤ 8 ይህ
ሁሉ ወደፊት ለሚደርሰውና አሰቃቂ ለሆ
ነው መከራ ዋዜማ ነው።
9 «በዚያን ጊዜ እናንተን ያሠቃዩዋች
ኋል፤ይገድሏችኋልም። የእኔ በመሆናችሁም
በዓለም ላይ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።
10 ብዙዎች በኃጢአት ይወድቃሉ፤ እርስ
በርሳቸው ይጠላላሉ፤አንዱም ሌላውን አሳ
ልፎ ይሰጣል፥ 11 ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት
ይነሣሉ ብዙ ሰዎችንም ያሳስታሉ።
12 ክፋት ከመብዛቱ የተነሣ የብዙ ሰዎች
ፍቅር ይቀዘቅዛል። 13 ነገር ግን እስከ መጨ
ረሻው ድረስ የሚጸና ሰው ይድናል።
14 ሕዝቦች ሁሉ ይሰሙት ዘንድ የእግዚአብ
ሔር መንግሥት ወንጌል በመላው ዓለም
ይሰበካል። እንግዲህ ይህ ከሆነ በኋላ ነው
የዓለሙ መጨረሻ የሚሆነው።
15 «ስለዚህ፥በነቢዩ በዳንኤል የተነገረው
አሳፋሪ ርኩሰት በተቀደሰው ሥፍራ ሲፈ
ጸም በምታዩበት ጊዜ፥ 16 ያኔ በይሁዳ ያሉ
ወደ ተራሮች ይሽሹ። 17 በቤታቸው ሰገነት
ላይ በመዝናናት ላይ ያሉም ተመልሰው
ወደ ቤት ሳይገቡ በዚያው ይሽሹ። 18 በእ
ርሻ ላይ ያሉም ልብሳቸውን ለመለወጥ
ወደ ቤታቸው አይግቡ። 19 በዚያን ጊዜ ለእ
ርጉዞችና ሕፃናትን ለሚያጠቡ እናቶች
ወዮላቸው! 20 ስለዚህ፥ሽሽታችሁ በክረምት
ወራት ወይም በሰንበት ቀን እንዳይሆን
ጸልዩ። 21 በዚያን ዘመን የሚደርሰው መከ
ራና ስደት፥ከዚያን በፊት በዓለም ላይ ታይ
ቶና ተሰምቶ የማይታወቅ፥እንዲሁም ወደ
ፊትም ይደርሳል ተብሎ የማይታሰብ ይሆ



ናል። 22 እነዚያ የመከራ ቀኖች ባያጥሩ
ኖሮ የሰው ዘር ሁሉ እንዳለ ከምድረ ገጽ
በጠፋ ነበር። እነዚያ የመከራ ቀኖች የሚያ
ጥሩትም ስለተመረጡት ሰዎች ሲባል ብቻ
ይሆናል።
23 «ስለዚህ ማንም ሰው፥ ‘መሲሕ ክርስ
ቶስ ከዚህ ወይም ከዚያ ቦታ ይገኛል፥በዚህ
ወይም በዚያ ቦታ ወይም በዚያ መንደር
ተገልጦአል’ ቢላችሁ አትመኑ። 24 ምክንያ
ቱም በዚያን ጊዜ ፥ ‘ክርስቶስ ማለት እኔ
ነኝ’ የሚሉ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያት ይነ
ሣሉ፤ድንቅ-ድንቅ ተአምራትም ያሠራሉ፤
ቢቻላቸው የተመረጡትን እንኳን ከማሳት
አይመለሱም። 25 ስለዚህ ሁኔታውን አስቀ
ድሜ ነግሬአችኋለሁና ተጠንቀቁ።
26 «ማንም ሰው ፥ ‘ክርስቶስ ተመልሶ
ወደ ምድር መጥቷል፤አሁን የሚገኘው እን
ዲህ ካለው በረሃ ውስጥ ነው’ ቢላችሁ፥ወደ
በረሃው ሄዳችሁ እውነቱን ለማረጋገጥ አት
ሞክሩ። ወይም ደግሞ ፥ ‘ተመልሶ መጥቶ
እንዲህ ካለው ቦታ ይገኛል’ ቢላችሁም
አትመኑ። 27 የመብረቅ ብልጭታ ከምሥ
ራቅ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ ሁሉ፥የእ
ኔም መምጣት እንደዚሁ በግልጽ እየታየ
እንጂ በድብቅ አይሆንም። 28 ጥንብ ባለበት
ሥፍራ ጆፌ አሞራዎች ይሰበሰባሉና።
29 «ከእነዚያ የመከራና የጭንቅ ቀናት
በኋላ፥ወዲያውኑ ፀሐይ ትጨልማለች፤ጨረ
ቃም ብርሃንዋን አትሰጥም። ከዋክብትም
ወደ ምድር ይወድቃሉ። የጠፈር ኃይላትም
ይናወጣሉ። 30 ከዚህ በኋላ የመምጣቴ ምል
ክት በሰማይ ላይ ይታያል። በዓለም ዙሪያ
በሙሉ ከባድ ልቅሶና ኀዘን ይሆናል፥የዓለ
ምም ሕዝቦች በታላቅ ክብርና ኃይል በደ
መና ሆኜ ስመጣ ያያሉ። 31 መላእክትንም
በታላቅ መለከት ድምፅ እልካቸዋለሁ። እነ
ርሱም የተመረጡትን ከዓለም ዙሪያና ከም
ድር ዳርቻዎች ሁሉ ይሰበስባሉ።
32 «ስለዚህ ጉዳይ ከበለስ ዛፍ ትምህርት
ልታገኙ ትችላላችሁ። የበለስ ዛፍ ቅርንጫ
ፎችም ሲለሰልሱ ቅጠሎቹም ሲያቆጠቍጡ
የበጋው ወራት መቃረቡን ትረዳላችሁ።
33 ልክ እንደዚሁ ፥ የነገርኳችሁ ነገሮች
አንድ በአንድ ሲፈጸሙ በምታዩበት ጊዜ፥
ዳግመኛ መምጣቴ እንደ ተቃረበ መረዳት
ትችላላችሁ። 34 ከዚያም የዘመናት ፍጻሜ
ይሆናል። 35 ሰማይና ምድር ያልፋሉ፤ቃሌ
ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል እንጂ ከቶ አያ
ልፍም።
36 «የዘመናት ፍጻሜ የሚሆንበትን ቀንና
ሰዓት ግን ከአብ በቀር መላእክትም ቢሆኑ
ወልድም ቢሆን፥ማንም የሚያውቅ የለም።
37-38 በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች ደግሰው
በመብላት በመጠጣት፥በሠርግ በምላሽ ሲፈ
ነጥዙ 39 በድንገት የጥፋት ውኃ መጥቶ እን
ዳጠፋቸው ሁሉ ፥ የዓለም ሕዝቦች ምን
ይመጣብናል ብለው በማይጠረጥሩበት ሰዓት
በድንገት ከተፍ እላለሁ።
40 «በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች አብረው
እርሻ ላይ ይውላሉ፤አንዱ ይወሰዳል ሌላው
ይቀራል። 41 እንዲሁም ሁለት ሴቶች የዕ
ለት ተግባራቸውን በመፈጸም ቤት ውስጥ
ጉድ ጉድ ይላሉ። አንድዋ ትወሰዳለች
ሌላዋ ግን ትቀራለች።
42 «ስለዚህ ጌታችሁ መቼ እንደሚመጣ
ስለማታውቁ ፥ ነቅታችሁና ተዘጋጅታችሁ
ጠብቁ። 43 ሌባ በምን ሰዓት እንደሚመጣ
ባለመታወቁ፥ንቁ ሆኖ ቤትን መጠበቅ እን
ደሚያስፈልግ ሁሉ፥ 44 እኔ የምመጣበትም
ሰዓት ስለማይታወቅ ሁል ጊዜ ዝግጁ ሆና
ችሁ መጠበቅ አለባችሁ።
45 «ጥበበኛና ታማኝ የጌታህ አገልጋይ
ነህን? ቤተሰቤን እንድትንከባከብና ልጆቼ
ንም በየዕለቱ እንድትመግብ ኃላፊነት ሰጥ
ቼህ የለምን? 46 ተመልሼ በምመጣበት ጊዜ
የሰጠሁህን ኃላፊነት በመፈጸም ላይ እንዳ
ለህ ካገኘሁህ ፥ ምስጋና ይገባሃል። 47 በበ
ኩሌ ፥ እንዲህ ያሉትን ታማኝ አገልጋዮች
በአለኝ ነገር ሁሉ ላይ ኃላፊ አድርጌ እሾማ
ቸዋለሁና።
48 «ነገር ግን ክፉ አገልጋይ ከሆንክና
‘ጌታዬ በቶሎ አይመለስም’ 49 በማለት
በሥራ ጓደኞችህ ላይ በደል የምትፈጽም፥
ብልሹ ኑሮ የምትኖርና የምትሰክር ከሆ
ንክ፥ 50 ባላሰብከውና ባልጠረጠርከው ጊዜ
ከተፍ ብዬ፥ 51 ተይዘህ እንድትገረፍና ለግ
ብዞች የሚገባውንም ፍርድ እንድትቀበል
አደርጋለሁ። ከዚያም ልቅሶና ጥርስ ማፋ
ጨት ይሆናል።»

## ምዕራፍ 25

1 ቀጥሎም እርሱ በሚመለስበት ጊዜ
የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደምት
መስል ለማስረዳት ኢየሱስ የሚከተለውን
ተናገረ፤ «የእግዚአብሔር መንግሥት ኩራዛ
ቸውን አብርተው ሙሽራ ለመቀበል የተዘ
ጋጁትን አሥር ልጃገረዶች ትመስላለች።
2-4 ከእነዚህ ከአሥሩ ልጃገረዶች መካከል
አምስቱ ልባሞች ስለነበሩ ፥ ኩራዛቸው
ውስጥ በቂ ዘይት ሲሞሉ፥የቀሩት አምስቱ

ሰነፎች ግን ኩራዛቸው ውስጥ በቂ ዘይት
አልጨመሩም ነበር። 5 ሙሽራው በተጠበ
ቀው ሰዓት ባለመምጣቱ ሁሉም እንቅልፍ
ስለ ተጫጫናቸው ተኙ።
6 «እኩለ ሌሊት ላይ፣ ‘ሙሽራው መጣ
ቷልና ወጥታችሁ ተቀበሉት!’ የሚል ጥሪ
ተሰማ። 7-8 ወዲያው አሥሩም ልጃገረዶች
ተነሥተው ኩራዛቸውን ማብራት ጀመሩ።
ይሁን እንጂ፣ የአምስቱ ሰነፍ ልጃገረዶች
ኩራዝ ዘይቱን በመጨረሱ፣ በሚያበሩበት
ጊዜ መብራቱ ለመጥፋት ይስለመለም
ጀመር። ስለዚህ አምስቱን ልባም ልጃገረ
ዶች፣ ‘እባካችሁን፣ ከኩራዛችሁ ቀንሳችሁ
ዘይት ስጡን!’ ሲሉ ለመኑዋቸው።
9 «ልባሞቹ ልጃገረዶችም፣ ‘እኛም ያለ
ችን ይችው ብቻ ስለሆነች ከዚችው ቀንሰን
ልንሰጣችሁ አንችልም። ይልቅስ ወደ ሱቅ
ሂዱና ከዚያ ግዙ’ ሲሉ መለሱላቸው።
10 «እነርሱም ዘይት ለመግዛት ወደ ሱቅ
እንደ ሄዱ ሙሽራው በድንገት ከተፍ አለ።
ተዘጋጅተው ያገኛቸውን አምስቱን ልጃገረ
ዶች ይዞ ወደ ሠርጉ አዳራሽ ገባ። እንደ
ገባም የአዳራሹ በር ተዘጋ።
11 «ከጥቂት ጊዜ በኋላ እነዚያ ዘይት
ለመግዛት ወደ ሱቅ የሄዱት አምስቱ ሰነፍ
ልጃገረዶች ተመልሰው መጡ። በሩ እንደ
ተዘጋ ባዩ ጊዜ፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ምነዋ በሩን
ክፈትልን እንጂ!’ ሲሉ ጮኹ። 12 ሙሽራ
ውም፣ ‘አላውቃችሁም፣ ወዲያ ሂዱ! በር
የሚከፈትበት ጊዜው አሁን አይደለም ፤
ሰዓቱ አልፏል!’ አላቸው።
13 «ስለዚህ እኔ የምመጣበት ቀን መቼ
እንደሆነ ስለማታውቁ ነቅታችሁና ተዘጋጅ
ታችሁ ጠብቁ።»
14 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው።
«የእግዚአብሔር መንግሥት፣ አገልጋዮቹን
ሰብስቦ ገንዘብ በመስጠት አትርፈው እንዲ
ጠብቁት አድርጎ ወደ ሩቅ አገር በሄደ ሰው
ትመሰላለች። 15 ሰውየው አገልጋዮቹን
ጠርቶ ለአንዱ አሥር ሺህ ብር፣ ለሁለተ
ኛው አራት ሺህ ብር፣ ለሦስተኛው ሁለት
ሺህ ብር እንደየችሎታቸው አካፍሎ ሰጣ
ቸው። 16 አሥር ሺህ ብር የተቀበለው ወዲ
ያውኑ በገንዘቡ መነገድ ስለ ጀመረ ሌላ
አሥር ሺህ ብር አተረፈ። 17 አራት ሺህ
የተቀበለውም እንዲሁ በገንዘቡ ስለ ሠራበት
ሌላ አራት ሺህ ብር ትርፍ አገኘ። 18 ነገር
ግን ያ ሁለት ሺህ ብር የተቀበለው አገል
ጋይ፣ ጉድጓድ ቆፍሮ ገንዘቡን መሬት
ውስጥ ቀበረው።

19 «ከብዙ ጊዜ በኋላ የእነዚህ ሦስት
አገልጋዮች ጌታ፣ ከሄደበት አገር ስለተመለሰ
ሒሳቡን ሊተሳሰባቸው ፈልጎ ጠራቸው።
20 በመጀመሪያም አሥር ሺህ ብር ተቀብሎ
የነበረው አገልጋይ ያተረፈውን አሥር ሺህ
ብር ጨምሮ በድምሩ ሃያ ሺህ ብር አስረ
ከበ።
21 «ጌታውም፣ ‘በጣም ጥሩ! አንተ
ታማኝና ቅን አገልጋይ! በዚህ በትንሽ ገን
ዘብ ታማኝነትህን አስመስክረሃል፣ ስለዚህ
በበለጠ ገንዘብና ንብረት ላይ እንድታስተዳ
ድር ሹሜሃለሁ። ግባና የጌታህን ደስታ ተካ
ፈል’ አለው።
22 «ቀጥሎም አራት ሺህ ብር የተቀበ
ለው አገልጋይ ካተረፈው አራት ሺህ ብር
ጋር ደምሮ ስምንት ሺህ ብር በማስረከብ፣
‘ጌታ ሆይ እኔም ይኸው እጥፍ አትርፌአ
ለሁ’ አለ።
23 «ጌታውም፣ ‘በጣም ጥሩ! አንተ
ታማኝና ቅን አገልጋይ! በዚህ በትንሽ ገን
ዘብ ታማኝነትህን አስመስክረሃል፣ ስለዚህ
በበለጠ ገንዘብና ንብረት ላይ ሹሜሃለሁ።
ግባና የጌታህን ደስታ ተካፈል’ አለው።
24-25 «በመጨረሻ ሁለት ሺህ ብር የተቀ
በለው አገልጋይ ቀረበና፣ ‘ጌታ ሆይ፣ እር
ስዎ ኃይለኛ ሰው እንደሆኑ አውቃለሁ።
በሰጡኝ ብር ሠርቼ ባተርፍ፣ ዋናውን ከነት
ርፉ እንደሚወስዱ ስላወቅሁ፣ ይህንኑ ፈርቼ
የሰጡኝን ገንዘብ ቀብሬ አስቀመጥኩ። እሁ
ንም ገንዘብዎ ይኸውሎት’ አለ።
26-27 «ጌታውም፣ ‘አንተ ሰነፍ! ከገን
ዘቤ ትርፍ ማግኘት የምፈልግ መሆኔን ካወ
ቅህ፣ ሌላው ቢቀር ገንዘቤን አራጣ አበድረህ
ወለድ እንዳገኝ ማድረግ ነበረብህ’ አለ።
28 አገልጋዮቹንም ጠራና፣ ‘ሁለት ሺህውን
ብር ተቀበሉትና ሃያ ሺህ ብር ላመጣው
ስጡት፤ 29 የተሰጠውን በሚገባ ለሚይዝ የበ
ለጠና የተትረፈረፈ ይሰጠዋል። ታማኝነቱን
ከሚያጉድል ግን፣ ያቺው ያለችው እንኳ
ትወሰድበታለች’ 30 ስለዚህ ይህንን የማይጠ
ቅምና ኃላፊነት የማይሰማውን አገልጋይ
ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ጨለማ
ውሰዱት» አለ።
31 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ እንዲህ አለ።
«በመላእክት ታጅቤ በክብር ዳግመኛ በም
መጣበት ጊዜ፣ በዙፋኔ ላይ እቀመጣለሁ።
32 በዚያን ጊዜ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ከፊቴ
ይሰበሰባል። እኔም እረኛ በጎቹን ከፍየ
ሎች እንደሚለይ እለያቸዋለሁ። 33 በጎቹን
በቀኜ በኩል፣ ፍየሎቹንም በግራዬ በኩል



አቆማቸዋለሁ።
34 «ከዚህ በኋላ በቀኜ በኩል የቆሙ
ትን፣ ‘እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ከተፈ
ጠረ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት
ኑና ውረሱ። 35 ተርቤ አብልታችሁኛል ፤
ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል፤እንግዳ ሆኜ አስ
ተናግዳችሁኛል ፤ 36 ታርዤ አልብሳችሁ
ኛል ፤ታምሜና ታሥሬም ጠይቃችሁኛል’
እላቸዋለሁ።
37 «እነርሱም፣ ‘ጌታ ሆይ፣ መቼ ነው
ተርበህ አይተን ያበላንህ? ተጠምተህ ያጠ
ጣንህ? 38 እንግዳ ሆነህ ያስተናገድንህ?
ታርዘህ ያለበስንህ? 39 ለመሆኑ ታመህና
ታሥረህ የጠየቅንህስ መቼ ነው?’ ይሉ
ኛል።
40 «እኔም፣ ‘ከእነዚህ ወንድሞቼ መካ
ከል አነስተኛ ከሆኑት ለአንዱ ያደረጋች
ሁት፣ ልክ ለእኔ እንዳደረጋችሁት ይቆጠ
ራል’ እላቸዋለሁ።
41 «ከዚህ በኋላ በግራ በኩል የቆሙትን
ደግሞ፣ ‘እናንተ የተረገማችሁ፣ ለሰይጣንና
ጭፍሮቹ ለሆኑት አጋንንት ወደ ተዘጋጀው
የዘላለም እሳት ሂዱ!’ 42 ተርቤ አላበላችሁ
ኝም፤ተጠምቼ አላጠጣችሁኝም፤ 43 እንግዳ
ሆኜ አላስተናገዳችሁኝም፤ታርዤ አላለበሳች
ሁኝም፤እንዲሁም ታምሜና ታሥሬ አልጠ
የቃችሁኝም» እላቸዋለሁ።
44 «እነርሱም፣ ‘ጌታ ሆይ፣ ለመሆኑ
መቼ ነው ተርበህ፣ ወይ ተጠምተህ፣ ወይ
እንግዳ ሆነህ፣ ወይ ታርዘህ፣ ወይ ታሥረህና
ታመህ አይተን አንተን ከመርዳት ወደ ኋላ
ያልነው?’ ይሉኛል።
45 «እኔም፣ ‘ከእነዚህ ወንድሞቼ መካ
ከል አነስተኛ የሆነውን አንዱን አንረዳም
ማለታችሁን፣ እኔን አንረዳም እንዳላችሁ
አድርጌ ነው የምቆጥረው’ እላቸዋለሁ።
46 «ከዚህ በኋላ፣ ኃጢአተኞች ወደ ዘላ
ለም ቅጣት ይወሰዳሉ፤ጻድቃን ግን ወደ ዘላ
ለም ሕይወት ይሄዳሉ።»

## ምዕራፍ 26

1 ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አስተምሮ
ከጨረሰ በኋላ እንዲህ አላቸው።
2 «ሁላችሁም እንደምታውቁት ከሁለት
ቀን በኋላ የፋሲካ በዓል ይከበራል። እኔንም
አሳልፈው ይሰጡኛል፤ይሰቅሉኛልም።»
3 ኢየሱስ ይህንን ለደቀመዛሙርቱ ሲነግ
ራቸው የካህናት አለቆች የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራንና የአገር ሽማግሌዎች፣
በሊቀ ካህኑ በቀያፋ ቤት ተሰብስበው፣
4 በምን ዘዴና ብልሃት ኢየሱስን ይዘው
ለመግደል እንደሚችሉ ይዶልቱ ነበር።
5 ነገር ግን የፋሲካ በዓል ከማለፉ በፊት
ኢየሱስን ቢይዙት ከፍተኛ ሁከት ይቀሰቀ
ሳል ብለው ፈሩ።
6 ኢየሱስም ለምጻሙ ስምዖንን ለመጎብ
ኘት ወደ ቢታንያ ሄደ። 7 በስምዖንም ቤት
በማብሥ ላይ ሳለ፣ እንዲት ሴት በጣም ውድ
በሆነ ዋጋ የተገዛ ሽቶ ይዛ መጥታ ራሱ ላይ
አፈሰሰች።
8-9 ደቀመዛሙርቱም በአድራጎቷ በመቆ
ጨት፣ «ሴትዮዋ ምን ማድረግዋ ነው? ይህ
ሽቶ ከፍ ያለ ዋጋ የሚያወጣ በመሆኑ፣ በከ
ንቱ ከምታባክነው ይልቅ ተሽጦ ለድሆች
ቢሰጥ አይሻልም ነበር?» ተባባሉ።
10 ኢየሱስ ግን አሳባቸውን በማወቁ፣ ደቀ
መዛሙርቱን፣ «ሴትዮዋን እንዲህ አድርጋ
ችሁ የምትነቅፏት ለምንድን ነው? እርሷ
እኮ ውለታ ነው የሠራችልኝ። 11 ድሆች
እንደሆኑ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ናቸው።
እኔ ግን ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖ
ርም። 12 ይህን ሽቶ በሰውነቴ ላይ በማፍሰ
ስዋ ለቀብሬ ሥነ ሥርዓት አስተዋጽኦ አድ
ርጋለች። 13 ይህም በጎ ሥራዋ ሲታወስላ
ትና ወንጌል በሚሰበክበትም ቦታ ሁሉ ሲነ
ገርላት ይኖራል» አላቸው።
14 ከዚህ በኋላ ከአሥራ ሁለቱ ደቀመዛ
ሙርት አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ ወደ ካህ
ናት አለቆች ዘንድ ሄዶ፣ 15 «ኢየሱስን ለመ
ያዝ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ! እርሱን
አሳልፌ ብሰጣችሁ ምን ትከፍሉኛላችሁ?»
አላቸው። እነርሱም ሠላሳ ብር ሰጡት።
16 ይሁዳም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ኢየሱስን
ጠቁሞ ለማስያዝ የሚችልበትን አመቺ
ጊዜና ቦታ እያደባ ይጠባበቅ ጀመር።
17 እርሾ ያልገባበት ቂጣ በሚበላበት
በዓል መጀመሪያ ቀን ላይ ደቀመዛሙርቱ
ኢየሱስን፣ «የፋሲካን ራት የት እናዘጋጅ
ልህ?» ሲሉ ጠየቁት።
18 እርሱም፣ «ወደ ከተማይቱ ስትገቡ
አንድ ሰው ታገኛላችሁ። ያንንም ሰው፣
‘ጌታ ጊዜዬ ስለተቃረበ ከደቀመዛሙርቴ
ጋር የፋሲካን ራት በቤትህ ለመብላት እፈ
ልጋለሁ ብሎሃል’ በሉት» አላቸው።
19 ደቀመዛሙርቱም ወደ ከተማይቱ ሄደው
ኢየሱስ ያዘዛቸውን ሁሉ በመፈጸም የፋሲ
ካን ራት አዘጋጁ።
20-21 በዚያች ምሽት ኢየሱስ ከአሥራ
ሁለቱ ደቀመዛሙርት ጋር ራት ላይ እን
ዳለ፣ «ከመካከላችሁ አንዱ አሳልፎ

ይሰጠኛል» አላቸው።
22 ኢየሱስ ከተናገረው ቃል የተነሣ የደ
ቀመዛሙርቱ ልብ በኀዘን ታወከ። ተራ በተ
ራም፣ «አሳልፌ የምሰጥህ እኔ እሆንን? እኔ
እሆንን?» እያሉ ጠየቁት።
23 ኢየሱስም፣ «አሳልፎ የሚሰጠኝ በአ
ንድ ሳህን አብሮኝ የሚያጠቅሰው ነው።
24 እኔስ ነቢያት የተናገሩት ይፈጸም ዘንድ
እሞታለሁ። አሳልፎ ለሚሰጠኝ ለዚያ ሰው
ግን ወዮለት! ባይወለድ ይሻለው ነበር»
ሲል መለሰላቸው።
25 ይሁዳም፣ቀበል አድርጎ፣ «ጌታ ሆይ፣
አሳልፌ የምሰጥህ እኔ እሆንን?» ብሎ ጠየ
ቀው። ኢየሱስም፣ «አዎን፣አንተው ተናግረ
ኸዋል» አለው።
26-28 ራት ላይ ሳሉም፣ኢየሱስ የምስጋና
ጸሎት አድርሶ በእጁ የያዘውን ዳቦ ቆርሶ
ደቀመዛሙርቱን፣ «እንካችሁ ብሉ፣ ይህ
ሥጋዬ ነው» አላቸው። እንደዚሁም ጽዋ
ውን አንሥቶ የምስጋና ጸሎት ካደረሰ
በኋላ፣ «እንካችሁ፣ከዚህ ጽዋ ሁላችሁም
ጠጡ። ይህ አዲሱን ቃል ኪዳን የሚያጸ
ናው ደሜ ነው፣የሚፈሰው ደሜ የብዙዎ
ችን ኃጢአት ያነጻል። 29 በአባቴ ቤት በአ
ንድ ላይ ሆነን እንደ ገና እስክንጠጣው
ድረስ፣ከእንግዲህ ወዲህ ይህን ወይን አልቀ
ምስም» አላቸው።
30 በአንድ ላይ መዝሙር ዘምረው እንዳ
በቁ፣ ተነሥተው ወደ ደብረ ዘይት ተራራ
ወጡ።
31 በዚያም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እን
ዲህ አላቸው፣ «ዛሬ ማታ ሁላችሁም ብቻ
ዬን ትታችሁኝ ትሸሻላችሁ። ይህም የሚሆ
ነው፣ ‘እረኛውን እመታለሁ፤ መንጋውም
ይበተናል’ ተብሎ በመጻሕፍት የተጻፈው
ይፈጸም ዘንድ ነው። 32 ከሞት ከተነሣሁ
በኋላ ግን፣ወደ ገሊላ ስለምሄድ በዚያ እንገ
ናኛለን።»
33 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «ጌታ ሆይ፣
ሁሉም ትተውህ ቢሄዱ፣የመጣው ይምጣ
እንጂ፣ እኔ ትቼህ አልሄድም» አለው።
34 ኢየሱስም፣ «በዚች ሌሊት ዶሮ ከመ
ጮኹ በፊት፣ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ!»
አለው።
35 ጴጥሮስም መልሶ፣ «እፊትህ ይገድሉ
ኛል እንጂ፣ ምንም ቢሆን አልክድህም!»
አለው። ሌሎቹም ደቀመዛሙርት የጴጥሮ
ስን አሳብ በመከተል የማይክዱት መሆናቸ
ውን አረጋገጡለት።
36 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ጌቴሴማኒ
ወደሚባለው የአትክልት ቦታ ይዟቸው
ሄደ። እዚያም የቀሩትን ደቀመዛሙርቱን
አረፍ እንዲሉ አድርጎ፣ 37 ጴጥሮስን፣ዮሐን
ስንና ያዕቆብን ብቻ አስከትሎ ለመጸለይ
ጥቂት እልፍ ብሎ ሄደ። ያዝን፣ይተክዝ፣
ይጨነቅም ጀመር። 38 ለነጴጥሮስም፣
«ነፍሴ በታላቅ ኀዘን ተጨንቃለች። እናን
ተም እዚህ ቆዩና ከእኔ ጋር ትጉ» አላ
ቸው።
39 ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ ሄደና
መሬት ላይ በግምባሩ ተደፍቶ፣ «አባት
ሆይ፣የሚቻል ከሆነ ይህ ጽዋ ከእኔ ይለፍ።
ሆኖም የእኔ ፍላጎት ሳይሆን የአንተ ፈቃድ
ይፈጸም» ሲል ጸለየ።
40 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ሦስቱ ደቀ
መዛሙርት ተመልሶ ቢመጣ ሲያንቀላፉ
አገኛቸው። ጴጥሮስንም ቀስቅሶ፣ «ለአንድ
ሰዓት እንኳን ከእኔ ጋር ነቅቶ መቆየት አቃ
ታችሁ? 41 ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታ
ችሁ መጸለይ አለባችሁ። መንፈስ ፈቃደኛ፣
ሥጋ ግን ደካማ ነው!» አለ።
42 እንደገናም ከእነርሱ እልፍ ብሎ፣
«አባት ሆይ፣ይህን ጽዋ መጠጣቴ የማይቀር
ከሆነ፣ፈቃድህ ይፈጸም» በማለት ጸለየ።
43 ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ ሦስቱ ደቀመ
ዛሙርት ወደ ነበሩበት ሥፍራ ተመለሰ።
አሁንም ሲያንቀላፉ አገኛቸው። 44 ለሦስ
ተኛ ጊዜ ሄዶ ቀደም ሲል የጸለየውን
ጸሎት ጸለየ።
45 ከዚህ በኋላ ወደ ደቀመዛሙርቱ ተመ
ለሰና፣ «ከእንግዲህስ ልትተኙና ልታርፉ
ትችላላችሁ። ለክፉ ሰዎች እኔን አሳልፈው
የሚሰጡበት ጊዜው ደረሰ! 46 በሉ ተነሡ
እንሂድ። አሳልፎ የሚሰጠኝ ሰው ያውላ
ችሁ መጣ» አለ።
47 ወዲያውኑም ከአሥራ ሁለቱ አንዱ
የሆነው ይሁዳ የካህናት አለቆችና የአገር
ሽማግሌዎች ከላኳቸው፣ሰይፍና ዱላ ከያዙ
ብዙ ሰዎች ጋር ከተፍ አለ። 48 ይሁዳም
እየመራ ያመጣቸውን ሰዎች፣ «እኔ የምስ
መው እርሱ ኢየሱስ ነው» የሚል መለያ
ምልክት ቀደም ሲል ሰጥቶአቸው ነበር።
49 በዚህም መሠረት፣በቀጥታ ወደ ኢየ
ሱስ ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፣እንደምንድነህ?»
በማለት ሳመው።
50 ኢየሱስ ግን፣ «በላ ወዳጄ፣የመጣህበ
ትን ጉዳይ ቶሎ ፈጽመው!» አለው። በዚህ
ጊዜ፣ በይሁዳ ጠቋሚነት የመጡት ሰዎች
ኢየሱስን ያዙት። 51 ከደቀመዛሙርቱም
አንዱ ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህኑን አገል



ጋይ ጆሮ ቆረጠው።
52 ኢየሱስም፣ «በል፣ ሰይፍህን ወደ
አፎቱ መልስህ ክተተው! ሰይፍ የሚመዙ
በሰይፍ ይጠፋሉ። 53 በሺህ የሚቆጠሩ መላ
እክቱን ልኮ እንዲከላከልልኝ አባቴን ብጠይ
ቀው ባንድ አፍታ እንደሚልካቸው አታው
ቅም? 54 ነገር ግን ይህን ባደርግ ደግሞ
በመጽሐፍ የተጻፈው ቃል ሊፈጸም አይች
ልም» አለው።
55-56 ከዚያም ሊይዙት የመጡትን
ሰዎች እንዲህ አላቸው። «ሰይፍና ዱላ ይዛ
ችሁ ልትይዙኝ የመጣችሁት እንደ ወንጀ
ለኛ ስለ ቆጠራችሁኝ ነው? ያኔ በቤተ
መቅደስ እናንተ በተገኛችሁበት ሳስተምር
ለምን አልያዛችሁኝም? ጊዜው አልነበረ
ምና! ዛሬ ግን ጊዜው ስለደረሰ በመጽሐፍ
የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ ልትይዙኝ ቻላ
ችሁ።» በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን
ብቻውን ትተውት ሸሹ።
57 ከዚያም ሰዎቹ ኢየሱስን ይዘው ወደ
ሊቀ ካህኑ ወደ ቀያፋ ቤት ወሰዱት። በዚ
ያም የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና የአ
ገር ሽማግሌዎች በሙሉ ተሰብስበው ነበር።
58 ጴጥሮስም ኢየሱስን ከሩቅ በመከተል
ወደ ሊቀ ካህኑ ግቢ ገብቶ ከወታደሮቹ
መካከል ተደባልቆ ተቀመጠ። የሚሆነው
ንም ነገር ይከታተል ጀመር። 59 ጉዳዩን
ለመመልከት የካህናት አለቆች፣የአገር ሽማ
ግሌዎችና የአይሁድ ሸንጐ ከፍተኛ ምክር
ቤት አባሎች ተሰበሰቡ። በኢየሱስ ላይም
የሞት ፍርድ ሊያስፈርድበት የሚችል የሐ
ሰት ምስክር የሚሆኑ ሰዎች መፈለግ ያዙ።
60-61 ይሁን እንጂ ብዙ የሐሰት ምስክሮችን
ቢያቀርቡም፣ በጉባዔው ፊት የተናገሩት
ቃል የአንዱ ከሌላው ጋር የሚጋጭ ሆነ።
በመጨረሻም ሁለት ሌሎች ምስክሮች ቀረ
ቡና፣ «ይህ ሰው፣ ‘ቤተ መቅደሱን አፍርሼ
በሦስት ቀን መልሼ እሠራዋለሁ’ ሲል ሰም
ተናል» ሲሉ መሰከሩ።
62 ሊቀ ካህኑም የምስክሮቹን ቃል
ሲሰማ ከመቀመጫው ብድግ ብሎ፣ «ብለ
ሃል አላልክም?» አለው።
63 ኢየሱስ ግን ምንም አልመለሰለትም።
ሊቀ ካህኑም ጥያቄውን በመቀጠል፣ «እንግ
ዲያው ክርስቶስ መሆን አለመሆንክን እንድ
ትነግረን በሕያው እግዚአብሔር ስም ይገዝሃ
ለሁ!» አለው።
64 ኢየሱስም፣ «መሆንማ አዎን፣ክርስ
ቶስ ነኝ። ወደፊትም ከእግዚአብሔር ቀኝ
ስቀመጥ፣ከዚያም በሰማይ ደመና ላይ ሁኜ
ስመጣ ታያላችሁ» ሲል መለሰለት።
65-66 ሊቀ ካህኑም በንዴት ልብሱን ቀደ
ደና፣ «እግዚአብሔርን መስደቡን ይኸው
የምትሰሙት አይደለም? ታዲያ ከዚህ
ወዲያ ምን ምስክር ያሻል? አሁን ያለውን
ሁላችሁም ሰምታችሁ የለም? አሁኑኑ ፍር
ዱን መቀበል አለበት!» ብሎ ጮኸ። የተሰ
በሰቡትም፣ ሁሉ፣ «ይገደል! ይገደል! ይገ
ደል!» በማለት ጩኸታቸውን አስተጋቡ።
67 ከዚያም በንቀት ምራቃቸውን ፊቱ
ላይ ተፉበት፤ በጡጫና በዱላም መቱት።
68 «አይ የእኛ ክርስቶስ! አይ የኛ መሲሕ!
እስቲ ትንቢት ተናገር እባክህ! አሁን የመ
ታህ ማን ነው?» እያሉም አፌዙበት።
69 ጴጥሮስም ይህ ሁሉ ሲሆን በሊቀ
ካህኑ ግቢ ተቀምጦ ነበርና አንዲት ሴት
መጥታ፣ «አንተ ሰው ከገሊላዊው ኢየሱስ
ጋር አልነበርክም?» አለችው።
70 ጴጥሮስም መልሶ፣ «የምትይው አይገ
ባኝም» ብሎ በሁሉም ፊት ካደ።
71 ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ጴጥሮስ ከደጃፉ
አጠገብ ቆሞ ሳለ ማንነቱን ያወቀች አንዲት
ሌላ ሴት ደግሞ፣ «ይህን ሰው እኮ ከናዝ
ሬቱ ኢየሱስ ጋር አይቼዋለሁ» አለች።
72 ጴጥሮስ እየማለ፣ «ምን ማለታችሁ
ነው፤እኔ በበኩሌ ይህን ሰው አላውቀውም»
ብሎ ካደ።
73 አሁንም ቆመው ከነበሩት ሰዎች መካ
ከል ጴጥሮስን፣ «አንተ ሰው ከደቀመዛሙ
ርቱ አንዱ መሆንህን አውቀናልና እውነቱን
አውጣ። አነጋገርህ ራሱ ያጋልጥሃል»
አሉት።
74 ጴጥሮስም፣እውነተኛ መስሎ ለመታ
የት እየማለና እየተራገመ፣ «ይህን የምትሉ
ትን ሰው ፈጽሞ አላውቀውም» ብሎ ካደ።
ወዲያውኑ ዶሮ ጮኸ።
75 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «ዶሮ ከመጮኹ
በፊት ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» በማለት ኢየ
ሱስ የተናገረው ቃል ትዝ ስላለው ከግቢው
ወጥቶ ተንሰቅስቆ አለቀሰ።

## ምዕራፍ 27

1 ሲነጋም የካህናት አለቆችና የአገር
ሽማግሌዎች እንደ ገና ተሰብስበው የሮም
ባለሥልጣኖች በኢየሱስ ላይ የሞት
ፍርድ ለማስፈረድ የሚያበቁ ናቸው፣
ብለው የሚያምኑባቸውን ነገሮች ተመካ
ከሩ። 2 በመጨረሻም ኢየሱስን በሰንሰለት
አሥረው በአገረ ገዢው በጲላጦስ ፊት አቀ
ረቡት።

3-4 ኢየሱስን ጠቁሞ ያስያዘው ይሁዳ፣
ኢየሱስ የሞት ፍርድ እንደ ተፈረደበት
በተረዳ ጊዜ በጣም ተጸጸተ። የካህናት አለ
ቆችና የአገር ሽማግሌዎች ከፍለውት የነበረ
ውንም ገንዘብ ይዞ በመምጣት፣ «ንጹሕ
ሰው ጠቁሜ በማስያዜና ለሞት አሳልፌ
በመስጠቴ ኃጢአት ሠርቻለሁ» አላቸው።
እነርሱም፣ «የራስህ ጉዳይ ነው» አሉት።
5 እርሱ ግን ተቀብሎ የነበረውን ገንዘብ
ከቤተ መቅደሱ ወለል ላይ ወረወረላቸው።
ከዚያም ሄዶ በራሱ እጅ በገመድ ተሰቅሎ
ሞተ።
6 የካህናት አለቆችም ይሁዳ የበተነውን
ገንዘብ ለቃቅመው ካነሡ በኋላ፣ «ይህ ገን
ዘብ የደም ዋጋ ስለሆነ፣መልሰን ቤተ መቅ
ደስ ሒሳብ ውስጥ መጨመር አንችልም።
ይህ በሕጋችን የተከለከለ ነገር ነውና» በማ
ለት ተወያዩበት።
7 በመጨረሻም፣ ወደ ኢየሩሳሌም መጥ
ተው በድንገት ለሚሞቱ የውጭ አገር
ሰዎች የመቃብር ቦታ እንዲሆን በማሰብ፣
ሸክላ ሠሪዎች በአፈሩ ይጠቀሙበት የነበረ
ውን መሬት ለመግዛት ወሰኑ። 8 ከዚህም
የተነሣ ያ የመቃብር ቦታ እስከ ዛሬ ድረስ፣
«የደም መሬት» ተብሎ ይጠራል።
9 ነቢዩ ኤርምያስ፣ «የእሥራኤል ልጆች
እርሱን የገመቱበትን ዋጋ ሠላሳ ብር ተቀ
በሉ፤ 10 ጌታም እንዳዘዘው፣ከሸክላ ሠሪዎች
የመቃብር ቦታ ገዙበት» በማለት የተናገ
ረው ቃል በዚህ አኳኋን ተፈጸመ።
11 ከዚያም ኢየሱስ በጲላጦስ ፊት
ቀረበ። ጲላጦስም፣ «አንተ የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?» ሲል ጠየቀው። ኢየሱስም፣
«አዎን፣ነኝ» ብሎ መለሰለት። 12 ቀጥሎም
የካህናት አለቆችና የአገር ሽማግሌዎች ተራ
በተራ የተለያየ ክስ በኢየሱስ ላይ አቀረቡ።
ኢየሱስ ግን ምንም መልስ አልሰጠም
ነበር። 13 በዚህ ጊዜ ጲላጦስ ኢየሱስን፣
«የሚሉህን አትሰማምን?» አለው። 14 ኢየ
ሱስ ግን አንድም ቃል አልወጣውም፤ዝም
አለ። ሁኔታው ጲላጦስን በጣም አስገረ
መው።
15 በየዓመቱ በፋሲካ በዓል ሰሞን፣ጲላ
ጦስ ለአይሁድ አንድ የሚፈልጉትን እሥ
ረኛ የመፍታት ልማድ ነበረው። 16 በዚያ
ዓመት ውስጥ በርባን የሚባል በጣም የታ
ወቀ ወንበዴ ታሥሮ ነበር። 17 በማለዳም
ሕዝቡ እንደተሰበሰበ፣ጲላጦስ እንዲህ ሲል
ጠየቃቸው። «ዛሬ ማንን ልፍታላችሁ? በር
ባንን ወይስ መሲሕችሁን ኢየሱስን?»
18 ጲላጦስ ይህንን ጥያቄ ሕዝቡን የጠየቀ
በት ምክንያት ነበረው። የአይሁድ መሪዎች
ኢየሱስን የያዙትና ያሠሩት፣በሕዝቡ ዘንድ
በመወደዱ ከቅንዓት የተነሣ መሆኑን ስለሚ
ያውቅ ነበር።
19 ወዲያውም ጲላጦስ ፍርድ ከሚሰጥ
በት ቦታ ላይ ተቀምጦ ሳለ፣ከሚስቱ ሰው
ተልኮ መጥቶ በጆሮው፣ «በዚያ ደግ ሰው
ላይ ክፉ ነገር እንዳታደርስበት። ሌሊት
በሕልሜ በእርሱ ምክንያት ስሠቃይ አድሬ
አለሁ» የሚል መልእክት ነገረው።
20 በመካከሉም የካህናት አለቆችና የአ
ገር ሽማግሌዎች በርባን ተለቅቆ ኢየሱስ
እንዲሰቀል የሚል ጥያቄ እንዲያቀርብ ሕዝ
ቡን አነሣሡት። 21 ጲላጦስም እንደገና፣
«ታዲያ ከሁለቱ ማንን እንድፈታላችሁ ትፈ
ልጋላችሁ?» ብሎ በጠየቀ ጊዜ፣ «በርባን
ይፈታልን! በርባን ይለቀቅልን!» በማለት
ተቀባበሉ።
22 ጲላጦስም፣ «ክርስቶስ የተባለውን
ኢየሱስንስ ምን ላድርገው?» ሲል ጠየቀ።
ሕዝቡም በአንድ ድምፅ፣ «ስቀለው! ስቀ
ለው!» ብሎ ጮኸበት።
23 ጲላጦስም መልሶ፣ «ስቀለውስ እላች
ሁኝ፣ ግን ጥፋቱ ምንድነው?» በማለት
ጠየቀ። እነርሱ ግን፣ «ስቀለው! ስቀለው!»
እያሉ ጩኸታቸውን ቀጠሉ።
24 በዚህ ጊዜ ጲላጦስ ነገሩ እየተካረረ
መሄዱን ሲረዳ፣ሁከት እንዳይፈጠር በመሥ
ጋት፣ በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበና፣ «እኔ
ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፣ኃላፊ
ነቱ በእናንተ ላይ ነው» አለ።
25 ሕዝቡም፣ «ደሙ በእኛና በልጆቻ
ችን ላይ ይድረስ!» በማለት ጩኸቱን አስተ
ጋባ።
26 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ በርባንን ፈታው።
ኢየሱስን ግን ካስገረፈው በኋላ ወስደው
እንዲሰቅሉት ለሮማውያን ወታደሮች አሳ
ልፎ ሰጣቸው።
27 ወታደሮቹም ኢየሱስን በመጀመሪያ
ወደ ሠፈራቸው ወሰዱትና ተጠራርተው
ተሰበሰቡ። 28 ልብሱንም አውልቀው ቀይ
ጨርቅ አለበሱት። 29 ከረጃጅም እሾህ የተ
ጐነጐነ አክሊል ሠርተው በራሱ ላይ ደፉ
በት። በቀኝ እጁ ዘንግ አስይዘው፣ «ሰላም
ላንተ! የአይሁድ ንጉሥ!» እያሉ በማሾሚ
ጠጥ እጅ ነሡት። 30 በፊቱ ላይም በንቀት
ምራቃቸውን ተፉበት። ያስያዙትን ዘንግ
ከእጁ ወስደው ራሱን መቱት። 31 ካፌዙበ
ትና ካሾሚጠጡት በኋላም፣ቀይ ልብሱን



አውልቀው የራሱን ልብስ በማልበስ ሊሰቅ
ሉት ወሰዱት።
32 ወደሚሰቀልበትም ቦታ ይዘውት
ሲሄዱ ስምዖን የሚባል አፍሪቃዊ የቀሬናን
ሰው መንገድ ላይ አገኙ። ወታደሮቹም ይህ
ንን ሰው በማስገደድ የኢየሱስን መስቀል
እንዲሸከም አደረጉት። 33 በዚህ አኳኋን
ተጉዘው ጎልጎታ ከሚባለው ቦታ ደረሱ።
«ጎልጎታ» ማለት «የራስ ቅል ኮረብታ»
ማለት ነው። 34 ወታደሮቹ ከሐሞት ጋር
የተቀላቀለ ወይን ለኢየሱስ ሰጡት። እርሱ
ግን ቀምሶ ተወው።
35 ወታደሮቹም ኢየሱስን ከሰቀሉ በኋላ
ዕጣ ጥለው ልብሱን ተከፋፈሉት። 36 ከዚ
ያም የተሰቀለበትን ቦታ ከበው ይጠብቁ
ጀመር። 37 «ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው»
የሚል ጽሑፍ ከኢየሱስ መስቀል ራስጌ ይነ
በብ ነበር። 38 በዚያኑ ቀን ጠዋት ሌሎች
ሁለት ወንበዴዎችም ከኢየሱስ ግራና ቀኝ
ተሰቅለው ነበር።
39 ኢየሱስ ከተሰቀለበት ሥፍራ አጠገብ
ያልፉ የነበሩ መንገደኞች ራሳቸውን በመነ
ቅነቅ፣ 40 «መቅደስን አፍርሼ በሦስት ቀን
እሠራለሁ ባይ! በእርግጥ የእግዚአብሔር
ልጅ ከሆንክ እስቲ ከመስቀል ላይ
ውረድ!» እያሉ አፌዙበት።
41-43 የካህናት አለቆች፣የሃይማኖት መም
ህራንና የአገር ሽማግሌዎችም በበኩላቸው፣
«ሌሎችን አዳነ፤ታዲያ ለምን ራሱን አያድ
ንም? አይ የእኛ ንጉሥ! እስቲ ከመስቀል
ላይ ውረድና እንመንብህ! እንደሰማነው
በእግዚአብሔር እተማመናለሁ ይል ነበር።
እስቲ እንግዲህ ያ የሚተማመንበት አምላኩ
ሲያድነው እንይ? አልፎ ተርፎስ 'የእግዚአ
ብሔር ልጅ ነኝ' ይል አልነበረም?» በማ
ለት አላገጡበት። 44 ከእርሱ ጋር ተሰቅለው
የነበሩት ወንበዴዎችም ሳይቀሩ አሾፉበት።
45 በዚያን ዕለት፣ ከቀኑ ስድስት ሰዓት
ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ፣ ከባድ
ጨለማ ምድሪቱን ለሦስት ሰዓት ሸፈናት።
46 በዘጠኝ ሰዓት ላይ ኢየሱስ፣ «ኤሎሄ!
ኤሎሄ! ላማ ሰበቅታኒ?» ብሎ ጮኸ። ትር
ጓሜውም፣ «አምላኬ! አምላኬ! ለምን
ተውከኝ?» ማለት ነው። 47 ይህንን ሲሰ
ሙም በዚያ የቆሙ ሰዎች፣ኤልያስን የሚ
ጠራ መሰላቸው። 48 ከወታደሮቹ አንዱ
ሮጥ አለና፣ኮምጣጤ የገባበት ወይን ውስጥ
ሰፍነግ በመንከር በዘንግ ጫፍ ላይ አድርጎ፣
የኢየሱስን አፍ ለማራስ አቀረበለት። 49 የቀ
ሩት ሰዎች ግን፣ «እባክህ ተወው፣እስቲ
ኤልያስ መጥቶ ሲያድነው እናያለን» አሉ።
50 ከዚያም ኢየሱስ እንደገና በታላቅ
ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ሰጠ።
51 ወዲያውም የቤተ መቅደስ መጋረጃ
ከላይ ጀምሮ እስከ ታች ድረስ ለሁለት ተቀ
ደደ። ምድርም ተንቀጠቀጠች። አለቶችም
ተሰነጠቁ። 52 መቃብሮችም ተከፍተው
ሞተው የነበሩ ብዙ ቅዱሳን እንደገና በሕይ
ወት ሥጋ ተነሡ። 53 ከሞት የተነሡትም
ሰዎች ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ከመ
ቃብር ወጥተው በቅድስት ከተማ ውስጥ
ለብዙዎች ታዩ።
54 ኢየሱስ የተሰቀለበትን ሥፍራ ይጠ
ብቁ የነበሩት ወታደሮችም በፍርሃት ተርበ
ደበዱ። መሬት በመናወጡና በደረሰው
ነገር ሁሉ ፍርሃት ያደረበት የመቶ አለ
ቃም፣ «ይህ ሰው በእርግጥ የእግዚአብሔር
ልጅ ነበር» ሲል ተናገረ።
55 ከገሊላ ድረስ ኢየሱስን ተከትለውት
የመጡት ሴቶችም በሩቅ ሆነው ሁኔታውን
ይከታተሉ ነበር። 56 ከእነርሱም መካከል
መግደላዊት ማርያም፣ የያዕቆብና የዮሴፍ
እናት የሆነችው ሌላዋ ማርያም፣እንዲሁም
የዘብዴዎስ ሚስት የያዕቆብና የዮሐንስ
እናት ነበሩ።
57 ሲመሽም፣ ከኢየሱስ ተከታዮች አን
ዱና የአርማትያ ሰው የሆነው ሀብታሙ
ዮሴፍ፣ 58 ጲላጦስ ዘንድ ሄዶ የኢየሱስን
በድን ለመቅበር እንዲፈቅድለት ጠየቀ።
ጲላጦስም ፈቀደለት። 59 ዮሴፍም የኢየሱ
ስን አስከሬን ወስዶ፣ከተልባ እግር ከተሠራ
ንጹሕ ጨርቅ ገነዘው። 60 ከዚያም ከአለት
አስፈልፍሎ ለራሱ ባሠራው አዲስ መቃብር
ውስጥ ቀበረው። የመቃብሩንም ደጃፍ በአ
ንድ ትልቅ ድንጋይ ገጥሞት ሄደ። 61 መግ
ደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያምም በአ
ቅራቢያው የሚሆነውን ሁሉ ይከታተሉ
ነበር።
62 በማግስቱ–ማለትም የሰንበት ቀን
ዋዜማ ማለቂያ ላይ–የካህናት አለቆችና ፈሪ
ሳውያን ጲላጦስ ፊት ቀርበው 63 እንዲህ
አሉ፣ «ጌታ ሆይ፣ ያ ሐሰተኛ አንድ ጊዜ
'በሞትሁ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ' ብሎ
ነበር። 64 ስለዚህ መቃብሩ እስከ ሦስት ቀን
ድረስ እንዲታሸግና ዘበኞች በጥንቃቄ እንዲ
ጠብቁት ትእዛዝ እንዲሰጥልን። ያለበለዚ
ያማ ደቀመዛሙርቱ አስከሬኑን ሰርቀው
በመውሰድ 'ከሞት ተነሥቷል' ብለው
ማውራት ይጀምራሉ። ይህ ከሆነ ደግሞ
ከበፊቱ ስሕተት የከፋ ይብሳል» አሉት።

65 ጲላጦስም ፣ «የቤተ መቅደስ ዘበኞች
ስላሉአችሁ ስለጥበቃው እናንተው እወቁ
በት» አላቸው።
66 ወደ መቃብሩም ሄደው በሩን አሽ
ገው ማኅተማቸውን አተሙበት። በአካባ
ቢው ማንም ሰው ዝር እንዳይል የሚጠብቁ
ዘበኞችም አቆሙ።

## ምዕራፍ 28

1 በሰንበት ማግስት ገና ጎሕ እንደ
ቀደደ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ
ማርያም ወደ ኢየሱስ መቃብር ሄዱ።
2 በድንገትም ታላቅ የምድር መናወጥ
ሆነ። የጌታም መልአክ ከሰማይ ወርዶ
መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባልሎ
በመክፈት ድንጋዩ ላይ ተቀመጠበት።
3 የመልአኩ ፊት ልክ እንደ መብረቅ
የሚያበራ ፣ ልብሱም በጣም የሚያንጸባርቅ
ነበር። 4 መቃብሩንም ይጠብቁ የነበሩት ዘበ
ኞች መልአኩን ባዩ ጊዜ ከድንጋጤ የተነሣ
ተንቀጠቀጡ ፤ እወደቁበትም ሥፍራ እንደ
ሞተ ሰው ተዘርረው ቀሩ።
5 መልአኩም ሴቶቹን፣ «አትፍሩ! የተሰ
ቀለውን ኢየሱስን የምትፈልጉ መሆናችሁን
አውቃለሁ። 6 እርሱ ግን ከዚህ የለም።
ከዚህ ቀደም እንደተናገረው ከሞት ተነሥ
ቷል። አላምን ካላችሁም አስከሬኑ አርፎ
በት የነበረበትን ቦታ ኑና እዩ። 7 ይልቅስ
በፍጥነት ወደ ደቀ መዛሙርቱ ሂዱና
ከሞት እንደ ተነሣና እነርሱንም ለመገና
ኘት ወደ ገሊላ እንደሚሄድ ንገሩአቸው»
አላቸው።
8 ሴቶቹ ፍርሃትም ደስታም እየተሰማ
ቸው ፣ መልአኩ የነገራቸውን የምሥራች
ለማድረስ ደቀመዛሙርቱ ወዳሉበት ሄዱ።
9 በመንገድ ላይ ሳሉም ኢየሱስ ከፊታቸው
ድቅን በማለት፣ «እንዴት አደራችሁ» ሲል
አናገራቸው። ሴቶቹም እግሩ ላይ ተደፍ
ተው ሰገዱለት።
10 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው።
«አትፍሩ! ሄዳችሁ ወንድሞቼን ወደ ገሊላ
እንዲሄዱ ንገሩዋቸው። እኔን እዚያው ያገ
ኙኛል።»
11 ሴቶቹ ወደ ከተማ ሲያመሩም ፣ መቃ
ብሩን ይጠብቁ ከነበሩት ዘበኞች መካከል
ጥቂቶቹ ወደ ካህናት አለቆች ዘንድ ሄደው
የሆነውን ሁሉ አንድም ሳይቀር በዝርዝር
አስረዱ። 12-13 የካህናት አለቆች ከአገር
ሽማግሌዎች ጋር በመሰብሰብ ከተወያዩ
በኋላ በደረሱበት ስምምነት መሠረት፣ ለዘበ
ኞቹ ጉቦ በመስጠት፣ «ተኝተን ሳለን ደቀ
መዛሙርቱ ሌሊት መጥተው መቃብሩን
ከፍተው አስከሬኑን ሰረቁት» ብለው እንዲ
ያወሩ አዘዟቸው። 14 ምናልባትም ጉዳዩን
አገረ ገዢው ሰምቶ ዘበኞቹንም ለመቅጣት
ቢያስብ፣ ከአገረ ገዢው ጋር ተነጋግረው ነገ
ሩን ለማብረድ በአንድ ድምፅ ተስማሙ።
15 ዘበኞቹም የተሰጣቸውን ጉቦ ተቀብለው፣
የካህናት አለቆቹና የአገር ሽማግሌዎቹ ባዘ
ዟቸው መሠረት ማስተጋባት ስለጀመሩ፣ በአ
ጭር ጊዜ ውስጥ አይሁድ ባሉበት ሥፍራ
ሁሉ ታሪኩ ተዳረሰ። እስከዛሬም ድረስ ይህ
ወሬ በአይሁድ ዘንድ እንደ እውነተኛ ነገር
ይነገራል።
16 ከዚህ በኋላ አሥራ አንዱ ደቀመዛሙ
ርት ኢየሱስን ሊያገኙ ወደሚችሉበት ወደ
ገሊላ ሄዱ። 17 ባገኙትም ጊዜ ሰገዱለት።
ሆኖም ካገኙት መካከል አንዳንዶቹ በእር
ግጥ ኢየሱስ መሆኑን እስከ መጠራጠር
ደረሱ።
18 ኢየሱስም ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ
አለ። «በሰማይና በምድር ያለ ሥልጣን
ሁሉ ለእኔ ተሰጥቶኛል። 19 ስለዚህ ወደ
መላው ዓለም ሂዱና ሰዎችን በአብ ፣ በወ
ልድ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁ
20 የሰጠኋችሁንም ትእዛዛት ሁሉ አውቀው
እንዲፈጽሙ እያስተማራችሁ ደቀመዛሙ
ርቴ አድርጉአቸው። እኔም እስከዓለም
ፍጻሜ ድረስ ሳልለያችሁ ሁልጊዜ ከእናን
ተው ጋር ነኝ።»

# ማርቆስ የጻፈው

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ቃል

### መግቢያ

ክርስቶስ ድንቅ–ድንቅ ተአምራትን እያደረገ በዚች ምድር ላይ በሚመላ ለሰበት ጊዜ ማር ቆስ ገና ለጋላጋ ወጣት ነበር። የጌታን ምድራዊ የሕይወት ታሪክ የጻፈው ፣ ለተፈጸሙት ድርጊቶች የዓይን ምስክር ከነበሩት ከመጀመሪያዎቹ ደቀ መዛሙርት አንዱ ከሆነው ፣ ከጴጥሮስ ያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ ነው። በወንጌሉም ፣ ክርስቶስ ለሰዎች የሚያስብና የሚጨነቅ ፣ በጎ ነገር ሲሠራ ቢውል የማይታክትና ፣ ሕይወቱንም ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ ፣ ለአባቱ ፍጹም የሚታዘዝ እንደ ነበር በጉልሕ ያስተ ምራል።

---

## ምዕራፍ 1

1 ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ
ክርስቶስ የተነገረው የምሥራች ቃል መጀ
መሪያ። 2 ነቢዩ ኢሳይያስ በመጽሐፉ
ውስጥ ፣ እግዚአብሔር ልጁን ወደዚህ ዓለም
እንደሚልክ ፤ በቅድሚያ ግን አንድ የተለየ
መልእክተኛ መጥቶ ዓለምን እንደሚያዘጋጅ
ተናግሮ ነበር።
3 ኢሳይያስ እንደተናገረው ፣ መልእክተ
ኛው በበረሃ ውስጥ ይኖራል ፤ ሰዎች ጌታ
በሚመጣበት ጊዜ ዝግጁ ሆነው መገኘት
የሚችሉት ፣ ሕይወታቸውን የቀና በማድረግ
መሆኑን ያሳውቃቸዋል።
4 ይህም መልእክተኛ በበረሃ ይኖር የነበ
ረው መጥምቁ ዮሐንስ ነበር። እርሱም ፣
ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ይቅርታ እንዲያገኙ
ንስሐ መግባትና በውኃ መጠመቅ እንዳለባ
ቸው ያስተምር ነበር።
5 ብዙ ሰዎችም ከመላው ይሁዳና ከኢየ
ሩሳሌም ከተማ ፣ ዮሐንስን ለማየትና ትምህር
ቱንም ለማዳመጥ ወደ ነበረበት በረሃ ይጎ
ርፉ ነበር። ዮሐንስም ኃጢአታቸውን ሲና
ዘዙ ፣ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ያጠምቃቸው
ነበር። 6 ዮሐንስ ከግመል ጠጉር የተሠራ
ልብስ ይለብስና የቆዳ ቀበቶ ይታጠቅ ነበር።
የሚበላውም አንበጣና የጣዝማ ማር ነበር።
7 ሕዝቡን ሲያስተምር ፣ «ዝቅ ብዬ የጫማ
ውን ማሠሪያ ለመፍታት እንኳን የማይገ
ባኝ ፣ ከእኔ እጅግ የበለጠ በቅርብ ጊዜ ይመ
ጣል። 8 እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ ፤ እርሱ
ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል» ይል
ነበር።
9 በዚያን ወራት ኢየሱስ በገሊላ አው
ራጃ ከምትገኘው ከናዝሬት ከተማ መጥቶ ፣
በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ
ተጠመቀ። 10 ኢየሱስ ከውኃው እንደ
ወጣም ፣ ሰማያት ተከፍተው መንፈስ ቅዱስ
በርግብ ተመስሎ ሲያርፍበት አየ። 11 ወዲ
ያውም ፣ «አንተ የማፈቅርህ ልጄ ነህ ፤ በአ
ንተ ያለኝ ደስታ ታላቅ ነው» የሚል
ድምፅ ከሰማይ ተሰማ።
12 ወዲያውኑ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ
ተመርቶ ወደ በረሃ ወረደ። 13 ለአርባ ቀና
ትም በሰይጣን ተፈተነ። እዚያም ብቻውን
በአካባቢው ከሚገኙት አራዊት ጋር ነበረ።
መላእክትም ያገለግሉት ነበር።
14 መጥምቁ ዮሐንስ በንጉሥ ሄሮድስ
ትእዛዝ ተይዞ ከታሠረ በኋላ ፣ ኢየሱስ የእግ
ዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል ለማስተ
ማር ወደ ገሊላ ሄደ። 15 በዚያም ፣ «ጊዜው
ደረሰ ፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለ
ችና ኃጢአታችሁን ተናዘዙ ፤ የምሥራቹንም
ቃል ተቀበሉ» እያለ ያስተምር ነበር።
16 አንድ ቀን ኢየሱስ በገሊላ ባሕር አጠ
ገብ ሲያልፍ ፣ ስምዖንና እንድርያስ የተባሉ
ወንድማማች ፣ ዓሣ ለማጥመድ መረባቸውን
ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ። ወንድማማቹ የሚ
ተዳደሩት ዓሣ በማጥመድ ነበር። 17 ኢየሱ
ስም ፣ «ኑ ፣ ተከተሉኝ ፤ እኔ የሰዎች ነፍስ
አጥማጆች አደርጋችኋለሁ» አላቸው።
18 እነርሱም ወዲያውኑ መረባቸውን ትተው
ተከተሉት።
19 ጥቂት እልፍ ብሎ ፣ የዘብዴዎስን
ልጆች ያዕቆብንና ዮሐንስን ጀልባ ውስጥ
ተቀምጠው አየ። እነርሱም መረባቸውን

ይጠቀቅሙ ነበር። 20 ኢየሱስም ጠራቸው።
እነርሱም አባታቸውን ዘብዴዎስን ከቅጥር
ሠራተኞቹ ጋር ጀልባ ውስጥ ትተው ተከተ
ሉት።
21 ኢየሱስ ከተከታዮቹ ጋር ሆኖ ቅፍርና
ሆም ወደምትባል ከተማ ሄደ። ዕለቱ የሰን
በት ቀን ስለነበር ፥ ምኩራብ ወደሚባለው
የአይሁዶች ጸሎት ቤት ገብቶ አስተማረ።
22 ያስተምር የነበረውም ሙሉ ሥልጣን
እንዳለው መምህር እንጂ ፥ በአድማጮቹ
ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው በማለት–የታ
ወቁት የሃይማኖት መምህሮቻቸው እንደሚ
ያደርጉት–የአበው መምህራንን ቃል በመጥ
ቀስ ብቻ አልነበረም። ከዚህም የተነሣ የሰ
ሙት ሁሉ ተደነቁ።
23 ከሕዝቡም መካከል ርኩስ መንፈስ
ያደረበት ሰው ስለ ነበር እንዲህ ሲል በኃ
ይል ጮኸ፤ 24 «የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ስለ
ምን ታስጨንቀናለህ? የመጣኸው እኛን
ርኩሳን መናፍስትን ልታጠፋ ነውን? እኔ
ማን እንደሆንክ አውቃለሁ፥የቅዱሱ የእግዚ
አብሔር ልጅ ነህ!»
25 ኢየሱስም ርኩሱን መንፈስ ጸጥ እንዲ
ልና ከሰውየው እንዲወጣ አዘዘው። 26 ርኩ
ሱም መንፈስ ሰውየውን በምድር ላይ ካንፈ
ራፈረው በኋላ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ለቀ
ቀው። 27 ይህንንም ያዩና የሰሙ ሰዎች በአ
ድናቆት ተውጠው፥ስለሆነው ነገር ይወያዩ
ጀመር። «ምን ዓይነት አዲስ ሃይማኖት
መጣ?» አሉ በመገረም። «አጋንንት እንኳ
ቃሉን ሰምተው ይታዘዙታል» ተባባሉ።
28 ኢየሱስ ያደረገው ነገር በገሊላ ዙሪያ
ወዲያውኑ ተሰራጨ።
29 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ያዕቆብንና ዮሐን
ስን በማስከተል ከምኩራብ ወጥቶ ወደ ስም
ዖንና እንድርያስ ቤት ሄደ። 30 እዚያም
እንደ ደረሱ የስምዖን ሚስት እናት፥ከትኩ
ሳት በሽታ የተነሣ ተኝታ አገኟት። ስለበሽ
ታዋ ሁኔታ ለኢየሱስ ነገሩት። 31 ኢየሱስም
ወደ ሕመምተኛዋ ቀረብ አለና እጅዋን ይዞ
ቀና ብላ እንድትቀመጥ አደረጋት። ሕመ
ሙም ወዲያውኑ ተዋት። ተነሥታም ቤት
ውስጥ ጉድ ጉድ በማለት ምግብ አዘጋጅታ
አቀረበችላቸው።
32-33 ምሽት ላይ፥ብዙ ሰዎች በልዩ ልዩ
በሽታና በርኩሳን መናፍስት የተለከፉ በሽ
ተኞችን ይዘው ወደ ኢየሱስ ማምጣት
ጀመሩ። ከቅፍርናሆም ከተማ ነዋሪዎች
መካከል እጅግ ብዙ ሰዎች ኢየሱስ በነበረ
በት ቤት ደጅ ተሰበሰቡ። 34 ኢየሱስም
በዚያ ምሽት ብዙ ሕመምተኞችን ከልዩ
ልዩ በሽታ ፈወሰ፤ ርኩሳን መናፍስትንም
ከሰዎች አስወጣ። ነገር ግን ርኩሳን መናፍ
ስት እርሱ ማን እንደሆነ ስለሚያውቁ፥ስለ
እርሱ እንዳይናገሩ ከለከላቸው።
35 በማግስቱ ሊነጋጋ ሲል፥በጸጥታ ሊጸ
ልይ ወደሚችልበት ወደ አንድ ጭር ያለ
ሥፍራ ሄደ።
36-37 ከነጋ በኋላም ስምዖንና ሌሎቹም
ኢየሱስን ፍለጋ ሄዱ። ባገኙትም ጊዜ፥
«ሰዎች ሁሉ እየፈለጉህ እኮ ነው!»
አሉት።
38 ኢየሱስም «ወደ ሌሎች ከተሞች
ደግሞ እንሂድ፤እነርሱም መልእክቴን መስ
ማት አለባቸው። የመጣሁበትም ዓላማ
ይኸው ነው» ሲል መለሰላቸው።
39 ከዚህ በኋላ በአይሁድ ምኩራቦች
ውስጥ እያስተማረ፥በአጋንንት ኃይል የተያ
ዙትንም ሰዎች ነፃ እያወጣ በገሊላ ክፍለ
ሀገር ይዘዋወር ጀመር።
40 አንድ ቀን ለምጽ በሽታ የያዘው ሰው
ወደ ኢየሱስ ቀረበና ከእግሩ ሥር ተንበር
ክኮ፥ «ብትፈቅድ እኮ ልትፈውሰኝ ትችላ
ለህ!» በማለት ለመነው።
41 ኢየሱስም ለሰውየው በመራራት ሰው
ነቱን እየዳሰሰ ፥ «ፈቅጃለሁ ተፈወስ!»
አለው። 42 ሰውየውም ወዲያውኑ ከለምጽ
በሽታው ተፈወሰ።
43-44 ከዚያም ኢየሱስ ሰውየውን፥ «ፈጥ
ነህ ሂድና ሰውነትህን በአይሁድ ካህን አስ
መርምር። ከበሽታህ መፈወስህንም ሰዎች
ሁሉ እንዲያውቁ ሙሴ ያዘዘውን መሥዋ
ዕት ይዘህ ሂድ። ነገር ግን እግረ መንገድህን
ከማንም ሰው ጋር ቆመህ እታውራ» ብሎ
በጥብቅ አስጠነቀቀው።
45 ሰውየው ግን ከደስታው ብዛት የተ
ነሣ፥በመንገድ ላይ ላገኘው ሁሉ ከበሽታው
መፈወሱን አወራ። ከዚህም የተነሣ ኢየሱስ
የሚሠራው ተአምር በብዙ ቦታ እየተሰማ
ሄደ። ወሬውንም እየሰማ የሚከተለው
ሕዝብ በመብዛቱ፥ኢየሱስ ወደ ማንኛውም
ከተማ በግልጽ መግባት ተሳነው። ስለዚህ
መኖሪያውን በምድረ በዳ ማድረግ ተገደደ።
ይህም ሆኖ ሕዝቡ ከያቅጣጫው እርሱ ወዳ
ለበት ከመጉረፍ አላቋረጠም።

## ምዕራፍ 2

1 ከጥቂት ቀናት በኋላ ኢየሱስ ወደ ቅፍ
ርናሆም ከተማ ተመልሶ መጣ። የመምጣ
ቱም ወሬ በከተማው ውስጥ በፍጥነት ተሰ



ራጨ። 2 ወዲያውም የከተማው ሕዝብ ኢየ
ሱስ ወደ ነበረበት ቤት ይጐርፍ ጀመር።
ከሰው ብዛት የተነሣ በቤቱና በግቢው
ውስጥ መተናፈሻ ቦታ አልነበረም። ኢየሱ
ስም የምሥራቹን ቃል ሰበከላቸው። 3 በዚህ
ጊዜ አራት ሰዎች አንድ ሽባ ሰው በአልጋ
ተሸክመው መጡ። 4 ከሕዝብ ብዛት የተነሣ
ወደ ቤቱ ውስጥ ገብተው በሽተኛውን ኢየ
ሱስ ፊት ማቅረብ ባለመቻላቸው ፥ ከቤቱ
አናት ላይ ወጥተው ጣራውን በመንደል
በሽተኛውን ከነቃሬዛው ኢየሱስ ፊት እንዲ
ወርድ አደረጉ።
5 ኢየሱስም የሰዎቹን ጽኑ እምነት ተመ
ልክቶ በሽተኛውን፥ «ልጄ ሆይ፥ኃጢአት
ህን ይቅር ብዬልሃለሁ» አለው። 6 በሥፍ
ራው የነበሩት የአይሁድ ሃይማኖት መምህ
ራን ይህንን ሲሰሙ በልባቸው፥ 7 «ይህ ሰው
ለምን እግዚአብሔርን እንዲህ ይዳፈራል?
ለመሆኑ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአትን
ይቅር ማለት የሚችል ማን አለ? ወይስ እግ
ዚአብሔር ነኝ ብሎ ያስብ ይሆን?» አሉ።
8-10 ኢየሱስ ግን በልባቸው ያሰቡትን ስላ
ወቀ፥ «በዚህ ጉዳይ ለምን ትጨነቃላችሁ?
ይህን ሰው ፥ ‘ኃጢአትህን ይቅር ብዬልሃ
ለሁ’ ከማለትና፥ከያዘው በሽታ ከመፈወስ፥
የቱ የሚቀል ይመስላችኋል? ነገር ግን እኔ
የሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ይቅር
ለማለት ሥልጣን እንዳለኝ እወቁ።» አለና፥
በሽተኛውን ሰው ፥ 11 «ተፈውሰሃል!
ተነሥ! አልጋህንም ተሸክመህ ሂድ!»
አለው። 12 ሽባውም ብድግ ብሎ አልጋውን
ተሸክመና በሥፍራው በነበሩት ሰዎች መካ
ከል አቋርጦ ሄደ። ሕዝቡም በመደነቅ፥
«እንዲህ ያለውን ተአምር ከዚህ ቀደም አይ
ተን አናውቅም» እያሉ እግዚአብሔርን
ከልብ አመሰገኑ።
13 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ ባሕር ዳርቻ
ሄደ። በዙሪያው የተሰበሰበውንም ሕዝብ
አስተማረ። 14 የባሕሩን ዳርቻ ይዞ ሲሄድ፥
ሌዊ የሚባለውን የእልፍዮስን ልጅ በቀረጥ
መቀበያው ሥፍራ ተቀምጦ አየውና፥ «ተከ
ተለኝ ደቀመዝሙሬም ሁን አለው።»
ሌዊም ከሥራው ቦታ ተነሥቶ ተከተለው።
15 በዚያን ምሽት ሌዊ ቀራጭ የሥራ
ባልደረቦቹንና ኃጢአተኞች ወዳጆቹን፥ከኢ
የሱስና ከደቀመዛሙርቱ ጋር እንዲገናኙ
ቤቱ እራት ጋበዛቸው። 16 ኢየሱስ ከቀረጥ
ሰብሳቢዎችና ከኃጢአተኞች ጋር መብላ
ቱን ያዩ የፈሪሳውያን ወገን የሆኑ የአይሁድ
ሃይማኖት መምህራን ፥ «ለምን ከእነዚህ
ስማቸው ከጐደፈ ኃጢአተኞች ጋር ይበ
ላል?» በማለት ደቀመዛሙርቱን ጠየቁአ
ቸው። 17 ኢየሱስም የሚናገሩትን እንደ
ሰማ፥ «በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም
አያስፈልጋቸውም። እኔ የመጣሁት ጻድቃ
ንን ሳይሆን ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ ለመ
ጥራት ነው» አላቸው።
18 የዮሐንስ ደቀመዛሙርትና ፈሪሳውያን
በሚጾሙበት ወራት፥ጥቂት ሰዎች ወደ ኢየ
ሱስ መጥተው የእርሱ ደቀመዛሙርት
ለምን እንደማይጾሙ ጠየቁት። 19 ኢየሱስም
እንዲህ ሲል መለሰላቸው፥ «በሠርግ ጊዜ
የሙሽራው ጓደኞች ከድግሱ አንበላም ይላ
ሉን? ሙሽራውስ በመካከላቸው እያለ ማዘ
ንና መተከዝ ይገባቸዋልን? 20 ነገር ግን
ሙሽራው አንድ ቀን ይለያቸዋል። በዚያን
ጊዜ ይጾማሉ። 21 በአሮጌ ልብስ ላይ አዲስ
ጨርቅ የሚጥፍ አለን? ይህ ከሆነ የተጣ
ፈው አዲስ ጨርቅ አሮጌውን ሲስበው ቀዳ
ዳውን የባሰ ያሰፋዋል። 22 ባሮጌ የወይን
ስልቻም አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር
የለም። አዲስ የወይን ጠጅ አሮጌ ስልቻ
ውስጥ ከተቀመጠ፥ስልቻው ይፈነዳና የወ
ይን ጠጁ ይፈሰሳል። አዲስ የወይን ጠጅ
መቀመጥ ያለበት አዲስ ስልቻ ውስጥ
ነው።»
23 በሌላ ጊዜ በሰንበት ቀን ኢየሱስና
ደቀመዛሙርቱ በስንዴ ማሳ መካከል ሲያ
ልፉ ፥ ደቀመዛሙርቱ እሸቱን ቀጥፈው
እያሹ ይበሉ ጀመር። 24 በዚህ ጊዜ አንዳ
ንድ ፈሪሳውያን ኢየሱስን፥ «ደቀመዛሙር
ትህ ማድረግ የማይገባቸውን ነው የሚያደር
ጉት። በሰንበት ቀን እህል መቅጠፍ በሕጋ
ችን ክልክል ነው» አሉት።
25-26 ኢየሱስም መልሶ ፥ «አብያተር
ሊቀ ካህን በነበረበት ዘመን፥ዳዊት ያደረገ
ውን አላነበባችሁምን? እርሱና ተከታዮቹ
ተርበው ስለነበር ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ
ለካህናት ብቻ ከተፈቀደው ምግብ በላ፤ለተ
ከታዮቹም ሰጠ። 27 ደግሞም ሰንበት ለሰው
ጥቅም ተሠራ እንጂ፥ሰው ለሰንበት ተብሎ
አልተፈጠረም። 28 እኔ የሰው ልጅ፥የሰንበት
ጌታዋ ነኝ።»

## ምዕራፍ 3

1 ኢየሱስ በቅፍርናሆም ሳለ፥ ምኩራብ
ተብሎ ወደሚጠራው የአይሁድ ጸሎት
ቤት ሄደ። በዚያም አንድ እጁ ሽባ የሆነ
ሰው አየ።
2 ዕለቱ ሰንበት ስለነበር፥ኢየሱስን ለመከ

ስለ ምክንያት ይፈልጉ የነበሩት ሰዎች በጥ
ንቃቄ ይከታተሉት ነበር። «የዚህን ሰው
እጅ ይፈውስ ይሆን?» ብለው በማሰብ፣ከፈ
ወሰው ሊያሳስሩት የሚችሉበትን መንገድ
ያውጠነጥኑ ነበር። 3 ኢየሱስም እጁ ሽባው
ሰው በጉባዔው ፊት እንዲቆም አደረገ።
4 ከዚያም ሊከሱት ወደሚፈልጉት ሰዎች
ፊቱን በማዞር፣ «በሰንበት ቀን መልካም
ሥራ መሥራት ይገባል? ወይስ ክፉ ሥራ
መሥራት? በሰንበት ቀን ሕይወትን ማዳን
ይገባል? ወይስ ማጥፋት?» ሲል ጠየቃ
ቸው። እነርሱ ግን ምንም አልመለሱለ
ትም። 5 በዚህ ጊዜ ኢየሱስ በሰዎቹ ርኅ
ራኄ ማጣት በማዘን፣ በቁጣ ከተመለከታ
ቸው በኋላ ሰውየውን፣ «እጅህን ዘርጋ!»
አለው። እርሱም እንደ ታዘዘው ሲዘረጋ
እጁ ወዲያውኑ ዳነለት።
6 ወዲያው ፈሪሳውያን ኢየሱስን ለመግ
ደል የሚያስችላቸውን እቅድ ሄሮድሳውያን
ከተባሉት የሮም አገዛዝ ደጋፊዎች ጋር
ለመመካከር ሄዱ። 7-8 በመካከሉም ኢየሱስ
ከደቀመዛሙርቱ ጋር ወደ ገሊላ ባሕር
ተመልሶ ሄደ። ያደርገው የነበረውን ተአም
ራት የሰሙና፣በጆሮአቸው የሰሙትን በዓይ
ናቸው አይተው ለማረጋገጥ የመጡ ብዙ
ሰዎች፣ ከገሊላ ግዛት፣ ከይሁዳ፣ ከኢየሩሳ
ሌም፣ከኤዶምያስ፣ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶና
እንዲሁም ከጢሮስና ከሲዶና ሳይቀር ተከት
ለውት ነበር።
9 ከሕዝቡ ብዛት የተነሣ አፍነው እንዳያ
ስጨንቁት፣አንድ ጀልባ አዘጋጅተው እንዲ
ያስቀምጡ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን አዘዛ
ቸው። 10 ብዙ ሕሙማንንም በመፈወሱ
በሕመም የሚሰቃዩ ሁሉ በኢየሱስ ዙሪያ
በመርመስመስ በእጃቸው ሊነኩት ጥረት
ያደርጉ ነበር። 11 እርኩሳን መናፍስት ያደረባቸው
ሰዎችም ሲያዩት ከፊቱ እየወደቁ፣ «አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!» በማለት
ይጮኹ ነበር። 12 እርሱ ግን ማንነቱን እን
ዳይገልጹ በጥብቅ ያስጠነቅቃቸው ነበር።
13 ከዚህ በኋላ ወደ ኮረብታማ ቦታ
ወጥቶ፣ የመረጣቸውን አንዳንዶቹን ወደ
እርሱ ጠራቸው።
14-15 ከዚያም ሁልጊዜ አብረውት እንዲ
ሆኑና እየተዘዋወሩም የምሥራቹን ቃል
እንዲሰብኩ፣ እርኩሳንንም እንዲያስወጡ
ከመካከላቸው አሥራ ሁለቱን መረጠ።
16 የተመረጡትም የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
ስም የሚከተለው ነው፣
17-19 ስምዖን (ኢየሱስ ጴጥሮስ ብሎ
የሠየመው)
ያዕቆብና ዮሐንስ (ኢየሱስ የነጐድጓድ
ልጆች ብሎ የጠራቸው የዘብዴዎስ
ልጆች)
እንድርያስ
ፊልጶስ
በርተሎሜዎስ
ማቴዎስ
ቶማስ
ያዕቆብ (የእልፍዮስ ልጅ)
ታዴዎስ
ስምዖን (የሮማን መንግሥት ቅኝ አገዛዝ
ለማስወገድ ይጥር የነበረው የፖለቲካ
ቡድን አባል)
የአስቆሮቱ ይሁዳ (ኢየሱስን አሳልፎ የሰ
ጠው)።
20 ኢየሱስ ወዳረፈበት ቤት ሲመለስ
እጅግ ብዙ ሰው እንደገና ስለተሰበሰበ እር
ሱና ደቀመዛሙርቱ እህል ለመቅመስ እን
ኳን ፋታ አላገኙም። 21 ቤተሰቡ ይህን
በሰሙ ጊዜ ወደቤት ሊወስዱት፣ ኢየሱስ
ካለበት ሥፍራ ድረስ መጡ። «እርሱ አእ
ምሮውን ስቷል» እያሉ ያወሩ ነበር።
22 ከኢየሩሳሌም መጥተው የነበሩ የአይ
ሁድ ሃይማኖት መምህራን ደግሞ፣ «እርሱ
የእርኩሳን አለቃ ብዔል ዜቡል አድሮበ
ታል። እርኩሳን የሚታዘዙለትም ስለዚህ
ነው» እያሉ ማውራት ጀመሩ።
23 ኢየሱስም እነዚህን ሰዎች ጠርቶ ሊገ
ባቸው በሚችል ምሳሌ እንዲህ አላቸው።
24 «ለመሆኑ ሰይጣን ሰይጣንን እንዴት አድ
ርጎ ሊያወጣ ይችላል? ውስጣዊ ኅብረት
የጐደለው መንግሥት ይወድቃል።
25 ጠብና መለያየት ያለበት ቤተሰብም ይፈ
ርሳል። 26 ሰይጣንም ራሱን በራሱ የሚጻረር
ከሆነ፣ የገዛ ኃይሉን ከማዳከም በቀር ሌላ
ምን ፋይዳ ሊፈጽም ይችላል? 27 እንዲ
ሁም የአንድ የኃበዝ ሰው ቤት ከመታሰሱና
ንብረቱ ከመወሰዱ በፊት፣ኃበዙ ሰው አስቀ
ድሞ መያዝና መታሠር አለበት። ከዚያ
በኋላ ንብረቱን መበዝበዝ ይቻላል።» ከዚ
ያም ንግግሩን በመቀጠል፣ 28 «እውነተኛ
ውን ነገር ልንገራችሁ፤ ሰዎች የሚሠሩት
ኃጢአትና የሚናገሩት ስድብ ሁሉ፣ይቅር
ይባልላቸዋል። 29 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስ
ድብ ቃል የሚሰነዝር ሰው ግን፣ለዘላለም
የማይፋቅ ኃጢአት ሠርቶአልና ምን ጊዜም
ይቅርታ የለውም።» 30 ኢየሱስ ይህንን ቃል
ለአይሁድ የሃይማኖት መምህራን የተናገረ
በት ምክንያት፣ 'ርኩስ መንፈስ አድሮበ
ታል' እያሉ ያወሩ ስለነበረ ነው።
31-32 ወዲያውም ኢየሱስ ያስተምር ወደ
ነበረበት ቤት እናቱና ወንድሞቹ መጥተው
ብቅ ብሎ እንዲያነጋግራቸው መልእክተ
ኞች ላኩበት። መልእክተኞቹም፣ «እናት
ህና ወንድሞችህ ሊያነጋግሩህ ፈልገው
ውጭ ቆመዋል» አሉት። 33 እርሱም፣
«እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን
ናቸው?» አለና፣በዙሪያው ወደተሰበሰቡት
ሰዎች እየመለከተ፣ 34 «እነሆ፣እናቴና ወን
ድሞቼ እነዚህ ናቸው። 35 የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚፈጽም ሁሉ ወንድሜ፣እኅቴ፣
እናቴም ነው» አለ።

## ምዕራፍ 4

1 በሌላ ጊዜ ደግሞ ኢየሱስ በገሊላ
ባሕር አጠገብ ሲያስተምር በዙሪያው እጅግ
ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። ከዚያም ባሕሩ ዳር
ከነበረ አንድ ጀልባ ውስጥ ተቀምጦ ማስተ
ማሩን ቀጠለ። 2 ሲያስተምርም፣ ብዙ ጊዜ
ምሳሌዎችን ይነግራቸው ነበር። ከምሳሌዎ
ቹም አንዱ እንዲህ የሚል ነበር።
3 «አዳምጡ፣ አንድ ገበሬ እህል ሊዘራ
ወጣ። 4 እህሉን ሲዘራ አንዳንዱ ዘር መን
ገድ ዳር ወደቀ። ወፎችም ይህንኑ መንገድ
ላይ የወደቀውን ዘር ለቅመው በሉት።
5-6 ሌላውም ዘር የአፈር ጥልቀት በሌለው
ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ። ዘሩም ቶሎ
በቀለ። ነገር ግን አፈሩ የሳሳና መሬቱም
ድንጋያማ በመሆኑ፣ ሥሩ እንደ ልብ ተንሰ
ራፍቶ ለቡቃያው የሚያስፈልገውን ምግብ
ማስተላለፍ ባለመቻሉና፣የፀሐዩዋም ግለት
ኃይለኛ በመሆኑ ወዲያው ጠውልጎ ደረቀ።
7 ሌላው ዘር ደግሞ በእሾህ መካከል
ወደቀ። ከበቀለም በኋላ እሾሁ አንቆ አስቀ
ረው። 8 ነገር ግን ከዘሩ መካከል አንዳንዱ
በጥሩ መሬት ላይ ወድቆ በቀለ። አድጎም
ፍሬ በሚሰጥበት ሰዓት አንዱ ሠላሳ፣ አን
ዱም ስድሳ፣ ሌላውም መቶ እጥፍ አፈራ።
9 የሚሰማ የልቦና ጆሮ ካላችሁ፣ስሙ!»
10 ኢየሱስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና
ከሌሎቹም ተከታዮቹ ጋር ብቻውን ሳለ፣
ከመካከላቸው፣ «የነገርከን ምሳሌ ትርጉሙ
ምንድነው?» ብለው ጠየቁት።
11-12 እርሱም እንዲህ አላቸው፤ «ከእግ
ዚአብሔር መንግሥት ውጪ ያሉ ሰዎች
ሊያስተውሉት የማይችሉትን መንፈሳዊ
ምሥጢር ማወቅ ለእናንተ ተሰጥቶአች
ኋል። እነርሱ ግን ቢያዩና ቢሰሙም ማስተ
ዋል ስለሚሳናቸው፣ ወደ እግዚአብሔር
ሊመለሱና ለበደላቸው ይቅርታ ሊያገኙ
አይችሉም።
13 «ይህንን ቀላል ምሳሌ መረዳት ካልቻ
ላችሁ ወደፊት የምነግራችሁን ነገር እን
ዴት ማስተዋል ትችላላችሁ?» አላቸውና፣
ስለ ዘሪው ምሳሌ እንደሚከተለው አብራራላ
ቸው።
14 «በምሳሌው ውስጥ የጠቀስኩት
ገበሬ፣የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሰዎች ልብ
እንዲደርስና በሕይወታቸው ውስጥ መል
ካሙ ዘር እንዲበቅል የሚያደርግ ማንኛ
ውም ሰው ነው። 15 ከዘሩ መካከል ጥቂቱ
የወደቀበት ያ የተደለደለ መንገድ የሚያመ
ለክተው፣ ቃሉን ከሚሰሙት ሰዎች መካከል
ደንዳና ልብ ያላቸውን ሰዎች ነው። እነዚህ
ሰዎች ቃሉን እንደሰሙ ሰይጣን ይቀርባቸ
ውና የሰሙትን እንዲረሱ ያደርጋቸዋል።
16 ጥልቅ የሆነ አፈር የሌለው ድንጋያማ
መሬት፣የእግዚአብሔርን ቃል ሲሰሙ ለጊ
ዜው በደስታ የሚቀበሉትን ሰዎች ልብ
ያመለክታል። 17 ይሁን እንጂ ሥሩን በጥል
ቀት አፈሩ ውስጥ ለመስደድ እንዳልቻለው
ቡቃያ አትክልት፣እምነታቸው ጽኑ ባለመ
ሆኑ መከራና ስደት ሲደርስባቸው ነገር ዓለ
ሙን ይተዉታል።
18 «በእሾህ መካከል የተዘራው ዘር የሚ
ያመለክተው፣ቃሉን ሰምተው የሚቀበሉትን
ሰዎች ልብ ነው። 19 ነገር ግን ብዙም ሳይዘ
ገይ የዚህ ዓለም አሳብና ጭንቀት፣የገንዘብ
ፍቅርና የተለያዩ ዓለማዊ ምኞቶች የሰሙ
ትን ቃል አፍነው ስለሚይዙት ሕይወታ
ቸው ፍሬ ሳይሰጥ ይቀራል።
20 «በጥሩ መሬት ላይ የወደቀው ዘር
ደግሞ፣ ቃሉን ተቀብለው ሠላሳ፣ስድሳ ከዚ
ያም አልፎ መቶ እጥፍ ፍሬ የሚያፈሩውን
የሰዎች ልብ ያመለክታል።»
21 ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፣
«ሰው መብራት አብርቶ ብርሃኑ እንዳይታይ
ሳጥን ውስጥ ወይም አልጋ ሥር ይደብቀዋ
ልን? እንደ እውነቱ ከሆነ ብርሃኑ በጣ ብሎ
እንዲታይ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል እንጂ
ሸፍኖ አያስቀምጠውም።
22 «እንደዚሁም ዛሬ የተሸሸገና የተሰወ
ረው ነገር አንድ ቀን ተገልጦ ይታያል።
23 የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው ይስማ»
አለ።
24 ቀጥሎም እንዲህ አላቸው፣ «የምነግ
ራችሁን በማስተዋል አድምጡ። የምትሰሙ
ትን በተግባር ላይ ስታውሉት፣ የምትቀበ
ሉት ደግሞ በዚያው መጠን፣እንዲያውም

የበለጠ ከፍ ይላል። 25 ላለው ይጨመርለ
ታል፤ከሌለው ያው ያለው እንኳን ይወሰድበ
ታል።»
26 የእግዚአብሔር መንግሥት ምን እንደ
ሚመስል የሚገልጽ ሌላ ምሳሌ እንዲህ
ሲል ነገራቸው። «አንድ ገበሬ እርሻውን
እህል አዘራበት። 27 ከጥቂት ቀናት በኋላ
የተዘራው እህል ያለ ገበሬው እርዳታ
በቀለ። 28 በመጀመሪያ ቡቃያው ቀንበጥ
አወጣ፤ቀጥሎ አገዳው ቅርጽ አበጀ፤በመጨ
ረሻም ፍሬው ደረሰ። 29 ገበሬውም ማጭ
ዱን ይዞ መጣና አጭዶ አመረተ።»
30 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ፥ «የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት እንዴት አድርጌ ላብራራላ
ችሁ? ምን ዓይነት ምሳሌስ ብነግራችሁ
ትረዱታላችሁ?» በማለት ጠይቆ ሲያበቃ
እንዲህ አለ፤ 31-32 «የእግዚአብሔር መንግ
ሥት የሰናፍጭ ዘር ትመስላለች። የሰናፍጭ
ዘር ከሌሎች ዘሮች አነስተኛ ብትሆንም እን
ኳን፥ከተዘራች በኋላ አድጋ ከሌሎች ተክ
ሎች ትበልጣለች፤ ትላልቅ ቅርንጫፎች
አውጥታ ለሰማይ ወፎች መኖሪያና መጠ
ጊያ ትሆናለች።»
33 ኢየሱስም እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ
ምሳሌዎች በመናገር ሰዎች ምሥጢሩን
ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ አስተማራ
ቸው። 34 ኢየሱስ፥ያለ ምሳሌ በጉባኤ አያስ
ተምርም ነበር። ብቻውን ከደቀመዛሙርቱ
ጋር ሲሆን ግን ማንኛውንም ነገር በይበልጥ
ያብራራላቸው ነበር።
35 ቀኑ ሊመሽ ሲል ኢየሱስ ደቀመዛሙ
ርቱን፥ «ወደ ማዶ እንሻገር» አላቸው።
36 ከሕዝቡም ተለይተው በጀልባ ጉዞ
ጀመሩ። ሌሎችም ጀልባዎች ይከተሉዋ
ቸው ነበር። 37 በጉዞ ላይ እንዳሉ ከፍተኛ
ማዕበል አጋጠማቸው። ውኃ በጀልባው
ውስጥ በመግባቱም ሊሰጥሙ ተቃረቡ።
38 ይህ ሁሉ ሲሆን ኢየሱስ ከጀልባው በስተ
ኋላ በኩል ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር።
ደቀመዛሙርቱም ፍርሃት እያርበደበዳቸው
ቀሰቀሱትና፥ «ጌታ ሆይ፥ማለቃችን እኮ
ነው! ዝም ብለህ ታያለህ?» አሉት። 39 እር
ሱም ተነሥቶ፥ «ጸጥ በል!» በማለት ነፋ
ሱን ገሠጸው። ማዕበሉ ቆመ፥ታላቅ ጸጥ
ታም ሆነ። 40 ከዚያም ደቀመዛሙርቱን፥
«ምነው እንደዚህ ፈራችሁ? በእኔ ላይ ገና
እምነት የላችሁምን?» አላቸው። 41 ደቀመ
ዛሙርቱም ከመጠን በላይ ተደንቀው፥
«ባሕርና ሞገድ የሚታዘዙለት ይህ ሰው
ማነው?» ተባባሉ።

## ምዕራፍ 5

1-2 ባሕሩን ተሻግረው ጌርጌሴኖን ወደ
ሚባለው አካባቢ ደረሱ። ኢየሱስ ከጀልባው
በሚወርድበት ጊዜ አንድ ርኩስ መንፈስ
ያደረበት ሰው ከመቃብር ቤት ወጥቶ እየ
ሮጠ መጣ። 3-4 ይህ ሰው ኑሮው መቃብር
ቤት ውስጥ ነበር። ብዙ ጊዜም እጁና
እግሩ የሚታሠርበትን ሰንሰለትና እግር
ብረት በኃይሉ ስለሚበጣጥስ ማንም ሰው
ሊይዘውና ሊገታው አይችልም ነበር።
5 ቀንም ሆነ ሌሊት ያለ ምንም ዕረፍት
በመቃብሩና በአካባቢው ኮረብታ ዙሪያ እየ
ተዘዋወረ ሰውነቱን ስለታም በሆነ ድንጋይ
እየቆራረጠ ይጮኽ ነበር።
6 ኢየሱስን ገና ከሩቅ ሲያየው ሊገናኘው
እየሮጠ ሄዶ ከእግሩ ሥር በግምባሩ
ተደፋ።
7-8 ኢየሱስም በሰውየው ውስጥ ያደረ
ውን ርኩስ መንፈስ፥ «አንተ ርኩስ መንፈስ
ከዚህ ሰው ውጣ!» ብሎ አዘዘው። ርኩሱ
መንፈስ ግን፥ «አንተ የልዑል እግዚአብ
ሔር ልጅ ሆይ፥ምን ልታደርገኝ ትሻለህ?
ስለ እግዚአብሔር ብለህ አታሠቃየኝ!»
እያለ ጮኸ።
9 ኢየሱስም፥ «ስምህ ማን ነው?» ሲል
ጠየቀው። ርኩሱም መንፈስ፥ «በዚህ ሰው
ውስጥ ያደርነው ብዙ ስለሆንን ስሜ ሌጌ
ዎን (ሠራዊት) ነው» አለ። 10 ወደ ሩቅ
አገር እንዳያባርራቸውም ኢየሱስን አጥብቆ
ለመነው። 11 ከባሕሩ ዳርቻ ባለው ኮረብ
ታማ ቦታ ላይ ትልቅ የአሳማ መንጋ ተሰማ
ርቶ ነበር። 12 ርኩሳን መናፍስቱም፥ «እነ
ዚያ አሳማዎች ውስጥ እንድንገባ ፍቀድ
ልን!» ሲሉ ኢየሱስን ለመኑት። 13 ኢየሱ
ስም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም
ከሰውየው ወጥተው አሳማዎቹ ውስጥ ገቡ።
በዚህ ጊዜ ቁጥራቸው ሁለት ሺህ ያህል የነ
በሩት አሳማዎች በሙሉ በርግገው ከገደሉ
ዘለው ወደ ባሕሩ እየገቡ ሰጥመው አለቁ።
14 አሳማዎቹን ይጠብቁ የነበሩት እረ
ኞች በአቅራቢያው ወደሚገኙት ከተሞችና
መንደሮች ሸሽተው በመሄድ በደረሱበት
ሁሉ የሆነውን ነገር አወሩ። ሕዝቡም
በጆሮ የሰማውን በዓይኑ ለማየት ከየቤቱ
ወጣ። 15 ወዲያውም ኢየሱስ በነበረበት
ሥፍራ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ። ነገር ግን
ርኩስ መንፈስ አድሮበት የነበረው ሰው
ልብስ ለብሶና ፍጹም ጤነኛ ሆኖ ሲያዩት
ፈሩ።



16 የሆነውን ተአምር ያዩ ሰዎችም ወሬ
ውን ላልሰሙት ሁሉ ተናገሩ። 17 ከሕዝ
ቡም ብዙዎቹ ኢየሱስ አገራቸውን ትቶ
እንዲሄድላቸው ለመኑት። 18 ከዚያም ኢየ
ሱስ ወደ ጀልባው ገባ። ርኩሳን መናፍስት
አድሮበት የነበረውም ሰው፥ተከትሎት እን
ዲሄድ እንዲፈቅድለት ኢየሱስን ለመነው።
19 ኢየሱስ ግን የሰውየውን ጥያቄ አልተቀበ
ለውም። «ወደ ቤትህ ሂድና ለወዳጆችህ
እግዚአብሔር ስለ ሠራልህ ታላቅ ሥራና
ስላሳየህ ምሕረት ተናገር» አለው። 20 ሰውየ
ውም በ'አሥሩ ከተማዎች' እየተዘዋወረ ላገ
ኘው ሰው ሁሉ ኢየሱስ ያደረገለትን ድንቅ
ነገር ማውራት ጀመረ። የሰሙትም ሁሉ
በታሪኩ እጅግ ተደነቁ።
21 ኢየሱስ ከባሕሩ ማዶ ወዳለው አካባቢ
እንደገና በጀልባ ተሻግሮ እንደደረሰ ብዙ
ሕዝብ በዙሪያው ተሰበሰበ። 22 በዚያም
ኢያኢሮስ የተባለ ከአጥቢያው ምኲራብ አለ
ቆች አንዱ፥ወደ ኢየሱስ ቀርቦ ከእግሩ ሥር
በመደፋት፥ 23 ሴት ልጁን እንዲያድንለት
ለመነው። ከልቡም፥ «ልጄ ልትሞት ተቃ
ርባለች፤እባክህን ወደ ቤቴ ናና እጅህን በላ
ይዋ ላይ ጭነህ አድንልኝ» ሲል ተማጸ
ነው። 24 ኢየሱስም አብሮት ሄደ። በዚያ የነ
በረውም ሕዝብ ተከተለው። ከሕዝቡም
ብዛት የተነሣ ታላቅ ግፊያ ነበር። 25 ከሕ
ዝቡ መካከል አንዲት አሥራ ሁለት ዓመት
ሙሉ ደም እየፈሰሳት የምትሠቃይ ሴት
ነበረች። 26 ሴቲቱም ወደ ተለያዩ ሐኪሞች
ዘንድ ሄዳ ብትመረመርና ብትታከምም ያላ
ትን ገንዘብ ከመጨረስ በስተቀር ፈውስ
ማግኘት አልቻለችም፤ እንዲያውም ሕመ
ምዋ እየጠናባት ሄደ። 27 ኢየሱስ በሽተኞ
ችን እንደሚያድን ወሬውን ሰምታ ስለነ
በር፥ከሕዝቡ መካከል ተጋፍታ በመጠጋት
ከኋላው በኩል የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች።
28 በልቧ፥ «እንደ ምንም ብዬ የልብሱን
ጫፍ እንኳን ብነካ እድናለሁ» የሚል እም
ነት ነበራት። 29 እንዳሰበችውም የልብሱን
ጫፍ ስትነካ ደሙ ወዲያውኑ በመቆሙ፥
ጤንነቷን ማግኘትዋ ታወቃት። 30 ኢየሱ
ስም ሕመምን የሚፈውስ ኃይል ከእርሱ
እንደ ወጣ በማወቁ፥ወደ ሕዝቡ ዞር አለና፥
«ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው?» ሲል ጠየቀ።
31 ደቀመዛሙርቱም፥ «ይህ ሁሉ ሕዝብ
ዙሪያህን ከቦ እየተጋፋ ይከቹልሃል፤ልብስ
ህን ማን እንደነካ እንዴት ሊታወቅ ይቻ
ላል?» ሲሉ መለሱለት። 32 እርሱ ግን ልብ
ሱን የዳሰሰውን ሰው ለማወቅ ዙሪያውን
ይመለከት ጀመር። 33 በዚህ ጊዜ የተፈወሰ
ችው ሴት ሙሉ ለሙሉ መዳኗን ስላወቀች
በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ከእግሩ ሥር ተደ
ፍታ ያደረገችውን ዘርዝራ ተናገረች።
34 ኢየሱስም፥ «ልጄ ሆይ እምነትሽ አድኖ
ሻል። በሰላም ሂጂ፥ ከሥቃይሽም ሁሉ
ዕረፊ» አላት።
35 ኢየሱስ ከሴትዮዋ ጋር በሚነጋገርበት
ጊዜ፥ከኢያኢሮስ ቤት መልእክተኞች ደር
ሰው፥ልጅቷ ሕይወትዋ እንዳለፈና ከእንግ
ዲህ መምህሩን ማስቸገር እንደሌለበት ነገ
ሩት። 36 ኢየሱስ መልእክተኞቹ ለኢያኢ
ሮስ የተናገሩትን ቃል ሰምቶ፥ «አትፍራ፥
ብቻ በእኔ እምነት ይኑርህ» አለው። 37 ከዚ
ያም ከተከተለው ሕዝብ መካከል፥ጴጥሮ
ስን፥ያዕቆብንና ዮሐንስን ብቻ ይዞ ወደ
ኢያኢሮስ ቤት አመራ። 38 እዚያም ሲደ
ርሱ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ በልቅሶና በዋ
ይታ ይተረማመስ ነበር። 39 ኢየሱስም ወደ
ቤት ገብቶ አልቃሾቹን፥ «ይህ ሁሉ ልቅ
ሶና ዋይታ ለምንድን ነው? ልጅቷ ተኝታ
ለች እንጂ አልሞተችም» አላቸው። 40 አል
ቃሾቹም ኢየሱስ የተናገረውን ሲሰሙ በማ
ሽሟጠጥ ሳቅ ሳቁበት። ኢየሱስ ግን አልቃ
ሾቹን ከቤት አስወጣና የልጅቷን አባትና
እናት እንዲሁም ሦስቱን ደቀመዛሙርት
ብቻ አስከትሎ ልጅቷ ወደምትገኝበት
ክፍል ገባ።
41 የልጅቱንም እጅ ይዞ፥ «አንቺ ልጅ
ተነሽ!» አላት። 42 ልጅቷም ወዲያው
ብድግ ብላ ወዲህና ወዲያም ተመላለሰች።
እድሜዋም አሥራ ሁለት ዓመት ነበር።
እናትና አባቷ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ
የሚሆኑትን አጡ። 43 ኢየሱስም የሆነውን
ነገር ለማንም እንዳያወሩ ከአስጠነቀቃቸው
በኋላ፥ለልጅቷ የምትበላው እንዲሰጧት ነገ
ራቸው።

## ምዕራፍ 6

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከነበረበት አካባቢ
ደቀመዛሙርቱን አስከትሎ የትውልድ ከተ
ማው ወደ ሆነችው ወደ ናዝሬት ተመለሰ።
2 በሚቀጥለውም ሰንበት ዕለት ለማስተማር
ወደ አቅራቢያው ምኲራብ ሄደ። ሕዝቡም
በኢየሱስ የማስተዋል ችሎታና በሚሠራ
ቸው ተአምራት በመገረም፥ 3 «ይህ ሰው
ይህን ሁሉ ዕውቀትና ችሎታ ከየት አመ
ጣው? ይህ አናጢው የማርያም ልጅ አይደ
ለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብ፥ዮሳ፥ይሁዳና
ስምዖን አይደሉምን? እኅቶቹም ቢሆኑ ከእ

ኛው ጋር ይኖሩ የለምን?» በማለት ሊያም
ኑበት አልቻሉም። 4 ኢየሱስም ፥ «ነቢይ
ድሮም ቢሆን በሌሎች ዘንድ ሲከበር፥በገዛ
አገሩ፥በዘመዶቹና በቤተሰቦቹ ዘንድ የተናቀ
ነው» አላቸው።
5 ከለማመናቸውም የተነሣ በጥቂት በሽ
ተኞች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በስተ
ቀር ፥ በገዛ አካባቢው ታላቅ ተአምራትን
መሥራት አልቻለም። 6 በእርሱ ለማመን
ፈቃደኛ አለመሆናቸው እያስገረመው፥በአካ
ባቢው ወዳሉት መንደሮች ሄዶ ማስተማሩን
ቀጠለ።
7 አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት በአንድ
ላይ ጠርቶ፥ሁለት ሁለቱን በማሠማራት በር
ኩሳን መናፍስት ላይ ሥልጣን ሰጣቸው።
8-9 ከያዙት በትር በስተቀር ለጉዞአቸው
ብለው ምንም ስንቅ ፥ ምንም ከረጢት ፥
ምንም ገንዘብ ፥ ሌላው ቀርቶ ለቅያሪ የሚ
ሆን ጫማ ወይም ልብስ እንዳይዙ አስጠነቀ
ቃቸው። 10 «አንድ መንደር ስትደርሱ ፥
ያንን ሠፈር እስክትለቁ ድረስ ማረፊያችሁ
አንድ ቤት ውስጥ ይሁን። 11 የሠፈሩ ሰዎች
'አንቀበላችሁም ፤ መልእክታችሁንም አንሰ
ማም' ካሉ ፥ ያንን ቦታ ለቅቃችሁ ስትሄዱ
የጫማችሁን አቧራ አራግፉችሁ ከዚያ
ውጡ። ይህም ፥ መልእክታችሁን ሰምተው
ላለመቀበላቸው በፍርድ ቀን ማስረጃ ይሆን
ባቸዋል» አላቸው።
12 ደቀመዛሙርቱም በየሥፍራው እየተዘ
ዋወሩ ያገኙአቸውን ሰዎች ሁሉ ኃጢአታ
ቸውን ተናዝዘው ወደ እግዚአብሔር እንዲ
መለሱ አስተማርዋቸው።
13 አያሌ ርኩሳን መናፍስትንም አወጡ፤
ዘይት እየቀቡም ብዙ ሕመምተኞችን
ፈወሱ።
14 የኢየሱስን ድንቅ ሥራዎችና ተአም
ራት ሕዝቡ በያለበት ያወራ ስለነበር ፥
ዝናው ከንጉሥ ሄሮድስ ጆሮ ደረሰ። ሄሮ
ድስ ስለ ኢየሱስ ሲሰማ ፥ መጥምቁ ዮሐንስ
ከሞት የተነሣ መሰለው። አንዳንድ ሰዎ
ችም ፥ «አዎን ፥ መጥምቁ ዮሐንስ ከሞት
ተነሥቶአል ይህንን ሁሉ ተአምር የሚያደ
ርገውም ስለዚህ ነው» አሉ። 15 አንዳን
ዶች፥ «ኤልያስ ነው» ሌሎች ደግሞ፥ «የቀ
ድሞዎቹን ነቢያት ይመስላል» ይሉ ነበር።
16 ንጉሥ ሄሮድስ ግን ፥ «የለም ፥ ይህ እኔ
አንገቱን አስቆርጬ ያስገደልሁት ዮሐንስ
ከሞት የተነሣ መሆን አለበት» አለ።
17-18 ሄሮድስ ፥ የወንድሙ የፊልጶስ
ሚስት የነበረችውን ሄሮድያዳን አግብቶ ስለ
ነበር ፥ የገዛ ወንድሙን ሚስት ማግባቱን
ዮሐንስ በይፋ በመቃወሙ ፥ ወታደሮቹን
ልኮ እሥር ቤት አስገብቶት ነበር። 19 ሄሮ
ድያዳ ቂም በቀሏን ለመወጣት ዮሐንስን
ለማስገደል ትመኝ ነበር። ነገር ግን ንጉሥ
ሄሮድስ በአሳቧ ካልተስማማ ምንም ማድ
ረግ እንደማትችል ታውቅ ነበር።
20 ሄሮድስ ዮሐንስ ቅንና ቅዱስ ሰው
መሆኑን ስለሚያውቅ ያከብረውና ክፉ ነገ
ርም እንዳይደርስበት ይንከባከበው ነበር።
በሌላ በኩል ደግሞ የዮሐንስን ንግግር ባደ
መጠ ቁጥር መንፈሱ ይታወክል። ቢሆንም
ትምህርቱን መስማት ይወድ ነበር።
21 ሄሮድስ የተወለደበትን ቀን ለማክበር
ትልቅ ድግስ ደግሶ የመንግሥት ሠራተኞ
ችን፥የጦር ሹማምንቶችንና የታወቁ የገሊላ
ነዋሪዎችን ወደ ቤተ መንግሥቱ ጠራ።
ሄሮድያዳም ያሰበችውን ተንኰል ለመፈ
ጸም ዕድል ያጋጠማት መሆኑ ተሰማት።
22-23 የሄሮድያዳ ልጅ ወደ ግብዣው
አዳራሽ ገብታ በመዝፈንና እስክስታ በመው
ረድ እንግዶቹን ሁሉ አስደሰተች። ሄሮድ
ስም ፥ «የምትፈልጊውን ነገር ጠይቂኝ።
የመንግሥቴን እኩሌታ እንኳን ቢሆን እሰጥ
ሻለሁ» አላት። 24 ልጅቱም ሄሮድስን ስለ
ምትጠይቀው ነገር እናቷን አማከረች። እና
ቷም «የዮሐንስን ራስ ይሰጠኝ ብለሽ
ጠይቂ» አለቻት። 25 ልጅቷም እንደተመከ
ረችው ፥ «የዮሐንስ ራስ በሳህን ተደርጎ አሁ
ኑኑ ይሰጠኝ» ብላ ጠየቀች።
26 ንጉሡ ሄሮድስ የልጅቱን ጥያቄ
ሲሰማ በጣም አዘነ። ይሁን እንጂ በእንግ
ዶቹ መካከል የገባላትን ቃል ማፍረስ አል
ቻለም። 27 ወዲያው ከወታደሮቹ አንዱን
ጠርቶ የዮሐንስን ራስ ቆርጦ እንዲያመጣ
አዘዘው። ወታደሩም ወደ ወህኒ ቤት ሄዶ
ዮሐንስን አረደው። 28 እንደ ታዘዘውም የዮ
ሐንስን ራስ በሳህን አድርጎ ለልጅቷ
ሰጣት። ልጅቷም ተቀብላ ወደ እናትዋ ይዛ
ሄደች።
29 የዮሐንስ ደቀመዛሙርትም የሆነውን
እንደ ሰሙ ሬሳውን ወስደው ቀበሩት።
30 በዚህ መካከል ሐዋርያት የተላኩበ
ትን ተግባር ፈጽመው ኢየሱስ ወደ ነበረ
በት ሥፍራ ተመለሱና ፥ በደረሱበት ሁሉ
ያደረጉትንና ያስተማሩትን በዝርዝር ነገ
ሩት።
31 እርሱም ፥ «ጥቂት እንድታርፉ ጸጥ
ወዳለ ሥፍራ እንሂድ» አላቸው። ምክንያ
ቱም ወደ እርሱ የሚመጡት ሰዎች ቊጥር



በጣም በመብዛቱ ለመብል እንኳን ጊዜ አል
ነበራቸውም። 32 ከዚያም በጀልባ ወደ
አንድ ሰዋራ ቦታ ሄዱ። 33 ነገር ግን ብዙ
ሰዎች የሄዱበትን አቅጣጫ ስላዩ በእግር
ሮጠው በመሄድ ቀድመው ጠበቁአቸው።
34 ኢየሱስ ከጀልባው ሲወርድ እንደተለመ
ደው ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ሲጠብቀው
ተመለከተ። እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች
ወዲያና ወዲህ በመንከራተታቸው አዘኔላ
ቸው። ሊያውቁት የሚገባቸውንም ብዙ
ነገር አስተማራቸው።
35-36 ወደ ማምሻው ግድም ደቀመዛሙ
ርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው ፥ «ጊዜው እየ
መሸ ነው። ያለንበት ቦታ በረሃ ነውና የሚ
በላ ነገር አይገኝበትም። ስለዚህ ሰዎቹ
በጊዜ በአካባቢው ወዳሉት መንደሮች
ሄደው ምግባቸውን እንዲፈልጉ አሰናብታ
ቸው» አሉት።
37 ኢየሱስ ግን ፥ «የሚበሉትን እናንተ
ስጡአቸው» አላቸው። እነርሱም ፥ «ለዚህ
ሁሉ ሰው ምግብ ለማቅረብ ብዙ ገንዘብ
ይጠይቃል» አሉት።
38 ኢየሱስም ፥ «ለመሆኑ ምን ያህል
ምግብ አላችሁ? እስቲ ሂዱና እዩ» አላ
ቸው። እነርሱም ያላቸውን ምግብ አይተው
ከተመለሱ በኋላ ፥ «አምስት ጥቢኛ ዳቦና
ሁለት ዓሣ ብቻ ነው ያለን» አሉት።
39-40 ኢየሱስም ሕዝቡን እንዲቀመጡ አደ
ረገ። ሕዝቡም በሃምሣና በመቶ እየተከፈለ
በለመለመው መስክ ላይ በተርታ ተቀመጠ።
41-42 ከዚያም አምስቱን ጥቢኛ ዳቦና
ሁለቱን ዓሣ ይዞ ፥ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ
ተመለከተ። ስለ ምግቡም ምስጋና ካቀረበ
በኋላም ዳቦውን ቆራርሶ ከዓሣው ጋር ደቀ
መዛሙርቱ ለሕዝቡ እንዲያድሉ ሰጣቸው።
ሰዎቹም እስኪጠግቡ ድረስ በሉ።
43-44 አምስቱን ጥቢኛ ዳቦና ዓሣ የበ
ሉት የወንዶች ቊጥር ብቻ አምስት ሺህ
ያህል ነበር። በልተው ከጠገቡ በኋላም ፥
አሥራ ሁለት ቅርጫት ፍርፋሪ ተሰበሰበ።
45 እርሱ ወደ ኋላ ቀረት ብሎ ሕዝቡን
ማሰናበት ስለ ነበረበት፥ደቀመዛሙርቱ ወዲ
ያውኑ በጀልባ ተሳፍረው ወደ ቤተሳይዳ
ሄደው እንዲጠብቁት አዘዛቸው። 46 ከዚያም
ለመጸለይ ከአንድ ኮረብታ ላይ ወጣ።
47-48 በምሽትም ላይ፥ኢየሱስ ብቻውን በኮ
ረብታው ላይ እንዳለ፥ደቀመዛሙርቱ የነበሩ
ባት ጀልባ ከባሕሩ መካከል ስትደርስ፥ኃይ
ለኛ ማዕበል ተነሥቶ ስለነበር ጀልባዋ እን
ዳትሰምጥባቸው ሲጨነቁና ለመቅዘፍ ሲታ
ገሉ አየ። ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ፥በባ
ሕሩ ላይ እየተራመደ ወደ እነርሱ መጣ።
49 በአጠገባቸው በውኃ ላይ እየተራመደ
ሲያልፍ ምትሀት ያዩ መሰላቸው።
50 ሁሉም በአንድ ላይ አይተውት ስለነበር
በድንጋጤ ጮኹ። በዚህን ጊዜም፤ «አይዞአ
ችሁ ፥ አትደንግጡ! እኔ ነኝ» አላቸው።
51 ኢየሱስም ጀልባው ውስጥ እንደገባ ማዕ
በሉ ጸጥ አለ። ደቀመዛሙርቱ ግን የሆነ
ውን ሁሉ ማስተዋል አቅቶአቸው ዝም
ብለው ተቀምጠው ነበር። 52 ባለፈው
ምሽት ምግቡን በመባረክ ያደረገው ተአ
ምር ትርጉም ስላልገባቸው፥ማንነቱን መረ
ዳትና ማመን ተሳናቸው።
53 ባሕሩን ተሻግረው ወደ ጌንሴሬጥ
ሲደርሱ ጀልባዋን ወደ ዳር አስጠግተው
አቆሙና ወረዱ። 54 በዚያን ሰዓት በአካባ
ቢው የነበሩት ሰዎች ኢየሱስን ለይተው ስላ
ወቁት 55 ወዲያው ወደየመንደሮቻቸው
ሮጠው ሄደው የኢየሱስን በአካባቢው መገ
ኘት ወሬ አሰራጩ። በሽተኞችንም በአል
ጋና በቃሬዛ እየተሸከሙ እርሱ ወዳለበት
አመጡ። 56 በመንደሮችና በከተሞች፥በባላገ
ርና በገበያ ቦታዎች ፥ በጠቅላላው ኢየሱስ
በደረሰበት ሥፍራ ሁሉ ፥ በሽተኞች በያለ
በት ተኝተው ይጠብቁት ነበር። አብዛኛ
ዎቹ የልብሱን ጫፍ እንኳ ለመዳሰስ እንዲ
ፈቅድላቸው ይለምኑት ነበር። የዳሰሱትም
ሁሉ ከያዛቸው ሕመም ይድኑ ነበር።

## ምዕራፍ 7

1 ፈሪሳውያንና አንዳንድ የአይሁድ ሃይ
ማኖት መምህራን ኢየሱስን ለመታዘብ ከኢ
የሩሳሌም ከተማ መጡ። 2 እነርሱም ከኢየ
ሱስ ደቀመዛሙርት መካከል አንዳንዶቹ
ምግብ ከመበላቱ በፊት መፈጸም የሚገባ
ውን የአይሁድ ሥርዓት የማይከተሉ መሆና
ቸውን ተመለከቱ። 3 የአይሁድ ሕዝብ፣በተ
ለይም ፈሪሳውያን ፥ ሲወርድ ሲዋረድ በመ
ጣው ወግና ሥርዓት መሠረት እጃቸውን
ሳይታጠቡ ምግብ አይቀምሱም ነበር። 4 እን
ዲሁም ገበያ ውለው ሲመለሱ ፥ እጃቸውን
ከማጽዳታቸው በፊት ምግብ አይነኩም
ነበር። አይሁዶች እስከ አሁን ድረስ የሚከ
ተልዋቸው ብዙ የቆዩ ወጎችና ልማዶች
አሏቸው። በተጨማሪም ለማሰሮ ፥ ለብርጭ
ቆና ለሳህን ጽዳት እንኳን የተለየ ሥርዓት
ነበራቸው።
5 ከኢየሩሳሌም የመጡት ፈሪሳውያንና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ኢየሱስን፣

«ደቀመዛሙርትህ የቆየውን የአባቶቻችንን
ወግና ሥርዓት በማፍረስ እጃቸውን ሳይታ
ጠቡ የሚበሉት ለምንድን ነው?» ሲሉ
ጠየቁት።
6-7 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው።
«እናንተ ግብዞች! ነቢዩ ኢሳይያስ፥ ‘ይህ
ሕዝብ ስለ እግዚአብሔር በአፉ ብዙ ያወ
ራል ፤ ልቡ ግን ከእምላኩ በጣም የራቀ
ነው። እግዚአብሔር ያላዘዘውንም የራሱን
ወግና ሥርዓት እያስተማረ በከንቱ ያመል
ካል’ ሲል ስለ እናንተ የተናገረው ትክክል
ነው። 8 እናንተም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ
ትታችሁ የራሳችሁን ወግና ሥርዓት ትከተ
ላላችሁ። 9 ወጋችሁንና ልማዳችሁን ለመጠ
በቅ ስትሉ እግዚአብሔር ያዘዘውን ሕግ ከን
ቱና ዋጋ ቢስ ታደርጉታላችሁ።
10 «ለምሳሌ ሙሴ፥ ‘አባትህንና እናት
ህን አክብር ፤ እናቱንና አባቱን የሰደበ
ይሙት–ቢቃ ይፈረድበት’ የሚል ትእዛዝ
ሰጥቶአችሁ ነበር። 11-12 እናንተ ግን፥ወላጆ
ቹን መርዳት ያለበት ሰው፥ ‘እናንተን መር
ዳት ስለማልችል አትቀየሙኝ። ምክንያቱም
ለእናንተ ያሰብኩትን ገንዘብ ለእግዚአብ
ሔር ሰጠሁ’ በማለት ችግረኛ ለሆኑ ወላ
ጆቹ እርዳታ ቢነፍግ ምንም አይወቀስበ
ትም እያላችሁ እንዳይረዳ ታግዱታላችሁ።
13 በዚህ ሁኔታ የራሳችሁን ወግና ሥርዓት
ለመጠበቅ ስትሉ የእግዚአብሔርን ቃል
ትሽራላችሁ። ይህንንም የመሰለ ብዙ ሌላም
ነገር ታደርጋላችሁ።» 14 ኢየሱስ ይህንን
ብሎ ሲያበቃ፥የተሰበሰቡትን ሰዎች ወደ
እርሱ ጠርቶ፥ «ስሙኝ! በማስተዋልም
አድምጡኝ!» አለና ነገሩን በመቀጠል፥
15-16 «የምትበሉት ምግብ ነፍሳችሁን አያረ
ክሰውም። የሚያረክሳችሁ ነገር ቢኖር በል
ባችሁ ውስጥ የምታውጠነጥኑት አሳብና
በአንደበታችሁ የምትናገሩት ቃል ነው»
አላቸው። 17 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከሕዝቡ
ለየት ለማለት ወደ ቤት ገባ። ደቀመዛሙር
ቱም ቀደም ሲል የተናገረውን ቃል ትርጉ
ሙን እንዲያብራራላቸው ጠየቁት።
18-19 እርሱም፥ «እናንተም ይህንን ማስተ
ዋል አትችሉምን? ሰው የሚመገበው
ምግብ ነፍሱን ሊያረክሰው እንደማይችል
አታውቁምን? ሰው የሚመገበው ምግብ
በሆድ ዕቃው ተላልፎ ወደ ውጭ ይወጣል
እንጂ ወደ ልቡ አይደርስም» በማለት መለ
ሰላቸው። (በዚህ ንግግሩም ምግብ ሁሉ
ንጹሕ መሆኑን አረጋገጠአል።)
20 ቀጥሎም፥ «ሰውን የሚያረክሰው
ከልቡ የሚመነጨው ክፉ አሳቡ ነው።
21 ስርቆት፥ሰው መግደል፥ዝሙት፥ 22 የሌላ
ሰው የሆነውን ነገር መመኘት፥ክፋት፥አታ
ላይነት፥ሴሰኝነት፥ምቀኝነት፥ሐሜት፥ትዕ
ቢት፥ስንፍና እነዚህ ክፉ ነገሮች ሁሉ
ከሰው ልብ ይመነጫሉ። 23 ሰውን የሚያረክ
ሱትና በእግዚአብሔርም ፊት የሚያዋር
ዱት እንዲህ ያሉት ክፉ አሳቦች ናቸው።»
24 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ገሊላን ትቶ ወደ
ጢሮስና ሲዶና አካባቢ ሄደ። እዚያም
እንደ ደረሰ ወደ አንድ ቤት ገብቶ መምጣ
ቱን ማንም እንዳያውቅ ፈለገ። ነገር ግን
ወደዚያ የመምጣቱ ወሬ፥እንደተለመደው
በከተማው ሁሉ በፍጥነት ተሰራጨ።
25 የኢየሱስን ዝና ብዙ ጊዜ የሰማች አን
ዲት ሴት መጥታ እግሩ ሥር ወደቀች።
26 ይህችም የሶርያና የፊንቄ ተወላጅና የአ
ሕዛብ ወገን የሆነች ሴት፥ልጅዋን ከያዛት
ርኩስ መንፈስ እንዲያድንላት ኢየሱስን
ለመነችው። 27 እርሱ ግን፥ «አስቀድሜ
የራሴ ወገን የሆኑትን አይሁድ መርዳት አለ
ብኝ ፤ የልጆችን ምግብ አንሥቶ ለውሾች
መጣል አይገባም» አላት።
28 ሴቲቱም፥ «ጌታዬ፥ያልከው ትክክል
ነው። ግን እኮ የውሻ ቡችሎችም ከገበታ
ሥር ሆነው ከልጆች የሚተርፈውን ፍርፋሪ
ይበላሉ» አለች። 29 ኢየሱስም፥ «ጥሩ መል
ሰሻል ፤ በሰጠሽው መልስ መሠረት ልጅሽን
ፈውሼልሻለሁ። ርኩሱ መንፈስ ልጅሽን
ለቅቆ ስለ ወጣ ወደ ቤትሽ በሰላም ሂጂ»
አላት።
30 ወደ ቤቷ ስትመለስ ልጅዋ ርኩሱ
መንፈስ ወጥቶላት በሰላም ተኝታ አገኘ
ቻት።
31 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ጢሮስን ትቶ
ወደ ሲዶና በማለፍ፥በ ‘አሥሩ ከተሞች’
በኩል ወደ ገሊላ ባሕር ተመልሶ ሄደ።
32 ከዚያም እንደደረሰ አንድ መስማትና
መናገር የማይችል በሽተኛ ሰው አምጥተው
እጁን ጭኖ እንዲፈውሰው ለመኑት።
33 ኢየሱስም በሽተኛውን ከሕዝቡ መካከል
ለይቶ ወሰደውና ጣቶቹን በጆሮዎቹ ውስጥ
አስገባ። ምራቁንም እንትፍ ብሎ በጣቱ የሰ
ውየውን ምላስ ዳሰሰና፥ 34 ወደ ሰማይ ቀና
ብሎ በመንፈስ ቃተተ። ከዚያም፥ «ተከ
ፈት!» ብሎ አዘዘ። 35 ወዲያውም ሰውየው
በትክክል መስማትና አጥርቶም መናገር
ቻለ።
36 ኢየሱስም ተአምራቱን ያዩትን
ሰዎች፥ለማንም እንዳያወሩ አስጠንቀቃ



ቸው። ይሁን እንጂ፥ኢየሱስ የሠራው ተአ
ምር ሰዎቹን ከልክ ያለፈ ስላስደነቃቸው፥
የተሰጣቸው ማስጠንቀቂያ የሰሙትንና ያዩ
ትን ከማውራት አላገዳቸውም። 37 በደረሰ
በት ሁሉ፥ «የሚያደርገው ነገር ሁሉ አስገ
ራሚ ነው። ሌላው ቀርቶ፥ደንቆሮዎች እን
ዲሰሙ፥ድዳዎችም አጥርተው እንዲናገሩ
ያደርጋል» ይሉ ነበር።

## ምዕራፍ 8

1 በሌላ ቀን ደግሞ፥ቁጥራቸው እጅግ
ብዙ የሆኑ ሰዎች ተሰበሰቡ የሚበሉት አል
ነበራቸውምና ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን
ጠርቶ፥ 2 «እነዚህ ሰዎች ያሳዝኑኛል። እን
ደምታውቁት ባለፉት ሦስት ቀናት እዚሁ
ነበሩ። አሁን ደግሞ የሚበሉት ነገር የላቸ
ውም። 3 የሚበላ ሳልሰጣቸው ባሰናብታ
ቸው፥በተለይ አንዳንዶቹ ከሩቅ ሥፍራ
የመጡ ስለሆነ፥በመንገድ ላይ ጠኔ ይጥላቸ
ዋል» አላቸው።
4 ደቀመዛሙርቱም፥ «ታዲያ፥በዚህ በረሃ
ለዚህ ሁሉ ሰው ምግብ ከየት ማግኘት ይቻ
ላል?» ሲሉ ጠየቁት። 5 ኢየሱስም፥ «ስንት
ጥቢኛ ዳቦ አላችሁ?» አላቸው። እነሱም፥
«ሰባት» አሉት።
6 ኢየሱስ ሰዎቹን እንዲቀመጡ አደረገ።
ሰባቱን ጥቢኛ ዳቦ ተቀብሎ እግዚአብሔርን
ካመሰገነ በኋላ እየቆራረሰ ለሕዝቡ እንዲያ
ድሉ ለደቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። ደቀመዛ
ሙርቱም ለሰዎቹ አደሉ። 7 እንደዚሁም
ጥቂት ዓሣዎችን ስላቀረቡለት እነርሱንም
ተቀብሎ ባረከና፥ለሰዎቹ እንዲያዳርሱ ለደ
ቀመዛሙርቱ ሰጣቸው። 8-9 ሰዎቹም እስኪ
ጠግቡ ድረስ በሉ። የሕዝቡም ብዛት አራት
ሺህ ያህል ነበር። ከበሉ በኋላ ሰባት ቅር
ጫት ሙሉ ፍርፋሪ ተሰበሰበ። ከዚያም
ወደየቤታቸው እንዲሄዱ አሰናበታቸው።
10 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ
ጋር በጀልባ ዳልማኑታ ወደሚባለው መን
ደር ሄደ።
11 የዳልማኑታ መንደር ፈሪሳውያንም፥
የኢየሱስን መምጣት እንደ ሰሙ፥ሊከራከ
ሩት ፈልገው እርሱ ወዳለበት መጡ። ሊፈ
ትኑትም በማሰብ፥ «እስቲ አንድ አስደናቂ
ተአምር አሳየን? በሰማይ ላይ አንድ ነገር
እንዲሆን ብታደርግ እኛም በአንተ እናምን
ነበር» አሉት። 12 ኢየሱስ ጥያቄአቸው
አዝኖ፥ «ለመሆኑ ይህ ትውልድ ልዩ ተአ
ምር ማየት ለምን ይፈልጋል? እውነቱን
ልንገራችሁ፥ለዚህ ትውልድ ምንም ምል
ክት አይሰጠውም» አላቸው።
13 ሰዎቹን ከዚያው እንዳሉ ትቷቸው
በጀልባ ተሳፍሮ ወደ ባሕሩ ማዶ ተሻገረ።
14 ነገር ግን ደቀመዛሙርቱ ጉዞ ከመጀመራ
ቸው በፊት ለስንቅ የሚሆን ምግብ አለመያ
ዛቸውን ተገነዘቡ። ጀልባው ውስጥ ከአንድ
ጥቢኛ ዳቦ ሌላ አልነበረም። 15 ባሕሩን በማ
ቋረጥ ላይ ሳሉ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፥
«ከንጉሥ ሄሮድስና ከፈሪሳውያን እርሾ
ተጠንቀቁ!» አላቸው። 16 እነርሱም፥ «ምን
ማለቱ ይሆን?» በማለት እርስ በእርሳቸው
ተጠያየቁ። በመጨረሻም፥ «ይህን ያለው
ምናልባት ስንቅ መያዝ ስለረሳን ይሆናል»
ብለው አሰቡ። 17 ኢየሱስ ግን፥የተነጋገሩ
ትን በመረዳቱ፥ «እኔ ያልኩት ስንቅ ስላለ
መያዛችሁ አይደለም። ለምን የምናገረውን
መረዳት ያዳግታችኋል? አእምሮአችሁ እስ
ከዚህ ደንዝዟል? 18 የማያዩ ዓይኖች፥የማይ
ሰሙስ ጆሮች ነው ያላችሁ? እንዲያው
ለመሆኑ ምንም ነገር አታስታውሱምን?»
አላቸው።
19 «አምስቱን ጥቢኛ ዳቦ ለአምስት ሺህ
ሰዎች በመገብኩ ጊዜ ስንት ቅርጫት ፍር
ፋሪ አነሣችሁ?» ብሎ ጠየቃቸው። እነር
ሱም፥ «አሥራ ሁለት ቅርጫት ሙሉ»
በማለት መለሱለት። 20 «ደግሞስ ሰባቱን
ጥቢኛ ዳቦ ለአራት ሺህ ሰዎች በመገብኩ
ጊዜ ስንት ቅርጫት ፍርፋሪ አነሣችሁ?»
ሲል እንደገና ጠየቃቸው። እነርሱም፥
«ሰባት ቅርጫት ሙሉ» አሉት።
21 «ታዲያ ስንቅ ባለመያዛችሁ የምጨነቅ
ይመስላችኋል?» አላቸው።
22 ወደ ቤተሳይዳ በደረሱ ጊዜ ሰዎች
አንድ ዓይነ ስውር ወደ ኢየሱስ አምጥተው
እንዲዳስሰውና እንዲፈውሰው ለመኑት።
23 እርሱም የዓይነ ስውሩን እጅ ይዞ እየመ
ራው ከመንደሩ ወጣ ካደረገው በኋላ ምራ
ቁን በዓይኖቹ ላይ እንትፍ ብሎ በእጁ ዳሰ
ሰውና፥ «አሁን የምታየው ነገር አለን?»
ሲል ጠየቀው። 24 ዓይነ ስውሩም ዙሪያውን
ከተመለከተ በኋላ፥ «አዎ፥ሰዎች ይታዩ
ኛል፤ነገር ግን አጥርቼ አላያቸውም። እንደ
ዛፍ ግንድ የሚራመዱ ይመስለኛል» አለ።
25 ኢየሱስ በድጋሚ እጁን በሰውየው ዓይ
ኖች ላይ ጫነበት። ሰውየውም ከዕውርነቱ
ፍጹም ዳነ። በዙሪያው ያለውን ነገር ሁሉ
አይቶ አለጠግብ አለ።
26 ከዚያም ኢየሱስ፥ «ወደ ቤተሰቦችህ
ሂድ እንጂ ወደ መንደሩ አትመለስ» ብሎ
አሰናበተው።

27ከዚህ በኋላ ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ
የገሊላን ሀገር ትተው በፊልጶስ ቂሣርያ
ወደሚገኙት መንደሮች ሄዱ። በመንገድ
ላይ እያሉም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ፣
«ሰዎች ስለ እኔ ምን ያወራሉ? ለመሆኑስ
ማን ይሉኛል?» ሲል ጠየቃቸው። 28እነር
ሱም ፣ «'አንዳንዶቹ መጥምቁ ዮሐንስ
ነው ፤ ሌሎች ደግሞ ኤልያስ ነው ፤ የቀሩት
ደግሞ ከነቢያት አንዱ ነው' ይሉሃል»
አሉት። 29እርሱም፣ «እናንተስ ማን ትሉኛ
ላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው። ጴጥሮስም ፣
«አንተ መሲሕ ክርስቶስ ነህ» አለ። 30ኢየ
ሱስም፣ «በሉ ይህንን ለማንም እንዳታወሩ»
በማለት በጥብቅ አስጠነቀቃቸው።

31ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደፊት ስለሚደ
ርስበት ከባድ መከራ ፣ እንዲሁም ከአገር
ሽማግሌዎች ፣ ከሊቀ ካህናቱና ከአይሁድ
ሃይማኖት መምህራን ስለሚደርስበት ተቃ
ውሞ ፣ ይዘውም እንደሚገድሉትና ከሦስት
ቀናት በኋላ ከሞት እንደሚነሣ በማብራ
ራት ገለጸላቸው።

32ይህንን በግልጽ ካስረዳቸው በኋላ ፣
ጴጥሮስ ኢየሱስን ለብቻው ገለል አድርጎ ፣
«አሁን የተናገርከው ነገር ከአንተ አፍ
መውጣት አልነበረበትም» ብሎ ገሠጸው።

33ኢየሱስ ዘወር ብሎ ደቀመዛሙርቱን
ተመለከተና ጴጥሮስን ፣ «ከእኔ ራቅ አንተ
ሰይጣን! አስተሳሰብህ ከእግዚአብሔር
ፈቃድ ጋር ሳይሆን ከሰው ፈቃድ ጋር የሠ
መረ ነው» ሲል ገሠጸው።

34ቀጥሎም ደቀመዛሙርቱንና ሕዝቡን
ጠርቶ እንዲህ አላቸው። «ከእናንተ ማንም
እኔን ሊከተል ቢፈልግ የራሱን ምቾትና
ደስታ ትቶ መስቀሉን ተሸክሞ ይከተለኝ።
35ነፍሱን የሙጥኝ ብሎ የሚይዛት ያጣ
ታል ፤ ነገር ግን ነፍሱን ለእኔና ለወንጌል
ሲል አሳልፎ የሚሰጥ ይታደጋታል።

36«ደግሞስ ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተ
ርፍ ፣ ነፍሱን ግን ቢያጣ ምን ጥቅም ያገ
ኛል? 37ለመሆኑ ለሰው ልጅ ከነፍሱ የበ
ለጠ ዋጋ ያለው ነገር ምን አለ? 38በዚህ
ከሃዲዎችና ኃጢአተኞች በበዙበት ዘመን
በእኔና በወንጌል ቃል በሚያፍር ፣ እኔም
የሰው ልጅ ፣ በአባቱ ክብርና በቅዱሳን መላ
እክት ታጅቤ ስመጣ አፍርበታለሁ።»

## ምዕራፍ 9

1ቀጥሎም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ፣
«እዚህ ካላችሁት መካከል አንዳንዶቻችሁ
በሕይወት ኖራችሁ የእግዚአብሔር መንግ
ሥት በታላቅ ኃይል ሲመጣ ታያላችሁ»
አላቸው። 2ከስድስት ቀን በኋላ ኢየሱስ
ጴጥሮስን ፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን ይዞ ወደ
አንድ ተራራ ጫፍ ላይ ወጣ። እዚያም
ብቻቸውን ነበሩ። ድንገትም ፊቱ በግርማ
ሞገስ ተሞልቶ ማብራት ጀመረ። 3ልብ
ሱም ከነጣቱ የተነሣ ከልክ ያለፈ የሚያንጸ
ባርቅ ሆነ። 4በዚያን ጊዜ ኤልያስና ሙሴ
ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ለሦስቱም ደቀመዛ
ሙርት ታዩአቸው።

5ጴጥሮስም ፣ «መምህር ሆይ ፣ ይህስ
ዕፁብ ድንቅ ነው። ከዚሁ እንድንኖር አንድ
ለአንተ ፣ አንድ ለኤልያስ፣ አንድ ለሙሴ የሚ
ሆን ሦስት ዳሶች እንሥራ» አለ።

6ጴጥሮስ ይህንን ያለው የሚያደርገው
ነገር ስለጠፋው ብቻ ነበር። ባዩት ነገር
ሦስቱም ደቀመዛሙርት በጣም ደንግጠው
ነበርና።

7ጴጥሮስ ንግግሩን ሳይጨርስ፣ ሥፍራው
በደመና ተጋረደ። የፀሐይዋም ብርሃን ተከ
ለለ። ከደመናውም ውስጥ ፣ «ይህ የምወ
ደው ልጄ ነው ፤ እርሱን ስሙት!» የሚል
ድምፅ ተሰማ።

8ወዲያውም ዘወር ብለው አካባቢያቸ
ውን ቢመለከቱ፣ ሙሴና ኤልያስ ተሰውረው
ኢየሱስ ብቻ አብሮአቸው መቅረቱን ተገነ
ዘቡ።

9ከተራራው በመውረድ ላይ ሳሉ ኢየ
ሱስ ፣ ያዩትን ነገር ከሞት ከመነሣቱ በፊት
ለማንም እንዳያወሩ አስጠነቀቃቸው።
10እነርሱም እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ ፣
«'ከሞት መነሣት' ማለት ምን ማለት
ይሆን?» ከመባባል በስተቀር ፣ ያዩትን ለማ
ንም አላወሩም።

11የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን ብዙ
ጊዜ ከመሲሑ መምጣት በፊት ኤልያስ
ቀድሞ መምጣት አለበት እያሉ ያስተምሩ
ስለ ነበር ፣ ስለዚህ ጉዳይ እንዲያስረዳቸው
ደቀመዛሙርቱ ኢየሱስን ጠየቁት።
12-13ኢየሱስም ፣ «እርግጥ ነው ኤልያስ
ቀድሞ መጥቶ ሁሉንም ነገር እንደሚሆን
አድርጎ ማዘጋጀት አለበት። እንደ እውነቱ
ከሆነ ግን፣ ኤልያስ ገና ድሮ መጥቷል። ነቢ
ያት እንደተነበዩትም አሰቃቂ መከራ ተቀብ
ሏል» ሲል መለሰላቸው። ቀጥሎም ፣ «ነቢ
ያት መሲሑ ሲመጣ መከራ ይቀበላል ፤ በሰ
ዎችም ዘንድ ይናቃል ብለው ሲጽፉ ምን
ማለታቸው ነው?» ብሎ ጠየቃቸው።

14ከተራራውም ሲወርዱ ዘጠኙን ደቀመ
ዛሙርት ብዙ ሕዝብ ከብቦአቸው ፣ የአይ



ሁድ ሃይማኖት መምህራን በጥያቄ ሲያጣድ
ፏቸው አገኟቸው። 15ሕዝቡ ኢየሱስ ወደ
እነርሱ ሲመጣ በመገረምና በአድናቆት አዩ
ትና ወደ እርሱ ሮጠው እጅ ነሱት። 16ኢየ
ሱስም ፣ «ክርክሩ ምንድነው?» ሲል
ጠየቀ። 17-18ከሕዝቡ መካከል አንድ ሰው፣
«መምህር ሆይ፣ ልጄ ርኩስ መንፈስ ስላደረ
በትና መናገርም ስለማይችል እንድትፈው
ሰው ወደ አንተ አምጥቼው ነበር። በሽታው
በሚነሣበት ጊዜ ርኩስ መንፈስ ከመሬት
ላይ ይጥለዋል ፤ አረፋም እያስደፈቀው ጥር
ሱን ያፋጫል ፤ ሰውነቱም ድርቅ ይላል።
ልጄን ወደ ደቀመዛሙርትህ ብወስደውም፣
ርኩሱን መንፈስ ሊያወጡት አልቻሉም»
አለው።

19ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ፣ «እምነ
ታችሁ ምንኛ ትንሽ ነው? ለመሆኑ እስከ
መቼ ድረስ ከእናንተ ጋር ብቆይ ነው እም
ነት የሚኖራችሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋ
ለሁ? በሉ ልጁን ወደ እኔ አምጡት!» አላ
ቸው።

20ልጁን ወደ ኢየሱስ እንዳቀረቡት ፣
ርኩሱ መንፈስ አንዘፈዘፈው። ከዚያም
መሬት ላይ ጣለው ፤ ካወራጨው በኋላም
አረፋ አስደፈቀው። 21ኢየሱስ ፣ «እንዲህ
ማድረግ ከጀመረው ስንት ጊዜው ነው?»
ሲል አባትየውን ጠየቀ። አባትየውም ፣
«ከሕፃንነቱ ጀምሮ እንዲህ ያደርገዋል።
22ሕመሙ ሲነሣበት ርኩሱ መንፈስ ሊገድ
ለው እየፈለገ አንዴ እሳት ላይ አንዴ
ደግሞ ውኃ ላይ ይጥለዋል። እባክህን የምት
ችል ከሆነ አንድ ነገር አድርግልን» ሲል
ለመነው። 23ኢየሱስም ፣ «ብትችል ለምን
ትለኛለህ? እምነት ካለህ ሁሉም ነገር ይቻ
ላል» አለው። 24አባትየውም መልሶ ፣
«ማመንስ አምናለሁ ፤ ነገር ግን ጥርጣሬዬን
አስወግድልኝ!» አለ።

25ኢየሱስም ሕዝቡ ወደ እነርሱ በብ
ዛት መምጣቱን ሲያይ ርኩሱን መንፈስ ፣
«አንተ ድዳና ደንቆሮ መንፈስ ይህን ልጅ
ለቅቀህ ውጣ! ሁለተኛም ተመልሰህ እንዳ
ትገባበት አዝዤሃለሁ!» ሲል ገሠጸው።
26ርኩሱም መንፈስ ልጁን ካመራጨውና
ካስጮኸው በኋላ ለቅቆት ወጣ። ልጁም
እንደ ሞተ ሰው ተዘረረ፤ ሰዎችም ይህን አይ
ተው ፣ «ልጁ ሞቶአል!» እያሉ አንሾካ
ሾኩ። 27ኢየሱስ ግን የልጁን እጅ ይዞ አስ
ነሣው ፤ ልጁም ጤነኛ ሆነ። 28ኢየሱስ ቤት
ውስጥ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ብቻ እንዳለ ፣
«ለመሆኑ ያንን ርኩስ መንፈስ እኛ ከልጁ
ማስወጣት ያልቻልነው ለምንድን ነው?»
ሲሉ ጠየቁት።

29እርሱም ፣ «የዚህ ዓይነቱ ርኩስ መን
ፈስ ሊወጣ የሚችለው በጾምና በጸሎት
ነው» ሲል መለሰላቸው። 30-31ከዚህ በኋላ
ያንን አካባቢ ትተው በገሊላ በኩል አድር
ገው ሄዱ። ኢየሱስም ከደቀመዛሙርቱ ጋር
ብቻ ሆኖ ሊያስተምራቸው ይፈልግ ስለነ
በር ያሉበትን ቦታ ማንም ሰው እንዲያውቅ
አልፈለገም። ሲያስተምራቸውም ፣ «እኔ
የሰው ልጅ ፣ በሰዎች ተይዤ ከተገደልኩ
በኋላ በሦስተኛው ቀን እነሣለሁ» አላ
ቸው። 32ደቀመዛሙርቱም የተናገረው አል
ገባቸውም። ጠይቀው መረዳቱንም ፈሩ።
33ከዚያም ወደ ቅፍርናሆም ከተማ መጡ።
ወደ ማረፊያ ቤታቸው ከገቡ በኋላ ፣ ኢየ
ሱስ ፣ «በመንገድ ላይ ሳለን ትከራከሩበት
የነበረው ጉዳይ ምን ነበር?» ሲል ጠየቃ
ቸው። 34እነርሱም ይከራከሩ የነበሩት 'እኔ
እበልጥ እኔ እበልጥ' እያሉ ስለነበር ይህንኑ
ለኢየሱስ መንገር አሳፈራቸው።

35እርሱም ከተቀመጠ በኋላ ደቀመዛሙ
ርቱን ጠርቶ ፣ «ከመካከላችሁ ከሁሉ መብ
ለጥ የሚፈልግ ቢኖር ከሁሉ አነስተኛ በመ
ሆን ሁሉንም ያገልግል» አለ። 36ከዚያም
አንድ ሕፃን ልጅ አምጥቶ በመካከላቸው
አቆመ ፤ አቅፎም እንዲህ አላቸው ፣ 37«እን
ደዚህ ያለውን ሕፃን በስሜ የሚቀበል ፣ እኔን
ይቀበላል ፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝን አባ
ቴን ይቀበላል።»

38በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ፣ «መምህር ሆይ ፣
አንድ ሰው በስምህ አጋንንት ሲያወጣ አየ
ነው። እንደ እኛም ስለማይከተልህ ፣ ሁለተኛ
በስምህ አጋንንት ከሰው እንዳያስወጣ ከለከ
ልነው» አለ።

39ኢየሱስም ፣ «ማንም በስሜ አጋንንትን
ሊያወጣ ከቻለ ፣ ወዲያው ተመልሶ ተቃዋ
ሚዬ ስለማይሆን አትከልክሉት። 40የማይቃ
ወመን አጋራችን ነው። 41ማንም ሰው የእኔ
ተከታዮች በመሆናችሁ ምክንያት አንድ
ብርጭቆ ውኃ እንኳን ቢሰጣችሁ ዋጋውን
አያጣም። 42በሌላ በኩል ደግሞ ፣ ማንም
ሰው በእኔ ከሚያምኑት ከእነዚህ ታናናሾች
አንዱን ከእምነቱ እንዲሰናከል ምክንያት
ከሚሆነው ፣ ከባድ የወፍጮ ድንጋይ በአን
ገቱ ላይ ታሥሮ ወደ ጥልቅ ባሕር ቢጣል
ይሻለዋል።

43-44«ስለዚህ እጅህ ኃጢአት እንድት
ሠራ ካደረገህ ፣ እጅህን ያሳተውን የልብህን
ክፉ አሳብ ከአንተ አስወግድ ፤ ከልብህ ክፉ

ምኞት ጋር ኖረህ እሳቱ ወደማይጠፋበት
ወደ ገሃነም ከመጣል፣የልብህን ክፉ አሳብ
አስወግደህ ወደ ዘላለም ሕይወት መግባት
ይሻልሃል። 45-46 እግርህም ወደ ክፉ ቦታ
ከመራህ፣እግርህን ያሳተውን የልብህን ክፉ
አሳብ ቆርጠህ ጣለው። ከክፉ አሳብህ ጋር
ኖረህ ወደ ገሃነም ከመውረድ ይልቅ ከክፉ
ልብ ነፃ ሆነህ ወደ ዘላለም ሕይወት መግ
ባት ይሻልሃል።

47-48 «ዓይንህም ወደ ኃጢአት ከሳበህ፣
ዓይንህን ያሳተውን የልብህን ክፉ ምኞት
አውጣና ጣለው። ከልብህ ክፉ ምኞት ጋር
የዘላለም ሥቃይ ወዳለበት ገሃነም ከምት
ጣል፣ክፉ ምኞትህን አስወግደህ ወደ እግዚ
አብሔር መንግሥት መግባት ይሻልሃል።
49 መሥዋዕት ሁሉ በጨው እንደሚቀ
መም፣ የሰው ሕይወትም እንዲሁ በእሳት
ይቀመማል።

50 «ጨው መልካም ነገር ነው፣ነገር ግን
ጨው የጨውነቱን ጠባይ ካጣ፣ ምግብን
የማያጣፍጥና እንዳይበላሽም የማይከላከል
ይሆናል። እናንተም ለዛና ጣዕማችሁን ያጣ
ችሁ አትሁኑ። እርስ በእርሳችሁም በሰላም
ኑሩ።»

## ምዕራፍ 10

1 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከቅፍርናሆም ተን
ሥቶ ወደ ደቡባዊ የይሁዳ ክፍልና፣ከዮርዳ
ኖስ ወንዝ በስተምሥራቅ በኩል ወደሚገ
ኘው ሥፍራ ሄደ። ከዚያም ሲደርስ እንደ
ወትሮው ብዙ ሕዝብ ተሰበሰበ። እርሱም
እንደተለመደው ያስተምራቸው ጀመር።
2 በዚህ ጊዜ ከፈሪሳውያን መካከል ጥቂቶቹ
ሊያጠምዱት ፈልገው፣ «ለመሆኑ መፋታት
ተፈቅዷልን?» ሲሉ ጠየቁት።

3 ኢየሱስም፣ «ስለ ፍቺ ጉዳይ ሙሴ
ምን አዘዚል?» በማለት መልሶ ጠየቃ
ቸው።

4 እነርሱም፣ «ሙሴማ፣ ባል ሚስቱን
ሲፈታ፣የፍቺ ወረቀቷን ይስጣት ብሎ ፈቀ
ዷል» አሉት።

5-7 ኢየሱስም፣ «ሙሴ ይህንን ለምን እን
ዳለ ታውቃላችሁ? ምክንያቱን እኔ ልንገራ
ችሁ። ሙሴ ይህንን የተናገረው የልባችሁን
ድንዳኔነት አይቶ እንጂ፣ የእግዚአብሔር
ፈቃድ እንዲህ ሆኖ አይደለም። እግዚአብ
ሔር ከመጀመሪያው አንሥቶ ወንድና ሴት
በጋብቻ ተጣምረው ሳይለያዩ እንዲኖሩ አደ
ረገ። ስለዚህ ሰው እናትና አባቱን ትቶ ከሚ
ስቱ ጋር ይጣመራል። 8 እነርሱም ሁለት
መሆናቸው ይቀርና አንድ አካል ይሆናሉ።
9 ስለዚህ እግዚአብሔር ራሱ ያጣመራቸውን
ማንም ሰው ሊለያያቸው አይገባም» አላ
ቸው።

10 ቆየት ብሎ፣ቤት ውስጥ ከደቀመዛሙ
ርቱ ጋር ብቻ ሳለ፣ስለ ፍቺው ጉዳይ እንደ
ገና ጠየቁት።

11 ኢየሱስም እንደሚከተለው አብራራላ
ቸው፤ «አንድ ሰው ሚስቱን ፈትቶ ሌላ
ሴት ቢያገባ በሚስቱ ላይ አመነዘረ ማለት
ነው። 12 እንደዚሁም ባሏን ፈትታ ሌላ
ወንድ የምታገባ ሴት አመነዘረች ማለት
ነው።»

13 አንድ ጊዜ፣እናቶች ሕፃናት ልጆቻቸ
ውን እንዲዳስስላቸውና እንዲባርክላቸው
ወደ ኢየሱስ አመጡ። ደቀመዛሙርቱ ግን
በሚረባውም በማይረባውም ጉዳይ ኢየሱስን
እንዳያስቸግሩት ሰላሰቡ ከለከሉዋቸው።

14 ኢየሱስ ግን ደቀመዛሙርቱ ያደረጉ
ትን አይቶ በማዘን እንዲህ አላቸው፣ «ሕፃ
ናት ወደ እኔ ይምጡ፤አትከልክሉዋቸው።
የእግዚአብሔር መንግሥት የተዘጋጀው
እንደ እነርሱ ላሉት ስለሆነ አታባርሩዋ
ቸው። 15 እንዲያውም፣ማንም ሰው የእግዚ
አብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን ካልተቀ
በለ ወደ መንግሥተ ሰማይ መግባት ፍጹም
አይችልም።»

16 ከዚያም ሕፃናቱን አንድ በአንድ አቀ
ፉቸው፤እጁንም ጭኖ ባረካቸው።

17 ወደሌላ ቦታ ሊሄድ ሲል አንድ ሰው
ወደ እርሱ ሮጦ በመቅረብ ሰገደለትና፣
«ደጉ መምህር ሆይ፣ የዘላለም ሕይወት
ለመውረስ ምን ማድረግ ይኖርብኛል?»
ሲል ጠየቀው።

18 ኢየሱስም፣ «ለምን ደግ ትለኛለህ?
ደግ እግዚአብሔር ብቻ ነው» አለውና ለጥ
ያቄው መልስ ለመስጠት፣ 19 «አትግደል፣
አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በውሸት አትመስ
ክር፣ አታታልል፣ አባትህንና እናትህን አክ
ብር የሚሉትን ትእዛዛት ታውቅ የለምን?»
አለው።

20 ሰውየውም፣ «ከእነዚህ ከዘረዘርካቸው
ትእዛዛት ውስጥ አንዱን እንኳን አፍርሼ
አላውቅም» አለ። 21 ኢየሱስ ሰውየውን በፍ
ቅር ዓይን ተመለከተውና፣ «እንግዲያው
አንድ ነገር ብቻ ይቀርሃል፤ያለህን ንብረት
ሁሉ ሽጠህ ገንዘቡን ለድሆች ስጥ። ዋጋህን
በሰማይ ታገኛለህ፤ከዚያም መጥተህ ተከተ
ለኝ» አለው።

22 ሰውየው በጣም ሀብታም ስለ ነበር



ይህንን ሲሰማ ፊቱ በኀዘን ጠቆረ፤እየተከ
ዘም ትቶአቸው ሄደ።

23 ኢየሱስም ሰውየውን በዓይኑ ተከተ
ለው። ወደ ደቀመዛሙርቱ ዞሮ ብሎ፣
«ለሀብታም ሰው መንግሥተ ሰማይ መግባት
በጣም ከባድ ነው!» አለ።

24 የተናገረው ቃል ደቀመዛሙርቱን አስ
ደነቃቸው። ኢየሱስ ግን መልሶ፣ «ለሀብታ
ሞች መንግሥተ ሰማይ መግባት ምንኛ
ከባድ ነው! 25 ሀብታም ሰው መንግሥተ
ሰማይ ከሚገባ፣ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾ
ልክ ይቀላል» አላቸው።

26 ደቀመዛሙርቱም እንደገና የባሰ ተገረ
ሙና፣ «ታዲያ በዚህ ሁኔታ ማን ሊድን
ይችላል?» ተባባሉ።

27 ኢየሱስ ትኩር ብሎ እየተመለከታ
ቸው፣ «ይህ በእግዚአብሔር እንጂ በሰው
ዘንድ ፍጹም አይቻልም። ለእግዚአብሔር
ግን የሚሳነው ነገር የለም» አላቸው።

28 በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ፣ «እነሆ እኛ
ሁሉን ነገር ትተን ተከትለንሃል» አለው።

29 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰ፤
«አንድ ነገር ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። ስለ
እኔ ፍቅርና ወንጌልን ለሰዎች ለማዳረስ
ብሎ ቤቱን፣ወንድሞቹን፣እኅቶቹን፣እናትና
አባቱን፣ ልጆቹን ወይም ንብረቱን ያጣ
30 ማንኛውም ሰው በዚህ ዘመን በስደት
ውስጥ እያለ እንኳን፣ እነዚህን ያጣቸውን
ነገሮች ቤት፣እናት፣አባት፣ወንድም፣እኅት፣
ልጆችና ንብረት መቶ እጥፍ የማያገኝ
የለም። በሚመጣው ዓለም ደግሞ የዘላለ
ምን ሕይወት ያገኛል።

31 «ዛሬ የፊተኞች ሆነው የሚታዩ የኋለ
ኞች ይሆናሉ፤ዛሬ የኋለኞች ናቸው ብለን
የምንገምታቸው ደግሞ የፊተኞች ይሆ
ናሉ።»

32 ከዚህ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ
ጀመሩ። ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ፊት
ለፊት ቀደም ብሎ ይሄድ ነበር። የደቀመዛ
ሙርቱ ልብ በመደነቅ ሲሞላ የተከተሉት
ሌሎች ደግሞ ፍርሃት አደረባቸው። ኢየ
ሱስ አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት ወደ
ጳር ወጣ አድርጎ ኢየሩሳሌም ሲገቡ ምን
እንደሚደርስበት ዳግመኛ እንዲህ ሲል ገለ
ጸላቸው።

33 «ኢየሩሳሌም ከተማ ስንደርስ፣ተይዤ
በካህናት አለቆችና በአይሁድ ሃይማኖት
መምህራን ፊት እቀርባለሁ። እነርሱም
የሞት ፍርድ ይፈርዱብኛል። የሞት ፍር
ዱም እንዲፈጸምብኝ ለሮማውያን ባለሥል
ጣኖች አሳልፈው ይሰጡኛል። 34 እነርሱም
ከዘበቱብኝና ከተፉብኝ፣እንዲሁም ከገረፉኝ
በኋላ ይገድሉኛል። ነገር ግን ከሦስት ቀን
በኋላ ከሞት እነሣለሁ።»

35 ከዚያም የዘብዴዎስ ልጆች፣ያዕቆብና
ዮሐንስ፣ወደ ኢየሱስ ቀረብ አሉና፣ «አንድ
ነገር እንድታደርግልን እንፈልግ ነበር»
አሉት።

36 እርሱም፣ «ምን እንዳደርግላችሁ ትፈ
ልጋላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው።

37 እነርሱም፣ «በመንግሥትህ አንዳችን
ከዙፋንህ በስተቀኝ አንዳችን በስተግራ እን
ድንቀመጥ ፍቀድልን» አሉት።

38 ኢየሱስም፣ «የምትለምኑትን አታው
ቁም። ለመሆኑ እኔ የምጠጣውን ጽዋ መጠ
ጣት ትችላላችሁ? እኔስ የምጠመቀውን
ጥምቀት መጠመቅ ትችላላችሁ?» አላ
ቸው።

39 እነርሱም፣ «አዎን፣እንችላለን» አሉ።
ኢየሱስም፣ «በእርግጥ እኔ የምጠጣውን
ጽዋ ልትጠጡ፣የምጠመቀውንም ጥምቀት
ልትጠመቁ ትችላላችሁ። 40 ነገር ግን ከዙ
ፋኔ ቀኝና ግራ እንድትቀመጡ የምወስነው
እኔ አይደለሁም። ይህን ለተዘጋጀላቸው
የሚሰጠው እግዚአብሔር አብ ነው» አላ
ቸው።

41 አሥሩ ደቀመዛሙርት ያዕቆብና ዮሐ
ንስ ኢየሱስን ምን እንደጠየቁት ባወቁ ጊዜ
በጣም ተቆጡ። 42 ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን
በአንድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «እንደ
ምታውቁት በአሕዛብ ዘንድ ነገሥታትና
ገዥዎቻቸው፣ሥልጣናቸው ይታወቅላቸው
ዘንድ ከበታቻቸው ያሉትን ሰዎች ሰጥ ለጥ
አድርገው ያስተዳድሯቸዋል። 43 በእናንተ
ዘንድ ግን እንደዚህ መሆን አይገባውም።
ከእናንተ መካከል ትልቅ ለመሆን የሚፈ
ልግ የሁሉም አገልጋይ ይሁን። 44 የሁሉ
በላይ መሆን የሚፈልግ ደግሞ የሁሉ ባርያ
ይሁን። 45 እኔ ራሴ እንኳን ወደዚህ ዓለም
የመጣሁት ሰዎች እንዲያገለግሉኝ ሳይሆን፣
ላገለግላቸውና ሕይወቴንም ለብዙዎች ቤዛ
አድርጌ ለመስጠት ነው።» 46 ከዚህ በኋላ
ኢያሪኮ ከተማ ገቡ። ከኢያሪኮ ከተማ
ሲወጡ ብዙ ሕዝብ ተከተላቸው። ከከተ
ማው ወጣ እንዳሉ፣የጤሜዎስ ልጅ ዓይነ
ስውሩ በርጤሜዎስ መንገድ ዳር ተቀምጦ
ይለምን ነበር።

47 የናዝሬቱ ኢየሱስ በአካባቢው መድረ
ሱን እንደሰማ፣ «የዳዊት ልጅ ኢየሱስ
ሆይ፣ እባክህን ማረኝ!» እያለ ይጮኸ

ጀመር።
48 አንዳንድ ሰዎችም ፣ «ዝም በል!»
በማለት ተቆጡት። እርሱ ግን ፣ «የዳዊት
ልጅ ኢየሱስ ሆይ ፣ እባክህን ማረኝ!» በማ
ለት ጩኸቱን ይበልጥ ቀጠለ።
49 ኢየሱስም ጩኸቱን እንደሰማ ቆም
አለና ፣ «ጥሩት ፣ ወደ እኔ ይምጣ» አለ።
ሰዎቹም ፣ «ደስ ይበልህ። ኢየሱስ ስለጠራህ
ተነሥተህ ፊቱ ቅረብ» አሉት። 50 በርጤሜ
ዎስም ከተቀመጠበት ዘሎ ተነሳና የለበሰ
ውን ደበሎ አውልቆ ጥሎ ኢየሱስ ፊት
ቀረበ።
51 ኢየሱስም ፣ «ምን እንዳደርግልህ ትፈ
ልጋለህ?» ሲል ጠየቀው። በርጤሜዎስም ፣
«መምህር ሆይ ፣ እንዳይ አድርገኝ!» አለ።
52 ኢየሱስም ፣ «በሰላም ሂድ! እምነትህ
አድኖሃል» አለው። ዓይነ ስውር የነበረውም
ሰው ወዲያው ማየት ቻለ። ኢየሱስንም ተከ
ትሎት ሄደ።

## ምዕራፍ 11

1 ከኢየሩሳሌም ወጣ ብሎ ፣ ደብረ ዘይት
ተራራ አጠገብ ወደሚገኙት ቤተ ፋጌና
ቢታንያ ወደተባሉት መንደሮች ሲደርሱ ፣
ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ሁለቱን እንዲህ
ሲል ላካቸው።
2 «እዚያ ማዶ ወዳለው መንደር ሂዱ።
እዚያም ስትደርሱ ማንም ሰው ተቀምጦበት
የማያውቅ የአህያ ውርንጫ ታሥሮ ታገኛላ
ችሁ። ፍቱና ይዛችሁ አምጡት። 3 ማንም
ሰው ፣ 'ለምንድን ነው ውርንጫውን የምት
ፈቱት?' ቢላችሁ ፣ 'ጌታችን ስለሚያስፈል
ገው ነው፤በቶሎ ይመልሰዋል' በሉ።»
4-5 ሁለቱ ደቀመዛሙርት ወደ መንደሩ
ሲገቡ ኢየሱስ እንዳላቸው የአህያ ውርንጫ
በመንገድ ዳር በሚገኝ አንድ ቤት ደጃፍ
ታሥሮ አገኙ። ውርንጫውን ፈትተው ሊወ
ስዱ ሲሉ በአካባቢው የነበሩት ሰዎች ፣
«ለምን ትፈቱታላችሁ?» ብለው ጠየቋ
ቸው። 6 ሁለቱ ደቀመዛሙርትም ኢየሱስ
ያዘዛቸውን ሲገልጹላቸው ሰዎቹ ዝም አሏ
ቸው።
7 ከዚያም የአህያውን ውርንጫ ወደ ኢየ
ሱስ ይዘው መጡ። ደቀመዛሙርቱ ልብሳቸ
ውን በውርንጫው ጀርባ ላይ በማንጠፍ
ኢየሱስ እንዲቀመጥበት አዘጋጁ።
8 ኢየሱስ በውርንጫው ላይ ተቀምጦ
በሕዝቡ መካከል በሚሄድበት ጊዜ ፣ ብዙ
ሰዎች መደረቢያቸውን በሚያልፍበት መን
ገድ ላይ ያነጥፉ ፣ ሌሎችም የዘንባባ ቅርን
ጫፍ እየቆረጡ ይጐዘጉዙ ነበር።
9 ከፊትና ከኋላው ይከተሉት የነበሩት
ሰዎችም ፣ «ሆሣዕና! በጌታ ስም የሚመጣ
የተባረከ ይሁን። 10 በመምጣት ላይ ያለው
የአባታችን የዳዊትም መንግሥት የተባረከ
ይሁን። ሆሣዕና በሰማያት!» እያሉ ይጮኹ
ነበር።
11 ከዚያም ኢየሩሳሌም ከተማ እንደገባ
ወደ ቤተ መቅደስ ሄደ። በቤተ መቅደሱም
አካባቢ የሚፈጸመውን ነገር ሁሉ በጥንቃቄ
ተመለከተ። በመምሸት ላይ ስለ ነበር
አሥራ ሁለቱን ደቀመዛሙርት አስከትሎ
ወደ ቢታንያ ሄደ።
12 በማግስቱ ከቢታንያ ወደ ኢየሩሳሌም
ሲመለሱ ኢየሱስ ራብ ተሰማው። 13 አንድ
የለመለመ የበለስ ዛፍ ከመንገድ ዳር አየና ፣
ፍሬ እንዳለው በማለት ወደ በለሱ ዛፍ
ተጠጋ። ነገር ግን የበለሱ ዛፍ ፍሬ የሚሰጥ
በት ወራት ስላልነበረ ፣ ከቅጠል በቀር
ምንም አላገኘበትም።
14 ኢየሱስም ዛፉን ፣ «ምን ጊዜም ፍሬ
አይብቀልብህ!» ብሎ ረገመው። ይህንንም
ሲናገር ደቀመዛሙርቱ ይሰሙት ነበር።
15 ኢየሩሳሌም እንደ ደረሱ ፣ ኢየሱስ ወደ
ቤተመቅደስ ገብቶ በቤተ መቅደሱ ውስጥ
የንግድ ሥራ ያካሂዱ የነበሩትን ነጋዴዎ
ችና ደንበኞቻቸውን ማስወጣት ጀመረ።
የገንዘብ መንዛሪዎችን ጠረጴዛና የርግብ
ሻጮችን መደብር ገለባበጠ። 16 ሸቀጣ ሸቀ
ጣቸውን ይዘው ወደ መቅደሱ የሚገቡትን
ሁሉ አገዳቸው።
17 እንዲህም አላቸው ፣ «በመጽሐፍ
ውስጥ 'ቤቴ ለሰዎች ሁሉ የጸሎት ሥፍራ
ይሆናል' ተብሎ ተጽፎአል። እናንተ ግን
የሌቦች ዋሻ አደረጋችሁት።»
18 የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራን ኢየሱስ ቤተ መቅደስ
ውስጥ ያደረገውን ሲሰሙ ፣ ሊገድሉት የሚ
ችሉበትን መንገድ መፈለግ ጀመሩ። ምክን
ያቱም ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ በመማረኩ
ኢየሱስን ፈርተውት ስለነበር ነው።
19 ማምሻው ላይ ኢየሱስና ደቀመዛሙ
ርቱ እንደ ልማዳቸው ከከተማይቱ ወጥተው
ሄዱ። 20 በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ደቀመዛ
ሙርቱ ኢየሱስ የረገመውን የበለስ ዛፍ
ከሥር እስከ ጫፉ ደርቆ አዩ። 21 ጴጥሮስም
ኢየሱስ የተናገረው ትዝ አለውና ፣ «ተመል
ከት መምህር! የረገምከው ዛፍ ደርቋል!»
አለ።
22-23 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን እንዲህ
አላቸው ፣ «በእግዚአብሔር እምነት ይኑራ
ችሁ። እምነት ካላችሁ ይህንን ተራራ
ከዚህ ተነቅለህ ባሕር ውስጥ ግባ ብትሉ ፣
ተነሥቶ ይገባል። ከእናንተ የሚፈለገው
ማመን ብቻ ነው። 24 እውነቱን ልንገራ
ችሁ። በእምነት የምትለምኑትን ማንኛው
ንም ነገር ታገኛላችሁ። 25 ነገር ግን ለጸ
ሎት በምትዘጋጁበት ጊዜ የሰማዩ አባታ
ችሁ የሠራችሁትን ኃጢአት ይቅር እንዲላ
ችሁ ፣ ቂም የያዛችሁባቸውን ሰዎች ይቅር
በሉ። ይቅር ባትሉ የሰማዩ አባታችሁ የናን
ተንም ኃጢአት ይቅር አይላችሁም።»
26-28 ከዚያም ኢየሩሳሌም ከተማ
ደረሱ። ኢየሱስ ቤተ መቅደሱ ቅጥር ግቢ
ውስጥ በመዘዋወር ላይ ሳለ ፣ የካህናት አለ
ቆች ፣ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንና የአ
ገር ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ቀርበው ፣
«ኧረ ለመሆኑ ነጋዴዎችን ከመቅደሱ
ውስጥ እንድታባርር ሥልጣን የሰጠህ ማን
ነው?» አሉት።
29 ኢየሱስም ፣ «ለማቀርብላችሁ ጥያቄ
መልስ ከሰጣችሁኝ ፣ እኔም የጠየቃችሁኝን
እመልሳለሁ። 30 መጥምቁ ዮሐንስ የተላ
ከው ከእግዚአብሔር ነው? ወይስ ከሰው?
በሉ መልሱን ስጡኝ» አላቸው።
31 እነርሱም እርስ በእርሳቸው ፣ «ምን
ብለን እንመልስለት? ከእግዚአብሔር ነው
የተላከው ብንል ፣ 'ታዲያ ለምን አልተቀበላ
ችሁትም?' ሊለን ነው። 32 ከሰው ነው የተ
ላከው እንዳንለው ደግሞ ፣ ሕዝቡ ዮሐንስን
ነቢይ አድርጎ ስለሚያምን ተቃውሞ ያጋጥ
መናል» ተባባሉ። 33 ስለዚህ ፣ «አናውቅም።
ለጥያቄህ መልስ የለንም» አሉት። ኢየሱ
ስም ፣ «እንግዲያውስ እኔም በምን ሥልጣን
እነዚህን ነገሮች እንደማደርግ አልነግራች
ሁም» አላቸው።

## ምዕራፍ 12

1 በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡ በምሳሌ
ዎች እንዲህ ሲል ይናገራቸው ጀመር።
«አንድ ሰው የወይን አትክልት ተከለና ዙሪ
ያውን አጥር አጠረበት። እንዲሁም ለወይኑ
መጭመቂያ የሚያገለግል ጉድጓድ ቆፈረ።
የወይኑን አትክልት ለሚጠብቅለት ዘበኛም
ማማ ሠራ። ከዚያ በኋላ የአትክልቱን ቦታ
በግብርና ለሚተዳደሩ ሰዎች አከራይቶ ወደ
ሩቅ አገር ሄደ። 2 የወይን ፍሬ መሰብሰቢያ
ጊዜ ሲደርስ ድርሻውን ተቀብሎ እንዲያመ
ጣለት ከአገልጋዮቹ አንዱን ላከ። 3 ገበሬ
ዎቹ ግን መልእክተኛውን ደብድበው ባዶ
እጁን ሰደዱት።
4 «የእርሻው ባለቤት እንደገና ሌላ መል
እክተኛ ላከ። ገበሬዎቹ ይህንንም መልእክ
ተኛ ይዘው ጭንቅላቱን በድንጋይ ፈንክተ
ውና አዋርደው መለሱት። 5 ለሦስተኛ ጊዜ
ሌላ መልእክተኛ ላከ። ያንንም ይዘው ገደ
ሉት። ከእርሱ በኋላ የተላኩትንም አንዳንዶ
ቹን ይዘው ገደሉአቸው፤የቀሩትንም ደብድ
በው አባረሯቸው። 6 የአትክልቱም ባለቤት ፣
'የምወደውን አንድ ልጄን ብልከው እርሱን
በአክብሮት ይቀበሉታል' ብሎ በማሰብ ወደ
ገበሬዎቹ ላከው።
7 «ገበሬዎቹ ግን ፣ 'ይህማ አባቱ ሲሞት
ይህን የአትክልት ቦታ የሚወርሰው ነው።
ይዘን እንግደለው፤እርሱ ከሞተ ርስቱ የእኛ
ይሆናል' በመባባል 8 ይዘው ገደሉት። ሬሣ
ውንም ከአትክልቱ ቦታ ውጭ ጣሉት።
9 «የእርሻው ባለቤት ይህንን ሲሰማ ምን
የሚያደርግ ይመስላችኋል? እርሱ ራሱ
መጥቶ ገበሬዎቹን ከገደለ በኋላ የአትክል
ቱን ቦታ ለሌሎች ገበሬዎች ያከራያል።
10 ለመሆኑ የሚከተለውን ቃል ከቅዱሳት
መጻሕፍት ማንበባችሁን አታስታውሱምን?
'ግንበኞች የናቁት ድንጋይ ፣ የማዕዘኖች ማዕ
ዘን ሆነ። 11 ይህም አስደናቂ የሆነ የጌታ
ሥራ ነው።'»
12 የካህናት አለቆች ፣ የአይሁድ ሃይማኖት
መምህራንና የአገር ሽማግሌዎች ኢየሱስ
በተናገረው ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሱት
«ክፉ ገበሬዎች» እነርሱን የሚመለከቱ
መሆናቸውን ስለተረዱ ፣ ሊይዙት ፈልገው
ሕዝቡን ስለ ፈሩ ተውት። 13 ነገር ግን እነ
ዚህ የአይሁድ ሕዝብ መሪዎች ፣ አንዳንድ
ፈሪሳውያንና የሄሮድስ ወገኖች ኢየሱስን
በንግግር አሳስተው እንዲያሲዙት ላኳቸው።
14 የተላኩትም ሰዎች ኢየሱስን እንዲህ
አሉት ፣ «መምህር ሆይ ፣ አንተ መቼም እው
ነትን ያለ ምንም ፍርሃት እንደምታስተምር
እናውቃለን። የእግዚአብሔርንም መንገድ
ያለ ምንም ይሉኝታና ሥጋት ቀጥተኛ
በሆነ መንገድ በትምህርትህ ታመለክታለህ።
እኛ አሁን ልንጠይቅህ የምንፈልገው አንድ
ነገር አለ። ለመሆኑ ፣ ለሮም መንግሥት
ቀረጥ መክፈል ይገባል? ወይስ አይገባም?»
15 ኢየሱስም ተንኰላቸውን ስላወቀ ፣
«እስቲ ሳንቲም ካላችሁ አሳዩኝና የጠየቃች
ሁኝን ጥያቄ እመልስላችኋለሁ» አላቸው።
16 እነርሱም ሳንቲሙን ከኪሳቸው አው
ጥተው ሰጡት። እርሱም ፣ «በዚህ ሳንቲም
ላይ የታተመው ምስልና የተጻፈው ስም

የማን ነው?» ሲል ጠየቃቸው። እነርሱም፣
«የሮም ንጉሥ ምስልና ስም ነው» አሉት።
17 ኢየሱስም ፣ «እንግዲያውስ ፣ የሮም
ንጉሥ የሆነውን ነገር ሁሉ ለሮም ንጉሥ
ስጡ ፤ ለእግዚአብሔር መስጠት የሚገባች
ሁን ደግሞ ለእግዚአብሔር ስጡ» አላ
ቸው። ኢየሱስ የሰጣቸው መልስ ያልጠበቁ
ትና ያላሰቡት ነበርና ግራ ተጋቡ።
18 ከዚህ በኋላ፣ 'የሙታን ትንሣኤ የሚ
ባል ነገር የለም' የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ
ኢየሱስ ቀርበው እንዲህ ሲሉ ጠየቁት ፤
19 «መምህር ሆይ፣ሙሴ የሰጠን ሕግ፣አንድ
ሰው ልጅ ሳይወልድ ከሞተ የሟቹ ወን
ድም ሚስቱን ያግባና ስም መጥሪያ ልጅ
ይውለድለት ይላል። 20-22 ባንድ ወቅት
ሰባት ወንድማማች ነበሩ። የሁሉም ታላቅ
ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ። ሁለ
ተኛው ወንድም የሟች ወንድሙን ሚስት
አግብቶ ሲኖር ፣ እርሱም ልጅ ሳይወልድ
ሞተ። ሦስተኛውም በተራው አገባትና እር
ሱም ልጅ ሳይወልድ ሞተ። በዚህ ዓይነት
ሰባቱም ወንድማማች አንዲቷን ሴት በየ
ተራ አግብተው ልጅ ሳይወልዱ ሞቱ።
በመጨረሻ ሴትዮዋም ሞተች። 23 ለማወቅ
የምንፈልገው ፣ ይህችን ሴት ሰባቱም ወንድ
ማማች ያገቧት በመሆኑ፣በትንሣኤ ቀን የማ
ንኛቸው ሚስት ትሆናለች?»
24 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው።
«እንደዚህ ያለው ስሕተት ውስጥ የምትወ
ድቁት የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጉምም
ሆነ የእግዚአብሔርን ኃይል ካለማወቃችሁ
የተነሣ ነው። 25 በትንሣኤ ዕለት ሙታን
ሲነሡ ፣ እንደ ሰማይ መላእክት ይኖራሉ
እንጂ አያገቡም አይጋቡም።
26 «ስለ ሙታን ትንሣኤ ግን፣እግዚአብ
ሔር ሙሴን ከሚነደው ቁጥቋጦ፣ 'እኔ የአ
ብርሃም ፣ የይስሐቅ ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ'
ብሎ እንዳናገረው ከአሪት ዘጸአት ውስጥ
አላነበባችሁምን?
27 «እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ
የተናገረው ፣ እነዚህ ሰዎች በሥጋ ከሞቱ
ብዙ መቶ ዓመታት ቢያልፍም ፣ በሕይወት
ከእርሱ ጋር ስለሚኖሩ ነበር። ስለዚህ እግዚ
አብሔር የሕያዋን እንጂ የሙታን አምላክ
አይደለም። ያለበለዚያማ እግዚአብሔር በሕ
ይወት የማይኖሩትን ሰዎች ስም ጠርቶ ፣
'አምላካቸው ነኝ' ባላለም ነበር። እናንተ
ግን እጅግ አድርጋችሁ ተሳስታችኋል።»
28 ይህ ሁሉ ሲሆን በአጠገባቸው ቆሞ
ክርክራቸውን ያዳምጥ የነበረ የአይሁድ ሃይ
ማኖት መምህር የኢየሱስን አንጀት የሚያ
ርስ መልስ ከሰማ በኋላ ፣ እንዲህ ሲል ጠየ
ቀው ፤ «ከእግዚአብሔር ትእዛዛት መካከል
በጣም ከፍተኛው የትኛው ነው?»
29-30 ኢየሱስም ፣ «የመጀመሪያው ትእዛዝ
'እሥራኤል ሆይ ፣ ስማ፣እግዚአብሔር አምላ
ክህ አንድ አምላክ ነው ፤ አንተም እርሱን
በፍጹም ልብህ ፣ በፍጹም ነፍስህ፣በፍጹም
አሳብህና በፍጹም ኃይልህ ውደድ' የሚ
ለው ሲሆን፣ 31 ሁለተኛው ደግሞ፣ 'ራስህን
የምትወደውን ያህል ጐረቤትህን ውደድ'
የሚለው ነው። ከእነዚህ የሚበልጥ ሌላ
ከፍተኛ ትእዛዝ የለም» ብሎ መለሰለት።
32 የሃይማኖት መምህሩም ኢየሱስን ፣
«መምህር ሆይ ፣ 'እግዚአብሔር አንድ
ነው ፤ ከእርሱም በቀር ሌላ አምላክ የለም'
ብለህ የተናገርከው እውነተኛ ነገር ነው።
33 ስለዚህም የተትረፈረፈ መሥዋዕት ለእግ
ዚአብሔር ከማቅረብ ይልቅ፣እግዚአብሔርን
በፍጹም ልቤ፣በፍጹም ነፍሴ፣በፍጹም አሳ
ቤና በፍጹም ኃይሌ መውደድ ፣ ሰውንም
ሁሉ እንደራሴ አድርጌ መውደድ እንደሚ
በልጥ አውቃለሁ» አለ።
34 ኢየሱስም የአይሁድ ሃይማኖት መም
ህሩ አስተውሎ መመለሱን ተገንዝቦ፣ «አን
ተስ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይ
ደለህም» አለው። ከዚህ በኋላ ማንም ሰው
ለኢየሱስ ጥያቄ ሊያቀርብለት የደፈረ አልነ
በረም።
35 ከዚያም ኢየሱስ በቤተ መቅደስ አካ
ባቢ በሚያስተምርበት ጊዜ እንዲህ ብሎ
ጠየቀ ፤ «የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን
'መሲሑ ከዳዊት ወገን መምጣት አለበት'
የሚሉት ለምንድን ነው? 36 ዳዊት ራሱ
በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ፣ 'ጌታ ጌታዬን፣
'ጠላቶችህን ከእግርህ ሥር እስክጥልልህ
ድረስ በቀኜ ተቀመጥ' አለው' ብሎ ተናግ
ሯል። 37 ዳዊት መሲሑን 'ጌታዬ' ብሎ
ከጠራው እንዴት አድርጎ ልጁ ሊሆን ይች
ላል?» ትምህርቱን ከሚሰሙት መካከል
አብዛኞዎቹ በጥሞናና በደስታ ይሰሙት
ነበር።
38 ትምህርቱን በመቀጠል እንዲህ አለ።
«ረጃጅም ልብስ ለብሰው ፣ በዕውቀታቸው
በመመካት ወዲያና ወዲህ እየዞሩ በገበያ
ቦታ ሰው ሁሉ እንዲያከብራቸው ከሚፈ
ልጉ ፣ 39 ወደ ጸሎት ቤትና ወደ ግብዣ
ቦታ ሲሄዱ የክብር ወንበር ለማግኘት ከሚ
ሽቀዳደሙ ፣ የአይሁድ ሃይማኖት መምህራን
ተጠንቀቁ። 40 እነዚህ ሐፍረት የሌላቸው



መምህራን ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች
ገንዘብ እያታለሉ ያግበሰብሳሉ። ይህ ሥራ
ቸው እንዳይታወቅባቸውም ጸሎተኛ ለመ
ምሰል በጉባኤ ላይ ረጅም ጸሎት ያደር
ሳሉ። ከዚህም የተነሣ የሚደርስባቸው
ቅጣት እጅግ የከበደ ነው።»
41 ይህንን ከተናገረ በኋላ በቤተ መቅደሱ
ግቢ የምጽዋት ገንዘብ ወደሚሰበሰብበት
ቦታ ሄዶ ተቀመጠ። ከዚያም ሰው ሁሉ እየ
መጣ በምጽዋት ሳጥኑ ውስጥ ገንዘብ ሲጥል
ይመለከት ጀመር። ሀብታም የሆኑ ብዙ
ሰዎች በርከት ያለ ገንዘብ ሲሰጡ አየ።
42 በዚህ ጊዜ አንዲት ባሏ የሞተባት ድሀ
ሴትም መጥታ ሁለት ሳንቲሞች ስትሰጥ
ተመለከተ።
43-44 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን ጠርቶ
እንዲህ አላቸው። «እውነቱን ልንገራችሁ።
ይህች ድሀ ሴት ከሀብታሞቹ ሁሉ የበለጠ
ምጽዋት አቅርባለች። ምክንያቱም እነርሱ
የሰጡት ከትርፋቸው ሲሆን ፣ እርሷ ግን
ካላት ምንም ሳታስቀር ሰጥታለች» አላ
ቸው።

## ምዕራፍ 13

1 በዚያኑ ዕለት ከቤተ መቅደስ በመው
ጣት ላይ ሳለ ፣ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ ፣
«መምህር ሆይ ፣ እነዚህ ሕንጻዎች እንዴት
ግዙፍና ውብ ሆነው እንደተሠሩ ታያለህ?»
አለው። 2 ኢየሱስም፣ «አዎን፣እንዲህ እንደ
ምታየው ድንጋይ በድንጋይ ላይ ተከቦ አይ
ቀርም። አንድ ቀን ሁሉም ይፈርሳል» ሲል
መለሰለት።
3-4 ኢየሱስ ፣ ከኢየሩሳሌም ከተማ ባሻገር
በቤተ መቅደሱ ትይዩ በሚገኘው የደብረ
ዘይት ተራራ ሥር ተቀምጦ ሳለ ፣ ጴጥሮስ ፣
ያዕቆብ ፣ ዮሐንስና እንድርያስ ብቻቸውን
ወደ እርሱ ቀርበው ፣ «አሁን ያልከው ሁሉ
የሚሆነው መቼ ነው? ጊዜው ሲቃረብ
ምልክቱ ምንድን ነው? እስቲ አስረዳን?»
ሲሉ ጠየቁት።
5 ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው ፤
«ማንም እንዳያሳስታችሁ ተጠንቀቁ።
6 ብዙዎች፣ 'እኔ መሲሕ ነኝ' በማለት ይመ
ጣሉ ፤ ብዙ ሰዎችንም ያስታሉ። 7 በቅርብም
ሆነ በሩቅ ቦታ የሚደረገውን ጦርነትና የጦ
ርነትንም ወሬዎች ትሰማላችሁ። ሆኖም
በዚህ አትደንቁ። ይህ ሊፈጸም የሚገባው
ምልክት እንጂ፣የመጨረሻው ጊዜ ገና ይመ
ጣል።
8 «አንድ ሕዝብ ከሌላው ሕዝብ ፣ መንግ
ሥት ከመንግሥት ጋር ጦርነት ይገጥማሉ።
በብዙ አገሮችም የመሬት መንቀጥቀጥ ፣
ራብና ሁከት ይሆናል። ይህ ሁሉ ወደፊት
ለሚደርሰው መከራ ዋዜማ ነው። 9 እነዚህ
ሁኔታዎች በመፈጸም ላይ መሆናቸውን
ስታዩ ተዘጋጁ። የእኔ ተከታዮች በመሆናች
ሁም ፣ ተይዛችሁ ትታሠራላችሁ ፤ በምኵራ
ቦች ውስጥ ትገረፋላችሁ ፤ ተከሳችሁ በነገ
ሥታትና በአገር አስተዳዳሪዎች ፊት ለፍ
ርድ ትቀርባላችሁ። ይህም በሚሆንበት ጊዜ
ስለ ወንጌል ቃል ለመመስከር አመቺ ይሆን
ላችኋል። 10 ከሁሉ አስቀድሞ የወንጌል
ቃል ለዓለም ሕዝብ ሁሉ መሰበክ ይኖርበ
ታል። 11 ተይዛችሁ ለፍርድ በምትቀርቡ
በት ጊዜ ፣ 'ለመከላከያ የሚጠቅመን መልስ
ምን ይሆን?' ብላችሁ አትጨነቁ። እግዚአ
ብሔር የሚሰጣችሁን ቃል ዝም ብላችሁ
ተናገሩ። በዚያን ጊዜ የምትናገሩት እናንተ
ሳትሆኑ መንፈስ ቅዱስ ራሱ በእናንተ
ውስጥ ሆኖ ነውና።
12 «ያን ጊዜ ወንድም ወንድሙን፣አባት
ልጁን ፣ ልጅም ወላጆቹን ለሞት አሳልፎ
ይሰጣል። 13 የእኔ በመሆናችሁም በሰው
ሁሉ ዘንድ ትጠላላችሁ። ነገር ግን እስከ
መጨረሻው እኔን ሳይክዱ በእምነታቸው
የሚጸኑ ሁሉ ይድናሉ።
14 «ቀደም ሲል በነቢዩ ዳንኤል የተነገ
ረው ፣ በመቅደሱ ውስጥ መገኘት የማይገባ
ውን ርኩስ ነገር በዚያ ቆሞ ስታዩ (ይህንን
የምታነቡ ሁሉ በሚገባ አስተውሉ) ያን
ጊዜ–የምትችሉ ከሆነ–ወደ ይሁዳ ተራራ
ዎች ሽሹ። 15-16 በዚያን ጊዜ በሠገነት ላይ
ከሆናችሁ ፣ ወደ ቤታችሁ ተመልሳችሁ አት
ግቡ። በእርሻ ሥራ ላይም ከሆናችሁ ፣ ገን
ዘብ ለመያዝና ልብስ ለመቀየር ወደ ቤታ
ችሁ አትመለሱ።
17 «በእነዚያ ቀናት ለእርጉዞችና ወል
ደው ለሚያጠቡ ወዮላቸው! 18 ሽሽታችሁ
በክረምት ወራት እንዳይሆን ጸልዩ። 19 ምክ
ንያቱም ፣ በዚያን ወራት የሚደርሰው ጭን
ቅና መከራ ፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ
አሁን ድረስ ታይቶ የማይታወቅ፣ወደፊትም
የማይታይ ይሆናል። 20 እግዚአብሔር እነዚ
ያን የመከራ ቀኖች ባያሳጥር ኖሮ ፣ በዓለም
ላይ ማንም አይተርፍም ነበር። ነገር ግን
ስለተመረጡት ሰዎች ሲል ፣ እግዚአብሔር
እነዚያን ቀኖች ያሳጥራቸዋል።
21 «ስለዚህ ማንም ሰው ወደ እናንተ
መጥቶ፣ 'መሲሑ ይህ ነው፣ወይም ያ ነው'
ቢላችሁ አትመኑ። 22 ምክንያቱም በዚያን

ወራት ድንቅ የሆኑ ተአምራቶችን የሚሠሩ
የሐሰት ነቢያትና የሚቻላቸው ከሆነም በእ
ግዚአብሔር የተመረጡትን እንኳን የሚያሳ
ስቱ፣ 'ክርስቶስ ነን' የሚሉ ሐሰተኞች ነቢ
ያት ይነሣሉ። 23 ስለዚህ አስቀድሜ ነግሬአ
ችኋለሁና ተጠንቀቁ!
24 «ይህ ሁሉ መከራ ካለፈ በኋላ ፀሐይ
ትጨልማለች፤ ጨረቃም ብርሃንዋን ታጣ
ለች። 25 የሰማይ ከዋክብትም ይወድቃሉ፤
የጠፈር ኃይላትም ይናወጣሉ።
26 «ከዚህ ሁሉ በኋላ ክርስቶስ በታላቅ
ኃይልና ክብር በደመና ሲመጣ፣ ሰው ሁሉ
ያየዋል። 27 ከመላው ዓለምና ከአራቱ ነፋ
ሳት የመረጥኋቸውን እንዲሰበስቡ መላእክ
ትን ወደ ምድርና ሰማይ ዳርቻ እልካቸዋ
ለሁ።
28 «ከበለስ ዛፍ የሚከተለውን ትምህርት
መቅሰም ትችላላችሁ። የበለስ ዛፍ ቅርንጫ
ፎች አቆጥቊጠውና ቅጠሎቹም ለምልመው
ሲታዩ፣ የበጋ ወራት መቃረቡን ታውቃላ
ችሁ። 29 እንደዚሁም እነዚህ የነገርኋችሁ
ነገሮች ተፈጽመው ሲታዩ፣ የመምጫዬ ጊዜ
መቅረቡን እወቁ።
30 «እውነቱን እነግራችኋለሁ። እነዚህ
ነገሮች ሁሉ እስኪፈጸሙ ድረስ በዚያን
ጊዜ ያለው ትውልድ አያልፍም። 31 ሰማ
ይና ምድር ያልፋሉ፤ ቃሌ ግን ለዘላለም
ጸንቶ ይኖራል።
32 «ሆኖም፣ ይህ ሁሉ የሚፈጸምበትን
ቀንና ሰዓት፣ ከአባቴ በስተቀር የሰማይ መላ
እክትም ሆኑ እኔም አናውቅም። 33 ስለዚህ
የመምጫዬ ቀኑ መቼ እንደሆነ ስለማታ
ውቁ ነቅታችሁ ጠብቁ። 34 የእኔ አመጣጥ፣
አገልጋዮቹ የተመደበላቸውን ሥራ እየሠሩ
እንዲቆዩት፣ ዘበኛውም ሳይተኛ እንዲጠብ
ቀው፣ አስጠንቅቆ በሄደ ሰው ይመስላል።
35-37 «ስለዚህ የምመጣበት ጊዜ ማታ
ይሁን፣ ሌሊት ይሁን፣ ንጋት ላይ ይሁን፣
ወይም ማለዳ ይሁን ስለማታውቁ፣ ነቅታች
ሁና ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ። ስመጣ ተኝታ
ችሁ እንዳላገኛችሁ ተጠንቀቁ። ይህም ለእ
ናንተ ብቻ ሳይሆን፣ ለሰዎች ሁሉ የማስተላ
ልፈው መልእክቴ ነው።»

## ምዕራፍ 14

1 የአይሁድ ፋሲካና እርሾ ያልገባበት
ቂጣ የሚበላበት በዓል ሊከበር ሁለት ቀን
ሲቀረው የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሃይ
ማኖት መምህራን፣ ኢየሱስን በስውር ይዘው
የሞት ፍርድ ሊያስፈርዱበት ይጥሩ ነበር።
2 እርስ በርሳቸውም፣ «ይህንን ዓላማች
ንን በዓመት በዓሉ ሰሞን ብንፈጽም ሕዝቡ
ሁከት ያስነሣብናል» ተባባሉ።
3 ይህ ሁሉ ሲሆን ኢየሱስ በቢታንያ፣
ለምጻሙ ስምዖን ቤት ነበር። በዚያም ራት
ቀርቦለት በመመገብ ላይ ሳለ፣ አንዲት ሴት
ዋጋው ውድ የሆነ የናርዶስ ሽቶ በአልባስጥ
ሮስ ብልቃጥ ይዛ መጣች። ብልቃጡንም
ሰብራ ሽቶውን በኢየሱስ ራስ ላይ አፈሰሰ
ችው፣
4-5 በሥፍራው ከነበሩት ሰዎች መካከል
አንዳንዶቹ እርስ በእርሳቸው፣ «ይህን የመ
ሰለ ሽቶ ለምን በከንቱ ይባክናል? ከፍ ባለ
ዋጋ ተሸጦ ገንዘቡን ለድሆች ማደል ይቻል
ነበር» በማለት ሴትዮዋን ነቀፏት።
6 ኢየሱስም፣ «መልካም ነገር ባደረገች
ልኝ ይህችን ሴት ለምን ትነቅፉአታላችሁ?
7 ድሆች እንደሆኑ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር
ናቸው። ልትረዱዋቸው ከፈለጋችሁ ምን
ጊዜም ቢሆን ትችላላችሁ። እኔ ግን በዚህ
ምድር ለብዙ ጊዜ አልቆይም።
8 «ይህች ሴት ሞቼ ከመቀበሬ በፊት
በላዬ ላይ ሽቶ በማፈሰስዋ የተቻላትን ሁሉ
አድርጋልኛለች። 9 እውነቱን ልንገራችሁ!
ወንጌል በሚሰበክበት በዓለም አካባቢ
ሁሉ፣ ይህች ሴት ያደረገችው መልካም
ሥራ ሲታወስና ሲመሰገን ይኖራል» አላ
ቸው።
10 ከዚህ በኋላ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
አንዱ የሆነው የአስቆሮቱ ይሁዳ፣ ኢየሱስን
ጠቊሞ የሚያስይዝበትን መንገድ ለመወያ
የት ወደ ካህናት አለቆች ሄደ።
11 የካህናት አለቆችም ይሁዳ ወደ እነ
ርሱ የመጣበትን ምክንያት ሲሰሙ በደስታ
ተቊነጠነጡ። ለይሁዳም ተገቢ ዋጋ እንደ
ሚከፍሉት ቃል ገቡለት። ይሁዳም ከዚያን
ጊዜ አንሥቶ ኢየሱስን ጠቊሞ የሚያስይዝበ
ትን ምቹ ጊዜና ቦታ ይፈልግ ነበር።
12 የፋሲካ ጠቦቶች በሚሠዉበት የቂጣ
በዓል መጀመሪያ ቀን፣ ደቀመዛሙርቱ የፋሲ
ካን ምግብ የት መብላት እንደሚፈልግ ኢየ
ሱስን ጠየቁት።
13 እርሱም፣ ከሐዋርያት መካከል ሁለቱን
ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ እንዲህ ሲል ላካ
ቸው፤ «ወደ ከተማው ስትሄዱ አንድ ሰው
የውኃ እንስራ ተሸክሞ ታገኛላችሁ። እር
ሱን ተከተሉት፣ 14 ወደሚገባበት ቤት
ግቡና የቤቱን ጌታ፣ 'ዛሬ ማታ ከደቀመዛ
ሙርቴ ጋር የፋሲካን ራት የምበላበት
ክፍል የትኛው ነው?' በሉት። 15 እርሱም



ወደ ፎቅ ወስዶ በሚገባ የተሰናዳ ትልቅ
ክፍል ያሳያችኋል፤ በዚያም አስፈላጊውን
ዝግጅት አድርጉልን።»
16 ሁለቱም ደቀመዛሙርት ወደ ከተ
ማው ሲደርሱ፣ ማንኛውም ነገር ልክ ኢየ
ሱስ እንደነገራቸው ሆኖ አገኙ። የፋሲካ
ንም ራት በዚያ አዘጋጁ።
17 ሲመሽ ኢየሱስ ከቀሩት ደቀመዛሙ
ርት ጋር መጣ። 18 ራትም ለመብላት በማ
ዕዱ ዙሪያ ተቀምጠው ሳሉ «እውነቱን ልን
ገራችሁ። በአሁኑ ጊዜ በማዕድ ዙሪያ ተቀ
ምጦ በመብላት ላይ የሚገኝ፣ ከእናንተ መካ
ከል አንዱ ጠቊሞ ያስይዘኛል» አላቸው።
19 ደቀመዛሙርቱም ኢየሱስ በተናገረው
ቃል በማዘን ተራ በተራ፣ «እኔ እሆንን?»
እያሉ ጠየቁት።
20 ኢየሱስም፣ «ከአሥራ ሁለታችሁ
አንዱ የሆነ፣ በአንድ ሳህን አብሮኝ እያጠ
ቀሰ የሚበላው ነው። 21 እኔስ ነቢያት
ቀደም ብለው በተናገሩት ቃል መሠረት
እሞታለሁ። ነገር ግን አሳልፎ ለሚሰጠኝ
ለዚያ ሰው ወዮለት! ጨርሶ ባይወለድ ይሻ
ለው ነበር» አለ።
22 ራት በመብላት ላይ ሳሉ፣ ኢየሱስ ዳቦ
አንሥቶ ለእግዚአብሔር የምስጋና ጸሎት
ካቀረበ በኋላ ቆርሶ ለደቀመዛሙርቱ፣ «እን
ካችሁ ብሉ፤ ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ሰጣ
ቸው።
23 ቀጥሎም፣ ወይን የተቀዳበትን ጽዋ
አንሥቶ ለእግዚአብሔር ምስጋና ካቀረበ
በኋላ፣ ለደቀመዛሙርቱ ሰጥቶአቸው ከወይኑ
ሁሉም ጠጡ።
24 ኢየሱስም፣ «በእግዚአብሔርና በሰ
ዎች መካከል የሚመሠረተውን አዲሱን
ቃል ኪዳን የሚያጸናና፣ ስለ ብዙ ሰዎች
የሚፈስ ይህ ደሜ ነው። 25 እውነቱን ልንገ
ራችሁ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት አዲሱን
ወይን እስከጠጣ ድረስ ከእንግዲህ ወይን
አልቀምስም» አላቸው። 26 መዝሙር ከዘ
መሩ በኋላም ወደ ደብረ ዘይት ተራራ
ሄዱ።
27 ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን፣ «እግዚአ
ብሔር በነቢዩ አፍ፣ 'እረኛውን እመታ
ለሁ፤ በጎቹም ይበተናሉ' ብሎ ተናግሮአልና
በዚህ ምሽት ሁላችሁም ጥላችሁኝ ትሸሻላ
ችሁ። 28 ነገር ግን፣ ከሞት ከተነሣሁ በኋላ
ቀድሜአችሁ ወደ ገሊላ እሄዳለሁ፤ እዚያም
እንገናኛለን» አላቸው።
29 ጴጥሮስም፣ «ሌሎቹ ሁሉ ትተውህ
ቢሸሹ እኔ አልለይህም!» አለ። 30 ኢየሱ
ስም፣ «እውነቱን ልንገርህ፣ ጴጥሮስ! ዛሬ
ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮህ፣ ሦስት
ጊዜ ትክደኛለህ» አለው።
31 ጴጥሮስ ግን መልሶ፣ «በፍጹም አይደ
ረግም! ሞት እንኳን ቢመጣ አብሬህ እሞ
ታለሁ እንጂ በፍጹም አልክድህም!» በማ
ለት ፎከረ። ሌሎቹም ደቀመዛሙርት ኢየሱ
ስን ላለመካድ ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት፣ የጴ
ጥሮስን ቃል በመድገም ገለጡ።
32 ከዚህ በኋላ ጌቴሴማኒ ወደሚባል የአ
ትክልት ሥፍራ ሄዱ። ኢየሱስም ደቀመዛ
ሙርቱን፣ «ጸሎት አድርጌ እስክመለስ
እዚሁ ቆዩኝ» አላቸው።
33 ጴጥሮስን፣ ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከ
ትሎ ሄደ። ያዝን ይጨነቅም ጀመር።
34 እንዲህም አላቸው፤ «ነፍሴ ለሞት በሚ
ያደርስ ኀዘን ተጨንቃለች፤ ከእኔ ጋር ሆና
ችሁ ትጉ።» 35 ትንሽ እልፍ ብሎ መሬት
ላይ በግምባሩ በመደፋት፣ የሚቻል ቢሆን
የሚጠብቀውን የመከራ ሰዓት እንዳያይ
ጸለየ።
36 እንዲህም አለ፣ «አባቴ ሆይ፣ ለአንተ
የሚሳንህ ነገር ስለሌለ ይህንን ጽዋ ከእኔ
አሳልፈው። ነገር ግን አንተ የፈቀድከው
ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን።»
37 ከዚያም ሦስቱ ደቀመዛሙርት ወደነ
በሩበት ቦታ ተመልሶ ሲመጣ፣ ተኝተው አገ
ኛቸው። «ስምዖን ሆይ፣ ተኝተሃል? ለአንድ
ሰዓት እንኳን ከእኔ ጋር ነቅቶ መጠበቅ እን
ዴት አቃተህ?
38 «ወደ ፈተና እንዳትገባ ተግተህ
ጸልይ። መንፈስ ፈቃደኛ፣ ሥጋ ግን ምንኛ
ደካማ ነው!» አለው።
39 እንደገናም እልፍ ብሎ በመሄድ
ቀደም ብሎ የጸለየውን ጸሎት ደገመ።
40 ዳግመኛም ሦስቱ ደቀመዛሙርት ወደ
ነበሩበት ሥፍራ ተመልሶ ቢመጣ፣ ደክሞአ
ቸው ስለነበር ተኝተው አገኛቸው። ከእንቅ
ልፋቸው ከነቁ በኋላም የሚናገሩት መላ
ቅጡ ጠፋቸው።
41 ለሦስተኛ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ ወደነበ
ሩበት ሥፍራ መጥቶ እንዲህ አላቸው።
«እስካሁን እንቅልፋችሁን አላበቃችሁ
ምን? እነሆ የመተኛው ጊዜ አብቅቶአል።
ዳሩ ምን ያደርጋል! የምያዝበት ጊዜም
ደረሰ። 42 ተነሡ እንሂድ፤ ጠቊሞ የሚያስይ
ዘኝም መጥቷል» አላቸው።
43 ኢየሱስ ንግግሩን ሳይጨርስ፣ ከደቀመዛ
ሙርቱ አንዱ የሆነው ይሁዳ፣ ከካህናት አለ
ቆችና ከአይሁድ ሃይማኖት መምህራን የተ

ላኩ ሾተልና ጐመድ የያዙ ሰዎች አስከ
ትሎ ከተፍ አለ።
[44] ይሁዳም አብረውት የመጡትን
ሰዎች፣ «የምትይዙት ጉንጬን የምስመ
ውን ሰው ነው። ስሟ ሰላም ካልኩት
በኋላ፣ በቀላሉ ልትይዙት ትችላላችሁ»
ብሎአቸው ነበር።
[45] ከስከተላቸው ሰዎች ጋር ኢየሱስ ወዳ
ለበት እንደደረሰ፣ ይሁዳ ወደ ኢየሱስ
ቀርቦ፣ «ጌታ ሆይ፣» ብሎ እንደ ወዳጅ
አቅፎ ሳመው። [46] ሰዎቹም ኢየሱስን
ያዙት። [47] ወዲያው ከደቀመዛሙርቱ አንዱ
ሰይፉን መዝዞ የሊቀ ካህኑን አገልጋይ ጆሮ
ቀንጥሶ ጣለ። [48] ኢየሱስም የያዙትን
ሰዎች፣ «ይህን ያህል መሣሪያ ታጥቃችሁ
እኔን ለመያዝ የመጣችሁ ወንበዴ አድርጋ
ችሁኝ ነውን? [49] በየዕለቱ በቤተ መቅደስ
ሳስተምር ለምን አልያዛችሁኝም? ነገር ግን
ይህ ሁሉ የሆነው ነቢያት ስለ እኔ የተናገ
ሩት ይፈጸም ዘንድ ነው» አለ።
[50] በዚህ ጊዜ ደቀመዛሙርቱ በሙሉ
ኢየሱስን ጥለውት ሸሹ።
[51-52] አንድ ነጠላ ያገለደመ ወጣት ግን
ኢየሱስ ተይዞ ሲሄድ ከኋላ ሆኖ ይከተለው
ነበር። ሰዎቹ አይተውት ሊይዙት ሲሞክሩ
ያገለደመውን ነጠላ ጥሎላቸው ራቁቱን
ሸሽቶ አመለጠ።
[53] ኢየሱስን የካህናት አለቆች የአገር
ሽማግሌዎችና የአይሁድ ሃይማኖት መምህ
ራን ወደ ተሰበሰቡበት፣ ወደ ሊቀ ካህኑ
ቤት ወሰዱት። [54] ጴጥሮስም በሩቅ ሆኖ፣
እስከ ሊቀ ካህኑ ግቢ ድረስ ኢየሱስን ተከተ
ለው። ከዚያም ቀስ ብሎ ሊቀ ካህኑ ግቢ
ገባና፣ ተሰብስበው እሳት ይሞቁ ከነበሩት
ሎሌዎች ጋር ተደባለቀ።
[55] የካህናት አለቆችና የከፍተኛው የአይ
ሁድ የሕግ ሸንጎ አባላት፣ ተሰብስበው ኢየ
ሱስን በሞት የሚያስቀጣው ወንጀል ለማግ
ኘት ይጶልቱ ጀመር። ነገር ግን አልሆነላቸ
ውም። [56] ብዙ የሐሰት ምስክሮችም በኢየ
ሱስ ላይ ለመመስከር ፈቃደኞች ሆነው
ቀረቡ። ነገር ግን የተናገሩት ቃል የአንዱ
ከሌላው ጋር የሚጋጭ ሆነ።
[57] በመጨረሻም አንዳንድ ሰዎች ተነሥ
ተው እንዲህ ሲሉ በሐሰት መሰከሩበት።
[58] «ይህን ሰው፣ 'እኔ ይህንን በሰው እጅ
የተሠራ ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን
ውስጥ በሰው እጅ ባልተሠራ ቤተ መቅደስ
እተካዋለሁ' ብሎ ሲናገር ሰምተነዋል።»
[59] ይህም ሆኖ፣ የምስክርነት ቃላቸው አንድ
አልሆነም።
[60] ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህኑ ከተቀመጠበት
ተነሥቶ ዳኞቹ ፊት በመቆም፣ «ለቀረበብህ
ክስ ለምን መልስ አትሰጥም? ምንስ መከላ
ከያ አለህ?» ሲል ኢየሱስን ጠየቀው።
[61] ኢየሱስ ምንም መልስ አልሰጠውም።
ሊቀ ካህኑም እንደገና መልሶ፣ «አንተ የእ
ግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ መሲሕ ነህን?»
ሲል ጠየቀው።
[62] ኢየሱስም፣ «አዎን፣ ነኝ። ደግሞም
ከእግዚአብሔር ቀኝ ስቀመጥና ከዚያም በደ
መና ላይ ሆኜ ወደ ምድር ተመልሼ ስመጣ
ታያለህ» አለው።
[63-64] ሊቀ ካህኑም ይህንን ሲሰማ ልብ
ሱን ቀደደና፣ «ከእንግዲህ ምን ሌላ ምስ
ክር ያስፈልገናል? እግዚአብሔርን ሲሳደብ
ይኸው ሁላችሁም በገዛ ጆሮአችሁ ሰምታች
ኋል! ከእንግዲህ የምትሰጡት ፍርድ ምን
ድን ነው?» ብሎ ጠየቀ። ሁሉም በአንድ
ቃል፣ «ሞት ይገባዋል!» ሲሉ ፈረዱበት።
[65] ከዚያም አንዳንድ ሰዎች በኢየሱስ
ላይ ምራቃቸውን ተፉበት። ዓይኑንም በጨ
ርቅ ሸፍነው፣ «እስቲ የመታህ ማን ነው?
ነቢይ አይደለህም እንዴ? እስቲ እወቅ?»
እያሉ በኩርኩም ይመቱት ነበር። ዘብ የቆ
ሙት ወታደሮች ሳይቀሩ በጥፊ እየመቱ
ወሰዱት።
[66-67] ይህ ሁሉ ሲሆን፣ ጴጥሮስ ሊቀ
ካህኑ ግቢ ውስጥ ተቀምጦ እሳት ይሞቅ
ነበር። ከሊቀ ካህኑ ገረዶች አንዷ ማንነቱን
ስላወቀች፣ «ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር አልነበ
ርክምን?» አለችው።
[68] ጴጥሮስ ግን፣ «የምትናገሪው ነገር
አይገባኝም» አለና ከእሳቱ ዳር ተነሥቶ
ወደ ሌላ ሥፍራ ዞር አለ። ወዲያውም ዶሮ
ጮኸ።
[69] ገረዲቱ ጴጥሮስን በሩቅ ቆሞ ስታየው
ለዘበኞቹ፣ «ያውላችሁ ያ ሰውዬ ነው የኢየ
ሱስ ደቀመዝሙር ነው ያልኳችሁ» በማ
ለት ወደ ጴጥሮስ አመለከተች።
[70] ጴጥሮስ ግን እንደገና ካደ። ጥቂት
ቆይቶም እሳት ይሞቁ ከነበሩት መካከል
አንዳንዶቹ፣ «የገሊላ ሰው በመሆንህ በእር
ግጥ ከእነርሱ ወገን አንዱ ነህ!» በማለት
ጴጥሮስን አፋጠጡት።
[71] ጴጥሮስ ግን፣ «ይህን የምትሉትን
ሰው እኔ አላውቀውም!» እያለ መማልና
መራገም ጀመረ።
[72] ወዲያው ለሁለተኛ ጊዜ ዶሮ ጮኸ።
ጴጥሮስም ኢየሱስ፣ «ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይ
ጮህ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ» ያለው ቃል
ትዝ ስላለው አለቀሰ።

## ምዕራፍ 15

[1] ሊቀ ካህኑን፣ የአገር ሽማግሌዎችንና
የአይሁድ ሃይማኖት መምህራንን የሚያጠ
ቃልለው ከፍተኛው የአይሁድ ሸንጎ፣ ማለዳ
ጠዋት ተሰብስቦ ተማከረ። ከምክሩ በኋላም
ኢየሱስ መሣሪያ በታጠቁ ወታደሮች
ታጅቦ፣ ከሮማዊው አስተዳዳሪ ከጲላጦስ
ፊት እንዲቀርብ ተወሰነ።
[2] ጲላጦስም ኢየሱስን፣ «የአይሁድ
ንጉሥ ነህን?» ሲል ጠየቀው። ኢየሱስም፣
«አዎን፣ አንተ እንዳልከው ነኝ!» አለው።
[3-4] የካህናት አለቆችም ኢየሱስን በሆነ ባል
ሆነው ያሳጡት ጀመር። ጲላጦስም፣
«ለምን ዝም ትላለህ? ለሚያቀርቡብህ ክስ
ለምን መልስ አትሰጥም?» ሲል ኢየሱስን
ጠየቀው።
[5] ኢየሱስ ግን ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ
ምንም አልመለሰም።
[6] ጲላጦስ በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል፣ ከእ
ሥረኞች መካከል ሕዝቡ የሚፈልገውን
አንድ አይሁዳዊ እሥረኛ፣ የመፍታት
ልማድ ነበረው።
[7] በዚያን ጊዜ በመንግሥት ላይ አምፀው
በመነሣት፣ በነፍስ ግድያ ተከሰው ወህኒ ከገ
ቡት እሥረኞች መካከል፣ በርባን የሚባል
ሰው ይገኝ ነበር።
[8] ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል በብዛት
ገፍተው ጲላጦስ ፊት በመቅረብ፣ ከዚህ
ቀደም እንዳስለመዳቸው እንዲያደርግላቸው
ጠየቁት።
[9] ጲላጦስም፣ «'የአይሁድን ንጉሥ' እን
ድፈታላችሁ ትፈልጋላችሁን?» ሲል ጠየቃ
ቸው። [10] የካህናት አለቆች ኢየሱስን እንዲ
ያዝ ያደረጉት፣ ሕዝቡ ስለሚወደው በቅናት
ተነሣስተው መሆኑን ጲላጦስ ያውቅ ነበር።
[11] የካህናት አለቆች ግን፣ ኢየሱስን ሳይ
ሆን በርባንን እንዲለቅላቸው እንዲለምኑት
ሕዝቡን አነሣሡ።
[12] ጲላጦስም፣ «እሺ፣ በርባንን ልፍታላ
ችሁ፤ ነገር ግን ይህን የአይሁድ ንጉሥ የም
ትሉትን ምን ላድርገው?» አላቸው። [13] እነ
ርሱም፣ «ስቀለው!» እያሉ ጮኹ።
[14] ጲላጦስም፣ «ምን ጥፋት ተገኘበትና
ልስቀለው?» ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱ
ግን፣ «ስቀለው!» እያሉ የባሰ ጩኸት
አሰሙ።
[15] ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሁከት ይነሣብ
ኛል ብሎ ስለፈራና፣ ሕዝቡንም ሊያስደስት
ስለፈለገ፣ በርባንን ፈታላቸው። ኢየሱስን
ግን፣ ካስገረፈው በኋላ ለሰቃዮች አሳልፎ
ሰጠው።
[16-17] የሮማ ወታደሮችም ኢየሱስን ቤተ
መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ወደሚገኘው ሠፈራ
ቸው ወሰዱት። በሠፈሩ የነበሩትን የክብር
ዘቦች በሙሉ ጠርተው ከሰበሰቡ በኋላ፣
ሐምራዊ ልብስ አለበሱት። የእሾህ አክሊል
ሠርተው በራሱ ላይ ደፉለት። [18] ከዚያም
«የአይሁድ ንጉሥ ለዘላለም ይኑር!» እያሉ
የቀልድ ሰላምታ በመስጠት አፌዙበት።
[19] ራስ ራሱንም በበትር መቱት፤ ምራቃ
ቸውን ፊቱ ላይ ተፉበት፤ አንገላቱትም።
በጉልበታቸውም ተንበርክከው በማሾፍ ሰገ
ዱለት።
[20] አሾፈውና ቀልደው ሲደክማቸው፣
ያለበሱትን ሐምራዊ ልብስ ከላዩ አውል
ቀው የራሱን ልብስ ካለበሱት በኋላ፣ ወደሚ
ሰቀልበት ቦታ ወሰዱት።
[21] በመንገድ ላይ ሳሉም፣ የአሌክስንድሮስ
ንና የሩፎስን አባት የቀሬናን ሰው ስምዖ
ንን፣ ከገጠር ወደ ከተማ ሲገባ አገኙት። የኢ
የሱስንም መስቀል እንዲሸከም አስገደዱት።
[22] ከዚያም ወደ ጎልጎታ–የራስ ቅል–ወደ
ተባለው ሥፍራ ወሰዱት። [23] እዚያም እንደ
ደረሱ ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ
እንዲጠጣ ሰጡት። እርሱ ግን አልጠጣም
አለ።
[24] ከዚህም በኋላ ሰቀሉት። ልብሱንም
ዕጣ ተጣጥለው የደረሳቸው ተከፋፈሉት።
[25] ኢየሱስን ሲሰቅሉት ጊዜው ከጠዋቱ
ሦስት ሰዓት ነበር።
[26] ከተሰቀለበት መስቀል ራስጌ ላይ፣ የተ
ፈረደበትን ወንጀል ዓይነት ለመግለጽ፣
«የአይሁድ ንጉሥ» የሚል ጽሑፍ ለጠፉ።
[27] የዚያኑ ዕለት ጥዋት ሁለት ወንበዴ
ዎች፣ አንዱ በቀኙ ሌላው በግራው በኩል
ተሰቅለው ነበር። [28] ይህም በመሆኑ፣ በመጽ
ሐፍ፣ «ከአመጸኞች ጋር ተቆጠረ» ተብሎ
የተነገረው የትንቢት ቃል ተፈጸመ።
[29-30] ኢየሱስ በተሰቀለበት ሥፍራ አጠ
ገብ ያልፉ የነበሩ ሰዎችም በንቀትና በማ
ሾፍ ራሳቸውን እየነቀነቁ፣ «ቤተ መቅደስን
አፍርሼ በሦስት ቀን እሠራዋለሁ ብለህ አል
ነበረም? ታዲያ ምነው አሁን ራስህን ማዳን
አቃተህ? እስቲ ከመስቀል ውረድና እን
ይህ!» እያሉ አሾፉበት።
[31] የካህናት አለቆችና የአይሁድ ሃይማ
ኖት መምህራንም ከሥፍራው ቆመው፣

«አይ ጉድ! ሌሎችን 'ለማዳን' ይሽቀዳደም
ነበር። ራሱን ግን ማዳን አልቻለም!»
እያሉ ይቀልዱበት ነበር።
32 «አንተ መሲሕ! የእሥራኤል ንጉሥ!
እስቲ ከመስቀል ውረድና እኛም እንመን
ብህ!» እያሉ አፌዙበት። አብረውት የተሰ
ቀሉት ሁለቱ ወንበዴዎች ሳይቀሩ አላገጡ
በት።
33 ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ
ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አገሩ በሙሉ ጨለማ
ለበሰ።
34 ዘጠኝ ሰዓት ላይ ኢየሱስ ከፍ ባለ
ድምፅ፣ «ኤሎሄ፣ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ?»
ብሎ ጮኸ። ትርጓሜውም፣ «አምላኬ፣አም
ላኬ፣ለምን ተውከኝ?» ማለት ነው።
35 አጠገቡ ቆመውም ከነበሩት ሰዎች
አንዳንዶቹ፣ኤልያስን የሚጠራ መሰላቸው።
36 ከመካከላቸውም አንዱ ሲሮጥ ሄዶ፣የኮ
መጠጠ ወይን በሰፍነግ ነክሮ ፣ በረጅም
በትር ላይ አድርጎ፣ወደ አፉ አስጠጋለት።
«እስቲ ኤልያስ መጥቶ ከመስቀል ላይ ሲያ
ወርደው እናያለን!» አለ ሰውየው።
37 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በታላቅ ድምፅ
ጮኾ ሞተ። 38 የቤተ መቅደስ መጋረጃም
ከላይ እስከ ታች በመቀደድ ለሁለት ተከ
ፈለ።
39 ከኢየሱስ መስቀል አጠገብ ቆሞ የነበ
ረው የመቶ አለቃ ፣ ኢየሱስ የሞተበትን
ሁኔታ ካየ በኋላ፣ «በእውነትም ይህ ሰው
የእግዚአብሔር ልጅ ነበር!» አለ።
40 ጥቂት ሴቶች ከሩቅ ቆመው ሁኔታ
ውን ይመለከቱ ነበር። ከእነርሱም መካከል
መግደላዊት ማርያም ፣ የታናሹ ያዕቆብና
የዮሳ እናት የሆነችው ማርያም፣እንዲሁም
ሰሎሜ ይገኙበት ነበር። 41 እነዚህና ሌሎ
ችም ብዙ ሴቶች ከገሊላ ጀምሮ ይከተሉ
ትና ያገለግሉት ስለ ነበር ፣ በመጨረሻም
አብረውት ወደ ኢየሩሳሌም መጥተው
ነበር።
42-43 ይህ ሁሉ የተፈጸመው በሰንበት
ቀን ዋዜማ ነበር። ወደ ማምሻው ላይ፣የአይ
ሁድ ከፍተኛ ሸንጎ አባልና፣የእግዚአብሔ
ርን መንግሥት መገለጥ በናፍቆት ይጠባበቅ
የነበረው የአርማትያስ ዮሴፍ ፣ በድፍረት
ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስ አስከሬን እን
ዲሰጠው ጠየቀ።
44 ጲላጦስም የኢየሱስ ቶሎ መሞት አስ
ገርሞት፣ተረኛውን መኰንን ጠርቶ ሁኔታ
ውን እንዲያረጋግጥለት አዘዘው። 45 መኰን
ኑም የኢየሱስን መሞት ስላረጋገጠለት፣አስ
ከሬኑን እንዲወስድ ለዮሴፍ ፈቀደለት።
46 ዮሴፍም የኢየሱስን አስከሬን ከመስቀል
ላይ አውርዶ ፣ በገዛው ከተልባ እግር በተ
ሠራ የከፈን ጨርቅ ገነዘው። ከዚያም ከዓ
ለት ድንጋይ ተጠርቦ ከተሠራ መቃብር
ውስጥ ቀበረው። ድንጋይም አንከባሎ የመ
ቃብሩን በር ዘጋው። 47 መግደላዊት ማርያ
ምና ማርያም የዮሳ እናት፣በአካባቢው ተገ
ኝተው ኢየሱስ ሲቀበር ይመለከቱ ነበር።

## ምዕራፍ 16

1 ሰንበት እንዳለፈ ማታውን መግደላዊት
ማርያም፣ሰሎሜና ማርያም የያዕቆብ እናት
ሆነው፣የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት ሽቶ
ገዙ። 2 በማግስቱ እሑድ ማለዳ ተነሥተው
ወደ መቃብሩ ሄዱ። 3 በመንገድ ላይ
ሳሉም ፣ «መቃብሩ የተከደነበትን ትልቅ
ድንጋይ ማን አንከባሎ ይከፍትልናል?»
እያሉ ይነጋገሩ ነበር።
4 ከሥፍራው እንደ ደረሱ ቀና ብለው
ቢመለከቱ፣ድንጋዩ ተንከባሎ መቃብሩ ተከ
ፍቶ አዩ። 5 ወደ መቃብሩ ውስጥ ሲገቡ
ነጭ ልብስ የለበሰ ጐልማሳ በስተቀኝ
በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ።
6 እርሱም፣ «አትፍሩ፣የተሰቀለው የናዝ
ሬቱን ኢየሱስ እንደምትፈልጉ አውቃለሁ።
እርሱ ከዚህ የለም፣ከሞት ተነሥቷል! አስ
ከሬኑ ያረፈበትም ቦታ ይኸው ተመልከቱ።
7 አሁኑኑ ሂዱችሁ፣ለደቀመዛሙርቱና ለጴጥ
ሮስም ቈምር ፣ 'ኢየሱስ ከመሞቱ አስቀ
ድሞ እንደ ነገራችሁ ፣ ወደ ገሊላ ቀድሟ
ችሁ ይሄዳል። በዚያም ታገኙታላችሁ' ብላ
ችሁ ንገሯቸው» አላቸው። 8 ሴቶቹም በፍ
ርሃትና በመንቀጥቀጥ አንዲት ቃል ሳይተነ
ፍሱ፣ከመቃብሩ ቦታ ወጥተው ሄዱ። 9 ኢየ
ሱስ ከሞት በተነሣበት እሑድ ጠዋት መጀ
መሪያ የተገለጠው ፣ ሰባት አጋንንት ላወጣ
ላት ለማርያም መግደላዊት ነበር።
10-11 እርስዋም ፣ በኀዘንና በልቅሶ ላይ
ይገኙ ወደ ነበሩት ደቀመዛሙርት ሄዳ፣ኢየ
ሱስ ከሞት መነሣቱንና በዓይንዋም ያየችው
መሆኑን ነገረቻቸው። እነርሱ ግን አላመንዋ
ትም።
12 በዚያው ቀን ፣ ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም
ተነሥተው ወደ ገጠር ይሄዱ ለነበሩ ሁለት
ደቀመዛሙርት በሌላ መልክ ተገለጠላ
ቸው።
13 እነዚህም ፣ ፈጥነው ወደ ኢየሩሳሌም
በመመለስ ለቀሩት ደቀመዛሙርት ነገሯ
ቸው። ይሁን እንጂ ከደቀመዛሙርቱ መካ



ከል የሰሙትን ቃል አንዳቸውም አምነው
አልተቀበሉም።
14 ከዚህ በኋላ፣አሥራ አንዱ ደቀመዛሙ
ርት ምግብ ለመብላት ተቀምጠው ሳሉ ተገ
ለጠላቸው። ባለማመናቸውና መነሣቱን
ያዩት የነገሩቸውን ባለመቀበላቸውም ወቀ
ሳቸው።
15 ከዚያም እንዲህ ሲል አዘዛቸው።
«ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱና ወንጌልን ለሰው
ሁሉ አስተምሩ። 16 ያመነና የተጠመቀ
ይድናል። ያላመነ ግን ይፈረድበታል።
17 የሚያምኑብኝ በስሜ አጋንንትን ያወ
ጣሉ፣በአዲስ ቋንቋም ይናገራሉ። 18 እባቦ
ችን በእጃቸው ቢይዙ ፤ መርዝ እንኳን
ቢጠጡ፣አይጐዳቸውም። እንዲሁም፣እጆቻ
ቸውን በሽተኞች ላይ ይጭናሉ ፤ በሽተኞ
ችም ይፈወሳሉ።»
19 ጌታ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ይህንን
ተናግሮ ካበቃ በኋላ፣ወደ ሰማይ ዐረገ፤በእግ
ዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።
20 ደቀመዛሙርቱም በየሥፍራው ሄደው
የምሥራቹን ቃል ሰበኩ። ጌታም ከእነርሱ
ጋር ሆኖ፣የሚያስተምሩትን የወንጌል ቃል
በተአምራት ያጸናላቸው ነበር።

# ሉቃስ የጻፈው
## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የምሥራች ቃል

### መግቢያ

ሉቃስ የሕክምና ባለሙያ ነበር። ከሐዋርያው ከጳውሎስ ጋር በመሆን፣በሐዋርያዊ ጉዞ
ዎቹ አብሮት ሳይለየው ወንጌል በማስተማር ተግባር ተሳትፎ አድርጓል። ሐኪሙ ሉቃስ
ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት በሚገባ ያወቀና በዝርዝር የተረዳም በመሆኑ ይህንኑ ለቴዎ
ፍሎስ ጽፎለታል። በጆሮው የሰማውንና በምርምር የገበየውን በጽሑፍ እንዲያሰፍር የእግ
ዚአብሔር መንፈስ ዶክተር ሉቃስን መሣሪያው አድርጎ የተጠቀመበት ፣ ለቴዎፍሎስ
ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለእኛም ጭምር ነው። የሉቃስ ወንጌል ስለ ኢየሱስ ፍጹም ሰው
መሆን አበክሮ ይገልጻል።

---

## ምዕራፍ 1

1-2 ወዳጄ ቴዎፍሎስ ሆይ፣
ከክርስቶስ ደቀመዛሙርትና ከሌሎችም
የዓይን ምስክሮች የተገኙትን መረጃዎች
መሠረት በማድረግ፣ ብዙ ሰዎች በመካከላ
ችን የሆነውን ነገር በታሪክ መልክ ጽፈው
ለማስቀረት ፣ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገ
ዋል።
3 እኔም እነዚህን በጽሑፍ የተላለፉ መረ
ጃዎች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በጥን
ቃቄ ከመረመርኩ በኋላ ፣ ጉዳዩን ሥርዓት
ባለው ሁኔታ በጽሑፍ ላቀርብልህ ወሰንኩ።
4 ይህንንም የማደርገው የተማርከው ትምህ
ርት ሁሉ እውነተኛ ለመሆኑ ማረጋገጫ
እንዲሆንህ ነው።
5 ሄሮድስ የይሁዳ ንጉሥ በነበረበት
ዘመን፣ አብያ በሚል ስም የታወቀች የካህ
ናት ወገን አባል የሆነ ፣ ዘካርያስ የሚባል
ካህን ነበር። ዘካርያስም ከአሮን ዘር የምት
ወለድ ኤልሳቤጥ የምትባል ሚስት ነበረ
ችው። 6 ዘካርያስና ሚስቱ ኤልሳቤጥ፣እግዚ
አብሔርን የሚፈሩና ትእዛዙን የሚያከብሩ
ባልና ሚስት ነበሩ። 7 ኤልሳቤጥ መካን
በመሆንዋ ልጆች አልነበሯቸውም። ሁለ
ቱም በዕድሜ ገፍተው ነበር።
8-9 ሰሞኑ ፣ የዘካርያስ ወገን የሆኑት ካህ
ናት በመቅደስ ውስጥ የሚያገለግሉበት ተራ
ቸው ነበር። ዘካርያስም በክህነት አገልግ
ሎቱ ላይ ሳለ ፣ ወደ እግዚአብሔር መቅደስ
ውስጥ ገብቶ ዕጣን ያጥን ዘንድ እንደ ካህ
ናት ሥርዓት በዕጣ ተመረጠ። 10 ዕጣን
በሚጨስበትም ጊዜ ፣ ወደ ቤተ መቅደስ
የመጣው ሕዝብ በሙሉ ውጪ ቆሞ ጸሎት
ያደርስ ነበር።
11-12 ዘካርያስ በቤተ መቅደስ ውስጥ